# መሠረተ ሕይወት

## በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
## የልጆች መማሪያ መጽሐፍ

### ሰባተኛ ክፍል

አዘጋጅ - ቀሲስ ሰሎሞን መሉጌታ

www.zeorthodox.org

ነሐሴ
፳፻፫ ዓ.ም

© ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ ዘውዴ ፳፻፩ ዓ.ም

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እምነት ሥርዓት እና ትውፊት መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ ሥርዓተ ትምህርት

አድራሺ፡-
ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ ዘውዴ
ፖ.ሳ.ቁ 43200
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

Email:- kesisolomon@gmail.com
Website፡- www.zeorthodox.org

የኮምፒውተር ሌይ አውት ዲዛይን
ልደት አስፋው

www.zeorthodox.org

## ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ ተሰራጭቶ የሚገኘው ገቢ በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም፣ በቦሌ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል፣ በቦሌ ሰሚት መካነ ሰላም መድኃኔዓለም እና ወደ ፊትም በተለያዩ አጥቢያዎች ለሚከናወኑ የሕፃናት፣ አዳጊዎች፣ ወጣቶችና ወላጆች ኦርቶዶክሳዊ ትምህርትና ተመሳሳይ አገልግሎቶች የሚውል ይሆናል፡፡

# መታሰቢያነቱ

በመስከረም ወር 1979 ዓ.ም. ወደ ዝዋይ ሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ገዳም
ገብቼ መንፈሳዊውን እውቀት የምቀስምበት እድል ለፈጠሩልኝ
ለሊቀ ኅሩያን ሥዩም ዳኜ ይሁንልኝ፡፡



# ምስጋና

ይህ የመማሪያ መጽሐፍ ሲዘጋጅ በቀጥተኛ ተሳታፊነት የተሰለፉትን ዲ. ዘላለም ረድኤትና ዲ. ዮናታን ኢያሱን፣ መጽሐፉን በማረም የተባበሩትን መጋቤ ብሉይ አእመረ አሸብርን፣ መምህር ካሕሳይ ገብረ እግዚአብሔርን፣ ዲያቆን ዳንኤል ክብረትን፣ እና አቶ አስራት ከበደን እንዲሁም በኮምፒዩተር የለቀማ ሥራ ያገለገሉትን ልደት አስፋውን፤ መጻሕፍቱን ለማጠናቀቅ ሳደርግ በነበረው ጥረት ውድ ባለቤቴና ልጆቼ የእንቅልፍና የእረፍት ሰዓታቸውን ሳይቀር መሥዋዕት በማድረግ ስላሳለፉ ስለ ከፈሉት መሥዋዕትነት እግዚአብሔር ዋጋ ከፋይ ነውና ዋጋቸውን ይክፈላቸው እላለሁ፡፡ በመጨረሻም የሚያስፈልገውን ሁሉ የሚያከናውኑ የመርሐ ግብራችን አስተባባሪ የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሰንበቴ የሥራ አስፈጻሚ አባላትን እግዚአብሔር በቸርነቱ ይጠብቅልኝ ሳልል አላልፍም፡፡

www.zeorthodox.org

# ማውጫ


| ተራ ቁጥር | አርእስተ ትምህርት | ገጽ |
|---|---|---|
| | አባታዊ ቡራኬ | |
| | መግቢያ | |
| | መቅድም | |
| 1 | የሄኖክ አካሄድ | 5 |
| 2 | ጌዴዎን - ፈትኖ የተቀበለ | 8 |
| 3 | አብርሃም እና ሎጥ | 10 |
| 4 | ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብ | 12 |
| 5 | መረጋጋት | 15 |
| 6 | ዘመነ ጽጌ - የጌታ ስደት መታሰቢያ | 18 |
| 7 | መጽሐፈ ሩት (፩) | 20 |
| 8 | መጽሐፈ ሩት(፪) | 23 |
| 9 | መጽሐፈ ሩት(፫) | 25 |
| 10 | አቡነ መድኃኒነ እግዚእ | 26 |
| 11 | የአምስቱ አዕማደ ምሥጢራት መግቢያ | 27 |
| 12 | ምሥጢረ ሥላሴ (፩) | 29 |
| 13 | ምሥጢረ ሥላሴ (፪) | 31 |
| 14 | ምሥጢረ ሥጋዌ | 33 |
| 15 | ምሥጢረ ጥምቀት | 35 |
| 16 | ምሥጢረ ቁርባን | 37 |
| 17 | ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን(፩) | 39 |
| 18 | ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን(፪) | 41 |
| 19 | ኮከብ የመራቸው ሰብአ ሰገል | 43 |
| 20 | ከተራ እና ገሀድ | 45 |
| 21 | ጌታ ይወደው የነበረ ደቀመዝሙር | 46 |
| 22 | ሁለተኛይቱ የዮሐንስ መልእክት | 48 |
| 23 | ሰሙነ ሕማማት | 50 |
| 24 | በኩረ ትንሣኤ | 52 |
| 25 | የመጽሐፍ ቅዱስ ዝግጅት | 54 |
| 26 | መጽሐፈ ምሳሌ | 55 |


www.zeorthodox.org

| | | |
|---|---|---|
| 27 | የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ፍሬ | 57 |
| 28 | የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ | 59 |
| 29 | ቅዱስ አግናጥዮስ(፩) | 61 |
| 30 | ቅዱስ አግናጥዮስ(፪) | 63 |
| 31 | ቅዱስ አትናቴዎስ | 65 |
| 32 | ቅዱስ ላል ይበላ | 67 |
| 33 | ኢያሱ ሕዝቡ የሚያመልኩትን አስመረጠ | 70 |
| 34 | ቤተ ክርስቲያን በዘመነ ሐዋርያት(፩) | 72 |
| 35 | ቤተ ክርስቲያን በዘመነ ሐዋርያት(፪) | 74 |
| 36 | ቤተ ክርስቲያን በዘመነ ሐዋርያት(፫) | 76 |
| 37 | ቤተ ክርስቲያን በዘመነ ሐዋርያት(፬) | 78 |
| 38 | ቤተ ክርስቲያን በዘመነ ሐዋርያት(፭) | 81 |
| 39 | የዜማ ምልክቶች | 83 |
| 40 | ወንጌል | 84 |
| 41 | ወንጌላውያን | 86 |
| 42 | ቅዱስ ማቴዎስ ወንጌላዊ | 88 |
| 43 | የተራራው ስብከት | 90 |
| 44 | መላእክት | 92 |
| 45 | እግዚአብሔርን ወደ መውደድ የሚመሩን የተግባር መንገዶች | 94 |
| 46 | ቅዱስ ኒቆላዎስ | 96 |
| 47 | የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንያን ታሪክ (-4 መ/ክ/ዘ) -፩ | 98 |
| 48 | የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ (-4 መ/ክ/ዘ) -፪ | 101 |
| 49 | አስተርእዮ | 103 |
| 50 | ተስፋ | 104 |
| 51 | መታመንና ከስህተት መማር | 107 |
| 52 | ሰው በክርስትና እይታ | 110 |


www.zeorthodox.org

# መቅድም

በአሁኑ ወቅት በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ የሚገኙ ኦርቶዶክሳውያን ሕፃናት፣ አዳጊዎችና ወጣቶች ቤተ ክርስቲያናቸውን እያወቁ በመልካም ሥነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ የሚያደርግ፣ ጥያቄዎቻቸውን የሚመልስ ብሎም ችግሮቻቸውን የሚፈታ መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት የመኖሩ አስፈላጊነት በብዙዎቻችን ዘንድ ይታመንበታል፡፡ ቤተ ክርስቲያናችንም በዚሁ ዙሪያ በርካታ ተግባራትን እንደምታከናውን እምነቴ ነው፡፡

ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ቤተ ክርስቲያን በመላክ ለተስተካከለ ዕድገታቸው አስተዋጽዖ በማድረግ የወላጅነት ሓላፊነታቸውን ለመወጣት ፍላጎቱ አላቸው፡፡ ሆኖም በአንዳንድ ሁኔታዎች አለመመቻቸት የተነሣም ይሁን በሌላ ምክንያት ከሕፃንነታቸው ጀምሮ እንዲማሩላቸው ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚያቀርቡ ምእመናን እጅግ ጥቂቶች መሆናቸውን የተለያዩ አጋጣሚዎች ማሳያዎች ሆነውኛል፡፡

ከዛሬ ሰባት ዓመት በፊት በእግዚአብሔር ፈቃድ በምሠራበት መሥሪያ ቤት በኩል ለተዘጋጀ ሙያዊ ሥልጠና ከአገር ውጪ ባደረግሁት ጉዞ ዘወትር አብረውኝ የሚቆሙ ቤተሰቦቼ ምክንያት ሆነው ግብጽንና ገዳማቱን የመጎብኘት ዕድል አገኘሁ፡፡ ይህም የተቀደሰ አጋጣሚ ስለ ልጆች፣ በቅድመ ጋብቻ ስላሉ ወጣቶችና በትዳር ስለሚኖሩ ኦርቶዶክሳዊያን የተናጠል መርሐ ግብር እንዳስብ አደረገኝ፡፡ በእግዚአብሔር ፈቃድም በኅዳር ወር ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም መጥምቀ ዮሐንስና አቡነ አረጋዊ ቤተክርስቲያን የልጆች መርሐ ግብር በሃያ አራት ልጆች ተጀመረ፡፡ አሁን ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል የሆኑ ከሦስት ሺህ በላይ የሚሆኑ ልጆች፤ በየሳምንቱ ቅዳሜና እሑድ ቀን ከአራት እስከ ስድስት ሰዓት በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚሰጠውን መንፈሳዊ ትምህርት ይከታተላሉ፡፡ በርካታ ምእመናንም በየሳምንቱ ረቡዕ ከምሽቱ አሥራ ሁለት እስከ ሁለት ሰዓት ለአዋቂዎች በተዘጋጀው የትምህርት መርሐ ግብር ተሳታፊዎች ናቸው፡፡

www.zeorthodox.org

ይሁን እንጂ ሁሉንም ልጆች በየትምህርት ደረጃቸው በመመደብ ማስተማር የሚያስችል መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ማዘጋጀቱ አስፈላጊ ነበር፡፡ በመሆኑም ቀድመው የተዘጋጁትን ትምህርቶች ተካተውበት ለዚሁ ሥራ እገዛ የሚያደርጉ ወንድሞች ጋር በመመካከር ዲያቆን ዮናታን ኢያሱ እና ዲያቆን ዘላለም ረድኤት ተገኝተውበት ለትምህርቱ አጋዥ የሆኑ መጻሕፍትን ለማዘጋጀት ጥረት ተጀመረ፡፡ እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ከአራት ዓመታት ጥረት በኋላ፤ ለሥርዓተ ትምህርቱ አጋዥ የሆኑ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ በኋላ አጋዥ የሆኑ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ የሆኑ አሥራ ሦስት ጥራዝ የማስተማርያ መጻሕፍት ዝግጅት ተጠናቅቆ ለኅትመት እንዲበቁ ለማድረግ ወደ ማተሚያ ቤት ገብተዋል፡፡

በማስተማርያ መጻሕፍቱ ዝግጅት፤ ለመረጃ የምንገለገልባቸው ምንጮች፣ የምእመናን የኑሮና የትምህርት ደረጃ፣ የመኖሪያ ሥፍራዎችና የባህል ልዩነቶች፣ እንዲሁም በአገር ውስጥ እና ከሀገር ዉጪ በሚገኙ ኢትዮጵያዊያን መካከል ያሉ የአኗኗርና የሥራ ሁኔታዎችና አካባቢያዊ ልዩነቶችን ታሳቢ በማድረግ ከግንዛቤ ውስጥ እንዲገቡ ተሞክሮአል። በዚህ ሥራ ቀጥተኛ ተሳትፎ ላደረጉት ለዲያቆን ዮናታን ኢያሱ እና ለዲያቆን ዘላለም ረድኤት፤ እግዚአብሔር በቸርነቱ ጠብቆ ረጅም ዕድሜ ይስጥልን እላለሁ።

ይኸው የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ ላሉ ወጣቶች ለሚሰጠዉ ‹‹መሠረተ ሕይወት›› መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ማስተማሪያ የሚሆኑ መጻሕፍት ለኅትመት በቅተዉ ለአገልግሎት የተዘጋጁ መሆናቸውን በታላቅ ደስታ እገልጻለሁ።

***“እስከ አሁን ድረስ እግዚአብሔር ረድቶናል።” ፩ኛ ሳሙኤል ፯ ፥ ፲፪***

www.zeorthodox.org

# መግቢያ

የዚህ መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ምንጭ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ሌሎችም የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትና ትውፊተ ቤተክርስቲያን ናቸው። በዚህም መሠረት ጥርት ያለውን የቅድስት ቤተ ክርስቲንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ታሪክ ከመልካም ሥነ ምግባር ጋር፤ በዓለማዊ ትምህርት ቤት ለሚማሩ ሕፃናት፣ አዳጊዎችና ወጣቶች እንዲደርስ ለማድረግ፤ በየትምህርት ደረጃቸው እና ዕድሜአቸው እንዲመጥን ሆኖ የሥርዓተ ትምህርት አዘገጃጀትን ስልት በመከተል ለማዘጋጀት ተሞክሮአል። አንዳንዶቹ ትምህርቶች ልጆች ትምህርቱን በሚገባ ተረድተዉ ማስታወስ እንዲችሉ በየደረጃዉ በሚገኙ የተለያዩ ክፍሎች ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ በድጋሚ ተካትተዋል።

ትምህርቶቹ በየወሩ ተከፋፍለው በቤተ ክርስቲያን ከሚከበሩ በዓላትም ጋር እየተቀራረቡ እንዲዘጋጁ ጥረት ተደርጎአል። በየመካከሉ ለሚኖሩ ክፍተቶች በሁሉም አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በቅደም ተከተል አገልግሎት ላይ እንዲውል ሆኖ የማሟያ ትምህርቶቹ ተወስደው ተካትተዋል። ያም ሆኖ እንደየ ጊዜው ሁኔታ ዘመኑን እንዲዋጅ መሻሻልና መዳበር ያለበት መሆኑ ግን የማይዘነጋ ነው።

በሙዓለ ሕፃናት የሚገኙ ልጆች በጣም አጫጭር ታሪኮችን ብቻ ሰምተው ጥቂቶቹን ብቻ ማስታወስ የሚችሉ ናቸው። ረጅም ጽሑፍና ሐሳብ በትኩረት አንብበዉ በቀላሉ ለመረዳትም ሆነ ለማስታወስ ስለማይችሉ ወይም ስለሚቸገሩ በመምህራን እንዲሁም በወላጆች መታገዝ ያስፈልጋቸዋል። በተረት፣ በታሪክ፣ በሕልምና በእውነታ መካከል ያለውን ልዩነት አገናዝቦ ለመረዳት ይቸገራሉ። በጣም ፈጠራ የታከለባቸው የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች የሚያስፈልጓቸው ቢሆኑም መምህራኖቻቸው የሚዘምሩላቸዉን መዝሙሮች ማስታወስና በአእምሮአቸው መያዝ፣ በትምህርታዊ ጨዋታዎቻቸውም ሆነ በማንኛውም ሁኔታ መምሰልና ማስመሰል ይችላሉ። በዚህ ደረጃ የሚገኙ ልጆች የሚንቀሳቀሱና የተለያዩ ድምፆች ያሉባቸውን ነገሮች እንዲሁም ከሌሎች ጋር መጫወትንና ያዩትን በተግባር ማሳየትን ይወዳሉ።

www.zeorthodox.org

ልጆች ቤተ ክርስቲያን መምጣታቸው ደስታን እንዲፈጥርላቸውና ፈጽመውም የሚወደዱ መሆናቸውን እንዲሰማቸው ማድረግ እንጂ ቶሎ ሊያስደነግጣቸው ወደ ሚችል አቀራረብና ቅጣት ማዘንበል አይገባም። በየደረጃው የሚገኙ ልጆችን የሚያስተምሩ መምህራን በተፈጥሮ ለልጆች ፍቅር ያላቸውና ፍቅራቸውንም መግለጽ የሚችሉ መሆን ይገባቸዋል። በዚህ ትምህርት የሚጠበቁ መልካም ውጤቶችም በሚቀርቡላቸው መርጃዎችና በመምህራኑ ጥረት ላይ የተመረኮዙ ናቸው። መምህራኑ ልጆችን ለመሳብ ብሩህ ፈገግታና ፍቅር ያለው አቀራረብ እንዲሁም፤ ደመቅ ያሉ ቀለማትን፣

ድምፅና ተንቀሳቃሽ ምስሎችን ቢጠቀሙ መዝሙራትንም ቢያዘምሩላቸው ለትምህርቱ ታላቅ ኃይል ይሆናል፡፡ ከሥርዓተ ትምህርቱ ጋር መምህራን ልጆቹን  በየዕለቱ የትምህርት መርሐ ግብሮች መዝሙራትን ሊዘምሩላቸውና ሊያስጠኑአቸው ያስፈልጋል፡፡ አንዳንድ ጊዜም ከትምህርቱ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ሥዕላትን ቢያሳዩአቸዉ፣ ቢሰጡአቸው የተማሩትን ትምህርት በቀላሉ ለማስታወስና ለሌሎችም ለማስረዳት የበለጠ ዕድል ይፈጥርላቸዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ቤተሰቡ ሁሉ ወደ ቤተክርስቲያን እንዲመጣ ልጆች ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉና፡፡ ይህንኑ ለማገዝም  በቀለም የሚቀቡ ሥዕሎችና የመዝሙር ጥራዞችን ዝግጅት አጠናቀናል፡፡ በሙዓለ ሕፃናት ደረጃ የሚገኙ ልጆች ከትምህርታቸዉ ጋር ተያያዥነት ያለውን ርእሰ ጉዳይ ሥዕሉን ቀለም በመቀባት የሚቀስሙት ትምህርት የበለጠ ስለሚሆን የተዘጋጁትን ሥዕሎች በአግባቡ ቀለም እንዲቀቡአቸው የወላጆች እገዛ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

በዓመቱ ውስጥ ባልተካተቱት ሁለት ሳምንታትም ገዳማትንና አብያተ ክርስቲያናትን መጐብኘታቸውና ክትትል ባለበት ሁኔታ በማኀበራዊ ነገሮች ተሳታፊ መሆናቸውም እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ግን መምህራን ለዚህ አገልግሎት በትጋት መጸለይና በየመካከሉ የሚቀሩ ወይም ጨርሰው ያልመጡ ልጆችንም መጐብኘት ይጠበቅባቸዋል፡፡ መምህራንን ማግኘት በማይቻልባቸው ሥፍራዎች ወላጆች በሥርዓተ ትምህርቱ በመመራት ልጆችን ማስተማር ይችላሉ፡፡ ልጆች በመንፈሳዊው ትምህርት እስከአሁን ድረስ ያደጉበት ሁኔታ ያልተመጣጠነ ስለሆነ የክፍል ደረጃቸው ከፍ ቢልም ከሙዓለ ሕፃናት መጽሐፍ ደረጃ ጀምረው መማራቸው ለመንፈሳዊዉ ዕዉቀታቸዉ መሠረት ስለሆነ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በዚህ አጋጣሚም በየአብያተ ክርስቲያናቱ የተከፈቱ ትምህርት ቤቶችም ይህንን ሥርዓተ ትምህርት መጠቀማቸው ልጆች በየደረጃው ቤተ ክርስቲያናችንን እያወቁ፣ ሃይማኖታቸውን ተረድተውና በበጐ ሥነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ የሚረዳቸው ይሆናል ብዬ አምናለሁ፡፡

በመጨረሻም ይኽን ዝግጅት የበለጠ ለማሻሻል የሁሉም አስተያየትና ምክር በጣም አስፈላጊ ስለሆነ እገዛችሁ እንዳይለየኝ እያልኩ አስቀድሞ በተጠቀሱት አድራሻዎች አስተያየቶቻችሁን እንድትልኩልኝ ስል በታላቅ ትሕትና እጠይቃለሁ፡፡

www.zeorthodox.org

# የሄኖክ አካሄድ

## አንደኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** በዘመናችን ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ስለመኖር የአባታችን የሄኖክን አብነት ልጆች እንዲገነዘቡ ማድረግ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"ሄኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ እግዚአብሔር ወስዶታል እና አልተገኘም ፤ "*** ዘፍ. 5፡24

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዕብ 11፡5-6 መጻሕፍተ ብሉያት ሁለቱ ትርጓሜ ፤ዘፍ 5፡21፤ዘፍ 5፡24

### መግቢያ፡-

ሄኖክ ከአዳም ሰባተኛው ትውልድ ነው ፡፡ ሞት በሰፈነበት እና በሠለጠነበት ዘመን በሕይወቱ ከእግዚአብሔር ጋር አንድነት የነበረው፤ በእምነቱ እግዚአብሔርን ደስ እንዳሰኘ የተመሰከረለትና እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የኖረ ሰው በመሆኑ፤ ***"አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ" "እግዚአብሔር ወስዶታል፡፡"*** ተብሎ የተጻፈለት እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰው ነው፡፡ ዘፍ.5፡21-24

በዛሬው ትምህርታችንም የዚህን አባት ***"አካሄድ"*** አርአያ በማድረግ ስለ መንፈሳዊ ጉዞ እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ሄኖክ ከስድስት ሺሕ ዓመታት በፊት የነበረ የእግዚአብሔር ሰው ነው፡፡ በምድራችን ረጅሙን ዕድሜ የኖረው የማቱሳላ አባት ሲሆን የኖኅ ቅድመ አያት ነው፡፡

www.zeorthodox.org

አዳም እና ሔዋን ሞት ተፈርዶባቸው ከገነት ወደዚህች ምድር ሲወርዱ ተስፋቸው በልጆቻቸው ነበር፡፡ ዘፍ 3፡21 ጠላት ግን በአቤል ሞት በቃየል መረገም ዳግመኛ አሳዘናቸው፡፡በኋላም የአቤል ***"ምትክ"*** ስለ ተወለደላቸው ስሙን "ሴት" አሉት፡፡

በምድር ላይም የተረገመው የቃየን ትውልድ እና የአቤል ምትክ የሴት ትውልድ መኖር ጀመሩ፡፡ በኦሪት ዘፍ.4፡16-24 የቃየን ልጆችን ምድራዊ አኗኗር እና ትውልድ እናነባለን፡፡

ከዘፍ 5፡1 ጀምሮም " ***የአዳም የትውልዱ መጽሐፍ ይህ ነው።*** " ብሎ የሴትን ትውልድ መቍጠር ይጀምርና " ***ተወለደ....ወለደ...ኖረ ሞተም*** " እያለ ስድስት ትውልድ ከቆጠረ በኋላ ሰባተኛው ላይ፤ ***"ያሬድም መቶ ስድሳ ሁለት ዓመት ኖረ ሄኖክንም ወለደ........ሄኖክም መቶ ስድሳ አምስት ዓመት ኖረ ማቱሳላንም ወለደ፤ ሄኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ፤ ማቱሳላንም ከወለደ በኋላ የኖረው ሁለት መቶ ዓመት ሆነ ወንዶችንም ሴቶችንም ወለደ። ሄኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ አልተገኘም፤ እግዚአብሔር ወስዶታልና ።"*** ዘፍ.5፡19-24 በማለት አዲስ ነገር ይነግረናል።

በዚህ *መሠረትም* ***"መኖር እና መሞት"*** ለተለመደው የሰው ኑሮ ***"መሄድ እና መወሰድ"*** የሚሉት *ቃላት* ደግሞ ለቅድስና ኑሮ ምሳሌ ሆነው ፤ በእግዚአብሔር በመመራት እና በራስ በመኖር ያለውን ልዩነት እና ውጤት ያመለክታሉ ።

ማንኛውም ሰው ተወልዶ በማደግ በመሥራት እና ራስን በመተካት ኖሮ ይሞታል። ይህም ከሥነ ባሕርያችን የምናገኘው ተፈጥሮአዊ ሂደት ነው። ይህን ሂደት እግዚአብሔርን ሳያውቁ ትእዛዛቱን ሳያከብሩ በኃጢአት ኖሮ ማሳለፍም አለ። የቃየን ልጆች " ***በክፉ የሥጋ ምኞት እርሱም ዝሙት መዳራት ነውር ባለበትም አምልኮ"*** ሲያሳልፉት ፤ከሴት እስከ ኖኅ ያሉት ደግሞ ከዚህ ተለይተው የአዳምን ተስፋ በመያዝ አካሄዳቸውን እንደ እግዚአብሔር ቃል በማድረግ እግዚአብሔርን ደስ አሰኝተው አሳለፉት።

በሁለቱም ትውልድ በአዳም የተፈረደው የሞት መርገም ሲያልፍ ከእነዚህ የተለየ ኑሮ የኖረው ሄኖክ ነበር። አባታችን ሄኖክ ከእነዚህ የሞት መርገም ከተፈረደባቸው ተለይቶ አልሞተም።

እንዴት ? ለምን ? አልሞተም ስንል፤ መጽሐፍ ቅዱስ ፦ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስለ አደረገ፣ እግዚአብሔርን ደስ አሰኘ ፣ እግዚአብሔርም ሞትን ሳያይ ወሰደው ይለናል። ዘፍ.5፡24 እና ዕብ.11፡5-6

የሄኖክን አካሄድ የቅዱስ ጳውሎስን ፣ የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን እና የቅድስት ቤተክርስቲያን ሊቃውንትን ትርጓሜ መሠረት አድርገን እንማራለን።

www.zeorthodox.org

## 1. እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘው የሄኖክ አካሄድ ፦

### *1.1 በእምነት መሄዱ*

በእምነት መኖር እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው አካሄድ ነው።" ***ያለ እምነት ደስ ማሰኘት አይቻልም ፤ ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉት ዋጋ እንዲሰጥ ያምን***

***ዘንድ ያስፈልገዋልና።"*** ዕብ11፥6

ቅዱሳን እግዚአብሔርን ደስ ያሰኙት በእምነት ነው።አብርሃም ***"የእግዚአብሔር ወዳጅ"*** የተባለው በእግዚአብሔር ብቻ በማመኑ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ***"በእስራኤልስ እንኳ እንዲህ ያለ ትልቅ እምነት አላገኘሁም"*** ብሎ የፈወሳቸው እና ያደነቃቸው በእምነታቸው ነበር። ሉቃ 7፥9

በተቃራኒው ጠላታችን የሚፈልገው በእግዚአብሔር ያለንን ጽኑዕ እምነት እንድንተው ነው። ለዚህም ክርስቶስ ለጴጥሮስ ***"ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ ፤ እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ አማለድሁ፤ አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አጽና አለ።"*** ሉቃ 22፥31-32 ተብሎ ተጽፎልናል። የጠላት ዓላማ ከእግዚአብሔር እንድንለይ ነው።

አሕዛብም ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ እና ሊታመን የሚገባው በእነርሱ ዘንድ ግልጥ ሆኖ ስላላወቁት እና ስላላመኑት በከንቱ ጠፉ።ሮሜ 1፥18-36 እስራኤልም በኃይሉ እና በአምላክነቱ ስላላመኑት ***"እግዚአብሔር ግን ከእነርሱ በሚበዙት ደስ አላለውም፥ በምድረ በዳ ወድቀዋልና"*** 1ኛ ቆሮ 0፥5

ተመልከቱ አባታችን ሄኖክ ግን ይህ ሁሉ ሳይጸፍ፤ የሞትን ድምፅ ሰምቶ ዓለም በጨለማ በኖረበት ዘመን አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር በማድረግ ቃሉን አክብሮ በእምነት ጸንቶ በመኖር እግዚአብሔርን ደስ አሰኝቷል።

## 2. በጽኑዕ ተስፋ መጽናቱ

ሰዎች በተለያየ ምክንያት ተስፋ ይቆርጣሉ። ክፉ ከመሆንም በላይ ይክዳሉ። ሄኖክ ተስፋ በሚያስቆርጥ ዘመን ኖሮ በእምነት ጸንቶ ተስፋውን የጠበቀ ነው።

ሄኖክ ከአቤል በኋላ የኖረ አባት ነው። አቤል በየዋህነቱ ሲሄድ ተገድሎዋል ። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ዘፍጥረትን ሲተረጉም ***ሄኖክ ከአቤል ይልቃል። የአቤል ደግነት መጨረሻው ሞት መሆኑ ክፉ ትምህርት ሳይሆነው ፤ የመልካም ሥራ ጥቅም ምንድነው ? ሳይል ፤ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ።*** ብሎአል።

www.zeorthodox.org

በእርግጥም አብነት የሚያደርገው ሳይኖር ለአዳም በተሰጠው ተስፋ የኖረ ታላቅ አባት ነው። ይህም ብቻ ሳይሆን ስለ ክርስቶስ እና የፍርድ ቀን ከሁሉም ቀድሞ የተነበየም ነው። የኃጥአን ክፋት እና ትዕቢት እንደሚፈረድበት እና ለጻድቃን ደግነት ቀድሞ ተስፋን የሰጠ ነው። የይሁዳ መልእ.1፡14-15 ; ሄኖ.1፡9

የቤተ ክርስቲያናችን መተርጉማንም የአቤል ሃይማኖት ምን ረባው ? ምን ጠቀመው ሳይል ፤ መልካሙን የእግዚአብሔርን ፍቃድ በመፈጸም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ ብለው አብራርተዋል፡፡

## 3. በጾም በጸሎት መኖሩ

ቅዱሳን ራሳቸውን በእግዚአብሔር ፊት በማዋረድ መንፈሳዊ ኃይልን የሚታጠቁት በጾም በጸሎት ነው፡፡እግዚአብሔርም ደስ ተሰኝቶባቸዋል፡፡ ሙሴ ጽላት የተቀበለው ዘፀ.24፥13 ኤልያስ እግዚአብሔር የተገለጠለት አርባ ቀንና ሌሊት ጾመው ነው፡፡1ኛ *ነገሥ* 19፥8-18

ሠለስቱ ደቂቅ እና ዳንኤል በባቢሎን *መንግሥት* ከሌሎቹ ተለይተው *ሥጋና* ቅባት ትተው ጥራጥሬ ብቻ እየበሉ ስለ ጾሙ እግዚአብሔር ደስ ተሰኘባቸው፡፡ ***"ለእነዚህ ለአራቱ ብላቴኖች እግዚአብሔር በትምህርትና በጥበብ ሁሉ ዕውቀትንና ማስተዋልን ሰጣቸው፤ ዳንኤልም በራእይና በሕልም አስተዋይ ነበረ፡፡"*** ዳን 1፥17 ተብሎል፡፡

በርናባስ እና ሳውል ለአገልግሎት የተለዩት እና በመንፈስ ቅዱስ የተመረጡት በአንፆኪያ ባለችው ቤተ ክርስቲያን ነቢያትና መምህራን……… ***"ጌታን ሲያመልኩና ሲጦሙ"*** ነው፡፡***"በዚያን ጊዜም ከጦሙ ከጸለዩም እጃቸውንም ከጫኑ በኋላ አሰናበቱአቸው፡፡"*** የሐዋ .*ሥ* 13፥1-3

ለዚህም ነው በኢሳይያስ በእግዚአብሔር ያልተወደደውን ጾም በእርሱ ከተወደደው ጾም ለይቶ በእውነት ለጾመው፤ ***"የዚያን ጊዜ ብርሃን እንደ ንጋት ይበራል፤ ፈውስህ ፈጥኖ ይበራል፤ ፈውስህም ፈጥኖ ይበቅላል፤ ጽድቅህም በፊትህ ይሄዳል፤ የእግዚአብሔርም ክብር በኋላህ ሆኖ ይጠብቅሃል፤ የዚያን ጊዜ ትጠራለህ እግዚአብሔርም ይሰማሃል"*** ኢሳ 58፥8-12

ሄኖክም እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ ጾም እና ጸሎት የኖረ አባት እንደሆነ የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት፤ ***"አዳም በመብል ምክንያት ብልየትን (እርጅናን) ቢያመጣ (ሄኖክ) ከመብል ተከልክሎ ተሐድሶን(ሳይደክም እና ሞትን ሳያይ መወሰድን) አምጥቷልና"*** (ቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ ገጽ 78-79) ሲሉ ይተረጉማሉ፡፡

www.zeorthodox.org

### *2. ሞትን ሳያዩ ወደ እግዚአብሔር መወሰድ*

ልጆች መልካም *ሥራ* ሁሉ ከእግዚአብሔር መልስ አለው፡፡

**አባታችን ሄኖክ ከተለመደው ተፈጥሮአዊ ሞት ውጪ ወደ እግዚአብሔር ተወስዶአል፡፡** ይህም በ2ኛ *ነገሥ* 2፥11-12 ከተገለጠው ከኤልያስ ዕርገት እና ***እስክመጣ ድረስ ይኖር ዘንድ ብወድስ*** ዮሐ.21፡22 ከተባለለት ከወንጌላዊው ዮሐንስ ጋር ያመሳስለዋል፡፡***"ኖረ ሞተ"*** ከተባሉት የእርሱ

ቀደምት እና ደኃርት አበውም ይለየዋል፡፡

ከእርሱ በኂላ የሚሆኑትን (የኖኅ ዘመን የጥፋት ውኃ እና የጌታችንን ማዳን ተንብዮአል፡፡) ከላይ እንደተመለከትነውም ትንሣኤ ሙታንንና የፍርድ ቀንን አስቀድሞ የተነበየውም አባታችን ሄኖክ ነው፡፡ ሄኖ. 1፥9 ይሁዳ 1፥14 በዚህም ከቃሉ ትንቢት ጋር በተግባርም የትንሣኤ ሙታን **ምሳሌ** ሆኖ ሞትን በእግዚአብሔር ኃይል አሸነፈ፡፡ምሳሌያዊው ትንቢት ምን ነበር ?

***እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት፡-"በፊተኛው ትንሣኤ ዕድል ያለው ብፁዕና ቅዱስ ነው፤ሁለተኛውም ሞት በእርሱ ላይ ሥልጣን የለውም ዳሩ ግን የእግዚአብሔር እና የክርስቶስ ካህናት ይሆናሉ፡፡*** ራእ 20፥6 የተባሉት እና ትንሣኤ ልቦና ያገኙ ክርስቲያኖች ምሳሌ ነው፤

***ወደ እግዚአብሔር መወሰዱም፡-*** የሁለተኛው ትንሣኤ ክርስቶስ ዳግም ሲመጣ የመነሣታችን እና በፊቱ የመቆማችን ምሳሌ ነበር፡፡ ***"ኢየሱስ እንደ ሞተና እንደ ተነሣ ካመንን፥እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉትን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋል"*** 2ኛ ተሰ.5፡14

***ሞትን ሳያይ መወሰዱም፡-*** *ጻድቃን* ***ሁለተኛው ሞት*** *ራእ.* 20፥14 በክርስቶስ ድል ነስተውት ሕያዋን የመሆናቸው ምሳሌ ነው፡፡

በዓለማችን መጨረሻ ጌታችን ለፍርድ ከመምጣቱ በፊት ሄኖክ እና ኤልያስ ተገልጠው ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን ጋር ስለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እውነት(ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ) ይመሰክራሉ፡፡ ራእ 11፥3-13 ፡፡ ይህ ሁሉ ክብር እና ኃይል አካሄድን ከእግዚአብሔር ጋር በማድረግ ተገኘ፡፡

## ተግባር

ሄኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር እንዳደረገ እኛም አካሄዳችንን ከእርሱ ጋር ብናደርግ እግዚአብሔር መንፈሳዊ ተግባራትን የምንፈጽምበት ኃይል ይሰጠናል፡፡

በእምነት በመልካም ሥራ እና በተወደዱ አጽዋማት እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት እንትጋ፡፡

www.zeorthodox.org

***" ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና፡፡ "*** ዕብ. 11፥6 ለመልካም ሥራችን እግዚአብሔርን ተስፋ እናድርግ፡፡

## ማጠቃለያ

ሄኖክ ብቻውን በሚባል ሁኔታ እግዚአብሔርን የተከተለ እና ደስ ያሰኘ አባት ነው፡፡

***ያደረጋችሁትን ይረሳ ዘንድ እግዚአብሔር አመጸኛ አይደለም*** ፤ እንደተባለም ለመልካምነቱ እግዚአብሔር መልካም መልሶለታል፡፡ ሞትን ሳያይ ሄደ፡፡ በዓለም መጨረሻም የቤተ ክርስቲያን ምስክር ሆኖ ይገለጣል፡፡ ራእ 11፥1

***"ይህም ሁሉ እንደ ምሳሌ … እኛንም የዘመናት መጨረሻ የደረሰብንን ሊገሥጸን ተጻፈ፡፡"*** 1ኛ. ቆሮ 10፥11

| **መዝሙር፡-** | **ትርጉም፡-** |
| --- | --- |
| እፎ አምሰጥዎ ለሞት | ሞትን እንዴት አመለጡት? |
| አደዉ እሞት ውስተ ሕይወት | እንዴትስ ከሞት ወደ ሕይወት ተሸጋገሩ? |

**መዝሙር፡-**

በምን ደስ ላሰኝህ ጌታዬ ሆይ፤ በምን ደስ ላሰኝህ አምላኬ ሆይ

ዓለሙ በሙሉ ያንተው አይደለም ወይ፤ የፈጠርከው ሁሉ ያንተው አይደለም ወይ?

www.zeorthodox.org

# ጌዴዎን - ፈትኖ የተቀበለ

## ሁለተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-**በእምነት ሆነን የምንጠይቀውን እግዚአብሔር እንደሚሰጠን ማስገንዘብ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"ባንተም ዘንድ ሞገስ ካገኘሁ የምትናጋረኝ አንተ እንደሆንክ ምልክት አሳየኝ፤"*** *መሳ.* 6፥17

**ምንባባት፡-** መጽ መሳፍንት 6፥7፤ ቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ፣ ፀምር ዘጌዴዎን

### መግቢያ፡-

የእስራኤል ልጆች ክፉ ሥራ ሠሩ፡፡ እግዚአብሔርም በምድያማውያን እጅ አሳልፎ ሰጣቸው፤ ምድያማውያንም እርሻቸውን እያቃጠሉ፣ያላቸውን ሁሉ እየዘረፉ አስጨነቋቸው፡፡ ምድያማውያን በእስራኤላውያን ላይ ከማየላቸው የተነሣ የእስራኤል ልጆች በተራራ ላይ ጉድጓድ ቆፍረው ዋሻ ምሽግ አዘጋጁ፡፡ይሄም ሁሉ ሳያድናቸው እስራኤል በጠላቶቻቸው ፊት መቆም አቅቶአቸው የተጠቁ ሆኑ፤ በዚህም ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ጮኹ፡፡

እግዚአብሔርም ነቢይ ልኮ ክፉ ስለሠሩ የአሕዛብን አማልክት ፈርተው ስለተከተሉ አዝኖ ቢመክራቸውም ድምፁን ስላልሰሙት ኃይል አጥተው በምድያማውያን እጅ እንደወድቁ ነገራቸው፡፡ የልባቸውን መመለስ እና ሐዘን፤ ጩኸታቸውንም ሰምቶ ከምድያማውያን እጅ ሊያድናቸው መልአኩን ወደ ጌዴዎን ላከ፡፡

በዛሬው ትምህርታችን ጌዴዎን ነጻ ታወጣለህ ሲባል የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ፈትኖ በመቀበል እንዳመነ እና እንደታዘዘ እንማራለን፡፡

www.zeorthodox.org

### የትምህርቱ ትኩረት

የእግዚአብሔር መልአክ ተገልጦ ጌዴዎንን ***"አንተ ጽኑዕ ኃያል ሰው እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነው "*** ሲለው በጠላቶቻቸው እጅ መሰጠታቸውን እና የእግዚአብሔር ረድኤት እንደተለያቸው ገልፆ ***"ይህ ሁሉ ነገር ለምን ደረሰብን?"*** አለ፡፡ እግዚአብሔርም ***"በዚህ ጉልበትህ ሂድ.......እስራኤልን አድን፤ እነሆ ልኬሃለሁ"*** አለው፡፡ ጌዴዎንም ከመሄዱ በፊት በቂ ማስተማመኛ ጠየቀ፤ ምክንያቱም የሚከተለው ነበር፡-

እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር እንደ ሆነ ንስሓቸውን እንደተቀበለ እና እንደማይተዋቸው ለማረጋገጥ ነው፡፡

በምድያማውያን ላይ በሚያገኙት ድል እርግጠኛ ለመሆን ፈልጓል፡፡ ብቸኛ ማረጋገጫውም እግዚአብሔር በጽኑዕ ክንዱ ከእነርሱ ጋር መሆኑ ነው፤በዚህም ጌዴዎን እግዚአብሔርን እየተፈታተነ ሳይሆን እየለመነና እያረጋገጠ ስለነበረ ጌታ መለሰለት፡፡

ጌዴዎን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ሆኖ ድል እንደሚሰጠው በሦስት ነገሮች ፈትኖ ተቀብሎአል፡-

***ለመጠራቱ ማረጋገጫ መሥዋዕቱን እንዲቀበልለት*** ጠየቀ፡- መሳ 6፥17-23 ይህንን ሲጠይቅም ***"በአንተ ዘንድ ሞገስ ካገኘሁ"*** መሳ 6፥17 ነበር ያለው፡፡ እሳት ከድንጋዩ *መሠዊያ* ወጥቶ መሥዋዕቱን እንደተቀበለለት ለማረጋገጥ መሥዋዕቱን በላው፡፡

**ፀምር (የተባዘተ የበግ ፀጉር) እና ጠል፡፡** ለጦርነት ለመዘጋጀት የተጠየቀ የፈቃደ እግዚአብሔር ማረጋገጫ ነበር፡፡ መሳ 6፥36-40 ጌዴዎን ***"እንደተናገርህ የእስራኤልን ልጆች በእኔ እጅ ታድን እንደ ሆነ፥"*** ብሎ ጠል በፀምሩ ላይ ብቻ እንዲሆን በሌላውም እንዳይሆን ፥ ከዚያም በነጋው ጠል በምድሪቱ ሆኖ በፀምሩ እንዳይሆን ለመነ ሆነለት፤ ሁለቱም ሆነለት፡፡

**የምድያማውያኑ ሕልም፡-** ፍርሃትን በሙሉ ከልቡናው ያጠፋ ነበር፡፡ መሳ 7፥9-15 እግዚአብሔር ጌዴዎንን እንዲህ አለው፡- ***"አንተም ለመውረድ ብትፈራ አንተ ከሎሌህ ከፉራ ጋር ውረድ የሚናጋሩትንም ትሰማለህ፤"*** መሳ. 7፥10 ፤ ጌዴዎን ሲወርድ ብዛታቸው እንደ አንበጣ መንጋ የሆኑ ሠራዊት በሸለቆው አየ፥ ከእርሱ ጋር የነበሩት ግን ሦስት መቶ ብቻ ነበሩ፡፡ በርግጥ ይህ የሚያስደነግጥ ነበር፡፡ ሲጠጋ ሁለት ሰዎች ይነጋገራሉ፡-አንዱም ሕልሙን አውርቶ ሲጨርስ ባልንጀራው መልሶ፤ ***"ይህ ነገር ከእስራኤል ሰው ከኢዩአስ ልጅ ከጌዴዎን ሰይፍ በቀር ሌላ አይደለም፤ እግዚአብሔር ምድያምንና ሠራዊቱን ሁሉ በእጁ አሳልፎ ሰጥቶአል"*** አለው ፡፡

www.zeorthodox.org

ጌዴዎንም ሕልሙንና ትርጓሜውን ሲሰማ ለእግዚአብሔር ሰገደ፥ ወደ ሰፈሩም ተመልሶ ***"እግዚአብሔር የምድያምን ሠራዊት በእጃችሁ አሳልፎ ሰጥቶአልና ተነሡ"*** አለ፤ በሦስት መቶ ሠራዊት ተዋግቶም አሸነፈ፡፡

### ምን ተማርን ?

ጌዴዎን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር መሆኑን ለማረጋገጥ በጣም የጓጓበት ምክንያት "እግዚአብሔር የድሉ ኃይል ነውና ከእርሱ ጋር መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡ እኛም ከዲያቢሎስ ጋር

ስንዋጋ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር መሆኑን በጾም በጸሎት እናረጋግጥ፤ ፈቃዱን ከፈጸምንና ትእዛዛቱን ከተከተልን እግዚአብሔር ከኛ ጋር ነው፡፡

በዙሪያችን ካሉ ሰዎች ጋር መልካም ግንኙነት እንዳለን ያረጋገጥነውን ያህል ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ለመሆናችንም እርግጠኞች እንሁን፡፡ እግዚአብሔር ወዳጅ ሊያደርገን ይፈልጋል፤ወዳጅነቱንም አይተውም፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር በወዳጅነት ለመኖር እንዘጋጅ፣ እንደ ጌዴዎንም ወዳጅነታችንን እናረጋግጥ፡፡

## ማጠቃለያ፡-

የእግዚአብሔር ሕዝብ ክፉ ሲያደርግ እግዚአብሔር በጠላቶቻቸው እጅ አሳልፎ ይሰጣል፤ ይሄም ለተግሣጽ ነው፡፡ ***"ለመቀጣት ታገሡ፤እግዚአብሔር እንደ ልጆች ያደርግላችኋልና ፤ አባቱ የማይቀጣው ልጅ ማን ነው ? "*** ዕብ 12፥7

ስንመለስም ከጠላቶቻችን እጅ ይታደገናል፥ ምሕረቱ እጅግ ብዙ ነውና፡፡ እስራኤልም በክፉ ሥራቸው በጠላቶቻቸው እጅ ቢወድቁም ንስሓ ገብተው ወደ እርሱ ሲጮኹ አዳናቸው፡፡

ጌዴዎን ሕዝቡን ለማዳን ሲጠራ የእግዚአብሔርን ምሕረትና ማዳን ድል እንደሚሰጣቸውም እርግጠኛ እስኪሆን በትዕግሥት ፈትኖ ተቀበለ፡፡

እግዚአብሔርም በልቡ ያለውን መልካም ሐሳብ አውቆ መለሰለት፤ እርግጠኛ እስኪሆንና ፍርሃት እስኪተወውም በብዙ መንገድ አጸናው፡፡

ድልም አድርጎ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ታደገ፡፡

### መዝሙር

ኃይል የእግዚአብሔር ነው፤ ማዳን የእግዚአብሔር፤ ጥበብ የእግዚአብሔር ፣

አንመካም በጉልበታችን፤ እግዚአብሔር ነው ለኛ ኃይላችን፣

www.zeorthodox.org

# አብርሃም እና ሎጥ

## ሦስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ከተለያዩ ነገሮች መካከል መምረጥ ሲኖርብን፣ እግዚአብሔር የሚበጀንን እንዲሰጠን በጸሎት መጠየቅን ከአብርሃም ፤ ለእኔ ብቻ አለማለትን ከሎጥ ጉዳት በመማር እንዲገነዘቡ ማድረግ።

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"ጌታ ሆይ አንተ ሁሉን ታውቃለህ "*** ዮሐ.21፡17 ።

**ምንባብ፡-**ዘፍ 13፥1 - ፍጻሜ ምዕራፍ

### *መግቢያ፡-*

### *የአብርሃም መጠራት፡-*

ኖኀ፤ ሴም፣ካም፣ያፌት የተባሉ ሦስት ልጆች ነበሩት።አባታችን አብርሃም ከሴም ልጆች ይወለዳል። አብራም ***"የክብር አባት"*** ማለት ሲሆን ፤ እግዚአብሔር ስሙን አብርሃም ብሎ ቀየረለት። ***"የብዙዎች አባት ማለት ነው"*** ዘፍ 17፥5

አብራም ጣዖት በሚመለክበት በኡር ይኖር ነበር። አብርሃም ከአባቱ ከታራ፣ከሚስቱ ከሦራ እና ከወንድሙ ልጅ ከሎጥ ጋር ወደ ካራን ወጡ፤ በዚያም ታራ ሞተ። ከዚያም እግዚአብሔር አብራምን ፡- ***" ከአገርህ ከዘመዶችህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ"*** ዘፍ. 12፥1-2አለው።

አብራምም ሚስቱን ሦራን የወንድሙን ልጅ ሎጥን እና በቤቱ የነበሩትን ይዞ ወደ ከነዓን ምድር ወጣ። እግዚአብሔርም ***"ይህቺን ምድር ለልጆችህ እሰጣለሁ"*** አለው። አብርሃምም ለተገለጠለት ጌታ መሠዊያን ሠራ።

www.zeorthodox.org

በረኃብ ምክንያት ወደ ግብጽ ሲሰደዱም ሆነ ሲመለሱ ሎጥ ከአብርሃም ጋር ነበር። የዛሬው ትምህርታችን የአብርሃምን እና የሎጥ መለያየት መሠረት አድርጎ ስለ ምርጫ ያስተምረናል።

### ትምህርቱ፡-

አብርሃም እና ሎጥ ከግብጽ ከተመለሱ በኋላ ሁለቱም ባለ ብዙ መንጋ ከብቶች፤ መሠማሪያም የሚጠባቸው ባለ ጠጐች ሆኑ፡፡ እረኞቻቸውም ለሚጠብቋቸው ከብቶች በግጦሽ ሳርና በውኃ ተጣሉ፤ ይህ ጠብ ሳያድግም አብርሃም ሎጥን ***" እኛ ወንድማማች ነንና በእኔና በአንተ በእረኞቼና በእረኞችህ መካከል ጠብ እንዳይሆን እለምንሀለሁ"*** ዘፍ 13፥8 አለው፡፡

ሎጥ በአብርሃም የእምነት ጉዞ የተባበረ ነበር፡፡ በልባቸው ግን ሰፊ ልዩነት ነበር፡፡ አብርሃም ቅን በእግዚአብሔር እና በሰው ፍቅር የተሸነፈ ነበር፡፡ በሌላው ገጽታ ያለው ሎጥ ደግሞ በሙሉ እምነት ከተጓዘው እና ለእግዚአብሔር ከታዘዘው ታላቅ አባት ጋር ተጓዥ ነበር፤ነገር ግን የሎጥ ልብ ዝግ ነበር፡፡የሎጥ ደካማነት የተገለጠው ከአብርሃም ጋር በእረኞቹ ምክንያት ሲጣላ ነው፡፡ሁለቱም ባለ ጠጐች ሆነዋል፡፡ ነገር ግን የአብርሃም ልብ ከእግዚአብሔር ጋር ሲሆን የሎጥ ልብ ከተገኘው ሀብትና ክብር ጋር ነበር፡፡

አብርሃም ሰላምን ፈለገ፡፡ አረጋዊው አብርሃም በሽምግልናም ሆኖ የምርጫውን ቅድሚያ ለሎጥ ሰጠው፤ ሎጥም መጀመሪያ መምረጥን ፈለገ፡፡ ይህም በእምነት የተመላውን የአብርሃምን ልብ እና በምድራዊ ሀብት የተያዘውን ቁሳዊውን የሎጥን አሳብ ይገልጠዋል፡፡ ***"ሎጥም ዓይኑን አነሣ በዮርዳኖስ ዙሪያ ያለውንም አገር ሁሉ ውኃ የሞላበት መሆኑን አየ፤ እግዚአብሔር ሰዶምንና ገሞራን ከማጥፋቱ አስቀድሞ እስከ ዞዓር ድረስ እንደ እግዚአብሔር ገነት በግብጽ ምድር አምሳል ነበር፡፡"*** ዘፍ.13፥10

ሎጥ እንደ እግዚአብሔር ገነት በሚመስለው ምድር የሚኖሩት እነማን እንደሆኑ አላስተዋለም፡፡ መጽሐፍ ***"የሰዶም ሰዎች ግን ክፉዎችና በእግዚአብሔር ፊት እጅግ ኃጢአተኞች ነበሩ፡፡"*** ዘፍ 13፥13 ይለናል፡፡ ሎጥ ሞትን የመምረጥ ያህል ነበር የተሳሳተው፡፡ ከምን አይነት ሰዎች ጋር እንደምንተባበር ማወቅ አለብን፡፡ እግዚአብሔርን ከማያውቁ ሰዎች ጋር ወዳጅነት መመሥረትም አይገባም፡፡ እዚህ ላይ ለማስተማር መቅረብ እና ከክፉ ሥራቸው ጋር ለመተባበር መቅረብ ይለያያሉ፡፡

www.zeorthodox.org

ምርጫውን ለእግዚአብሔር የሰጠው አባታችን አብርሃም የመጣለት ውድ መልስ ግን ***"ዓይንህን አንሣና ……እይ፤ የምታያትን ምድር ሁሉ ለአንተና ለዘርህ ለዘላለም እሰጣለሁና፡፡ ዘርህንም እንደ ምድር አሸዋ አደርጋለሁ፤ የምድርን አሸዋን ይቆጥር ዘንድ የሚችል ሰው ቢኖር ዘርህ ደግሞ ይቆጠራል፡፡ ተነሣ በምድር በስፋትዋም ሂድ እርስዋን ለአንተ እሰጣለሁና"*** ዘፍ 13፥14 -17 የሚል ነበር፡፡

አብርሃም በተጓዘበት ሁሉ የሚሠራው ሁለት ነገሮችን ነበር፡፡ መኖሪያውን ድንኳን እንዲሁም መሥዋዕቱን የሚያቀርብበትን እና ወደ አምላኩ የሚጸልይበትን መሠዊያ፡፡ በዚህ ቦታም ***"በመምሬ የአድባር ዛፍ"*** (እግዚአብሔር ልጅ እንደሚሰጠው ቃል በገባለት ቦታም) ይህንኑ አደረገ፡፡ ድንኳኑን ተከለ መሠውያን ሠራ፡፡ዘፍ 13፥18

ሎጥ ግን በባለ ጠጋይቱ ነገር ግን ኃጢአት በሞላባት በገሞራ እና በሰዶም ምድር ሊቀመጥ ሄደ፡፡ በዚያም መጀመሪያ በጦርነት (ዘፍጥ 14፥1-ፍጻሜ) በኋላም ከተማይቱን እግዚአብሔር ሲያጠፉት ሎጥ ያለውን ሁሉ አጣ፡፡ ሎጥ የእግዚአብሔርን ቃል ባለመታዘዟ የጨው ሐውልት የሆነችውንም ሚስቱን አጣ፡፡

## አብርሃም ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን ጉዞ ቀጠለ፡፡

### ምን ተማርን ?

1. ሕይወታችን በማያቋርጥ ሂደት ውስጥ ነው፡፡ ጥፋት ወደ ተቀጠረለት ሰዶም ወይም የሕይወት ሰጪ የሆነው እግዚአብሔር ወዳለበት ወደ መምሬ አድባር ዛፍ፡፡
2. በሕይወታችን ዛሬ የምንመርጠው ነገን የምንኖረው ይሆናል፡፡ ቅድሚያ ለማን እንሰጣለን ? ለምድር ክብር ወይስ ለእግዚአብሔር ፍቃድ፡፡

### ተግባር ፡-

1. የመንፈሳዊ ሕይወታችንን እድገት ዕለት ዕለት መከታተል እና ማዳበር አለብን፡፡
2. በምርጫችን ጠንቃቆች አስተዋዮች መሆን እና በእግዚአብሔር ፈቃድ መመራትን መልመድ አለብን፡፡
3. ለመንፈሳዊው እና ለምድራዊው ሕይወታችን ጉዳት እና ጥፋት ከሚያመጡ ሰዎች እና አካባቢዎች ተጠንቅቀን ራሳችንን በመጠበቅ ልንርቅ ይገባናል፡፡

www.zoorthodox.org

### ማጠቃለያ፡-

ሎጥ ከአብርሃም ጋር ጉዞ ቢጀምርም አልፈጸመውም፡፡ የዚህ ምክንያትም የሁለቱም ልብ እና ምርጫ ለየብቻ ስለነበር ነው፡፡

ከዚህም በእግዚአብሔር በመታመን ቃሉን አክብረን ትእዛዙን ፈጽመን እንደፈቃዱ በመመራት ራስን መመርመር እና ትክክለኛ ምርጫን ማድረግን ተምረናል፡፡

# ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብ

## አራተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-*መጽሐፍ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያናችን ያለውን ክብር ማሳወቅ፡፡***

የሚጠና ጥቅስ፡-*" **ከሕፃንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን÷መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳት መጻሕፍትን አውቀሃል" 2ኛ ጢሞ.3፡15*** 

**ምንባብ፡-**ኢሳ.34፡16

## *መግቢያ፡-*

*መጽሐፍ ቅዱስ የእውነት ቃል ነው* ዮሐ.17፡17፡፡ የበረከት እና ድኅነት ምስጢርን ይዟል፡፡ ዘዳ.28፡1-6 እግዚአብሔርን የማወቅ ምሥጢር በመጽሐፍ ቅዱስ አለ፡፡ ከተከበሩ ማዕድናት በላይ የሆኑ ውድ ጥበቦችን ይዟል፡፡ በመንፈሳዊ ውጊያ ድል የምናደርግበትም ምስጢር በቃሉ አለ፣ ቃሉም ዲያብሎስን መውጊያ ሰይፍ ተብሎዋል፡፡ (ኤፌ.6፡18) የነፍሳችን ምግብ ነው፡፡(ማቴ.4÷4) *ለሥጋችንም ፈውስ እና መመሪያ ነው፡፡ ቃሉን ማጣት ረኃብ ነው* አሞ.8፡13፡፡ *ቃሉን ማሰብ የስኬት* እና የልምላሜ ጉዞ ነው፡፡ (*መዝ*.1፡2-3) *ቃሉን ብናስብ ማንም አይቋቋመንም* ፡፡ (ኢያ.1፡7-8) እንደ ክርስቲያን በትምህርት ተወልደንበታል (1ኛ.ጴጥ. 1፡23-25) ያሳድገናልም፡፡***"የእግዚአብሔር ቃላት የነጹ ቃላት ናቸው"*** መዝ.11(12)፡6 ሰሚዎችን ያነጻል፡፡ የዚህ ሁሉ ምንጭ እግዚአብሔርም ***አንብቡት አፌ አዝዞአልና*** ይለናል፡፡

www.zeorthodox.org

በዛሬው ትምህርታችን *መጽሐፍ ቅዱስን* እንዴት እናንብበው? ቤተ ክርስቲያን እና ምእመናን ለመጽሐፍ ቅዱስ የምንሰጠው ክብርና ቦታስ ምን ያህል ነው? የሚለውን እናያለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

### መጽሐፍ ቅዱስ በቤተክርስቲያን

*ሀ.ልዩ ቦታ አለው፡፡* ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ለመጽሐፍ ቅዱስ ያላት ክብር አሥራው ከሚለው ስያሜዋ ይጀምራል፡፡ የሌሎች መጻሕፍት እና የትምህርቶቿ ሁሉ ሥር እና መሠረት

ለማለት የተሰጠ ስያሜ ነው። በሥርዓተ አምልኮዋ እና በትምህርቶቿም ለመጽሐፍ ቅዱስ ታላቅ ክብር ትሰጣለች።

**ለ.ሥርዓተ አምልኮዋ ይመራበታል።** በየዕለቱ በሚቀደሰው ቅዳሴ ላይ ከመጽሐፍ ቅዱስ የወጡ ምዕራፎች ይነበባሉ። መልእክታት እና ወንጌል ይነበባል፣ የዳዊት መዝሙር በዜማ ይሰማል። ወንጌል እየተነበበ ሁለት ዲያቆናት ‹‹የእግዚአብሔር ***ሕግ ለእግራችን መብራት ለመንገዳችን ብርሃን ነው*** ›› ብለው ለማመስጠር የጧፍ መብራት ይይዛሉ።

ወንጌሉን ለመስማት በሚደረገው ጸሎትም ካህኑ ***‹‹እኛንም እንደነርሱ ወንጌልህን ሰምተን ለመሥራት የበቃን ታደርገን ዘንድ በቅዱሳን ጸሎት እንለምንሃለን››*** ይላል። ዲያቆኑም ***‹‹ስለ ወንጌል ጸልዩ ››*** በማለት ሲያውጅ ሕዝቡ ***‹‹ወንጌልህን ለመስማት የተዘጋጀን አድርገን››*** ይላሉ። ክርስቲያኖች ከወንጌል ክብር የተነሣ ወንጌል ሲነበብ አይቀመጡም። የወንጌሉ ቃል ለዓለም መዳረሱን ለማመልከት ካህኑም ወንጌሉን ከራሱ በላይ ከፍ አድርጎ በመያዝ መንበሩን ይዞራል።

የሕማማት ሥርዓተ ጸሎት፣ የጸሎተ ሐሙስ፣ የእግር መታጠብ ሥርዓት ፣ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አርአያ በሆነን መሠረት እና በወንጌል ትምህርት የተዘጋጁ ናቸው።

በማሕሌት ያለው ሥርዓት በመጽሐፍ ቅዱስ ከተጻፈውና በሰማይ ካለው የቅዱሳን መላእክት የምስጋና አፈጻጸም ሥርዓት ጋር አንድ ነው።ኢሳ.6፡1-3 እና ራእ.4፡4;8-11

**ሐ.የዶግማ እና ቀኖናዋ ምንጭ ነው።** የቤተ ክርስቲያናችን ዶግማ (መሠረተ እምነት) ፣ ሥርዓት ፣ ስብከት እና ትምህርት የተመሠረተው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ነው። ቤተ ክርስቲያን ለትውፊት የምትሰጠው ክብርም ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የማያጋጭ እና እርሱን የሚያብራራ ነው።

የቤተ ክርስቲያን ምስጢራት የሚፈጸሙትም በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረትነት ነው ። ለዚህም ነው በተክሊሉ መሐላ እና ቡራኬ የመጽሐፍ ቅዱስ አበው እና እማት የሚነሡት። በተጨማሪም ሁሉም ምስጢራት ሲፈጸሙ የታዘዘ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ አለ።

www.zeorthodox.org

**መ.በጥልቀት ታስተምረዋለች።** ከቤተ ክርስቲያን አራቱ የትምህርት መደቦች አንዱ መጽሐፍ ቤት ይባላል። በዚያም ብሉይ ኪዳን፣ ሐዲስ ኪዳን፣ መጻሕፍት ሊቃውንት እና መጽሐፈ መነኮሳት የተባሉ መጻሕፍት ይተረጎማሉ። ትምህርት አሰጣጡም መጽሐፍ ቅዱስን በቃል በማወቅ እና ምስጢሩን በመተርጎም የሚሰጥ ነው።

ከዚህ የምንረዳውም ቤተ ክርስቲያን ለመጽሐፍ ቅዱስ ልዩ ክብር በመስጠት ; በተግባር እና በመንፈሳዊው ትርጉምም መመሪያዋ እንዳደረገችው ነው ። ወደ ራሳችን ስንመጣ መጽሐፍ ቅዱስ

በሕይወታችን ውስጥ ያለው ቦታ ምን ያህል ነው ? በማንበብ ስለሚገኘው የሕይወት ጥቅምና እንዴት ማንበብ እንዳለብን ከመጽሐፍ ቅዱሳችን ጋር ስላለን ግንኙነትም ቀጥለን እናያለን፡፡

## ክርስቲያን እና መጽሐፍ ቅዱስ

ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ያለን ግንኙነት መጽሐፉን የራስ ማድረግ፣ እንደተወዳጅ እና ምስጢረኛ ጓደኛ መጠበቅ፣ ማንበብ፣ መረዳት፣ በቃሉ መመሰጥ ናቸው፡፡ በተጨማሪም እንደ ቃሉ መኖር ፣ ትእዛዛቱን መተግበርና የሕይወት አካል ማድረግንም ያካትታል ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን ክርስቲያኖች በሕይወታቸው የሚከተሉትን በማድረግ ሊጠቀሙ ይገባቸዋል፡፡

***የራስ በማድረግ ፡፡***

እንደ እውነተኛ ክርስቲያን በቤታችን እና በምንሄድበት ቦታ ሁሉ የማይለየን የምንማርመበትም መጽሐፍ ቅዱስ ሊኖረን ይገባል፡፡ በዘመናችን እያዳንዳችን ተንቀሳቃሽ ስልኮች እንዳለን ሁሉ የራሳችን መጽሐፍ ቅዱስም መኖር አለበት፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በማንኛውም ጊዜ የማይለየን ጓደኛ ሊሆን ይገባል፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ዋነኛው የሕይወታችን መመሪያ ሆኖ ከዚያ ውጪ ምንም ላለማድረግ መወሰን ይገባናል፡፡ ይህን ማድረግ በእግዚአብሔር ለመመራት መዘጋጀት ነው ፡፡

ይህ የሕይወት መጽሐፍ በንባብ ወይም በጸሎት ክፍላችን ቦታ ይኑረው ፡፡ ይህ ማለት ግን እንደ ውድ እና ውብ ዕቃ በጌጥነት ብቻ ተወስኖ እንዲኖር አይደለም፡፡ ማለቂያ የሌለውን መንፈሳዊ ጥቅሙን፣ ስፍር ቁጥር የሌለውን ሀብቱን ለመውረስ ለቃሉ በመታዘዝ በትምህርቱ በመኖር የራስ ማድረግ ነው፡፡

***እውነተኛ ወዳጅ ማድረግ ፡፡***

መጽሐፍ ቅዱስ በማይገለጥ እና በማይገደብ ፍቅር ከሚወደን አምላካችን ከአባታችን ከእግዚአብሔር የመጣ መልእክት ነውና በፍቅር ተቀበሉት ፡፡ ዳዊት ***‹‹ከወርቅና ከክቡር ዕንቍ ይልቅ ይወደዳል፣ ከማርና ከማር ወለላም ይጣፍጣል››*** ያለው፡፡ (መዝ 18፣10) ይህንኑ ፍቅር ስለቀመሰ ነው፡፡ እናንተም እውነተኛ ወዳጅ አድርጉት እርሱም በእውነተኛው መንገድ ስንደክም እያበረታ፣ ጉድለታችንን እየሞላ፣ ስሕተታችንን እያረመ፣ ስናጠፋም እየገሠጸ በሐዘናችን የሚያጽናና በደስታና በዝማሬ የሚመራ ሆኖ ታገኙታላችሁ፡፡

***ዘወትር ማንበብ ፡፡***

መጽሐፍ ቅዱስን ዘወትር ባለመሰልቸት እና በትዕግሥት የማንበብ ልምድ ማለት ነው፡፡

www.zeorthodox.org

መዝሙረኛው ዳዊት እንደገለጸው መንፈሳዊ ሰው ደስታው በእግዚአብሔር ቃል ነው ፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል በቀንና በሌሊት እያሰበ ይመሰጣል፡፡ (መዝ.1፡2) ቋሚና የማይቆራረጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ወደር የሌለው ጥቅም አለው፡፡ በውስጡ ያለው የተቀደሰ መንፈስ እንዲዋሐደን ከማድረጉም በላይ የሚያመጣው በጎ ተፅዕኖና ለውጥም የጸና ይሆናል ፡፡ በዚሁ ከቀጠልንም ማንበብን የተቀደሰ ልማድ እናደርገዋለን ፡፡

ዕለታዊ መጽሐፍ ቅዱስ የማንበብ ልምድ አዳብሩ ፡፡ በማለዳ ማንበብ ቀኑን ሙሉ እንደ ቃሉ ራስን በመግዛት ለመዋል ያስችላል፡፡ ይህም አስፈላጊውን ዕለታዊ መመሪያ እንዳገኘ ሰው አስተዋዮች እንድንሆን ያግዘናል፡፡ ከመኝታ በፊት ማንበብም ፤ ሕልማችንን የእግዚአብሔር ቃል ይሆናል፡፡ በየዕለቱ ቃሉን ማንበብ በከፍተኛ ሓላፊነት ላይ ለነበሩት ለንጉሥና ነቢይ ቅዱስ ዳዊት እንዲሁም ለታላቁ መሪ ለኢያሱ እንኳን የተቻለ ነበር (መዝ.1፡2 ኢያ.1፡8)፤ ለእኛ ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ የምናገኘው እውነተኛው የእግዚአብሔር ቃል የእምነታችን መሠረት፣ የብርታታችን ምንጭና የጽናታችን ኃይል ሆኖ በቀናው መንገድ ይመራናል፡፡

***በማስተዋል አንብቡት፡፡***

መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት የሚያስችለው የማንበብ ዘዴ በማስተዋል የሚደረግ ንባብ ነው፡፡ ጌታችን ስለ ዘር ባስተማረበት ክፍል በመንገድ ዳር የወደቀውን ዘር ሲተረጉም ***"የመንግሥትን ቃል ሰምቶ በማያስተውል ሁሉ ÷ክፉው ይመጣል በልቡ የተዘራውንም ይነጥቃል "*** መቶ ፣ስድሳ እና ሠላሳ ያፈራው እና በመልካም መሬት የተዘራዉም ***"ይህ ቃሉን ሰምቶ የሚያስተውል ነው"*** ማቴ.13፡18-23፤ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ቃላት በጥልቀት ለመግባትና ምን እየነገረን እንደሆነ ለመረዳት በሙሉ ትኩረት፣ሐሳብን በማስገዛት፣ በተመስጦም ማንበብ አስፈላጊ ነው፡፡

## 5. በትሕትና አንብቡት፡፡

***በትሕትና ማንበብ ሲባል፦***

www.zeorthodox.org

5.1 መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር የተነገረ መሆኑን አምነን በቃሉ ለመመራት በትሕትና መዘጋጀት ከእኛ ይጠበቃል ማለት ነው፡፡

5.2 ያልገባንን ለመጠየቅ የተዘጋጀ ልብ ይኑረን ማለት ነው፡፡ ለዚህም ማስታወሻ በመያዝ ያልተረዳንን በጸሎት ከመንፈስ ቅዱስ እና ከቤተ ክርስቲያን መምህራን በመጠየቅ መረዳት ማለት ነው፡፡ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ***"የሚመራኝ ሳይኖር እንዴት ይቻለኛል... እባክህ ስለማን ይናገራል ?"*** የሐዋ.ሥ.8፡26-38 እንዳለ ያልገባንን ለመጠየቅ መዘጋጀት ትሕትና ነው ፡፡ መጽሐፍ ***"አባትህን***

***ጠይቅ ያስታውቅሀማል ፤ ሊቃውንቶችህን ጠይቅ ይነግሩሀማል”*** ይላልና (ዘዳ.32÷7) መጠየቅ ከእግዚአብሔር የተማርነው ነው፡፡

### ምን ተማርን ?

መጽሐፍ ቅዱስ ከአምላካችን የተቀበልነው ስጦታ ነው፡፡ ብንከተለው ሕይወት እና በረከት ይሆነናል፡ ፡(ዘዳ.28፡2-6)

ቤተ ክርስቲያናችን ለመጽሐፍ ቅዱስ የተለየ ክብር ትሰጣለች፡፡ ትምህርቷ፣ አገልግሎቷ እና እምነቷም በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

እኛም ከቤተ ክርስቲያን በተማርነው መሠረት መጽሐፍ ቅዱስን የሕይወታችን መመሪያ ማድርግ እንዳለብን ተምረናል፡፡

***መዝሙር 1***

***መዝሙር 2***

ቃልህን ሰምቼ ሕይወትን እንዳገኝ ፤

ማስተዋል እና ጥበብን ስጠኝ፡፡

**መጽሐፍ ቅዱስን ሁሉም ያነበዋል፡፡**

(ሊቀ መዘምራን ኪነጥበብ ወልደ ቂርቆስ)

www.zeorthodox.org

# መረጋጋት

## አምስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-**በውስጥና በውጭ ሁከት ያለባቸው ወጣቶች መረጋጋትን ማግኘት እንደሚችሉ ማሳወቅ

**የሚጠና ጥቅስ ፡-** ***" ለሚያምን ሁሉ ይቻለዋል"***

**ተጨማሪ ምንባብ** ገድለ ማርያም ግብጻዊት ፣ 2ኛ ቆሮ 6፡4-5

### መግቢያ

የሰው ልጅ ሁሉንም በሰላም የፈጠረው እና በፍጹም እርጋታ ያከናወነው የእግዚአብሔር እጆች ሥራ ነው፡፡ ከዚህም በላይ በመልኩ እና በምሳሌው ተፈጥሮአል፡፡ እግዚአብሔርን ከምንመስልባቸው አንዱ ቅድስና ነው፡፡ በቅድስና መኖር ማለትም በእግዚአብሔር አምሳል መኖር ማለት ነው፡፡ በእግዚአብሔር የቅድስና መንገድ ለመሔድና ሌሎችንም የተቀደሰውን መንገድ ለማሳየት፣ በፈተናዎችም ለመጽናት መረጋጋት አለብን፡፡ ብዙ ወጣቶች የሚፈልጉትን ለማግኘት ትዕግሥት የላቸውም፣ ነገሮችን በሰላም አይፈጽሙም፣ ስሜታዊነትና ችኩልነት ስለሚታይባቸው የልብ ሰላም እና ጸጥታ ያጣሉ፡፡ መረጋጋት አይታይባቸውም፡፡ ይህንኑ እነዚህን ችግሮቻቸውን ተገንዝበው በተረጋጋ መንፈስ የሚያጋጥማቸውን ፈተና ከማሸነፍ ይልቅ እጅ ይሰጡታል፡፡ እንዲያውም በችኩልነትና በስሜታዊነት መንፈስ ቁጣን፣ ሁከትን፣ ረብሻንና ሌሎችን ማስጨነቅን ይመርጣሉ፡፡ ወጣትነታቸውን ምክንያት በማድረግ ‹‹ተፈጥሮዬ ነው ፣ ዕድሜዬ ነው›› በማለት ያሳብባሉ፡፡ በየትኛውም ዕድሜ ያለ ክፉ ጠባይ ግን ተፈጥሮ አይደለም፣ሊሸነፍ የሚችል ጊዜያዊ ችግር ነው፡፡

www.zeorthodox.org

በዛሬው ትምህርታችንም በዘመናችን ከኑሮ ጥድፊያ እና ከዘመናዊነት ጋር ከተንሰራፋው ስሜታዊነት፣ ችኮላ፣ ሰላም ማጣት እና መታወክ ውጭ ስለሆነው እውነተኛው መረጋጋት እንማራለን፡፡

### የሳምንቱ ትምህርት፡-

እግዚአብሔር ሁሉንም በሰላም ይሁን አለ፡፡ ሁሉም በሰላም ተከናወኑ፡፡ ለሰው እና ለመላእክት

በሰጣቸው ነጻ ፈቃድ ተጠቅመው እንዲኖሩ ሲፈቀድላቸውም፤ ሰላማዊ ነበሩ፡፡ ያልተፈቀደላቸውን መፈለግም ጸጋን መገፈፍ፣ ፍርሃት እና ከልጅነት ክብር መውጣትን አስከተለ፡፡ ይህ መረገምን ሲያመጣ ምድር ጠላት አራዊትም አስጨናቂዎች ሆኑ፡፡ በገነት ፈርቶ የተደበቀው የሰው ልጅ በምድርም ሽሽት፣ ቅናት እና ግድያን አስፋፋ፡፡ ይህም የሰውን ልጅ የውስጥ ሰላም አሳጥቶ መረጋጋትን እያራቀ ሁከትና ጦርነትን አነገሠ፡፡ የውስጥ ሰላም የሌላቸው ሌሎችንም ይረብሻሉ፡፡ ለጥቅም፤ ለበላይነት፣ ለጊዜያዊ ደስታ ወዘተ ሲባል ውስጣዊውን የመንፈስ ሰላም እና መረጋጋትን ለማጣት የሰው ልጆች ሕይወት መገለጫ ሆነ፡፡

በሌላ አቅጣጫ ይህንኑ ሁከት ለማምለጥ በአደንዛዥ ዕፅ፣ በአልኮል መጠጥ፣ በጭፈራ ፣ በመዝናናትም ለመረጋጋት እና ሰላማቸውን ለማግኘት የሚጥሩ ብዙዎች ናቸው፡፡ እውነተኛው መረጋጋት ግን በዚያም የለም፡፡ ጌታችን ***ዓለም የሌለውን ሰላም*** እንደሚሰጠን ቃል ገብቶልናል ፤ (ዮሐ.14፡27) ልባችሁም አይታወክ ብሎናል፡፡ ለመሆኑ እውነተኛው መረጋጋት እንዴት ያለ ነው? እውነተኛውን መረጋጋት ከማየታችን በፊት የመረጋጋትን መሠረታዊ መገለጫዎች እናስቀድማለን፡፡

## የመረጋጋት ባሕርያት

መረጋጋት በሰው ልጅ ውስጣዊ እና ውጫዊ ሕይወትና ሁኔታ በግልጽ እና በኀቡዕ ሊገለጥ የሚገባው ነው፡፡ ከእነዚህም ፡-

የውስጥ እርጋታ፡- የአእምሮ ሰላም እና ጸጥታ፤ የልብ ንጽሕናና የአንደበት መቀደስም ነው፡፡

የአካል መረጋጋት ፡- የስሜት አለመዘበራረቅ እና በማስተዋል የሚደረግ የእንቅስቀቀሴ መረጋጋትን ያካትታል፡፡

የነርቭ መረጋጋት፡- ስሜትን በሚያስቆጣ ሁኔታ ውስጥ ቢሆኑም እንኳን ሰላም መሆን፣ በትዕግሥትና በቅን መንፈስ መመራት እና የደስታ መንፈስ አለማጣት ናቸው፡፡

የንግግር መረጋጋት ፡- የድምፅ መረጋጋትን የሐሳብ አለመከፋፈልን አለመዘበራረቅን ያካትታል፡፡

www.zeorthodox.org

የጠባይ መረጋጋት፡- በሐሕሕይወት፣ በተለያዩ አጋጣሚዎች ለሚከሠቱ ማናቸውም ሁኔታዎች በተረጋጋ መንፈስ ተቀብሎ እንደየሁኔታው በማስተዋል መመራትን ያመለክታል፡፡ በሐዘንም ሆነ በደስታ በተረጋጋ መንፈስ ስሜትን ማስተናገድ ለሚያጋጥሙ ችግሮች በትዕግሥትና በማስተዋል ተረጋግቶ መፍትሔ መፈለግ መፍታት መቻልም ናቸው፡፡

ከእነዚህ ዓይነቶቹ መረጋጋቶች ጋር የሚያያዙ ሌሎች መረጋጋቶችም አሉ፡፡ እነርሱም፡-

የተፈጥሮ ሰላም ፣ ሰላማዊ አካባቢ እና ለመኖር ምቹ የሆኑ ጸጥታ የሰፈነባቸው ቦታዎች፡፡

ከመረጋጋት ጋር የሚተባበሩ መልካም ባሕርያት ፡፡

የተፈጥሮ መረጋጋት ያላቸው አንዳንድ ሰዎችም አሉ፡፡ እዚህ ላይ ይህ መረጋጋት በእውነት ሰላማዊ ነው ? ወይስ በውጭ ብቻ የሚታይ? ጊዜያዊ መረጋጋት ነው? ወይስ በልምምድ የተገኘ መረጋጋት ነው? የሚሉት ለራስ የሚመለሱ የመንፈሳውያን ጥያቄዎች ናቸው፡፡ እውነተኛ የመረጋጋት ተግባራዊ ምሳሌዎች አሉ፡፡ እነርሱም በቅዱሳት መጻሕፍት የምናነባቸው ቅዱሳን እና በአካል ያሉ ብርቱ መንፈሳውያን ሕይወት ናቸው፡፡መገለጫዎቹን ቀጥለን እንመለከታለን፡-

## እውነተኛ መረጋጋት

**አንድ ሰው የመረጋጋት አቅሙ በክፉም ሆነ አስቸጋሪ አጋጣሚዎች ተፈተኖ ሳይታይ የተረጋጋ ነው ወይም አይደለም ማለት አይቻልም፡፡** አንድ ሰው በዙሪያው ያለው ከባቢያዊ ሁኔታ የሚያረጋጋ ስለሆነ ብቻ የተረጋጋ ሊመስለን ይችላል፡፡ ምንም ዓይነት ችግር ወይም የሚያስቆጣ፣ ስሜቱን የሚረብሽ፣ የተረጋጋ መንፈሱን የሚፈታተን ነገር አጋጥሞት የማያውቅ ሰው በአንድ አጋጣሚ ቢጣላ ወይም መንፈሱን የሚፈታተን ግጭት ቢያጋጥመው እውነተኛው ማንነቱ ገሐድ ወጥቶ የሚታየው ወይም የሚለካው ያን ጊዜ ነው፡፡ የተረጋጋ መሆን አለመሆኑም ይገለጣል፡፡

አንዳንድ ሰው ደግሞ ሰብእናውን የሚነካ፣ ስሜቱን የሚረብሽ ወይም መንፈሱን የሚጎዳ ስድብ ወይም የዘለፋ ቃል ቢደርስበት፤ ሰብአዊ ክብሩን ወይም ማንነቱን የሚጎዳ ግጭት ሲያጋጥመው፤ ያጋጠመውን ፈታኝ ሁኔታ በትዕግሥትና በማስተዋል ተመልክቶ የሚሰጠው ምላሽና በሚገለጠው ማንነቱ የመረጋጋት አቅሙና የሰከነ ሰብእናው ደረጃ ይታወቃል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ፈታኝ በሆኑ ችግሮች ፣ በሕመም፣ በሐዘን ወዘተ ክፉ አጋጣሚዎች የሚሰጠው ምላሽ ያለበትን ሁኔታ ለማወቅ እና ስሜቶችን ለመቆጣጠሩ ማሳያዎች ናቸው፡፡

እንዲህ ዓይነት ፈታኝ ሁኔታዎችን በምን ስሜትና የመንፈስ ብቃት ተቋቁሞ፤ ምን ዓይነት መፍትሔ? እንዴት ሊሰጥ ይችላል? መረጋጋት ይሳነዋል? ወይስ በትዕግሥት በሰከነ መንፈስ መፍትሔ ይሰጣል? እነዚህም የእውነተኛ መረጋጋት መገለጫ የመጀመሪያ ደረጃዎች ልንላቸው እንችላለን፡፡ ከዚህ ውጭ በዙሪያው ያለው ከባቢያዊ ሁኔታ የተመቻቸለት ሁሉ የተረጋጋ ሊመስል ይችላል፡፡

www.zeorthodox.org

**ሁለተኛው መለኪያ የመረጋጋት ብቃቱ ምን ያህል ይቆያል? የሚለው ነው፡፡** እውነተኛ መረጋጋት ቀጣይነት ያለው ሰላም ሆኖ እንደ ባሕርይ የሚገለጥ ነው፡፡ ለተወሰኑ ጊዜያት የሚኖር

መረጋጋት ሆኖ ችግር ሲያጋጥም የሚለወጥ ከሆነ ይህ መረጋጋት እውነተኛ እና ዘላቂ አይደለም ።

እውነተኛ መረጋጋት ለተወሰነ ጊዜ ብቻ በጸጥታ ቆይቶ ፈታኝና አስቸጋሪ ሁኔታ ሲያጋጥመው የሚቆጣ፣ የሚረበሽ አይደለም፡፡ በማናቸውም የጊዜ ርዝመትና ፈተና ውስጥ ጸንቶ የሚኖር የጸጥታ ወይም የሰከነ ሰላማዊ ባሕርይ ነው፡፡ እውነተኛ ሰላም ዕረፍት የለሽነት ውስጣዊ ሰብዕናን የሸፈነ ማስመሰል አይደለም ፤ በማይገመቱ አጋጣሚዎችም ወደ ብርሃን የሚመጣ ሰብእና ነው፡፡ በተፈጥሮው እርጋታ እና ውስጣዊ ጸጥታ ያለው ሰው በችግር እና ግጭቶች አይረበሽም፡፡ በተቃራኒው በትዕግሥትና በማስተዋል ጸንቶ ፍቅሩን መልካምነቱንና መረጋጋቱን የሚያሳይባቸው አጋጣሚዎች ናቸው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ተከቦ ይኖር ነበር ፡፡ ***"በመከራ ፣ በችግር ፣ በጭንቀት ፣ በመገረፍ በወኅኒ ፣ በሁከት ፣ በድካም ፣ እንቅልፍ በማጣት......"*** ነገር ግን እነዚህን ሁሉ የተጋፈጠበትን መንገድ ***በብዙ መጽናት*** ሲል ይገልጠዋል፡፡(2ኛ ቆሮ 6፦4-5) በእምነት መንፈስ ሆኖም እንዲህ ብሎ ነበር ፡፡***"...ስለዚህ አንታክትም ነገር ግን የውጭው ሰውነታችን ቢጠፋ እንኳን የውስጡ ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል፡፡"*** (2ኛ ቆሮ 4፦16) ያጋጠሙትን ችግሮች እና አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲገልጥም፤ ***"የማይታየውን እንጂ የሚታየውን ባንመለከት ቀላል የሆነ የጊዜው መከራችን የክብርን የዘላለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅ ያደርግልናል፡፡"*** (2ኛ ቆሮ 4፡17)

***እውነተኛ መረጋጋት ውጫዊ ሳይሆን የውስጥ ነው፡፡*** የዚህ ዓይነት መረጋጋት፤ በውስጥ ትዕግሥት የማጣት፣ የመረበሽ፣ የቁጣ እሳተ ገሞራ አምቆ በውጪ የሚታይ ሰላምና ጸጥታ አይደለም፡፡ በአንጻሩ የዚህ ዓይነት ሰው ውስጣዊ ሰላም የውጫዊው መረጋጋቱ ምንጭ ነው፡፡

በመንፈሳዊ ሕይወቱ የተረጋጋ ሰው ሌሎችን ወደ መልካምና የተረጋጋ ሕይወት ይመራል፡፡ ሌሎች በሰላምና በመረጋጋት እንዲኖሩ ያደርጋል፤ይንከባከባል፡፡ የወዳጆቹን ስሜት ለመጠበቅ እና ወደ ሰላማዊነት ለመምራት የሚጥር ኃላፊነት የሚሰማው ሰው ነው፡፡ ውስጣዊ ማንነቱ ሰላም ወዳድ ነው፡፡ ለእርሱ የሚፈልገውን ሰላም ለሌሎችም እንዲሆን ይፈልጋል፡፡

www.zeorthodox.org

ውስጣዊ ሰላም ያለው ሰው በሌሎች መውደቅ የሚደሰት አይደለም፤ በእርሱ መረጋጋት ለሌሎቹም የሰላም ምንጭ ይሆንላቸዋል፡፡ ከእርሱ ጋር ሆኑም አልሆኑም ሌሎቹን የሚያገኘው በሰላማዊ እና በተረጋጋ መንገድ ነው፡፡ በቁጣ የመጣበትንም በለዘበ አንደበት ይመልስለታል፡፡ (ምሳ.15፡1)

***የተረጋጋው ሰው ጠባይ ሰላማዊ ነው፡፡*** ከዕለት ወደ ዕለት ሳይለወጥ ጸንቶ የሚታይ እና በተግባር የሚገለጥ መረጋጋት አለው፡፡ በተፈጥሮው የተረጋጋ ሰው ወደ ጸጥታ ወደብ ለመድረስ ብዙ

አቅም አይጠይቀውም፡፡

በመንፈሳዊው ዓለም መረጋጋትን ለመያዝ በቅንነት በሚደረገው በእያንዳንዱ ትግል እና ጥረት መንፈሳዊ ጸጋ እና ዕውቀት ይገኛል፡፡ የተረጋጉ ሰዎች የተሰጣቸውን ጸጋ በአግባቡ ጠብቆ የማቆየት ሓላፊነት እና ፈተና አለባቸው፡፡ ከነዚህ በበለጠ ግን በመንፈሳዊው ልምምድ መረጋጋት ያገኙት በሒደቱ ይማራሉ፡፡ በእግዚአብሔር ርዳታ ከፍጹም ሁከት ወደ ፍጹም የመረጋጋት አርአያነት የሚደርሱም አሉ፡፡ ለዚህ ሙሴ ጸሊም(ኢትዮጵያዊው) ጥሩ ምሳሌያችን ነው፡፡ ተወልዶ ያደገው በተረጋጋ መንፈስ እና ሁኔታ አልነበረም፡፡ እንዲያውም የባሰ ክፉ እና ነፍሰ ገዳይም ነበር፡፡ ወደ ምንኩስና ሕይወት ሲገባ ግን ራሱን በመረጋጋት አነጸ ፣ ለሹመት ተጠርቶ አበው ሲፈትኑትና በማይገባ ቃል ሲቆጡት አልተበሳጨም፡፡ ራሱን እየወቀሰ ወጣ፤ ሲያስጠሩትም ሰብአዊ ክብሩን አልጎዳም ነበር፡፡

## ማጠቃለያ

በተፈጥሮዬ የተረጋጋሁ አይደለሁም በሚል ምክንያት በራሳችን ላይ ስንፍና እንዲሠለጥንብን ዕድል መስጠት አይገባም፡፡ ከአደግንበት ቤተሰብ እና ማኅበረሰብ ቁጣን፣ በቀላሉ የሚረበሽ መንፈስን እና አለመረጋጋትን ብንወርስም እንኳን በቅን ልቡና በሚደረግ መንፈሳዊ ጥረትና ልምምድ ራስን መለወጥ ይቻላል፡፡ በጠባዩ መረጋጋት የሌለው ሰው÷ራሱን በትዕግሥትና በማስተዋል በማሠልጠን መረጋጋትን ሊይዝ ይችላል÷ይህን መያዝ ግን ከባድ ሊሆንበት ይችላል፡፡ ሲወለድ የተያዙ መልካም ሰብእናዎች ሊጠፉ÷ሊበላሹም ይችላሉ፡፡ በተቃራኒውም ክፉ ሰብእናዎች ተለውጠው በመልካም እይታ፣ በመልካም ተግባር፣ እንዲተኩ በከፍተኛ ጥረት ስንታገለው እግዚአብሔር እውነተኛውን መሻታችንን አይቶ አዲስ ልብ ይሰጠናል÷የድንጋዩንም ልብ ያወጣልናል፤ የሥጋውን ልብ ይሰጠናል፡፡ (ሕዝ36÷26)

### ምን ተማርን ?

www.zeorthodox.org

እውነተኛ መረጋጋት የሚገለጠው በፈታኝ ሁኔታዎች ውስጥ በጽናት ሲያልፍ ነው፡፡ በምንፈተንበትም ወቅት ትዕግሥትና ማስተዋልን ገንዘብ እናድርግ፡፡

ይሄን በማድረግም እነ ቅዱስ ጳውሎስን እንመስላቸዋለን፡፡ እርሱም “እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ” ብሎአል፡፡ (ቆሮ 11÷1፡፡) ጌታችንን ወደ መምሰል ዓለምንና ጥፋትዋን ከመሆን መውጣት ማለት ነው፡፡

በልዩ ልዩ ለውጦች፣ በአጋጣሚ እና ባልተመቻቸ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ራስን ስሜታቸውን

ተቆጣጥረው ራሳቸውን ለማሸነፍ በሚያደርጉት ቀና ጥረት ሒደት ውስጥ በረከትን ያገኙበታል፡፡ በውጤቱም የተሻለውን ሰብእና ይቀዳጃሉ፡፡

## ማጠቃለያ፡-

መረጋጋት የመንፈሳዊ ሕይወት ዓምድ ነው፡፡ በመንፈሳዊ ተጋድሎ ጽናትን የሚያስታጥቅ እና በፈተናዎች ሁሉ የሚያበረታ እግዚአብሔር ከልብ የሆነ መሻታችንን እና ቀና ጥረታችን ባርኮ ለዚህ በመረጋጋት የተሞላ ሰላማዊ መንፈሳዊ ሕይወትና ማንነት ያበቃናል፡፡

## ተግባር፡-

የመረጋጋት ሕይወትን ገንዘብ ለማድረግ ዛሬውኑ ከልባችሁ ወስናችሁ ጥረት ጀምሩ፡፡

ለዚህም የቅዱስ ጳውሎስን፣ የሙሴ ጸሊምን እና የማርያም ግብጻዊትን ታሪክ በምሳሌነት አጥኑ፡፡

www.zeorthodox.org

# ዘመነ ጽጌ - የጌታና የእመቤታችን ስደት መታሰቢያ

# ስድስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-**የጌታችንንና የእመቤታችንን ስደት ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደምታስብ ማሳወቅ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-*"ሕፃኑን እና እናቱን ይዘህ ወደ ግብጽ ሽሽ፡፡"*** (ማቴ 2፣13)

**መግቢያ፡-**ቤተ ክርስቲያናችን በየዓመቱ ከመስከረም 26 - ኅዳር 6 ያለውን ወቅት ዘመነ ጽጌ ትለዋለች፡፡ /የአበባ ወራት ማለት ነው፡፡/ አበቦች በምድር ላይ የሚያብቡበት ወቅት ስለሆነ ይህ ስያሜ ተሰጥቶታል፡፡

በአርባው ቀናት ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እቅፍ እና ጀርባ ሆኖ፣ በዮሴፍ መሪነት ከምድረ እስራኤል ወደ ግብጽ መሰደዳቸው ይታሰባል፡፡

በዛሬው ትምህርታችን የስደቱን ታሪክ እና በቤተ ክርስቲያን ለስደቱ መታሰቢያ የሰየመችውን ወቅት ከሥርዓቱ ጋር እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

1. የስደቱ ምክንያት፡-

ጌታችን በተወለደ በሁለተኛው ዓመት ሰብአ ሰገል በኮከብ ተመርተው ***"የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው? ኮከብን በምሥራቅ አይተን ልንሰግድለት መጥተናልና እያሉ ከምሥራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መጡ፡፡"*** (ማቴ 2÷2) በዚህም ንጉሡ እና ኢየሩሳሌም ታወኩ፡፡ በወቅቱ በኢየሩሳሌም የነበረው ንጉሥም ሄሮድስ ይባላል፡፡ የካህናት አለቆችን፤ ክርስቶስ ወዴት እንደሚወለድ ጠይቆ፤ ሰብአ ሰገልን ጠርቶ ሲመለሱ መንገዳቸውን በእርሱ በኩል አድርገው፤ ‹‹እርሱም እንድሰግድለት ንገሩኝ›› አላቸው፡፡

እነርሱም ቤተልሔም ሄደው በበረት የተወለደውን ጌታችንን አግኝተውት ፣ ሰግደው ፣ ስጦታ

www.zeorthodox.org

አቅርበው ፣ ሲመለሱ ÷ በሕልም ሄሮድስ ሊገድለው እንደሚፈልገው በሕልማቸው ተገለጠላቸውና በሌላ መንገድ ሄዱ። ሄሮድስ የመግደል ሐሳቡ እንዳልተሳካለት ሲያውቅ ሁለት ዓመት የሞላቸውን ሕፃናት በሙሉ ሰብስቦ አስገደለ።

2. ስደትና መልስ፡-

በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ ለዮሴፍ በሕልም ታይቶ ሕፃኑን እና እናቱን ይዞ ፤ ወደ ግብጽ እንዲሸሽ ነገረው ። እስክነግርህም በዚያ ተቀመጥ አለው ። ሄሮድስም እስኪሞት ሦስት ዓመት ከስድስት ወር በዚያ ተቀመጡ። የበረሐው ሙቀት÷የውኃ ጥም እና የሄሮድስ ወታደሮች ክትትል ለሰብአዊ አእምሮ ከባድ ፈታናዎች ነበሩ። ነገር ግን ሄሮድስ ከነጥፋቱ ሞተ።

ሄሮድስ ከሞተ በኋላ፤ አሁንም የጌታ መልአክ በግብጽ ለዮሴፍ በሕልም ተገለጠለት። ‹‹የሕፃኑን ነፍስ የፈለጉት ሞተዋልና ተነሣ÷ሕፃኑንና እናቱን ይዘህ ወደ እስራኤል አገር ሂድ›› አለው። እርሱም የተባለውን አደረገ። በገሊላም መኖር ጀመሩ።

ሄሮድስ ከዚያ በኋላ አራት ዓመት ለማይኖርበት ሥልጣን ብዙ ሕፃናት ገደለ÷ የታየውም ምድራዊ ሥልጣኑን መቀማቱ ነበር። ክርስቶስ ግን ዘለዓለማዊና ሰማያዊ መንግሥት እንጂ ምድራዊ ንጉሥ አልነበረም ።

3. የስደቱ መታሰቢያ በቤተ ክርስቲያን፡-

በቤተ ክርስቲያን ይህ የስደት ወቅት በየዓመቱ ይታሰባል።

የስደቱ መታሰቢያ ወቅት በቅዱስ ያሬድ ዘመነ ጽጌ ይባላል ። ይህ ወቅት ከመስከረም 26 - ኅዳር 6 ቀን ሲሆን በምድር ላይ የሚገለጡት አበቦችን ለማመልከት የተሰጠው ስያሜ እና በዚህም ዘመናትን ለሚመግብ ጌታ ለእግዚአብሔር ምሥጋና የሚቀርብበት ነው። በዚህ ወቅት ማሕሌተ ጽጌ እና ሰቆቃወ ድንግል የተባሉ መጻሕፍት በዜማና በንባብ ይደረሳሉ።

**ማሕሌት** (ምስጋና ማለት ነው።) መዘምራን በቤተ ክርስቲያን በቀን እና በሌሊት ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት ምስጋና ነው ። በዘመነ ጽጌ የጌታችንን ስደት የሚያመለክቱ ዜማዎች ይቀርባሉ።

www.zeorthodox.org

**ማሕሌተ ጽጌ** በቁሙ የጽጌ ምስጋና ማለት ሲሆን የጌታችንን እና የእመቤታችንን ስደት አስመልክቶ በአባ ጽጌ ድንግል የተደረሰ በያሬድ ዜማ የሚቀርብ ምስጋና ነው።

**ሰቆቃወ ድንግል** (የድንግል ሐዘን ማለት ነው።) ይሄም በአባ ጽጌ ድንግል የተደረሰ ሲሆን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ልጅዋን ከሄሮድስ ወታደሮች እና ከበረሐ ወንበዴዎች ለማዳን

በስደቱ ወቅት ያሳለፈችውን መከራ በግጥም የሚያስታውስ መጽሐፍ ነው፡፡ በዚህ ወቅት በዜማ እና በንባብ ይደረሳል፡፡

በየሳምንቱ ቅዳሜ ሌሊት ለእሑድ አጥቢያ በየቤተ ክርስቲያኑ ማሕሌተ ጽጌ እና ሰቆቃወ ድንግል ይደረሳሉ፡፡

**ይህንን ወቅት ለመዘከር** ምእመናንም የወርኃ ጽጌን እሑዶች በየነፍስ አባቶቻቸው ተከፋፍልው አገልጋዬችን የሚያስተናግዱበት እና ችግረኞችን የሚመግቡበት ትውፊት አለ፡፡

**የፈቃድ ጾም፡-** በዚህ ወቅት የታወጀ ጾም የለም፡፡ ነገር ግን በገዳም ያሉ መነኮሳት እና መናንያን እንዲሁም አንዳንድ ምእመናን የጌታችንን እና የእመቤታችንን ስደት ለማሰብ በፈቃዳቸው ይጾማሉ፡፡

## ምን ተማርን ?

ዘመነ ጽጌ በቤተ ክርስቲያናችን ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእናቱ ከቅድስት ድንግል ማርያም እና ከቅዱሳን ጋር ወደ ግብጽ መሰደዱ የሚታሰብበት ወቅት ነው፡፡

በሀገራችን አበቦች ምድርን የሚሸፍኑበት ወቅት ስለሆነ ፤ ቅዱስ ያሬድ ይህንን ወቅት ዘመነ ጽጌ(የአበባ ወቅት) ብሎ ሰይሞታል ፡፡

በዚህ ወቅት ስደታችንን ለካሰ ጌታ ምስጋና ሲቀርብ አዝላው ለተሰደደች እናቱ እና ለእርሱም ስደት በማሕሌት ፣ በተዝካር …..በመሳሰሉት መታሰቢያ ይደረጋል፡፡

# ተግባር

እንደ ቤተ ክርስቲያን እናንተም የአምላካችሁን ውለታ አትርሱ፡፡

ከቤተሰብ ጋር ማሕሌተ ጽጌን ተሳተፉ ፡፡

***መዝሙር*** www.zeorthodox.org

ማርያም ኅየይኪ እም ገጸ ሄሮድስ

ለአርእዮ(2)ተአምረ ግፍዕ

# መጽሐፈ ሩት(1)

## ሰባተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ**፡-ከመጽሐፈ ሩት መንፈሳዊ እድገትን መማር፡፡

**የሚጠና ጥቅስ**፡- ***" ሕዝብሽ ሕዝቤ አምላክሽ አምላኬ ይሆናል፡፡"*** (ሩት 1፡17)

**ተጨማሪ ምንባብ**፡-መጽሐፈ ሩት፤ ምዕራፍ 1 በሙሉ፡፡

**መግቢያ፡-** መጽሐፈ ሩት ከአሕዛብ ወገን በሆነች ሴት ስም የተሰየመ መጽሐፍ ነው፡፡ ሩት ቃልዋንም አክባሪ፣ እግዚአብሔርንም የፈልገች ሴት ናት፡፡ እግዚአብሔርም እውነተኛ መሻቷን አይቶ አከበራት፤ ከእምነት እናቶች አብነት በመሆን ከክርስቶስ ትውልድ በመቆጠርም የተስፋው ዘር ሆነች የሩት ታሪክ መልካም አርአያነት ያለው ታላቅ ትምህርት ይሰጠናል፡፡

የሁሉም ትውልድ ታሪክ በሆነው በመጽሐፈ ሩት ሁለት ታላላቅ እናቶችን እናገኛለን፡-

### ኑኃሚን እና ሩት

**ኑኃሚን** እንደማንኛውም አይሁዳዊት ሴት ከሕግና ከነቢያት በረከቶች ተሳታፊ ሆና የኖረች ናት፡፡ ቀደምት የእምነት አባቶቿ ከአምላካቸው ጋር ያደረጉትን ቃል ኪዳንና በመሲሑ የሚመጣውንም ፍጹም የሆነ የነፍስ ድኅነት ሰምታለች፡፡

ነገር ግን ክፉ ቀን በመጣ ጊዜ ከይሁዳ ቤተልሔም ወደ ሞዓብ ተሰደደች፡፡ ስደቷ ከይሁዳ ነገድ ከተገኘው ከክርስቶስ ርቆ እንደመሔድ ያለ ትርጓሜን ይሰጣል፡፡

ይህም ማለት አንዲት ነፍስ የአምላኳን ረድኤት ቀምሳ፤ ነገር ግን በመከራና ችግር ጊዜ በእምነቷ ከመጽናት ይልቅ አምላኳን ከድታ ወደ ዓለም በመግባት በዚያ ለመጠለል እንደተሰደደች የሚያሳይ ታሪክ ነው፡፡

www.zeorthodox.org

**ሩት** በአንጻሩ ያደገችው በኢ-አማኒው አባቷ ቤት በሞዓብ ነው፡፡ እውነተኛ አምላክ መኖሩን ሰምታና በእምነት ወደ ቤተልሔም አቅንታ ሰው የሆነውን ክርስቶስን በመንፈስ በማግኘት እርካታና ዕረፍት ስታገኝ እናያለን፡፡ክርስቶስ ለብዙዎች መነሣትና መውደቅ ተገለጠ (ሉቃ.4፡34) መጽሐፈ ሩትም የኑኃሚን ከአምላክ እምነት መሰናከል፤ለሩት መነሣት እንደሆነ ያሳየናል፡፡

በተከታታይ ሳምንታት በታሪኩ ውስጥ ባለው መንፈሳዊ ትርጉትም ላይ አተኩረን እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

### ስለ መጽሐፈ ሩት፡-

1.1 **መቼ ተጻፈ?** ፡- ይህ መጽሐፍ በነቢዩ ሳሙኤል በንጉሥ ዳዊት ዘመን የተጻፈ ነው። ታሪኩ የተፈጸመውም በዘመነ መሳፍንት (ሩት 1፡1)ነው።በጌዴዎን የመሪነት ጊዜ መሆኑም በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ይገመታል።

1.2 **ዓላማ** ፡-የእውነተኛን ፍቅር እና መታመን ኃይል ሲገልጥ ሕዝብ እና አሕዛብን አንድ ስላደረገው ክርስቶስ ቀድሞ የተሰጠ ትንቢታዊ ምሳሌም ነው።

1.3 የመጽሐፈ - ሩት ጠቀሜታና ውክልና

በምርትና ድግስ /ደስታ/ ጊዜ ተዘውትሮ ይነበብ የነበረው ይህ መጽሐፍ፤ በዚህ ወቅት የሚነበብበትን መነሻ ያገኘው፤ በመጽሐፉ ውስጥ በዋናነት የተጠቀሰችው ሩት አጫጆች ሰብል ሲሰበስቡ የሚተርፈውን ቃርሚያ ቀጥላ ትቃርም እንደነበር በማሰብ ነው። ይህ የመኸር መጽሐፍ በአንዲት አረማዊት ሴት ትጋት የአይሁዳዊት አማችዋ ቤት ባዶነት ሲሞላ በዚህም በረከት ሲጠግቡ እናያለን። የዚህች ሴት እምነት እና ትጋት አዲስ መንፈሳዊ ጎብስት የመገኘቱን ዜናም አብሣሪ ነው። ይህም አማናዊውን ኅብስት ክርስቶስን በቀጣይ የትውልድ ሐረጓ ማስገኘቷንና ከዚህም የደስታ ሰብል የአማንያንን ርኃብ ማርካቷን የሚገልጽ ነው።

በክርስቶስ የዘር ግንድ ውስጥ በሐዲስ ኪዳን (ማቴ.1፡5) በስም የተጠቀሰችው ሩት ከሌሎች ብዙዎች በላይ ከመሆኗ የተነሣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በስሟ መጽሐፍ ተሠይሞ የተጻፈላት እስራኤላዊት ያልሆነች ብቸኛዋ ሴት ናት።

ከቦዔዝ ጋር በምታደርገው ጋብቻም፤ የሰው ነፍስ ከእውነተኛው ሙሽራዋ ከክርስቶስ ጋር የሚኖራትን አንድነት በማሳየት የእውነተኛው መዳን ምስጢር የተገለጠበት ነው። ዋርሳ ዘመድና ወገን ተብለው በመጽሐፉ የተገለጹት አገላለጾች ትርጉም የሰው ዘርና የክርስቶስን ዝምድና የሚወክሉ ናቸው።

www.zoorthodox.org

መጽሐፈ ሩት የአይሁዳውያንን ልማድና ሥርዓት የሚያሳዩ ድርጊቶችን የያዘ ሲሆን፤ መጻዒውን የእምነት ሕይወት ሥርዓትና ባሕርይ፡- በኑኃሚንና በሩት፣ በቦዔዝና በሩት፣ በመስክ ሠራተኞችና በቦዔዝ መካከል በተደረጉ ቃለ ምልልሶች ውስጥ ያሳየናል።

ሩትም በእምነት እና በፍቅር ክርስቶስን የተከተሉትን እውነተኞቹን ክርስቲያኖች የምትወክል ሕያው ምሳሌ ሆና ቀርባለች፡፡ቦዔዝ ኃይልና ብርታት ማለት ሲሆን  እርሱም ባለሰፊ ማሳ (እርሻ) ነው፡፡ ***" እነሆም ቦዔዝ ከቤተልሔም መጣ "*** (ሩት 2፡4) ተብሎ የተጻፈለት ደግ ባለ ጸጋም ነበር፡፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነበር፡፡

## የመጽሐፈ - ሩት አከፋፈል

ራብ በቤተልሔም ስደት ወደ ሞዓብ (ሩት 1) (ዓለሙና ባዶ መሆን)

እውነተኛው ደስታ እና ቦታው (ሩት 2-4) (በክርስቶስ ያለው የነፍስ እርካታ)

ሀ. ሩት በቦዔዝ እርሻ ውስጥ (ሩት 2)

ለ. ሩት ከቦዔዝ ግርጌ (ሩት 3)

ሐ. ሩትና ሰርግ (ሰማያዊው በዓል) (ሩት 4)

**የመጽሐፉ ይዘት እና መንፈሳዊ ምሳሌዎቹ፡፡**

**2.1 ምዕራፍ  አንድ - ዓለሙና ባዶ መሆን**

**ሀ. የታሪኩ መነሻ በአጭሩ**

በይሁዳ ቤተ ልሔም የነበረው አቤሜሌክ ራብ በሆነ ጊዜ ከቤተሰቡ ጋር ወደ ሞዓብ ተሰደደ፡፡

ነገር ግን የራሱንና የቤተሰቡን ሕይወት ለማትረፍ የተሰደደባት ሞዓብ ለጊዜው ራቡን ብታስታግስለትም መጀመሪያ ራሱን በኋላም የልጆችን ሕይወት ነጠቀችው፡፡ ደጓ ሴት ኑኃሚንም ከሞዓባውያን ምራቶችዋ ጋር ብቻዋን ቀረች፡፡

የተስፋ ድምፅ ከእንጀራ ቤት... ***"እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደጐበኘ እንጀራም እንደሰጣቸው"*** ተሰማ፡፡ ሁሉን ካጡ በኋላ የተሰማ ተስፋ ነው ፡፡ ጉዞ ወደ ቤተልሔም ሲደረግ ፥ ምራቶችዋ ኑኃሚንን ተከተሉ፥ መርቃ ብታሰናብታቸውም አብረው ለመሄድ ተነሡ፡፡

www.zoorthodox.org

ሩት ወደ ኑኃሚን ተጠግታ ቤተልሔምን ስትመርጥ ዖርፋ ወደ ሞዓብ ተመለሰች፡፡ ጉዞ ወደ ቤተልሔም ሆኖ ደጉዋ ሩት ስትገባ ቤተልሔም ተንጫጫ፡፡ ሐዘኑ ከባድ ነውና ***ማራ*** በሉኝ ኑኃሚን አትበሉኝ አለች፡፡

**ለ. መንፈሳዊው ትርጉም፡-**

ቅዱስ ጳውሎስ ስለመንፈሳዊው ትርጓሜ ሲያስተምረን፥ ***" መንፈሳዊውን ነገር ከመንፈሳዊው***

*ነገር ጋር አስተያይተን መንፈስ በሚያስተምረን ቃል ይህን ደግሞ እንናገራለን "* 1ኛ ቆሮ.2፡13 እንዳለ ከዚህ የመጽሐፈ ሩትን መንፈሳዊ ታሪክ እንማራለን፡፡

አቤሜሌክ በረኃብ ምክንያት ሚስቱን ኑኃሚንና ሁለቱን ወንድ ልጆቹን መሐሎንና ኬሌዎንን ይዞ ከቤተልሔም ወደ ሞዓብ ሄደ፡፡ ይህ ማለት፤ አንድ ነፍስ ክርስቶስን በመከተል ክርስቲያን መሆን ፤ ውጤቱ ሥቃይና መከራ መሆኑን አስቦ ከቤተ ክርስቲያን መጥፋትን ያሳያል፡፡ አቤሜሌክ ከባለቤቱ ጋር መሄዱ ሥጋዊ ሕይወቱን ይወክላል፡፡ ሁለቱ ወንድ ልጆቹም ብርታትና ተሰጥዖውን ያመለክታሉ፡፡

አቤሜሌክ የተሰደደበት ዓለም ፍላጎቱን ሁሉ አጎናጽፎ፣ ሰብእናውን ምሉዕ የሚያደርግለት፣ ብርታትና ተሰጥዖውንም የሚያሳድግለት ይምሰለው እንጂ፤ በውጤቱ ያለውን ሁሉ አሳጥቶት በፍጻሜውም ሕይወቱን ጭምር ነጥቆታል ፡፡ምንም እንኳን አቤሜሌክ የሚለው ስም ***‹‹አምላኬ ንጉሤ››*** የሚል ትርጉም የሚሰጥ ቢሆንም፤አቤሜሌክ ግን በልቡ አምላኩን ስላላነገሠው ከሞዓባዊው ምድራዊ ንጉሥ በታች ሊጠለል ኮበለለ፡፡ አምላኬ ንጉሤ የሚለውን የስሙን ኃይል ባለመደገፉም እርሱና ከአብራኩ የተገኙት ፍሬዎች ለጥፋትና መከራ ሆኑበት፡፡

አቤሜሌክና ቤተሰቡ ከርስታቸው ተነቅለው በባዕድ ምድር መጻተኞች ሆኑ፡፡ ከሌሎች ከማያምኑ ሕዝቦች ጋር የጋብቻ ኅብረት ሲፈጥሩ የሚደርስባቸውን ውርደትና ጥፋት እግዚአብሔር በሕግ አስጠነቀቃቸው (ዘዳ.7፡3-4) በማስጠንቀቂያው በቃሉ መሠረት ኑኃሚን ባለቤቷን አጣች፡፡ ልጆቿም ሞዓባውያኑን አገቡ፤ ቀጥሎም ሁለቱም ልጆቿም ያለወራሽ ሞቱ፡፡

ከዚያ በኂላ ያለው የኑኃሚን ሐዘን፣ በስሜት መራር መሆንና ባዶነት፤ እንዲሁም ደግሞ ወደ ይሁዳ ቤተልሔም የመመለስ ፍላጎት፤ ሰዎች ከእውነት አምባ ሸሽተው ከቆዩ በኂላ ከልብ ተፀፅተው እውነተኛ በሆነ ንስሐ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚያደርጉትን መመለስ ያመለክታል፡፡

ሩት ኑኃሚንን በመከተል በምታሳየው ቁርጠኝነት፤ በነጻ ምርጫው ከካራን ወደ ከንዓን አምላኩን በመፈለግ የወጣውን የአብርሃምን እምነት በልቧ መያዟን ያመለክታል፡፡ በዚህም ሩት ከሞዓብ ወደ ከነዓን በመምጣት እውነተኛውን አምላክ በማምለክ እግዚአብሔር ለአሕዛብ ያሰበውን ጸጋ የምትወክል እና የምትቀበል የመጀመሪያዋ ምልክት ሆነች፡፡

www.zoorthodox.org

## ምን ተማርን ?

የአቤሜሌክን ቤተሰብ ታሪክ ፡፡ ከበረከት ቦታ ወደ ሞት ቦታ መሰደድን ያመለክታል፡፡ ለእኛም በፈተና ውስጥ በእግዚአብሔር ቤት መጽናትን ያስተምረናል፡፡

ሩት በቃል መታመንን እና በቆራጥ ልብ ወደ እግዚአብሔር መቅረብን ታስተምረናለች፡፡

**ተግባር፡-** በመከራ ጊዜ እግዚአብሔርን ተስፋ አድርጉ፣ ለቃላችሁ ታማኝ ሁኑ፣ በእውነተኛ ፍቅር እግዚአብሔርን ለመከተል የቆረጠ ልብ ይኑረን፡፡

www.zeorthodox.org

# መጽሐፈ ሩት(2)

## ስምንተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-**ከመጽሐፈ ሩት መንፈሳዊ እድገትን መማር።

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***" በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።"*** (2ኛ ቆሮ 2፡14)

**ተጨማሪ ምንባብ፡-**መጽሐፈ ሩት ምዕራፍ 2 እና 3 በሙሉ።

**መግቢያ፡-**ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን ስለመጽሐፈ ሩት አጠቃላይ መግቢያ እና ሩት በቦዔዝ እርሻ መቃረምዋን ተመልከተናል።በዛሬው ትምህርታችንም ቀጣዩን ክፍል እንማራለን።

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

### በእምነት እና በተስፋ መሰማራት፡-

ሩት ኑኃሚንን ተከትላ ወደ ቤተልሔም መምጣቷ፤ ከቦዔዝ እርሻ ውስጥ ሰብል መቃረሟ ፤ አሕዛብ በክርስቶስ አምነው በቤተ ክርስቲያን ተሰብስበው ለድኅነት መጠራታቸውን የሚያመለክት ነው።

በታሪኩ እንደተገለጸው ሩት የሕግ ምሳሌ በሆነችው ኑኃሚን ታምና በዚያ ብቻ አላበቃችም። በቤተ ክርስቲያን ከሁሉ የሚልቀውን፤ አባቶችና ነቢያትም ወደ መሰከሩለት ወደ ክርስቶስ ደርሳለች።

ሩት በቦዔዝ መስክ ተሰማርታለች፣ ቃርማለችም ። ምእመናንም በአማናዊው ቦዔዝ ክርስቶስ ማሳ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመኖር ቅዱስ ሥጋውን በልተው ክቡር ደሙንም ጠጥተው የዘላለም ሕይወት ያገኛሉ።

www.zoorthodox.org

### ሩት በቦዔዝ እርሻ ውስጥ

ሩት ቤተልሔም እንደገባች ያገኘችው ዘመዷ የሆነውን ቦዔዝን ነው። እኛም የቤተክርስትያን አባል ስንሆን የምናገኘው አዳኝ የሆነውን ክርስቶስን ነው።

ቦዔዝ ኃይልና ብርታት ማለት እንደሆነ ሁሉ ክርስቶስም ኃይልና ብርታታችን ነው። እርሱ

ከሲዖል ውርደት ያነሣን ነውና። በክርስቶስ ኢየሱስ አሸናፊዎች ሆነናል እንደተባለ።(2ኛ ቆሮ 2:14)

ሩት የአማቷን ፈቃድ በመጠየቅ ወደ ቦዔዝ እርሻ ዘልቃ ከአጫጆቹ በኋላ ለመቃረም ስትተጋ፤ በአንጻሩ የሕግ ተምሳሌት የሆነችው ኑኃሚን በቤቷ ተወስና መቅረቷ አይሁድ ክርስቶስን ለመቀበል ያሳዩትን እንቢተኛነት ይወክላል።

ሩት በእርሻው ላይ ተገኝታ ገበሬዎቹ የተውትን በምትቃርምበት ወቅት ቦዔዝ ***‹‹ይህቺ ወጣት ሴት ማናት››*** በማለት ሲጠይቅ፤ ይህቺ ሴት ከአሕዛብ የሆነች የትዳር አጋር የሌላት ናት ፤ የሚል መልስ ተሰጥቶታል። በዚህም ሁሉም ሕዝቦች ሕያው ሙሽራቸውን ክርስቶስን ከመጠባበቃቸው እውነት ጋር ይዛመዳል።

ቦዔዝ በማሳው ላይ ከተገኘችው ሩት ጋር በተነጋገረበት ጊዜ የሚከተሉት ነጥቦች ተጠቅሰዋል፦

ሀ. የባዕድ ሃገሯን ሴት **ልጄ** ብሎ መጥራቱ ፦ ጠላቶቹ ሳለን የልጅነት ሥልጣን ሰጥቶን የእግዚአብሔር ልጆች የመሆናችን ምሳሌ ነው።

ለ. ከገዛ ራሱና ከቤተሰቦቹ ጋር አብራ እንድትሆን መፍቀዱ ፦ ጌታችን ወዳጆቹ እንዳደረገን የተነገረ ትንቢት ነበር።

ሐ. ርስቱን እንደ ራሷ አድርጋ እንድትመለከተው መፍቀዱ ፦ የመንግሥቱ ወራሾች እንዳደረገን ያመለክታል።

መ. ከፅዋው እድትጎነጭ መፍቀዱ ፤ምእመናን በቤተክርስቲያን ከመንፈስ ቅዱስ ጸጋ እንደሚጠጡ ምልክት ነበር።

ሩት ለቦዔዝ ምስጋናዋን የገለጸችበት መንገድ እግዚአብሔር በነጻ ለሰጠን ጸጋ የምንመልሰው ምስጋና ነው።

ቦዔዝ ሩትን ከማዕዱ እንድትካፈል የመጋበዙ ምስጢርም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የቀረበልንን የቅዱስ ቁርባን አንድነት የሚየሳይ ነው። በመጽሐፉ የተደረጉት ቃለ ምልልሶች የክርስቶስን ፍቅርና ስጦታዎች የሚገልጹና የሩትን ትሕትናና ምስጋና የሚያሳዩ ናቸው። ሩትም የሰበሰበችው ሰብል የሥጋን ረሃብ የሚያስታግሰውን እህል ብቻም ሳይሆን መንፈስንም የሚያጠግበውን ፍሬ ጭምር አማናዊውን ቦዔዝንም ነው።

www.zeorthodox.org

***ሩት ከቦዔዝ ግርጌ፦***

ኑኃሚን ሩት ከቦዔዝ ወለል ሥር እንድትሆንና ቦዔዝን በመኝታ ጊዜው እንድታገኘው ምክር ተሰጥቷታል፡፡ ይህም ለጥቂት ጊዜያት ያለባል የኖረችው ሩት ቦዔዝ ዋርሳዋ ይሆን ዘንድ እንድትጠይቀው ረድቷታል፡፡ የኑኃሚን ምክር ሩት ከቦዔዝ ጋር ያደረገችውን ሁነኛ አንድነት በሚከተሉት መገለጫዎች ገሀድ እንዲሆን አስችሏል፡፡

ሩት ታጠበች፤ ተቀባች፤ ለበሰች፤ ቀረበች፤ ብቻውን እስኪሆን ጠበቀችው፤ ሩት እነዚህን አድርጋ በቦዔዝ ተመሰገነች፡፡ይህም የጥምቀት፣የሜሮን፣ጸጋ ማግኘት፣ወደ እግዚአብሔር መቅረብ፣ነገረ መለኮትን መረዳት፣እና ጻድቃን እስከሞት አምላካቸውን መከተላቸውን ያሳያል፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ሩት አማትዋን ኑኃሚንን ለመመገብ ከቦዔዝ እርሻ ማሳ ቃርሚያ ለመቃረም ሄደች፡፡ በደግነትዋም የበለጠ ሰበሰበች፡፡

ኑኃሚን በመከረቻት መንገድ ሄደች፤ቃል ተገብቶላትም ተመለሰች፡፡መልካም ምክር መልካም ቦታ ያደርሳል፡፡

ቤተ ክርስቲያንም የእውነት ቤት ስለሆነች ጌታችንን በእውነት ትከተላለች ፤ ምስጢራቱንም ትፈጽማለች፡፡

## ተግባር፡-

በቤተ ክርስቲያን ልጅነታችን የተፈጸሙልንን ምስጢራት በትክክል እየፈጸምን በአግባቡ ልንኖርበት ይገባል፡፡

ወዳጆቻችንን ይልቁንም በቤት ያሉትን አረጋውያን ልናግዛቸው ልንደግፋቸው ይገባል፡፡ ምክራቸውንም መስማት አለብን፡፡

www.zeorthodox.org

# መጽሐፈ ሩት(3)

## ዘጠነኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፦**ከመጽሐፈ ሩት የጀመርነውን ትምህርት በመቀጠል ስለ በጉ ሰርግ ማስገንዘብ፡፡

***የሚጠና ጥቅስ፦" ወደዚህ ና የበጉንም ሚስት ሙሽራይቱን አሳይሃለሁ አለኝ፡፡"*** (ራእ.21፡9)

**መግቢያ፦** ያለፈውን ትምህርት በመከለስ፤ የመጽሐፈ ሩትን ሦስተኛና የመጨረሻ ክፍል መማር፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፦

***የቦዔዝና የሩት መገናኘት፦***

በመጽሐፉ በምዕ.3፡6-13 በተገለጸው የቦዔዝና የሩት መገናኘት ታሪክ ውስጥ፤ ቦኤዝ የሩትን ጥበብና ፍቅር እስኪያመሰግናት እና እስኪባርክ ድረስ መደነቁን እንመለከታለን፡፡ ከቍጥር 14-18 በተገለጸው ታሪክ ውስጥም ሩት ወደ ቤት ተመልሳ በጥረት ሳይሆን በቦዔዝ ችሮታ በእጥፍ ባገኘችው ፍሬ ኑኃሚን ተገርማለች፡፡

ከክርስቶስ ጋር ዕለት ዕለት በምናደርገው ግንኙነት ሕይወታችን በሚደነቅ ጸጋ እየተሞላች፤ በክብር ላይ ክብር፤ በበረከት ላይ በረከት እንደምትጎናጸፍ የሚያሳይ ምሳሌ ነው፡፡

***ሩትና ሰማያዊው በዓል (ሰርግ)***

በመጽሐፈ ሩት አራተኛው ምዕራፍ ውስጥ ቦዔዝ በከተማው በር አደባባይ ወጥቶ በመቀመጥ የጠራቸው ዐሥር ሽማግሌዎች ዐሥርቱን ትእዛዛት ይወክላሉ፡፡ እነርሱም የሰው ነፍስ ምሳሌ ለሆነችው ሩት ከቀደመው የአረማዊነት ሥርዓት የሚቤዧት ናቸው፡፡

www.zeorthodox.org

ቦዔዝም ከአቤሜሌክ ርስት ይልቅ ራሷን ሩትን መርጦ በማዳን አግብቷት በጠፋው ዘር ምትክ ልጆችን ሊወልድላት በመቻሉ እርሱንና ቤቱን ባረከው ፡፡

ሩትም ከቦዔዝ የወለደችው የእምነት ልጇ ኢዮቤድ ከሁሉ የሚበልጠው የክርስቶስ ምሳሌ ነው፡፡ ኑኃሚን በኢዮቤድ መደሰቷም በመሲሑ ሕግ ነቢያት መደሰታቸውን ያመክለታል፡፡

መጽሐፈ ሩት አቤሜሌክን ከነቤተሰቡ ለስደት ባደረገው ረኃብ ይጀምራል፡፡ ሩት በልጅ

ተባርካለች በዚህ አማካኝነት ዓለም ሁሉ እውነተኛ ድኅነት የሚያገኝበትና የሰው ዘር ሁሉ ምኞት የሆነውን የዳዊት ልጅ አማናዊው ኢዮቤድ የኢየሱስ ክርስቶስን መምጣት በማብሰር ይፈጸማል፡፡

ይህም ***" ወደዚህ ና የበጉንም (የክርስቶስን) ሚስት ሙሽራይቱን (ቤተ ክርስቲያንን) አሳይሃለሁ አለኝ"*** (ራእ.21፡9) የተባለላት የቤተ ክርስቲያን ሰማያዊ ደስታን ያመለክተናል፡፡

በሕግ የተመሰለችው ኑኃሚንም ሩትን ወደ ቦዔዝ ዘንድ የመራቻት ከአዝመራው እንዲለግሳት ብቻ ሳይሆን ራሱን ቦዔዝን አግኝታ ከጻድቃን ማኅበር አንድ እንድትሆንም ነበር፡፡ ከዚያም እውን የሆነውን ሰማያዊ ድግስ እንድትካፈልም ጭምር ነው፡፡ አሪት አማኞችን ወደ ቤተ ክርስቲያን መምራትም ጭምር እንጂ በአምላክ የሚገኘውን የሥጋ በረከት በመፈለግ ብቻ የተወሰነች አይደለችም፡፡ ከሰማያዊው ርስት እንድንካፈልም የተሰጠችን ናት፡፡

## ማጠቃለያ፡-

### *የመጽሐፈ-ሩት አጭር ቅኝት፡-*

ነቢዩ ሳሙኤል ስለአንዲት ከአይሁድ ወገን ያይደለች ነገር ግን እስራኤላዊን ስላገባች ወጣት ዘግቦልናል፡፡ እርሷ ባልተለመደ ሁኔታ የባሏን እናት አማትዋን በመውደድ ከእግዚአብሔርና ከአማቷ ሕዝቦች ጋር የጠበቀ ትስስር አድርጋለች፡፡ይህ የሆነው በእስራኤል መሳፍንቶች ዘመን መሆኑ ይበልጡንም የተጠቀሰው ረኃብ በጌዲዎን የመሪነት ዘመን ነው፡፡ (መሳ 6፡1-16፡11)

**ጠቀሜታው፡-**

ሩት ሴቶች ከወንዶችም በላቀ ሁኔታ ታላላቅ ሥራዎችን ለመሥራታቸው አንድ ማሳያ ናት፡፡ በመሪነትና በወታደራዊ ሚና ንጉሥን ያንበረከከችው ነቢይቱ ዲቦራ፣ ሕዝቦቿን ያዳነችው አስቴርና እንዲሁ ያደረገችው ዮዲት ተጨማሪ ምሳሌዎች ናቸው፡፡

ሩት ከአይሁድ ወገን አለመሆኗ ሳያግዳት በእግዚአብሔር ቤት ሥራ ውስጥ ድርሻ ለመውሰድ በቅታለች፡፡ ሁሉም የእስራኤል ሴቶች እንዲሆንላቸው የተመኙትን በዘር ግንዷ በኩል መሲሑ መጥቷል፡፡

www.zeorthodox.org

እርሷ በሌላ ወገን (እስራኤላዊ ባልሆነው) ዘንድ ለተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን ምልክት ሆናለች፡፡ እግዚአብሔር ከሌሎች ሕዝቦችም ጭምር የተመረጡ ወገኞት እንዳሉት ለማሳወቅ ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ በክርስቶስ የትውልድ ሐረግ ዝርዝር ውስጥ ስሟን በሚገባ አስፍሮታል፡፡

## ተግባር

ቅዱስ ቁርባንን በመቀበል ከክርስቶስ ጋር ያለንን አንድነት እንግለጥ፡፡

# አቡነ መድኃኒነ እግዚእ

## ዐሥረኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የቅዱሳን አባቶቻችንን ሕይወት እና ታሪክ በትምህርትነቱ በመውሰድ አርአያቸውን እንድንከተላቸው እና በረከታቸውን እንድንቀበል ማበረታታት፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***" ዓለም አልተገባቸውምና በምድረ በዳና በተራራ ፤ በዋሻና በምድር ጕድጓድ ተቅበዘበዙ፡፡"*** (ዕብ.11፡38)

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** የኅዳር 3 ስንክሳር፣

### መግቢያ፡-

በዐሥራ ሦስተኛው እና በዐሥራ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ በተለያዩ አቅጣጫዎች የተነሡ አበው ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋት በብዙ ደክመዋል፡፡የአቡነ ኢየሱስ ሞዐ የሐይቅ ገዳምና ትምህርት ቤት፣የአቡነ ተክለ ሃይማኖት እና ተከታዮቻቸው ሐዋርያዊ ጉዞ እና ገዳማትን ማስፋፋት ፣ የአቡነ መድኃኒነ እግዚእ ገዳማዊ ሕይወትን ማጠናከር እና ሐዋርያዊ አገልግሎት ይጠቀሳሉ፡፡ በዛሬው ትምህርታችን የአቡነ መድኃኒነ እግዚእን ተጋድሎና ሐዋርያዊ አገልግሎት እንማራለን፡፡ የቅዱሳን አምላክ በጸሎታቸው ይርዳን አሜን!!

### የሳምንቱ ትምህርት፡-

**የቅዱሱ ትውልድ እና እድገት፡-** በኤርትራ አካለ ጉዛይ ከአባታቸው ከቀሲስ ሰንበተ ተስፋ እና ከእናታቸው ኂሩተ ማርያም የተወለዱት መድኃኒነ እግዚእ ፣ ከቤተሰባቸው የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት እየተማሩ እና እያገለገሉ አደጉ፡፡ ቤተሰቦቻቸው ሲያርፉም ጉና በተባለ የቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ቤተክርስቲያን በምናኔ እና በትምህርት ኖሩ ፡፡

www.zeorthodox.org

**ምንኵስና፡-** በደብረዳሞ ከአቡነ ዮሐኒ የምንኩስና የመጨረሻውን መዓርግ አስኬማ የተቀበሉት አቡነ ተክለ ሃይማኖት፤ አቡነ መድኃኒነ እግዚእ ካሉበት ገዳም ለማገልገል ሲሄዱ አግኝተው አመነኮሷቸው፡፡

***ገዳማዊ ኑሮና ሐዋርያዊ አግልግሎት፡-*** ከምንኵስና በኋላም ከአክሱም ሠላሳ ኪሎ ሜትር ርቀት በምትገኘው ደብረ በንኮል በብህትውና መኖር ጀመሩ፡፡ በዚያም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ጠይቀው የደብረ በንኮልን ገዳም መሠረቱ፡፡ በእመቤታችን ስም በኖራና በድንጋይ ቤተ ክርስቲያን ሠሩ፡፡ ከዚያም ብዙ ደቀመዛሙርት እየተሰባሰቡ እና እየበዙ መጡ፤ ቍጥራቸውም ሰባት መቶ ደረሰ፡፡

አርድእትን ማስተማር የተጠመዱበት ዋነኛው ሥራ ሆነ፡፡ ከእነዚህም ዐሥራ ሁለቱን መርጠው ለሐዋርያዊ ተልእኮ አዘጋጁ፤ ሰባቱ ከዋክብት የሚባሉትን አቡነ ሳሙኤል ዘቍየጻ፣ አቡነ ሳሙኤል ዘጣሬጣ፣ አቡነ ያሳይ ዘመንዳባ፣ አቡነ ሳሙኤል ዘዋልድባ፣ አቡነ ዮሐንስ ዘጉራንቋ፣ አቡነ ታዴዎስ ዘባልተዋር እና አቡነ ያፍቅረነ እግዚእ ዘጉጉቤን በጣና ሐይቅ ዙርያና በጐንደር አሰማሩ፡፡

ከዚያም አምስቱ ከዋክብት የሚባሉትን አቡነ አሮን ዘክቱር፣ አቡነ መርቆሬዎስ ዘዶባ፣ አቡነ ዘካርያስ ዘኬፋ፣ አቡነ ገብረ ክርስቶስ አቡነ ዳንኤል ዘጸዐዳን በወሎ፣ በትግራይ እና ኤርትራ እንዲያስተምሩ አሰማሩ፡፡ የተላኩት ደቀ መዛሙርትም ሕዝቡን አስተምረው ያላመነውን አሳምነው ሲያጠምቁ ፤ ያመነውን በመንፈሳዊ ትምህርት አሳደጉ፡፡ ጌታችን እያስተማረ ወደ ተራራ ወጥቶ ይጸልይ እንደነበረው፤ ዮሐ.6÷15 አበው በየተራራዎቹ የጾም የጸሎት ቦታ ነበራቸው፡፡ እነዚያም ፍለጋቸውን በተከተሉት ምእምናን የተሞሉ ገዳማት ሆኑ፡፡

ዛሬ የምናውቃቸው የዋልድባ፣ ደብረ ቆዬ በዚያን ዘመን የተገደሙ ናቸው፡፡ አቡነ መድኃኒነ እግዚእ በገዳማዊ ሕይወታቸው ለገዳማውያኑ እና ለሌላውም የጽድቅ ምልክት ሆነው አገልግለው በመቶ ሰማንያ ዓመታቸው ኅዳር 3 ቀን ዐርፈዋል፡፡ በረከታቸው ይደርብን አሜን፡፡

## ምን ተማርን?

ቅዱስ ጳውሎስ የራሱን የድንግልና ሕይወት መሠረት አድርጎ ሲያስተምር ፡-" ***ሰው ሁሉ እንደ እኔ ሊሆን እወዳለሁና፤ ነገር ግን እያንዳንዱ ከእግዚአብሔር ለራሱ የጸና ስጦታ አለው፣ አንዱ እንደዚህ /በድንግልና/ ሁለተኛው እንደዚያ፡፡ /በጋብቻ/"*** 1ኛ ቆሮ 7፡7 ብሏል፡፡ አቡነ መድኃኒነ እግዚእም በምንኵስና ኖረው፣ የጽድቅን አክሊል አግኝተዋል፡፡ እኛም በተሰጠን ጸጋ ከኖርን ጌታችን ይባርከናል፡፡

www.zeorthodox.org

በሐዋርያዊ ተልእኮ ወንጌልን መስበክ ከጥንት ጀምሮ አባቶቻችን ሲፈጽሙት ነበር ፡፡ እኛም የተማርነውን ማስተማር አለብን፡፡

አቡነ መድኃኒነ እግዚእ በቤተሰባቸው ከነበራቸው ሕይወት ቤተሰብን መታዘዝ እና ማገልገልን ፣ በትጋት መማርንም ተገንዝበናል። በሕይወታችን በትንሹ ስንታመን ጌታችን በበለጠው ይሾመናል። ቤተሰብን በማገልገል የታመኑትን አቡነ መድኃኒነ እግዚእ ፣ በዮሐንስ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ታማኝ ሆነው በአባትነት በአስተዳዳሪነት እንዲሾሙ አደረገ። በዚያ ሲታመኑም አቡነ ተክለ ሃይማኖትን አምጥቶ በምንኩስና ታላቅ መዓርግ ሾማቸው። በራሳቸው ምንኩስና ጸንተው ሲታመኑም የብዙ መነኮሳት እና የበርካታ ገዳማት አባት ለመሆን አበቃቸው። እኛም ወደ ትልቁ አገልግሎት ለመድረስ ከትንሹ እንጀምር፤ እግዚአብሔር በጎ ሥራችንን ሁሉ የማይረሳ በበረከቱ በእጥፍ የሚከፍለን ቸር አምላካችን ነው። ያሳድገናል፣ በበለጠውም ይሾመናል።

**ተግባር ፦** በትምህርት በርቱ፤

በጸሎት ጽኑ፤

ቤተሰቦቻችሁን ታዘዙ፤

ለራሳችሁ እና ለእግዚአብሔር ታመኑ።

www.zeorthodox.org

# አምስቱ አዕማደ ምስጢር

## ዐሥራ አንደኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-**የቤተ ክርስቲያናችንን መሠረተ እምነት ማሳወቅ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***" እልፍ ቃላት በልሳን ከመናገር ይልቅ አምስት ቃላት በአእምሮዬ ልናገር እወዳለሁ"*** (1ኛቆሮ.14፡19)

***መግቢያ፡-*** ሃይማኖት መሠረት ነው፡፡ ***"ጻድቅ ግን በእምነቱ በሕይወት ይኖራል ፤"*** ዕንባ.2፡4 እንደተባለ፡፡ ዘላለም በሕይወት የሚያኖረን የቀና እምነት ነው፡፡ እግዚአብሔርን ማን ብለን እናምናለን? በዚህ ምድር አምነን የምንፈጽመውን ማወቅ፤ ተስፋ የምናደርገውንም መረዳት አለብን፡፡ ቤተክርስቲያን የምታምነውና የምታስተምረው እምነት በቅዱሳት መጻሕፍት በብሉይ ኪዳንና በሐዲስ ኪዳን ከዚህም ጋር ከሐዋርያት ጀምሮ በቤተክርስቲያን ሊቃውንት ትምህርትና ትውፊት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን መሠረተ እምነቷን የምትገልጥባቸውና የምታስተምርባቸው አምስት አዕማደ ምስጢር አሏት፡፡ ከዚህ ቀጥሎ በተከታተይ የምንማረው የእምነታችን መሠረት የሆኑት አምስቱ አዕማደ ምስጢር፤ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹አምስት ቃላት በአእምሮዬ ልናገር እወዳለሁ፡፡›› 1ቆሮ.14 19፤ በማለት እንደተናገረው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያላቸው ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት አምስቱ አዕማደ ምስጢር የእምነታችን መግለጫ በሆነው በጸሎተ ሃይማኖት ተዘርዝረው ይተረጎማሉ፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም ስለ አምስቱ አዕማደ ምስጢር እንማራለን፡፡

### ትምህርቱ

www.zeorthodox.org

**አዕማደ ምስጢር** የምስጢር ምሰሶዎች /አምዶች/ ማለት ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያን መምህራን ለሌሎቹ ትምህርቶች እና ምስጢራት መሠረት ለሆኑት የሰጡት ስያሜ ነው፡፡ቀጥሎ ይብራራል፡-

አምድ (በብዙ ቁጥር አዕማድ ይባላሉ፡፡) ቋሚ ምሰሶ ማለት ነው፤ ቤት ለመቆም አምድ ያስፈልገዋል፤ ግድግዳ እና ጣሪያው የሚዋቀረው በአምዱ ላይ ነው፡፡ ስለዚህ ቤት በምሰሶ ተደግፎ ይጸናል፡፡ ቤተ ክርቲያን ትምህርተ ሃይማኖት መሠረቶችም አምስቱ አዕማደ ምስጢር ናቸው፡፡ ቤት በምሰሶ ተደግፎ እንደሚጸና ምእመናንን በትምህርተ ሃይማኖት ደግፈው በጽኑ እምነት መሠረት ላይ

የሚያጸኑ ስለሆነ የምስጢር ምስሶዎች ተብለዋል፡፡ በእግዚአብሔር ቤት ***"የእውነት አምድና መሠረት"*** 1ኛጢሞ.3፡15 የሆኑትን ማወቅ እና መማር ቀዳሚው እና መሠረታዊው ጉዳይ ነው፡፡ ሌሎቹ ትምህርቶች እና ምስጢራት በእነዚህ ላይ ይመሠረታሉና አምድ ተባሉ፡፡

እግዚአብሔርን ማን ብለን እናምነዋለን ? ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማን ነው ? ለምን ሥጋን ለበሰ? የእግዚአብሔርን ልጅነት የምናገኝበት ጥምቀትስ ምንድነው? ለዘላለም ሕይወት የምንቀበለው ቅዱስ ቁርባን እና ስለ ዘላለማዊው ሕይወታችን ተስፋ ስለምናደርገው ትንሣኤ ሙታንስ ምን ብለን እናምናለን? የሚሉትን ……የምናውቅበት የመሠረተ እምነታችን ትምህርቶች ስለሆኑ አዕማድ ተብለዋል፡፡

**ምስጢር፡-** የተሰወረ ማለት ነው፡፡ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለተከተሉት ደቀ መዛሙርቱ ***" ለእናንተ የመንግሥተ ሰማያትን ምስጢር ማወቅ ተሰጥቶአችኋል ለእነርሱ ግን አልተሰጣቸውም፡፡"*** ማቴ.13፡11 እንዳለ ፤ ለሁሉም የማይታወቁ ስለሆኑ ምሥጢር ይባላሉ፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም ***"የክርስቶስን ምስጢር እንድንነግር"*** ቆላ.4፡3 ብሎ የሃይማኖትን ምስጢራት ያነሣል፡፡ በዚህ መሠረትም አምስቱ አዕማደ ምስጢራት ይባላሉ፡፡

አምስቱ አዕማደ ምስጢራት፡-

***"እልፍ ቃላት በልሳን ከመናገር ይልቅ አምስት ቃላት በአእምሮዬ ልናገር እወዳለሁ "*** 1ኛ ቆሮ.14፡19 ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ የተናገራቸው አምስት ቃላት እነዚህን እንደሆነ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ይተረጉማሉ ፡፡

1. **ምስጢረ ሥላሴ፡-**እግዚአብሔር በመለኮት አንድ ሲሆን በአካል፣ በስም እና በግብር ሦስት ነው፡፡ ይህንን የእግዚአብሔርን የአንድነት የሦስትነት ምስጢር የምንማርበት ምስጢረ ሥላሴ ይባላል፡፡

2. **ምስጢረ ሥጋዌ፡-** ሰው የመሆን ምስጢር ማለት ነው፡፡***" እግዚአብሔርን የመምሰል ምሥጢር ያለጥርጥር ታላቅ ነው፤በሥጋ የተገለጠ በመንፈስ የጸደቀ ለመላእክት የታየ በአሕዛብ የተሰበከ በዓለም የታመነ በክብር ያረገ"*** 1ኛ ጢሞ.3፡16 እንደተባለ፡፡ የክርስቶስን ሰው መሆን እና በሥጋ መገለጥ የምንማርበት ነው፡፡

www.zeorthodox.org

3. **ምስጢረ ጥምቀት፡-**ሰው ከውኃ እና ከመንፈስ ካልተወለደ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አይገባም፡፡ የዚህን ዳግመኛ ልደት ምስጢር የምናውቅበት ምስጢረ ጥምቀት ይባላል፡፡‹‹ሕዝቡም ሁሉ ከተጠመቁ በኋላ ኢየሱስ ደግሞ ተጠመቀ፡፡ ሲጸልይም ሰማይ ተከፈተ፤ መንፈስ ቅዱስም

በአካል መልክ እንደ ርግብ በእርሱ ላይ ወረደ፤ የምወድህ ልጄ አንተ ነህ፤ በአንተ ደስ ይለኛል የሚል ድምፅ ከሰማይ መጣ፡፡›› /ሉቃ.3 20-23/ ፤ "ይህም ውኃ ደግሞ ማለት ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድነናል" /1ኛ ጴጥ.3÷21/

4. **ምስጢረ ቁርባን፡-**ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ *ሥጋዬ* እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነው፡፡*ሥጋዬን* ያልበላ ደሜንም ያልጠጣ የዘላለም ሕይወት የለውም ፤ ባለን መሠረት የምንቀበለው የቅዱስ ቁርባንን ምስጢር የምንማርበት ነው፡፡ "እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ የወልደ እጓለ እመሕያው ክርስቶስን *ሥጋ* ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ የዘላለም ሕይወት የላችሁም፡፡ *ሥጋዬን* የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው÷እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሳዋለሁ፡፡" /ዮሐ.6÷53-59/ ተብሎ ተጽፎአል፡፡

5. **ምስጢረ ትንሣኤ ሙታን፡-** ጌታችን ዳግም ይመጣል፤ በሕያዋን እና በሙታንም ላይ ይፈርዳል፤ ስለዚያች ቀን ስለሙታን አነሣስ እና ስለ ዘለዓለማዊው ሕይወት ***"አንቀላፍተው (ሞተው) ስላሉቱ ታውቁ ዘንድ እንወዳለን፡፡"*** ተብሎ እንደተጻፈ ስለዚህ ለማወቅ የምንማረው ትምህርት ***" ኢየሱስ እንደ ሞተና እንደ ተነሣ እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉቱን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና"*** /1ኛ ተሰሎ.4፡14/ ተብሎ እንደተጻፈ በተስፋ የምንጠብቀው እና የምናምነው እምነት ነው፡፡

እነኚህ የሕያው እግዚአብሔር ቤት የቤተ ክርስቲያን የእውነት አምድ እና መሠረቶች ናቸው ፡፡

## ምን ተማርን ?

የቤተ ክርስቲያናችን መሠረተ እምነት የሆኑት አምስቱ አዕማደ ምስጢራት ናቸው፡፡ እነዚህን የእምነታችን መገለጫዎች የሆኑ የምስጢር ምሰሶዎች ማወቅ መሠረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም እነዚህን ለይተናል፡፡

www.zeorthodox.org

ምስጢር ማለት ምን እንደሆነ እና ለምን እንደሚያስፈልግም ተምረናል፡፡

## ተግባር

የአምስቱን አዕማደ ምስጢራት ስያሜ በቃላችሁ ያዙ፡፡

የሃይማኖት መጻሕፍትን አንብቡ፡፡

# ምስጢረ ሥላሴ(1)

## ዐሥራ ሁለተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ** ፡-የእግዚአብሔርን አንድነት እና ሦስትነት ምስጢር ማሳወቅ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ**፡-*“ እኔና አብ አንድ ነን ”* ዮሐ.10፡30

**ተጨማሪ ምንባባት**፡-ማቴ.3፡16-17;2ኛ ቆሮ.13፡14

### መግቢያ፡-

በቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት ከመሠረተ እምነቶች የመጀመሪያው ምስጢረ ሥላሴ ነው፡፡ሥላሴ ሦስትነት ማለት ነው፡፡ይህም እግዚአብሔር በአካል፣ በስም ፣ በግብር ያለውን ሦስትነት የሚያመለክት ቃል ነው፡፡አካል ስም እና ግብር ማለት ምን ማለት ነው? የማይመረመረው የእግዚአብሔር ባሕርይ እንዴት ታውቆ ሦስትነቱ ተረዳን ? በዛሬው ትምህርታችን እነዚህን እንመለከታለን፡፡

### የሳምንቱ ትምህርት፡-

#### የእግዚአብሔር አንድነት፡-

**እግዚአብሔር አንድ ነው**፡፡ በቤተ ክርስቲያን ትምህርት መሠረት የምናምነው በአንድ እግዚአብሔር ነው፡፡ ብዙ አማልክት የሉንም ፤ ቤተ ክርስቲያን ይህንኑ *“ ነአምን በአሐዱ አምላክ - በአንድ አምላክ እናምናለን ”* ስትል ትመሰክራለች፡፡ *“በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ”* *“ አሐዱ አምላክ - አንድ አምላክ አሜን ”* የምንለው አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር አንድ መሆኑን ለመመስከር ነው፡፡ ሥላሴ በስም፣ በግብር፣ በአካል ሦስት ናቸው ብንልም በባሕርይ፣ በመለኮት፣ በህልውና፣ በፈቃድ አንድ ስለሆኑ አንድ አምላክ እንጂ ሦስት አማልክት አይባሉም፡፡ በአንድነት ስማቸው ግን እግዚአብሔር አምላክ በመባል ሦስቱም ይጠሩበታል፡፡ አብ አምላክ፣ ወልድ አምላክ፣ መንፈስ ቅዱስ አምላክ፤ አንድ አምላክ ይባላል፡፡ የቅድስት ሥላሴ አንድነት በምንድነው ?.......

**በመለኮት (በአገዛዝ) አንድ ነው**፡፡ሦስቱም ልዩነት በሌለው መለኮታዊ አንድነት ፈጥረው ይገዛሉ፡፡

www.zeorthodox.org

**በሥልጣን** የአብ የሆነ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ ያልሆነ ሥልጣን የለም። ለዚህ እንደ ምሳሌ የክርስቶስ ትንሣኤ ያለውን አንድነት እንይ። ጌታችን ስለ ትንሣኤው ከመሞቱ በፊት ሞቶ እንደሚነሣ ሲገልጥ ***"እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም።ላኖራት ሥልጣን አለኝ፤ ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ፤ይህችን ትእዛዝ ከአባቴ ተቀበልሁ"*** አለ። (ዮሐ.10፡18) በሌላም ቦታ አብ አስነሣው ለማለት ***"እግዚአብሔርም ከሙታን ባስነሣው"*** በሐ.ሥ.4÷10 ተብሎአል።መንፈስ ቅዱስ አስነሣውም ተብሎ ተጽፎአል ***"ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው የእርሱ መንፈስ"*** (ሮሜ 8÷11) ከዚህም የሥልጣናቸውን አንድነት እናስተውላለን።

**በፈቃድ፡-**በአብ ልብነት አስበው በወልድ ቃልነት የሚናገሩት በመንፈስ ቅዱስ ሕይወትነት የሚኖሩ ናቸው። አብ ለራሱ ለባዊ ሆኖ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ ልባቸው ነው። ወልድ ለራሱ ቃል ሆኖ ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው ነው። መንፈስ ቅዱስ ለራሱ እስትንፋስ /ሕይወት/ ሆኖ ለአብና ለወልድ አስትንፋስ /ሕይወት/ ነው። የአንዱ የሆነ የሌላው ያልሆነ ፈቃድ የለም። ለዚህም ክርስቶስ ***"የላከኝን ፈቃድ ለማድረግ ከሰማይ ወርጃለሁና።"*** ዮሐ.6፡37-38 በማለት ተናግሯል። በዚህም መሠረት በመፍጠር፣ ፍጥረቱን በመመገብ እና በማሳለፍም አንዲት ፈቃድ፣ሥልጣን እና አገዛዝ አላቸው።

**በህልውና፡-** (መኖር ማለት ነው።) የሰማይና የምድርን ህልውና በቅድስት ፈቃዳቸው በጽንዒት ሥልጣናቸው የሰጡ ቅድስት ሥላሴ ፤ ከጊዜ በፊት የነበሩ ሕያዋን ዓለምን አሳልፈው የሚኖሩ ዘላለማውያን ናቸው። በዚህ መሠረትም አንዱ ከሌላው ተለይቶ የነበሩበት ጊዜ አልነበረም አይኖርምም፤ ***"ከአብርሃም ሳይወለድ እኔ ነበርኩ።"*** (ዮሐ.8፡58)

ከዚሁም ጋር አብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ህልው ነው። ወልድም በአብ በመንፈስ ቅዱስ ህልው ነው። መንፈስ ቅዱስም በአብ በወልድ ህልው ነው። አንዳቸው በሌላቸው ይኖራሉ። "እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ እመኑ ። " (ዮሐ 14÷10)

www.zoorthodox.org

የተለያየ ህልውና ወይም አኗኗር አለ። ቅዱስ አውግስቲን ግኡዝ ፍጥረታት፣ከዕፀዋት፣ዕፀዋት ከእንስሳት፣እንስሳት ከሰው፣ሰው ከመላእክት በህልውና እንደሚለያዩ ፣ የእግዚአብሔርም ህልውና ከእነዚህ የረቀቀ ነው ይላል።እነኚህን ተጨማሪ ጥቅሶች ፤ዘፍ.1 26-27፤2 18፤3 22፣ዮሐ 10፣30፤14 26፣ ኢሳ. 3 3-10፤44 6-10)

በዚህና በመሳሰሉት እግዚአብሔር አንድ ነው። ይህንንም ሦስት መቶ ዐሥራ ስምንቱ ሊቃውንት በሃይማኖተ አበው ሲያስረዱ፤ ‹‹በእግዚአብሔር አብ፣ በእግዚአብሔር ወልድ፣ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እናምናለን›› ብለዋል። /ሃይማኖተ አበው ዘሠለስቱ ምእት፤ ምዕ 09

ክፍል 1 ቁጥር 30/ በቅዳሴ ማርያምም *"ሦስቱ ስም አንዱ እግዚአብሔር ነው"* ቍጥር 54 አማልክቶቻቸው ብዙ ....የሆኑ በጣዖት እንደሚያመልኩ አረማወያን.... ከአንድ በላይ አማልክት እንደሚያመለኩ ሦስት አማልክት አንልም። *"መለኮት ግን አብ ወወልድ መንፈስ ቅዱስም ነው። አንድ አምላክ አንዲት መንግሥት አንዲት ሥልጣን አንዲት አገዛዝ ነው"* እግዚአብሔር በመመለክ፣በሥልጣን ፣ በአገዛዝ በፈቃድም አንድ ነው።

አንድ ገጽ አንድ አካል ብለው እንደሚያምኑት እና የእግዚአብሔርን አንድነት እንደካዱትም በገጽ በስም እና በግብርም አንድ ነው ብለን አናምንም።አንድ ሲሆኑ ሦስት ሦስት ሲሆኑ አንድ ነው ብለን እናምናለን።

በሰይጣን ተንኮል እንዳንሳሳት የሚጠነቀቅልን እግዚአብሔር ሦስትነቱ በመጽሐፍ ፣ በፍጥረታት እና በተሰጠን አእምሮ እንድንረዳ አድርጐአል።

## የእግዚአብሔርን ሦስትነት የሚያስረዱ ጥቅሶች፡-

*"የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች÷የእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ አደረገችኝ ፤የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች ።"* መዝ 117(118)÷15-16

*"እግዚአብሔር ይባርክህ ይጠብቅህም÷እግዚአብሔር ፊቱን ያብራልህ ይራራልህም÷እግዚአብሔር ፊቱን ወደ አንተ ያንሣ ሰላምንም ይስጥህ።"* (ዘኁል. 6÷24-26) ሦስት ጊዜ እግዚአብሔር ማለቱ ሦስትነትን ለመግለጥ ነው።

*" የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ÷የእግዚአብሔርም ፍቅር ÷የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችን ጋር ይሁን።"* 2ኛ ቆሮ 13÷14 ብሎ ቅዱስ ጳውሎስም ሦስትነትን አስተምሮአል።

*"ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር"* ኢሳይ. 6÷3 ሦስት ጊዜ ቅዱስ ማለቱም ለአብ ለወልድ እና ለመንፈስ ቅዱስ ነው።

www.zeorthodox.org

*"መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል ÷የልዑል ኃይልም ይጸልልሻል።ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል።"* ሉቃ 1÷38 ወልድን *የእግዚአብሔር ልጅ* ብሎ ÷ መንፈስ ቅዱስ ብሎ ሦስተኛውን አካል ÷ልዑል ብሎ አብን እየጠቀሰ ቅዱስ ገብርኤል አስተምሮዋል።

**የቅድስት ሥላሴን አንድነት እና ሦስትነት የሚያስረዱ ምሳሌዎች፡-**

ሰው፡- ሰው በነፍሱ ሦስትነት አለው። ልብነት (ዕውቀት)፣ ቃልነት (ተናጋሪነት)፣

እስትንፋስነት (ሕያውነት) ፤ ሰው ሲፈጠር ሦስቱም አብረው ተሰጥተውታል÷አይቀዳደሙም፤ሥላሴም በአብ ልብነት ያስባሉ፣በወልድ ቃልነት ይናገራሉ፣ በመንፈስ ቅዱስ ሕይወትነት ይኖራሉ። ሰው እግዚአብሔርን በዚህ ስለሚመስለውም የፈጠረው እግዚአብሔር ***" ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር አለ።"*** (ዘፍ 1÷26)

**ፀሐይ እና እሳት፡-** ሁለቱም ሙቀት፣አካል እና ብርሃንነት አላቸው። በአንዱ እግዚአብሔርም ሦስትነት አለ። ነገር ግን ሦስት እሳት ሦስት ፀሐይ እንደማንል እግዚአብሔርም በግብር፣በአካል እና በስም ሦስትነት አለው፤ ነገር ግን አንድ እግዚአብሔር ነው።

**አቶም (Atom)፡-** አንድ አቶም (Atom) ኒውትሮን (neutron) ፣ ፕሩቶን (proton) ፣ ኤሌክትሮን (electron) አሉት። ሦስቱም በዓይን አይታዩም፤ ኃይል ሲሠጡ ግን ያታወቃሉ። ስለ እግዚአብሔር አንድነት ሦስትነት የምንማረውንም በዚህ ምሳሌነት መረዳት እንችላለን ። በአንዱ እግዚአብሔር ሦስትነት አለ፤ እግዚአብሔርንም በፍጥረቱ እና በሥራው እናውቀዋለን እንጂ በሥጋ ዓይናችን አናየውም።

የነዚህ ሁሉ ምሳሌነት ምሉዕ መገለጫ ሆነው÷ሳይሆን አባቶቻችን ***"ምሳሌ ዘየሐጽጽ-ጐዶሎ ምሳሌ"*** እንደሚሉት ለእኛ ለማስረዳት የተመሰሉ ናቸው።

## ማጠቃለያ

የምናመልከው አባታችን እግዚአብሔር አንድ ነው። አንድነቱም በመለኮት በሥልጣን፣ በፈቃድ እና በህልውና ነው ። እንዲሁም ሦስትነቱ በአካል፣በግብር እና በስም ነው።

በአብ ልብነት ያስባሉ ፤ በወልድ ቃልነት ይናገራሉ፤በመንፈስ ቅዱስ ሕያዋን ይሆናሉ።

## ተግባር

የተሰጡአችሁን ጥቅሶች አንብቡ።

ያልገባችሁን ከመምህራን ጠይቁ እርስ በእርስም ተወያዩ።

www.zeorthodox.org

***መዝሙር 1***

ነአምን በአብ ወነአምን በወልድ

ወነኣምን ነአምን በመንፈስ ቅዱስ

***መዝሙር 2***

እናምናለን በአብ

/የይልማ ኃይሉ መዝሙር/

# ምስጢረ ሥላሴ(2)

## ዐሥራ ሦስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-የእግዚአብሔርን ሦስትነት ማስገንዘብ፡፡**

**የሚጠና ጥቅስ፡-*"መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል÷ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል፤ ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል፡፡"*** (ሉቃ.1፡35)

**መግቢያ፡-** ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን የእግዚአብሔርን አንድነት እና ሦስትነት መነሻ በማድረግ አንድነቱን ተምረናል፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም የቅድስት ሥላሴን ሦስትነት እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

**በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጠው ሦስትነት፡-**

ስለ አንዱ እግዚአብሔር ባሕርይ የሚነግረን መጽሐፍ ቅዱስ ሦስትነቱንም በምስጢር እና በገሀድ ገልጾልናል፡፡ ይህንንም ከመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ጀምሮ እናያለን፡-

***"እግዚአብሔርም አለ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር "*** (ዘፍ.1፡26) ከዚህም፡- **እግዚአብሔር አለ፡፡** የሚለው ነጠላ አጠራር አንድነቱን ፤ በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር በሚለው ብዙ ቁጥር ደግሞ ፤ የሦስትነቱን ነገር አስቀድሞ እየነገረን ነው፡፡

ሰው የእግዚአብሔር አርአያ እና አምሳል ተብሎአል፡፡ በዚህ መሠረትም ሕያውነታችን፣አዋቂነታችን እና ተናጋሪነታችን (ሕያዊት ፤ ለባዊት ፤ ነባቢት ነፍሳችን የሦስትነቱ ምሥክር ) ነው ፡፡

www.zeorthodox.org

***"አዳም....ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ፡፡ "*** (ዘፍ.3፡22) ይህ ትንቢተ ቃል ሥጋ ሲሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተፈጸመ ነው፡፡ ***ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ*** የሚለው ሐረግ ግን እግዚአብሔር በነገሥታት ልማድ እኛ የሚል ለሚመስላቸው እርማት የሚሰጥ እና የአካላትን ልዩነት የሚያመለክተን ነው፡፡

***"እግዚአብሔርም አለ ፡- ...........ኑ እንውረድ "*** (ዘፍጥ. 11፡6-7) አሁን ደግሞ አንዱ

ሌሎችን እየጠራ ነው፡፡ ኑ የተባሉት ከአንድ በላይ ሲሆኑ ጠሪው በነጠላ ‹‹አለ››፤ በሚል ነጠላ ቁጥር ተጠርቷል፡፡

***“በቀትርም ጊዜ እርሱ በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ እግዚአብሔር በመምሬ የአድባር ዛፍ ተገለጠለት ፡፡ ዓይኑንም አነሣና እነሆ ሦስት ሰዎች በፊቱ ቆመው አየ፤ ባያቸውም ጊዜ ሊቀበላቸው ከድንኳኑ ደጃፍ ተነሥቶ ሮጠ ወደ ምድርም ሰገደ÷ እንዲህም አለ፡- አቤቱ በፊትህ ሞገስ አግኝቼ እንደሆነ ባርያህን አትለፈኝ ብዬ እለምናለሁ፤ጥቂት ውኃ ይምጣላችሁ እግራችሁን ታጠቡ … ዕረፉ፡፡”*** (ዘፍ.18፡1-5) የእምነት አባት አብርሃም አንድነት ከሦስትነት ተገልጠውለት ሦስት ሰዎች በፊቱ ቆመው በነጠላ ***በፊትህ …ባርያህን አትለፈኝ*** ብሎ ፤ተመልሶ በብዙ ቁጥር ***ይምጣለችሁ እግራችሁን ታጠቡ …ዕረፉ…*** ይላል፡፡ በሰው ምሳሌ በተገለጠለት ምስጢር አንድነት እና ሦስትነትን ያመሰጥራል፡፡ በዚህም የአካል ሦስትነትን የፈቃድ አንድነትንም እናስተውላለን፡፡

***“አሁንም ጌታ እግዚአብሔርና መንፈሱ ልከውኛል ”*** ኢሳ.48፡12-16 ተላኪ(ሰው የሆነ) ወልድ ፤ ላኪ አብ እና መንፈስ ቅዱስ ናቸው፡፡

**የእግዚአብሔር ሦስትነት፡-** ከላይ አንዱ እግዚአብሔር ሦስትነት እንዳለው ከመጻሕፍ ቅዱስ ተምረናል፡፡ ይህ ከሆነ ታዲያ የእግዚአብሔር ሦስትነት በምንድነው ? በስም በግብር እና በአካል እግዚአብሔር ሦስት ነው፡፡

**ሀ. የስም ሦስትነት፡-*‹‹አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ››*** (ማቴ 28÷19)

**ለ. የአካል ሦስትነት፡-**አብ የራሱ መልክ ፣ ገጽ እና አካል አለው፡፡ ወልድ የራሱ መልክ፣ ገጽ እና አካል አለው፡፡ መንፈስ ቅዱስም የራሱ መልክ ፣ ገጽ እና አካል አለው፡፡ ይህም የአካል ሦስትነት በጥምቀት ወልድ በተለየ አካሉ ሲጠመቅ፣ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል በአካል ሲገለጥ፣ አብ በደመናት ሆኖ ይናገር ነበር፡፡(ማቴ 3፡16-17) ቅዱስ እስጢፋኖስም ሰማያት ተከፍተው አካል ከሕልውና ተገልጦለት ክርስቶስን በአብ ቀኝ ተመልክቶታል፡፡ (የሐ.ሥ 7÷56)

www.zeorthodox.org

**ሐ.የግብር ሦስትነት፡-**በቁሙ ሲፈታ ሥራ ማለት ነው፡፡ በዚህ ግን ግብር የሚለውን ቃል በግእዙ እንጠቀማለን፡፡ የአብ ግብሩ ወላዲነትና አሥራፂነት፣ የወልድ ግብሩ ልጅነት፣ የመንፈስ ቅዱስ ግብሩ ሠራፂነት ነው፡፡ አብ ወላዲና አሥፃ ነው፡፡ ወልድ ተወላዲ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስም ሠራፂ ነው፡፡ አብ ወልድን ወልዶታል ግብሩ ወላዲነት ነው፡፡ አብ ወልድን ወለደ ማለትም ወልድ ከአብ ከአካሉ ከባሕርይው ተገኝቷል ማለት ነው፡፡ እንደ ፍጡራን እምኃበ አልቦ ወይም ከሌላ ፍጥረት የተገኘ አይደለም፡፡ ለዚህም ነው በጸሎተ ሃይማኖት ***“ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ከአምላክ የተገኘ አምላክ ”*** የምንለው፡፡ የወልድ ከአብ መወለድም በመጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ባለቤቱ ***‹‹አንተ ልጄ***

***ነህ እኔ ዛሬ ወለድኩህ››*** (መዝ.2÷7) ***‹‹የምወደው ልጄ እርሱ ነው››*** (ማቴ.3÷17) መንፈስ ቅዱስ ከአብ ሠረፀ ማለትም ከአካሉ ከባሕርይው ተገኘ ማለት ነው፡፡ ከላይ ለወልድ እንዳልነውም አብን አህሎ እና መስሎ ነው የወጣው፤ ሠራጺ ማለት የሚወጣ ማለት ነው፡፡***‹‹እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል፡፡ ››*** (ዮሐ.15÷26)

ኩነት ፡- መሆን ማለት ነው፡፡ የአብ ኩነት ልብነት ነው፡፡ የወልድ ኩነት ቃልነት ነው፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ኩነት እስትንፋስነት ነው፡፡ ***‹‹የእግዚአብሔር ቸርነት ምድርን ሞላች፣ በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ፣ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ፡፡››*** መዝ 32፣6 የሚከተሉትን ጥቅሶች በማስተዋል አንብቡ፡፡ ***‹‹የምነግራችሁ ቃል የእኔ አይደለም፣ በእኔ የሚኖር የአብ ነው እንጂ፡፡››*** ይህም በአብ ልብነት የሚታሰበውን ማለቱ ሲሆን፣ ቃላቸው እርሱ ወልድ ስለሆነ ***"ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር ያም ቃል እግዚአብሔር ፡፡"*** (ዮሐ.1፡1-3) ተብሎአል፡፡ መንፈስ ቅዱስም ***‹‹እስትንፋስ››*** መዝ 32-6 ተብሎአል፡፡ ሰው በልቡ (በአእምሮው) አስቦ ፣ በቃሉ እንዲናገር፣ እስትንፋስ እስካለው ሕያው ሆኖ እንዲኖር ማለት ነው፡፡

አብ በወልድ ቃልነት ይናገራል፤ በመንፈስ ቅዱስ ሕያው ነው፡፡ ወልድም በአብ ልብነት ያስባል፤ በመንፈስ ቅዱስ ሕያው ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ በአብ ልብነት ያስባል፤ በወልድ ቃልነትም ይናገራል፡፡ እንጂ ለሦስቱም የየራሳቸው ልብነት ቃልነት፣ እስትፋስነት የላቸውም፡፡ ከላይ እንደተገለጸው በፈቃድ፣ በሥልጣን በህልውና ሳይለያዩ በአንዲትም መለኮት ይኖራሉ፡፡

**የመንፈስ ቅዱስ አካላዊነት፡-** መንፈስ ቅዱስ እንደ አብ እና ወልድ ሙሉ አካል ሙሉ ገጽ ያለው ነው፡፡ ይህንንም መጽሐፍ ቅዱስ ያረጋግጥልናል፡፡

ለእግዚአብሔር የተባለው ለመንፈስ ቅዱስ መነገሩ፡፡ (ኢሳ. 6፡1-10፣የሐዋ 28፡25-27)

በዮርዳኖስ ጌታ ሲጠመቅ ‹‹በአካል መልክ›› መገለጡ፡፡ ሉቃ 3፣22

www.zeorthodox.org

የሚመሰገን እና የሚነቀፍ አካል ሕይወት ያለው ነው፡፡ ጌታችን ***‹‹መንፈስ ቅዱስን ለሰደበ ኃጢአቱ አይሠረይለትም››*** (ማቴ 12፡31-32) ብሎዋል፡፡

ሌሎችን ለመውቀስም ሆነ በሌሎች ለመፍረድ የሚችል አካል ያለው አዋቂም የሆነ ነው ***‹‹እኔ እንድሄድ ይሻላችኋል፡እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ፡፡ እርሱ መጥቶ ስለ ኃጢአት ስለ ጽድቅም ስለፍርድም ዓለምን ይወቅሳል፡፡››*** (ዮሐ.16፡7-8)

## ማጠቃለያ፡-

በሥላሴ (በሦስትነት) አለማመን ከድኅነት/ከጽድቅ ሕይወት/ መውጣት ነው፡፡ በእግዚአብሔር አምናለሁ የሚል ሦስትነቱን ማጉደል መጠራጠር የለበትም፡፡ *"ብዙ አሳቾች ወደ ዓለም ገብተዋልና እነርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ መጣ የማያምኑ ናቸው፡፡ ይህ አሳቹና የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው፡፡"* (2ኛ ዮሐ. ቁ 7-8) *"ስለዚህ እላችኋለሁ ኃጢአትና ስድብ ሁሉ ለሰዎች ይሰረይላቸዋል፤ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን ለሰደበ አይሰረይለትም፡፡"* (ማቴ 12÷31-32)

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ መበላለጥ፣መቀዳደም የለባቸውም፡፡

የስም ፣የግብር፣የአካል ሦስትነት በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጦአልና ይህንኑ እናምናለን፡፡

## ተግባር፡-

እግዚአብሔርን የምንመስለው በፍቅር እና በቅድስና ስንኖር ነው፡፡ ፍቅርን ሰላምና እና እውነትን በመያዝ ነው፡፡

www.zeorthodox.org

# ምስጢረ ሥጋዌ

## ዐሥራ አራተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-የጌታችንን ሰው የመሆን ምስጢር ማስገንዘብ፡፡**

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***" እግዚአብሔርን የመምሰል ምስጢር ያለጥርጥር ታላቅ ነው፤በሥጋ የተገለጠ በመንፈስ የጸደቀ ለመላእክት የታየ በአሕዛብ የተሰበከ በዓለም የታመነ በክብር ያረገ፡፡"*** 1ኛጢሞ.3፡16

**ተጨማሪ ምንባባት፡-**

***መግቢያ፡-*** ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው የሆነ አምላክ ነው፡፡ ይህ ሰው የመሆኑ ምስጢርም *ሥጋዌ* ይባላል፡፡በዛሬው ትምህርታችን የጌታችንን ሰው የመሆን ምስጢር እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ዋና ትምህርት፡-

### ሰው የመሆን ምስጢር

*ሥጋዌ*፡-ሰው መሆን ማለትነው፡፡ ይህም የማይዳሰሰው እና የማይታየው አምላክ ተገልጦ ፣ መታየት እና ሰው መሆኑን ያመለክታል፡፡ የክርስቶስን ***"በሥጋ መገለጥ "*** ወይም ***" በሥጋ እንደመጣ የሚታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው ፡፡"*** (1ኛ.ዮሐ.4÷2) ይህም የክርስቶስ ሰው መሆን ነው ፡፡

**ሰው ከመሆኑ በፊት ምን ነበር?**

ክርስቶስ ሰው ከመሆኑ በፊት እንደ አብ እና እንደ መንፈስ ቅዱስ በዘላለማዊ ክብሩ የሚኖር አምላክ እና ጌታ ነው፡፡ ወንጌላዊው ዮሐንስ ይህንኑ ሲገልጥ ‹‹በመጀመሪያው ቃል ነበረ፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፣ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ፡፡›› ዮሐ.1 1

www.zeorthodox.org

ሁሉን የፈጠረም ነው፡1 ‹‹ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለእርሱ አልሆነም›› ዮሐ.1 3

በእግዚአብሔር መልክ ያለና ከእግዚአብሔር ጋር ትክክል የሆነ ነው፡፡

‹‹እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት

እንደሚገባ አልቆጠረውም›› ፊልጵ.2 6፡፡

**ሰው የሆነው ማን ነው ?**

**ሰው የሆነው እግዚአብሔር ነው፡፡ ክርስቶስ ሰው ከመሆኑ በፊት እንደ አብ እና እንደ መንፈስ ቅዱስ በዘላለማዊ ክብሩ የሚኖር አምላክ እና ጌታ ነው፡፡ በእግዚአብሔር መልክ ያለ እግዚአብሔር ነው ፡፡ *“ እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ አልቆጠረውም ”* ፊልጵ.2፡6**

**ሰው የሆነው ወልድ አካላዊው ቃል ነው፡፡ ከሦስቱ አካላት አንዱ ወልድ በተለየ አካሉ ሰው ሆነ፡፡ ወንጌላዊው ዮሐንስ ይህንኑ ሲገልጥ *“በመጀመሪያው ቃል ነበረ ÷ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ÷ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ፡፡ ”* ( ዮሐ.1፡1) እርሱም ሁሉን የፈጠረ ነው፡፡*“ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም፡፡”* ዮሐ.1፡3** /ሀርድ ኮፒው ላይ የሌለ ነው/

## ለምን ሰው ሆነ ?

**1.የሰው ልጆች ሳቱ፡-**

አዳም እና ሔዋን በእግዚአብሔር መልክ እና ምሳሌ በክብር ተፈጥረው ሲኖሩ ፤ “በምድር የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ” ከሚል ሹመት ጋር ነበር፡፡ የእነሱን ምድራዊ ገዥነት፤ የእግዚአብሔርን የሰማይና የምድር አምላክነት መለያ ትእዛዝ ተሰጣቸው፡፡ ትእዛዜቱም ***“..አትብላ... በበላህ ቀን ትሞታለህና ”*** (ዘፍጥ.2÷17) የምትል ነበረች፡፡

አዳም እና ሔዋን በእባብ ላይ ባደረ በዲያብሎስ ምክር ተሳሳቱ ፤ ***አትብሉ*** የተባሉትን በሉ ሞትንም አመጡ፡፡ ሞቱም በሥጋ ወደ መቃብር በነፍስ ወደ ሲዖል የመውረድ የነፍስ እና የሥጋ ሞት ነበር፡፡ይህም ከእግዚአብሔር ፍቅር ጋር ያለውን እውነተኛ ፍርድ ያመለክተናል፡

**2. ተጸጸቱ፡-**

www.zeorthodox.org

ከእግዚአብሔር መጣላት ከገነት መባረር እና የልጅነትን ሥልጣን እና ጸጋ ማጣት የሰው ልጆች አሳዛኝ ዕጣ ሆነ በዚህም አዳም እና ሔዋን ተጸጸቱ ፡፡

**3. የተሰጣቸው ተስፋ እና ዘመኑ ፡-**

መጸጸታቸውም ከሴቲቱ የሚወለደው ወንድ የአሳሳቹን ራስ ***ይቀጠቅጣል*** የሚል ሌላ ተስፋ አመጣ ፤ አዳም ፣ ሔዋን እና በሃይማኖት የኖሩ ልጆቻቸውም ይህንኑ ተስፋ አድርገው ኖሩ፡፡ ***“ እጅህን ከአርያም ላክ አድነንም ” መዝ. 143፡7*** እያሉ ተስፋውን ይዘው በሱባኤ ቢቆጥሩ

ልመናቸውን ሰምቶ በቀጠረው ዘመን መጣ፡፡

ይህ ዘመን በቤተ ክርስቲያን ትውፊት 5500 (አምስት ሺሕ አምስት መቶ ዘመን)ነው፡፡ ዳንኤል ይህን ዘመን በሱባኤ ሲቈጥር (ዳን.9፡26-27)፤ ቅዱስ ጳውሎስም የተቆጠረውን ዘመን ***"የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ"*** (ገላ.4፡4) ብሎ አብራርቶታል፡፡

## 4. ሌላ አዳኝ ስላልተገኘ ለማዳን ሰው ሆነ፡፡

ከአቤል ጀምሮ የፈሰሰው የጻድቃን ደም ዓለምን ሊያድን አልቻለም፡፡ *መሥዋዕቱም በሥጋ* የተሠራ ኃጢአትን ከማንጻት አልፎ ***"ኃጢአትን እንዲያስወግድ የማይቻል"*** (ዕብ.10፡4) ነበር፡፡ የሰው ልጅ ጽድቅ እንዳልረባ ያስተዋሉት ቅዱሳን ነቢያት "ጽድቃችን የመርገም ጨርቅ ሆነ" አሉ፡፡ ስለ ሰው ልጅ ካሳ የሚክስ ድኅነትን በነፍስ እና በሥጋ የሚሰጥ በታጣበት ፤ እግዚአብሔር የገዛ ክንዱ መድኃኒት አደረገለት፡፡ ***" የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ በሥጋ ተገለጠ "*** ( 1ኛ ዮሐ.3፡8) በጸሎተ ሃይማኖት ***"ስለ እኛ ስለ ሰዎች ስለመዳናችን ከሰማያት ወረደ፣ በመንፈስ ቅዱስ ግብር ከቅድስት ድንግል ማርያም ፈጽሞ ሰው ሆነ "*** ተብሎ እንደተገለጸው ሰውን ለማዳን ነው፡፡ ***" ለጽዮን ታዳጊ ይመጣል "*** (ኢሳ. 59፡20)

## 5. ከፍቅሩ የተነሣ፡-

ቅዱስ ጳውሎስ ይሄን ሲገልጥ፤ ***‹‹ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለጸጋ ስለሆነ፤ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳን በሆን ጊዜ በክርስቶስ ሕይወትን ሰጠን ››*** ኤፌ. 2፡5

***"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና፡፡ ዓለም በልጁ እንዲድን እንጂ፣ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና ፡፡"*** (ዮሐ. 3፡16-17)

www.zeorthodox.org

## እንዴት ሰው ሆነ ?

### ታሪኩ እና ምስጢሩ

የወልደ እግዚአብሔርን ሰው መሆን ወንጌል ይተርክልናል፡፡

*ቃል ሥጋ ሆነ፤ ጸጋን እና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ አደረ፡፡* (ዮሐ.1፡14)

በመንፈስ ቅዱስ ግብር ከድንግል ማርያም ተፀነሰ፡፡ (ማቴ.1፡18 ሉቃ.1፡26-38)

በድንግልና ተወለደ። (ሉቃ.2፡1-10፤ ማቴ.2፡1)

ሠላሳ ዓመት ሲሞላው ራሱን ለዓለም ገለጠ። (ማቴ.3፡1-17;ሉቃ.3፡1-ፍጻሜ፤ ማር.1፡1-ፍጻሜ፤ ዮሐ.2፡1-11።)

በመጠመቁ ልጅነታችንን መለሰ፤ በጦሙ በመብል የመጣውን ፍዳ ካሰልን፤ ጽድቅን በተግባር እና በትምህርት መፈጸምን አሳየን፤ የሐዲስ ኪዳኑን መሥዋዕት ሠርቶ ያለፈውንም ሽሮ፤ ሥጋውን ልንበላው ደሙንም መጠጥ አድርጎ ሰጠን፤ ተገርፎ እና ተሰቅሎ በሞቱ ሞትን ኃጢአትን ዲያብሎስን እና ሲዖልን ድል አደረገ፤ በትንሣኤውም የዘላለም ሕይወት እና የዳግም ትንሣኤያችን በኵር ሆነ።ወደ ሲዖል የነበረው ጉዞም በዕርገቱ ወደ ሰማይ ሆነ።

## *ምስጢሩ*

የጌታችንን ሰው የመሆን ምስጢር መግለጥ የሚችል የለም። ነገር ግን እርሱ በለጋስነቱ በገለጠው መጠን እና በሰጠን አእምሮ ለመረዳት በቻልነው መጠን እንማራለን። ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው ይህ ምስጢር ደግሞ ታላቅ ነው። ***"እግዚአብሔርን የመምሰል ምስጢር ያለጥርጥር ታላቅ ነው ። በመንፈስ የጸደቀ፣ ለመላእክት የታየ፣ በአሕዛብ የተሰበከ፣ በዓለም የታመነ፣ በክብር ያረገ"*** (1ኛ.ጢሞ. 3፡16)

**ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ፣ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ አምላክ ሰው ሆነ፣ ሰውም አምላክ ሆነ** (ኢሳ. 7፣14፣ ማቴ 1፣18።) ከባሕርይ ክብሩ ምንም ሳይጎድልበት ሰው ሆነ። ከባሕርይ አባቱ ከአብ፣ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ካለው አንድነት ምልዓት፣ ስፋት፣ ሥልጣን፣ ቅድምና፣ ዕሪና (እኩልነት) እና ኃይል ምንም ሳይጎድለው ማለት ነው። ይህንንም ወንጌላዊው ዮሐንስ ***"ጸጋንና ጽድቅን ተሞልቶ"*** (ዮሐ. 1፡14) ሲል ይገልጠዋል።

## *በተዋሕዶ ሰው ሆነ*

www.zoorthodox.org

ተዋሕዶ ማለት አንድ መሆን ማለት ነው። ክርስቶስ ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ፤ ከሁለት አካል አንድ አካል የሆነ ነው። ሁለት ባሕርያት ሁለት አካላትም አሉ። እነዚህም የአምላክ እና የሰው ባሕርያት እና አካላት ናቸው።

የአምላክ ባሕርይ፡- በሁሉ ምሉዕ ፤ ዘላለማዊ ፤ ሁሉን ቻይ፤ሁሉን ማድረግ የሚችል ነው።

የሰው ባሕርይ፡-ውሱን፤የሚሞት፤የተገደበ አቅም ያለው ነው።

የአምላክ አካል ረቂቅ፣የማይታመም፣ የማይደክም ነው።

የሰው አካል ግዙፍ፣ታማሚ፣ድካም የሚስማማው ነው።

ክርስቶስ ከእነዚህ ሁለት ባሕርያት አንድ ባሕርይ ከሁለቱ አካላት አንድ አካል ስለሆነ በተዋሕዶ ሰው ሆነ እንላለን።

**ማጠቃለያ፡-** *ሥጋዌ የጌታችንን ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ሰው መሆን እና ዓለምን ማዳኑን የምንማርበት ነው።*

**ምን ተማርን**? በሥጋዌ የጌታችንን ሰው መሆን እና ሰው የሆነበትን ምክንያት ተምረናል።

www.zeorthodox.org

# ምስጢረ ጥምቀት

## ዐሥራ አምስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ** ፡-ስለ ጥምቀት ማወቅ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ**፡-" *ሰው ዳግመኛ ከውኃ እና ከመንፈስ ካልተወለደ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አይገባም፡፡" ዮሐ .3፡5*

**ተጨማሪ ምንባባት**፡-

**መግቢያ፡-** ከአምስቱ አዕማደ ምስጢር ሁለቱ (ጥምቀት እና ቁርባን)በተግባር የሚፈጸሙ ናቸው ፤ በዚህ መሠረትም በሰባቱ ምስጢራት ውስጥ የሚዘረዘሩ ናቸው፡፡ በዚህ ትምህርታችን መሠረተ እምነት መሆናቸውን /ዶግማነታቸውን/ እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

**ጥምቀት**፡- መነከር፣ ማለት ሲሆን፤ በሥላሴ ስም በተጸለየበት ውኃ ሙሉ አካልን መነከር ማለት ነው፡፡

ጥምቀት ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ልጅነትን የሚያገኙበት ምስጢር ነው፡፡ ክርስቲያን ሆኖ የሚወለድ የለም፤ ስንጠመቅ ክርስቲያን እንሆናለን፡፡ በዚህ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት የሚያስችለንን ሥልጣን እናገኛለን፡፡ ‹‹ሰው ከውኃና ከመንፈስ ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም፡፡›› /ዮሐ.3 5/

ጥምቀት ሰዎች እንደገና የሚወለዱበትና የቤተ ክርስቲያን አካላት የሚሆኑበት ነው፡፡ ይህንኑ መሠረት በማድረግ ምእመናን መጀመሪያ ሊፈጽሙት ይገባል፡፡

www.zeorthodox.org

ጌታችን በመጠመቅ፣በማስተማርም ምጥምቀትን ሲያሳውቀን፤ ከሙታን ከተነሣ በኋላም፡- ‹‹ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ፡፡ እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፤ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው. . . .›› /ማቴ. 28 18 20/ በማለት ጥምቀትን መሥርቷል፡፡

## የጥምቀት ምሳሌዎች፡-

***የኖኅ መርከብ***

‹‹ጥቂቶች ማለት ስምንት ነፍስ በውኃ የዳኑበት መርከብ ሲዘጋጅ÷ የእግዚአብሔር ትዕግሥት በኖኅ ዘመን በቆየ ጊዜ አልታዘዙም፡፡ ይህም ውኃ ደግሞ ማለት ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድነናል›› /1ጴጥ.3 2 -21/፡፡

***ግዝረት***

በብሉይ ለአብርሃም እና ልጆቹ የእግዚአብሔር ሕዝቦች የመሆናቸውና እሱን የማመናቸው ምልክት ነበር፡፡ /ዘፍ. 17 9-01/ ይህም ለሐዲስ ኪዳን ጥምቀት ምሳሌ ሆኖ የተሰጠና የተፈጸመ መሆኑን ቅዱስ ጳውሎስ አስተምሯል፡፡ ‹‹*የሥጋንም ሰውነት በመገፈፍ÷ በክርስቶስ መገረዝ÷ በእጅ ባልተደረገ መገረዝ በእርሱ ሆናችሁ ደግሞ ተገረዛችሁ በጥምቀትም ደግሞ ከሙታን ባስነሣው በእግዚአብሔር አሠራር በማመናችሁ ከእርሱ ጋር ተነሣችሁ. . .* ›› ቆላስ.2 11-12፡፡

***3. ባሕረ ኤርትራን መሻገር***

‹‹አባቶቻችን ሁሉ ከደመና በታች ነበሩ ሁሉም በባሕር መካከል ተሻገሩ ሁሉም ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመናና በባሕር ተጠመቁ፡፡›› 1ኛ ቆሮ.0 1-2/

***የዮሐንስ ጥምቀት***

ከሰማይ የተሰጠ ነበር፡፡ ነገር ግን ‹‹ለኃጢአት ስርየት የንስሐ ጥምቀት›› /ሉቃ.3 3-6/ ብቻ እንጂ ዳግም ልደት የማስገኘት ሥልጣን አልነበረውም፡፡ ለክርስቶስ ትምህርትና ማዳን ማዘጋጀት ነበር ዓላማው፡፡ በተጨማሪም ለክርስና ጥምቀት ምሳሌ እና ማዘጋጃም ነበር፡፡

**ከክርስቶስ መሞት በፊት ሐዋርያት ያጠምቁ ነበር**

ጌታ በምድር በተመላለሰባቸው ዘመናት ሐዋርያት እንዳጠመቁ ተጽፏል፡፡/ዮሐ.4 2/ ነገር ግን ይህም ጥምቀት የዝግጅት ነበር፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም ‹‹እንደ ዮሐንስ መጥምቅ ዓይነት ነበር፡፡›› ሲል አብራርቶታል፡፡ የጥምቀትን አጀማመር እና አፈጻጸም በሚቀጥለው እናያለን፡፡

www.zeorthodox.org

**በጥምቀት ምን እናገኛለን ?**

***የልጅነት ሥልጣን“ለተቀበሉት ሁሉ ግን ÷ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ”*** ዮሐ.1፡12

***ሁለተኛ ልደት “ ሰው ዳግመኛ ከውኃ እና ከመንፈስ ካልተወለደ ወደ እግዚአብሔር***

*መንግሥት አይገባም፡፡" ዮሐ .3፡5*

***የኃጢአት ስርየት" ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ "*** የሐዋ.ሥ.2፡38

## ማጠቃለያ

ጥምቀት መነከር ማለት ሲሆን ትንቢት እና ምሳሌ የተነገረለት፤ በጌታችን የተሰጠን ነው፡፡

በጥምቀት የኃጢአት ስርየት ልጅነት እና ደግመኛ መወለድን እናገኛለን፡፡

www.zeorthodox.org

# ቅዱስ ቊርባን

## ዐሥራ ስድስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ**፡-ስለ ቅዱስ ቊርባን መማር፡፡

**የሚጠና ጥቅስ**፡-*" ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ ለዘላለም ሕይወት አለው ፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ ። ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና ። "* ዮሐ.6፡54-56

**ተጨማሪ ምንባብ** ፦ ዮሐ.4፡13-14

**መግቢያ፡-** ስለ አምስቱ አዕማደ ምስጢራት የጀመርነውን ትምህርት በመቀጠል፤ በዛሬው ትምህርታችን ስለ ቅዱስ ቊርባን እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

ቊርባን፡-የሱርስት ቃል ሲሆን ለአምላክ የሚቀርብ ስጦታ የሚል ትርጒም አለው፡፡ ጥንታውያኑ ግብጻውያን ኤውክሪስት ሲሉት *"ምስጋና ማቅረብ "* ማለት ነው ፡፡ በክርስትና ትምህርትም ቅዱስ ቊርባን እኛ ለአምላክ የምናቀርበው እርሱም ለእኛ የሚሰጠን አምኃ(ስጦታ) ነው፡፡ ይኸው ቊርባን የተለያዩ ስሞች አሉት፡፡እነርሱም፡-

"የጌታ ራት"

"ምስጢራዊው ራት "

"አንድ የመሆን ምስጢር "

"ክቡር ሥጋውና ቅዱስ ደሙ" ወ.ዘ.ተ.....ተብሎ ይጠራል፡፡

www.zeorthodox.org

**የምስጢረ ቊርባን አጀማመር**

ቅዱስ ቊርባን በጌታችን የተመሠረተ ሲሆን አመሠራረቱም፡-

**በትምህርት**፡- ዮሐ.6፡47-51 *"ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፡፡.....እኔ ከእርሱ ጋር እኖራለሁ እርሱም ከእኔ ጋር ይኖራል " " ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ*

*መጠጥ ነው ።”*

በተግባር፡- ጌታችን በምሴተ ሐሙስ “ *የመጨረሻውን ራት* ” ለደቀ መዛሙርቱ ሲያበላቸው በተግባር ያደረገውና ያስተማረው እንዲህ ተጽፎልናል፡፡“ *ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ ባረከ ቆርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና፡-እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ ። ጽዋንም አንሥቶ አመስግኖም ሰጣቸው እንዲህም አለ፡-ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የሐዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው፡፡”*ማቴ.26፡26-28

ካህናት በመሾም፡- ይህንን ምስጢር የመሠረተው ጌታችን ዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያት ብቻ ሰብስቦ ነው፡፡ (ማቴ.26፡26) ንስሓንና የኃጢኣት ስርየትን እንዲሰጡም የክህነት ሥልጣን እና ትእዛዝ ሰጥቶአቸዋል፡፡(ማቴ 28፡19-20;1ኛቆሮ.11፡23-26፣ሉቃ.24፡47፣22፡19-20)

## ቅዱስ ቊርባን ምንድነው ?

እውነተኛ የጌታችን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ነው፡፡“ *እንጀራን አንሥቶ ባረከ ቆርሶም.... ይህ ሥጋዬ ነው፡፡ ጽዋንም አንሥቶ .... ደሜ ይህ ነው አለ”* (ማቴ.26፡26)

*ሥጋው* እውነተኛ መብል ደሙም እውነተኛ መጠጥ ነው፡፡ይህም ማለት በልተን እና ጠጥተን ነገ እንደሚርበን ሳይሆን፤ ለዘላለም ከእኛ ጋር ሆኖ ዘለዓለማዊ ምግብ እና መጠጥ የሚሆነን ነው፡፡*“ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ ሰውም ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል፤ እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው፡፡ ”* (ዮሐ.6፡51) *“ እውነት እውነት እላችኋለሁ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም፡፡ ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ ለዘላለም ሕይወት አለው÷እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ፡፡ ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና፡፡”* ዮሐ.6፡53-56

መለኮት የተዋሐደው ነፍስ የተለየው ነው፡፡ የምንቀበለው *ሥጋና* ደም በዕለተ አርብ የተሠዋውን ነው፤ ጌታ በዚህች ቀን በነፍስ ወደ ሲዖል ሲወርድ በሥጋ በመስቀል ላይ ነበር፡፡ መለኮት ደግሞ ከሁለቱም ጋር የተዋሐደ ነው፡፡ በዚህ መሠረትም መለኮት የተዋሐደው ነፍስ የተለየው ብለን በማመን እንቀበላለን፡፡ ምሳሌ፡- እስራኤል የበሉት የፋሲካ በግ ሲበሉ የታዘዙት “ *ጥሬውን በውኃም የበሰለውን አትብሉ ነገር ግን... በእሳት የተጠበሰውን ብሉት ”* (ዘጸ.12፡9) ተብለው ነበር፡፡ ያም በግ የክርስቶስ ምሳሌ ነበር (1ኛ.ቆሮ.5፡7) እሳቱም የመለኮቱ ምሳሌ ነው፡፡

www.zeorthodox.org

ይህ ምስጢር ደም አልባ *መሥዋዕት* እንደሆነና ለመዳናችንም እንደሚቀርብ እናምናለን ፡፡ ይህንንም ከሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ማረጋገጥ እንችላለን፡፡ *“ስለ እናንተ የሚሰጠው /*

*የሚሠዋው / ሥጋዬ ይህ ነው ።  ይህ ጽዋ ስለእናንተ የሚፈሰው /የሚሰጠው / በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው።"* (ሉቃ.22÷19-20)

ቅዱስ ጳውሎስም በአሕዛብ እና በክርስቲያኖች መሥዋዕትና መሠዊያ መካከል ሲያነጻጽር (1ኛቆሮ.10÷18-21) የጌታን ማእድ (ቅዱስ ቊርባንን) እውነተኛ መሥዋዕት መሆኑን ማረጋገጫ ሰጥቶናል ።

በዕብ.13÷10 ላይም እውነተኛውን የክርስቲያኖች መሠዊያ ጠቅሶታል ።

ይህ የሐዲስ ኪደን መሥዋዕት በብሉይ ኪዳን ተተንብዮለት ነበር ። ***"ከፀሐይ መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያዋ ድረስ ስሜ በአሕዛብ ዘንድ ታላቅ ይሆናልና ፤ በየስፍራውም ለስሜ ዕጣን ያጥናሉ ፤ ንጹሕም ቊርባን ያቀርባሉ ፣ ስሜ በአሕዛብ ዘንድ ታላቅ ይሆናልና ፣ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።"*** (ሚልክ. 1÷11) ነቢዩ ስለ ሐዲስ ኪዳን መሥዋዕት እየተናገረ እንደሆነ ግልጽ ነው ፤ ይህም በወንጌል የቀረበው የጌታ ሥጋና ደም ነው ። ይህን ጥቅስ የተረጐሙ የተለያዩ ተርጓሚያንም ይህንኑ ነው ያረጋገጡት።

እንደ ካቶሊካውያን ሥጋውን ብቻ አንቀበልም ምክንያቱም ጌታ***"ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ "*** ዮሐ.6÷56  ነው እንጂ ያለው ሥጋዬን ብቻ አላለም። ለሐዋርያት ሲሰጣቸውም ኅብስቱን ቆርሶ ብሉ እንዳላቸው ጽዋውንም ቀድቶ ***"ሁላችሁም ከእርሱ ጠጡ"*** (ማቴ.26÷27) ነውና ያለው። የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖችም በሐዋርያት አማካኝነት ሁለቱንም ይቀበሉ እንደነበር ቅዱስ ጳውሎስ ***"የሚበላና የሚጠጣ"***  ***" ይበላልና ይጠጣልምና"*** በማለት ስለ ቅዱስ ቊርባን ሲናገር ጽፎልናል።

ሌሎቹ ደግሞ መታሰቢያ እና ምሳሌ ብቻ ነው ይላሉ። ለመሆኑ ጌታ ለመታሰቢያዬ አድርጉት ሲል ምን ማለቱ ነው? መከራ መስቀሌን እያሰባችሁ ፈጽሙት ማለት እንደሆነ ፤***" ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነው"*** (ዮሐ.6÷54) ሲል አረጋግጦልናል። ለሐዋርያት ሲሰጣቸው***"ነገ የሚፈስ ሥጋዬ"*** ***"ደሜም"*** (ማቴ.26÷26-27) ሉቃ.22÷29 አለ እንጂ ምሳሌ ነው አላላቸውም ። ቅዱስ ጳውሎስም ***" ከጌታ ሥጋ ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን "*** ብሎ አንድነቱን (አማናዊነቱን)  ያመለክታል ።

www.zeorthodox.org

***ይህን ምስጢር መፈጸም የሚችለው ማነው?*** ጌታ ዐሥራሁለቱን ሐዋርያት ብቻ መርጦ ***" ይህን ለመታሰቢያ አድርጉት"*** (ሉቃ 22÷19) ብሎም አዝዟቸዋል። ሐዋርያትም ለተከታዮቻቸው ጳጳሳት አስተላለፉ፤ ክርስትና እየተስፋፋ ሲሄድም፤ ካህናት እንዲፈጽሙት ተፈቅዷል፤ ዲያቆናት

በመራዳት ብቻ ያገለግላሉ። ምእመናን ግን ቀድሶ ማቍረብ አይችሉም ።

**ቅዱስ ቊርባንን መቀበል ያለበት ማነው ?**ጥሙቃን ክርስቲያኖች እንዲቀበሉ ታዝዞአል። ቀደምት ክርስቲያኖችም ***" ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ"*** (ዮሐ. 6÷56) ያለውን ይዘው በየሳምንቱ ይቆርቡ ነበር ።

በዓመት ሦስቴ መቁረብ ለእያንዳንዱ ክርስቲያን ይገባል። ኃጢአት ከተፈጸመም ወዲያው ንስሓ በመግባት ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ልንቀበል ይገባናል ።ቅዱስ ቊርባን ***ስለ ኃጢአት ስርየት የሚቀርብ*** ነውና ።

ነገር ግን ከመቍረባችን በፊት ራሳችንን በንስሐ ማዘጋጀት ይገባናል።***" ሰው ግን ራሱን ይፈትን እንዲሁም ከእንጀራው ይብላ ከጽዋውም ይጠጣ ፤ ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና ይጠጣልምና "*** (1ኛ ቆሮ.11÷28-29) ተብሎ እንደተጻፈ መቀበል የሚገባቸው በንስሓ የታጠቡ አማንያን ናቸው ።

ጥምቀት የተፈጸመላቸው ሕፃናትም ይህን የነፍስ ምግብም ሊከለከሉ አይገባምና ቅዱስ ቊርባን መቀበል አለባቸው ።

### ምን ተማርን ?

ቅዱስ ቊርባን የጌታችን ሥጋና ደም ነው ። ስንቀበለውም ከእርሱ ጋር እንሆናለን። የዘላለምንም ሕይወት እናገኛለን።

ቅዱስ ቊርባንን ለመቀበል በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም የተጠመቁ ክርስቲያኖች ከዚሁ ጋር በንስሐ የታጠቡ አማንያን እንጂ ከዚህ የተለየ የዕድሜ፣ የኑሮ ሁኔታ፣ የዕውቀት ወዘተ መመዘኛ አልተቀመጠም።

### ተግባር፡-

www.zeorthodox.org

ከቅዱስ ቊርባን የተለየ ሕይወት ሊኖረን አይገባም።

የሞት መውጊያ ኃጢአት በንስሐ ይወገዳል። የዘለዓለም ሕይወትን ለመቀዳጀት ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን እንቀበል።

# ምስጢረ ትንሣኤ ሙታን(1)

## ዐሥራ ሰባተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-**ስለ ክርስቶስ ዳግመኛ መምጣት እና ስለ ሙታን ትንሣኤ ማስገንዘብ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-*«ጻድቃንም ዓመጸኞችም ከሙታን ይነሡ ዘንድ እንዳላቸው ተስፋ በእግዚአብሔር ዘንድ አለኝ»*** (የሐ. ሥራ 24፡15)

**መግቢያ፡-** የዛሬው ትምህርታችን ትኩረት ከአምስቱ አዕማደ ምስጢር የመጨረሻው እና አምስተኛው ስለ ትንሣኤ ሙታን ነው፡፡

**የሳምንቱ ትምህርት፡-**

አምላካችን ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሰው ሲል ከሞተ በኋላ በሦስተኛው ቀን ተነሥቶአል፡፡ በዚህም ሙስና መቃብርን ድል ነሥቶአል፡፡ በአርባኛውም ቀን አርጎአል፡፡ ዳግመኛ ሲመጣም በምድር ልብ ውስጥ ያሉ የሰው ልጆች በነፍስና በሥጋ ይነሣሉ፡፡ ይህን የምናምንበትና የምናስተምርበት መሠረት ምስጢረ ትንሣኤ ሙታን ነው፡፡ (ማቴ 24፡31 1ኛ ቆሮ 15፡29)

ሰው ሁሉ ሞቶ ከበሰበሰ በኋላ (መክ.3፡14፣ኢዮ.11፡7) ነፍስና ሥጋ ተዋሕደው መነሣትና ከሞት በኋላ በነፍስና በሥጋ ሕይወት ማግኘት ማለት ነው፡፡ (ማቴ. 25፡31-46 ዮሐ.5፡25-29 ዳን.12፡2 )

*ሀ. ሞት ምንድን ነው? መጽሐፍ ቅዱስ ሞትን በብዙ መንገድ ተርጒሞልናል፡፡*

ከእግዚአብሔር መለየት፤የነፍስ ሞት ነው፡፡ ይህ ሞት ከእግዚአብሔር ፍቅር እና አንድነት መለየት ሲሆን በዚህ ምድር በኃጢአት ኖረው በኋላም በገሀነመ እሳት ለዘላለም መቃጠል ነው፡፡ (ራእ.20፡14) የዚህ ምክንያቱም አለማመንና ከምግባር መለየት ናቸው፡፡ አንድ ሰው ከበጎ ምግባር ተለይቶ የሚመላለስ ከሆነ ሙት ነው ፡፡ ***«አንተ ተከተለኝ ሙታናቸውን እንዲቀብሩ ሙታንን ተዋአቸው»*** (ማቴ.8፡21) በማለት ኢየሱስ ክርስቶስ ሊከተለው ለጠየቀው ጎልማሳ የመለሰለት መልስ ማስረጃችን ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም በሥጋ ፈቃድ እየተቀማጠለች ያለችን ሴት ሙት መሆንዋን ገልጦአል፡ ***« ቅምጥሊቱ በሕይወት ሳለች የሞተች ናት»*** (1ኛ ጢሞ. 5፣6)፡፡

www.zeorthodox.org

***የነፍስና የሥጋ መለያየት፦*** አንድ ሰው ሕይወት አለው፣ ተንቀሳቃሽ ነው የምንለው በነፍስና በሥጋው መዋሐድ ነው። ነገር ግን ለሁሉም ጊዜ አለውና ነፍሱ ከሥጋው ስትለይ ያ ሰው ሞተ ይባላል። ***« በእጅህ ነፍሴን እሰጣለሁ»*** (መዝ. 130፣5) ተብሎ እንደተጻፈ እስከ ጊዜ ምጽዓት ነፍስ በእግዚአብሔር እጅ ሥጋ በመቃብር ይቆያል። ስለዚህም አብነት የሆነን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። (ሉቃ. 23፣46) ሊቀ ዲያቆናት እስጢፋኖስ አይሁድ በድንጋይ እየወገሩት ለሞት በቀረበ ጊዜ ጌታ ኢየሱስ ሆይ ነፍሴን ተቀበል በማለት ጸልዮአል። ቅዱስ ያዕቆብ ሞት ማለት የነፍስና የሥጋ መለየት ማለት መሆኑን ተናግሮአል። ***‹‹ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደሆነ እንዲሁም ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው››*** (ያዕ.2፡26) ። የራሔል አሟሟት በተጻፈበት ክፍል ***‹‹እርሷም ስትሞት ነፍሷ በምትወጣበት ጊዜ››*** (ዘፍ. 35፡18) ተብሎ ተገልጾአል። ይህም ሞት ማለት የነፍስና የሥጋ መለያየት መሆኑን ያስረዳናል። ስለዚህ ሞት ስንል ነፍስ ወደ ፈጣሪዋ ሥጋ ወደ መቃብር መሄዳቸውን መናገራችን ነው።

በዚህ መሠረት በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ሞት ፈረዱበት (ሜቴ. 20፣18)። ***‹‹በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ በእርሱም ደግሞ ሄዶ በወህኒ ለነበሩ ነፍሳት ሰበከላቸው››*** (1ኛ ጴጥ. 3፡19) ተብሎ በተጻፈው መሠረት መለኮት የተዋሐደው ሥጋው ወደ መቃብር ነፍሱም መለኮት እንደተዋሐደው ወደ መቃብር፤ መሄዱን መናገራችን ነው። (ዮሐ. 19፣40-42) መለኮት የተዋሐደች ነፍሱ ግን በሲኦል ይሰቃዩ የነበሩ የአዳምን ልጆች ነጻ ለማውጣት ነጻነትን ሰበከችላቸው።

ነቢዩ ኤልያስ ትመግበው የነበረች ባልቴትን ልጅ ከሞት አስነሥቶላታል። ***‹‹አቤቱ አምላኬ ሆይ፣ የዚህ ብላቴና ነፍስ ወደ እርሱ ትመለስ ዘንድ እለምንሃለሁ ብሎ ጮኸ እግዚአብሔርም የኤልያስን ቃል ሰማ የብላቴናው ነፍስ ወደ እርሱ ተመለሰች፣ እርሱም ዳነ።››*** (1ኛ ነገ. 17፣ 19-23) ከዚህ የምንረዳው የባልቴቲቱ ልጅ ሞተ ሲባል የነፍስና ሥጋ መለያየት መሆኑን ይህንንም ***‹‹ነፍሱ ወደ እርሱ ተመለሰች››*** በሚለው መረዳት ይቻላል። ነቢዩ ኤልሳዕም የሱናማዊቱን ልጁ ከሞት ሲያስነሣ ነፍሱ እንድትዋሐድ፣ አስከሬኑ እንዲሞቅና እንዲነቃ አድርጎአል። (2ኛ. 4፣ 32-37) ቅዱስ ጳውሎስም ሞት ማለት የሥጋና የነፍስ መለያየት ማለት መሆኑን ሲያስረዳ አውጤኪስ የሚባል ጎበዝ የቅዱስ ጳውሎስ ትምህርት እየረዘመ ሲመጣ እንቅልፍ አሸንፎት ከ3ኛው ደርብ ወደ ታች ወድቆ ሳለ ሰዎች ሲያነሡት ቅዱስ ጳውሎስ ***“ ነፍሱ አለችበትና አትንጫጩ አላቸው ”*** (የሐ. ሥራ 20፣7-11) በማለት ገልጾአል። ዮሐንስ ወንጌላዊ በራእይ መጽሐፉ ብዙ ነፍሳት በበጉ ፊት ያመሰግኑ እንደነበር ገልጾአል።(ራእ.7፡9-11) ሞት ማለት የሥጋና የነፍስ መለያየት ነው።

www.zeorthodox.org

**ለ. በሞት ምክንያት ሥጋ በመቃብር በስብሶ አይቀርም፡-**

ቅዱስ ጳውሎስ ስለዚህ ነገር ሲያስረዳ *"የሙታን ትንሣኤ ደግሞ እንዲሁ ነው ፣ በመበስበስ ይዘራል፣ ባለመበስበስ ይነሣል፣ በውርደት ይዘራል፣ በክብር ይነሣል፣ በድካም ይዘራል፣ በኃይል ይነሣል፣ ፍጥረታዊ አካል ይዘራል መንፈሳዊ አካል ይነሣል"* (1ኛ ቆሮ.15፡42-43) በማለት ገልጾታል፡፡ ነቢዩ ኢሳይያስም ቀደም ብሎ *"ሙታንህ ሕያዋን ይሆናሉ፣ ሬሳዎችም ይነሣሉ፣ በምድር የምትኖሩ ሆይ፣ ጠልህ የብርሃን ጠል ነውና፣ ምድርም ሙታንን ታወጣለችና ንቁ ዘምሩም "* (ኢሳ. 26፡19) ብሎአል፡፡

በትንሣኤ ነፍስና ሥጋ ተዋሕደው ይነሣሉ፡- ስለዚህ ነገር ነቢዩ ዳንኤል *‹‹በምድር ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉቱ ብዙዎች ይነቃሉ እኩሌቶቹ››* (ዳን 12፡12) በማለት በማያሻማ ቋንቋ አስረድቶአል፡፡ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ *‹‹በመቃብር ያሉቱ ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፤ መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና በዚህ አታድንቁ››* (ዮሐ. 5፣28) ሲል በማይታበል ቃሉ አረጋግጦአል፡፡ *‹‹ጻድቃንም ዓመጸኞችም ከሙታን ይነሡ ዘንድ እንዳላቸው ተስፋ በእግዚአብሔር ዘንድ አለኝ››* (የሐ. ሥራ 24፡15) ተብሎ የተገለጸው ይህንኑ ያጠናክርልናል፡፡ ይልቁንም ቅዱስ ጳውሎስ በተብራራ መልኩ ሲገልጸው *‹‹ክርስቶስ ከሙታን እንደተነሣ የምንሰብክ ከሆነ ግን ከእናንተ አንዳንዶቹ ትንሣኤ ሙታን የለም እንዴት ይላሉ? ትንሣኤ ሙታንስ ከሌለ ክርስቶስ አልተነሣም ክርስቶስም ካልተነሣማ እንግዲያስ ስብከታችን ከንቱ ነው፡፡ እምነታችሁም ደግሞ ከንቱ ናት ደግሞም ክርስቶስን አስነሥቶታል ብለን በእግዚአብሔር ላይ ስለመሰከርን ሐሰተኛ የእግዚአብሔር ምስክሮች ሆነን ተገኝተናል፡፡ ሙታን ግን የማይነሡ ከሆነ ክርስቶስ አልተነሣማ ክርስቶስም ካልተነሣ እምነታችሁ ከንቱ ናት እስከ አሁን ድረስ በኃጢአታችሁ አላችሁ እንግዲያስ በክርስቶስ ያንቀላፉት ደግሞ ጠፍተዋል፡፡ በዚህች ሕይወት ብቻ ክርስቶስን ተስፋ ያደገግን ከሆነ ከሰው ሁሉ ይልቅ ምስኪኖች ነን፡፡ አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኵራት ሆኖ ከሙታን ተነሥቶአል፡፡ ሞት በሰው በኩል ስለመጣ ትንሣኤ ሙታን በሰው በኩል ሆኖአልና፡፡ ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና››* (1ኛ.ቆሮ.15፡22)፡፡

www.zeorthodox.org

**ማጠቃለያ** ሁለት ዓይነት ሞት አለ፡፡ አንዱ ከእግዚአብሔር መለየት እና የሥጋ ሞት ፡፡ ሁለተኛው ሞት ግን ትንሣኤ አለው፡፡

## ተግባር

በመልካም ሥራ ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖር እንወስን፡፡

ትንሣኤ እንዳለን እንመን፡፡

# ምስጢረ ትንሣኤ ሙታን(2)

## ዐሥራ ስምንተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-**ስለ ክርስቶስ ዳግመኛ መምጣት እና ስለ ሙታን ትንሣኤ ማሳወቅ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-**" ***ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት፣ እንዲሁ ይመጣል*** " (የሐዋ.1፡11)

***መግቢያ፡-*** ባለፈው ሳምንት የትንሣኤ ሙታንን ተምረናል፤ በዛሬው ትምህርታችንም ስለጌታችን ዳግም ምጽዓት እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት ፡-

**3. ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ ይመጣል**

የትንሣኤያችን በኵር ኢየሱስ ክርስቶስ ይመጣል፡፡ በዕርገቱ ቀን ቅዱሳን መላእክት ለደቀ መዛሙርቱ ***‹‹የገሊላ ሰዎች ሆይ፣ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለምን ቆማችኋል? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት፣ እንዲሁ ይመጣል አሉአቸው››*** (የሐ.ሥራ 1፡11) ተብሎ እንደተጻፈ ክርስቶስ ዳግም ይመጣል፡፡

በእርግጥ ክቡር ዳዊት በትንቢቱ፤ ***‹‹እግዚአብሔር ግልጥ ሆኖ ይመጣል፡፡ አምላካችን ይመጣል ዝምም አይልም››*** (መዝ 49፡2) በማለት እንደተናገረ ጌታችን ይመጣል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ኢየስስ ክርስቶስ ከቅዱሳኑ ሁሉ ጋር ሲመጣ (1ኛ ተሰ. 3፥13) ***‹‹ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔር መለከት ከሰማይ ይወርዳልና››*** (1ኛ ተሰ. 4፥16) በማለት ጽፎልናል፡፡ በተለይም ዮሐንስ በራእይ መጽሐፉ፤ ***‹‹እነሆ ከደመና ጋር ይመጣል ዓይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል የምድርም ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ አዎን አሜን››*** (ራእ.1፥7) ሲል ጌታችን ለፍርድ እንደሚመጣ አስቀድሞ ተናግሯል፡፡

www.zeorthodox.org

**4.በትንሣኤ ዘጉባኤ ፍርድ ሰጪው ክርስቶስ ነው፡-**

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በትንሣኤ ዘጉባኤ ሲመጣ ለሰው ልጆች ሁሉ ዋጋቸውን ይከፍላል፡፡ ዮሐንስ በራእዩ ***‹‹እነሆ በቶሎ እመጣለሁ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ››*** (ራእ.22፥12) ያለውን የአምላካችን ቃል ገልጾልናል፡፡

ጳውሎስም ***‹‹መልካም ቢሆን ወይም ክፉ እንዳደረገ እያንዳንዱ በሥጋው የተሠራው በብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናልና››*** (2ኛ ቆሮ.5፡10) በማለት ነግሮናል፡፡ በዚህ መሠረት በትንሣኤ ዘጉባኤ ኢየሱስ ክርስቶስ ጻድቃንን በቀኙ ኃጥአንን በግራው አቁሞ ዋጋቸውን ይከፍላቸዋል፡፡ (ማቴ.25፡31-47 ፣ ሮሜ 14፡10፣ ሮሜ 2፡6)

5. የትንሣኤ ዓይነት

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳስተማረን ሁለት ዓይነት ትንሣኤ አለ፡፡ ***‹‹በመቃብር ያሉቱ ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፤ መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና በዚህ አታድንቁ››*** (ዮሐ. 5፣28)

**የፍርድና የውርደት ትንሣኤ፡-** እነዚህ ሃይማኖትን ያላጸኑ (1ኛ ጢሞ. 4፣1-2) የአምልኮት መልክ ያላቸው የእግዚአብሔርን ኃይል ግን የካዱ (2ኛ ጢሞ. 3፣5) የአምላኩን ትእዛዝ በልቡ ጽፎ የማይሠራ (ምሳ 7፣3) በዝሙት፣ በመዳራት፣ በክርክር፣ በቅንዓት፣ በአድመኘነት፣ በቁጣ፣ በርኩሰት፣ በስካር፣ በዘፋኝነትና በመሳሰለው ሁሉ ዘመናቸውን የጨረሱ (› 5፣19) በአጠቃላይ በሞት መንገድ ላይ የቆሙ (ምሳ 14፣12) ሁሉ የውርደት ትንሣኤ ይጠብቃቸዋል (ማቴ 25፣41)፡፡

6.ተስፋችን ምንድን ነው?

የሰው ልጆች ሁሉ ትንሣኤ ካለን የክርስቲያኖች ተስፋችን ምንድን ነው? በመሠረቱ የሕይወት ተስፋችን ክርስቶስ ነው፡፡ (ዮሐ .11፣25) ቅዱስ ጳውሎስ የክርስቲያኖችን ተስፋ ሲገልጽ፤ ***‹‹ድንኳን የሚሆነው ምድራዊ መኖሪያችን ቢፈርስ በሰማይ ያለ በእጅ ያልተሠራ የዘላለም ቤት የሚሆን ከእግዚአብሔር የተሠራ ሕንፃ እንዳለን እናውቃለንና››***(2ኛ ቆሮ 5፣1) ብሏል፡፡

በዚህ መሠረት ክርስቲያኖች ከሁሉ አስቀድመው ተስፋቸውን እንዲፈልጉ ኢየሱስ ክርስቶስ አስተምሮአል፡፡ (ማቴ 6፣33) ስለዚህ ይህች ተስፋ ገነትን የማናያት ግን የምንወርሳት በመሆንዋ በትዕግሥት እንጠባበቃለን፡፡ የደማስቆው ሐዋርያ ጳውሎስ ***‹‹በተስፋ ድነናልና ነገር ግን ተስፋ የሚደረግበቱ ነገር ቢታይ ተስፋ አይደለም የሚያየውንማ ማን ተስፋ ያደርገዋል? የማናየውን ግን ተስፋ ብናደርገው በትዕግሥት እንጠባበቃለን››*** (ሮሜ 8፣24-25) ሲል ተናግሮአል፡፡ ስለዚህ ተስፋችን ዘላለማዊ ነው (2ኛ ቆሮ 4፣17)፡፡ ይህች ተስፋ እንድንጠባበቃት ያደረገን እስከ አሁን በዓይን ያልታየች በጆሮ ያልተሰማች ነገር ግን እግዚአብሔር ለወዳጆቹ ያዘጋጃት በመሆኗ ነው፡፡ (1ኛ ቆሮ 2፣8)

www.zeorthodox.org

ይህች ከተማ ለባልዋ እንደተሸለመች ሙሽራ ለክርስቲያኖች አምራ ከእግዚአብሔር

ተዘጋጅታለች ተሰጥታለች።(ራእ 21፣2) ከተማይቱ ብርሃናዊት ናት። (ራእ. 21፣ 11) በዚህች የተስፋችን ከተማ ከበጉ ክርስቶስ ጋር አብረን እንኖራለን፣ አንራብም አንጠማም። ከሕይወት ዛፍ እንበላ ዘንድ ይፈቀድልናል። በጉ ክርስቶስ እንባችንን ሁሉ ያብሳል፣ ሐዘናችንን ያርቅልናል። የበጉ ስም በግንባራችን ታትሞ ይኖራል። (ራእ. 21:3-4 ራእ 22:1-5) ስለዚህ ተስፋችን መንግሥተ ሰማይን እንደተስፋ ቃሉ እንጠብቃታለን። (2ኛ ጴጥ. 3፣10-13)

7. ወደ ተስፋችን የሚገቡ እነማን ናቸው?

ዓለምንና ምኞቷን ድል የነሱ፤ (ራእ. 21፣6-7)፣ በክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት ያመኑ (1ኛ ዮሐ. 5፣4-5)፣ ልብሳቸውን ያጠቡ ማለት ንስሓ ገብተው ሥጋውን የበሉ ደሙን የጠጡ፤ (ራእ. 6:53-57) ማቴ.25:34 ፣ ዮሐ. 6፣56፣ በፍቅር የሚሠራ እምነት ያላቸው፤ (ገላ. 5፣ማቴ 3፣10)

8. ወደ ተስፋ ምድር የማይገቡ እነማን ናቸው?

የተስፋይቱን ምድር የማይገቡባት ሰዎች አሉ። እነሱም በሕይወት መጽሐፍ ያልተጻፉት ናቸው። *‹‹ለበጉም በሆነው በሕይወት መጽሐፍ ከተጻፉት በቀር ጸያፍ ነገር ሁሉ ርኩሰትንና ውሸትም የሚያደርግ ወደ እርሷ ከቶ አይገባም።››* (ራእ.21:27) በተጨማሪም *‹‹አምስቱ ውሾች ግን ከዚያች አገር ወጥተው ይሄዳሉ። እኒህም ሥራይን የሚያደርጉ፣ ሴሰኞች፣ ነፍስ ገዳዮች፣ ጣዖትን የሚያመልኩና የሐሰት ሥራ የሚወዱት ሁሉ ናቸው››* (ራእ. 22:15) በማለት ዘርዝሮ አቅርቦአቸዋል።

ከላይ የተዘረዘሩትን ተግባራት የሚፈጽሙ ሁሉ ሀገራቸው ወይም ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነውና (ራእ 21፣8) ምክንያቱም ሞት የሚገባው ኃጢአትን ሠርተዋልና። (1ኛዩሐ. 5፣16፣ ራእ.20፣10)

## ማጠቃለያ ፦

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ይመጣል ፤

www.zeorthodox.org

ሁለት ዓይነት ትንሣኤ አለ። የክብር እና የውርደት።

## ተግባር ፦

ስለ ትንሣኤ ሙታን ጠይቁ እና አንብቡ።

# ኮከብ የመራቸው ሰብአሰገል

## ዐሥራ ዘጠነኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የሰብአ ሰገልን ታሪክ በማወቅ ለእግዚአብሔር የምናቀርበውን መረዳት፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-*"ወደ ቤትም ገብተው ሕፃኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር አዩት፣ ወድቀውም ሰገዱለት፣ሳጥኖቻቸውንም ከፍተው እጅ መንሻን ወርቅ፣ዕጣን ከርቤም አቀረቡለት፡፡"*** ማቴ.2፡12

**ምንባብ፡-** ማቴ 2፡1-12

**መግቢያ፡-** ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲወለድ ብዙ ምልክቶች ተደርገዋል፤ መላእክት ለእረኞች ተገልጠዋል፣ አብረውም አመስግነዋል፡፡ ታላቅ ብርሃንም ሆኗል፡፡

በዛሬው ትምህርታችንም በልደት ከተፈጸሙት እና ከሚዘከሩት አንዱ የሰብአ ሰገልን ወደ ቤተልሔም መምጣት፣ ስጦታቸውን ማቅረባቸውንም እንመለከታለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ሰብአ ሰገል፡-የጥበብ ሰዎች ማለት ነው፡፡***"የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው? ኮከቡን በምሥራቅ አይተን ልንሰግድለት መጥተናልና እያሉ ከምሥራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መጡ፡፡"*** (ማቴ.2፡1-2) ለጌታችን ስግደት እና ስጦታ ማቅረባቸው በወንጌል የተጻፈላቸው ሰብአ ሰገል ረጅም መንገድ ተጉዘው ፤ ኢየሩሳሌም ደረሱ፤ ቊጥራቸውም ብዙ እንደሆነ ***"አይተን ልንሰግድለት መጥተናልና እያሉ . . . . መጡ፡፡" "በሌላ መንገድ ወደ አገራቸው ሄዱ፡፡"*** ከሚለው ኃይለ ቃል ፣ ሦስት ስጦታ (ወርቅ፣ ዕጣን፣ ከርቤ) ማቅረባቸው (ማቴ 2፡11) ስለተገለጠ እና በቤተ ክርስቲያን ትውፊትም እንደምንረዳው ማንቱሲፋር፣ በልዳድስፎር እና ሜልኩ የሚባሉ ነገሥታት መሆናቸው ስለሚተረክ ሦስት መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ እንደ ነገሥታትም ብዙ ሠራዊት አስከትለው ነበር፡፡

ከየት መጡ ? በወንጌል ***"ከምሥራቅ"*** ይላል( ማቴ 2፡2)፤ ቀደም ብሎ በነቢዩ ንጉሥ ዳዊት ***‹‹በፊቱም ኢትዮጵያ ይሰግዳሉ፣ ጠላቶቹ አፈር ይልሳሉ፡፡ የተርሴስና የፋርስ ነገሥታት ስጦታን ያመጣሉ እጅ መንሻን ያቀርባሉ፡፡››*** መዝ. 71/72/ 9-10 ተብሎ በተነገረው ትንቢት መሠረትም ከአንድ ቦታ ሳይሆን ከተለያየ አህጉር የተሰባሰቡ እና ከምሥራቅ ተነሥተው የመጡ መሆናቸውን

www.zoorthodox.org

እንረዳለን፡፡

### ለምን መጡ ?

እራሳቸው እንደገለጡት ትንቢት የተነገረለት ንጉሥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መወለዱን አውቀው *" ልንሰግድለት "* መጣን ብለዋል፡፡ ሲያገኙትም *"ወደ ቤትም ገብተው ሕፃኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር አዩት ፣ ወድቀውም ሰገዱለት "* ማቴ 2፡11 ጉልበት ሁሉ የሚሰግድለት ጌታን ቀድመው የተረዱት እነዚህ ጥበበኞች ወደ ቤተልሔም መጡ፡፡

**እንዴት አወቁ?** *" ኮከቡን በምሥራቅ "* አይተው (ማቴ.1፡2) ጌታችን መወለዱን አወቁ፣ በተጨማሪም ከአሕዛብ ወገን የሆነው የበለዓምን *" አየዋለሁ አሁን ግን አይደለም፤ እመለከተዋለሁ÷በቅርብ ግን አይደለም፤ ከያዕቆብ ኮከብ ይወጣል÷ ከእስራኤልም በትር ይነሣል÷. . . "* ዘኁል.24፡15-17 የሚለውን ትንቢት ኃጢአትን የሚያስቀር የአይሁድ ንጉሥ እንደሚወለድ ይጠብቁ ነበር፡፡ ኮከቡን ሲያዩም ጥበበኞች ስለነበሩ አስተዋሉት፡፡

ኢየሩሳሌም እንደደረሱ *"የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው?"* አሉ ፡፡ ንጉሡ ሄሮድስ ምድራዊ ንጉሥ የተወለደ መስሎታልና ሰምቶ ደነገጠ ፣ ኢየሩሳሌምም ከሰብአ ሰገል አጃቢዎች ብዛት የተነሣ ከሄሮድስ ጋር ደነገጠች፡፡ ወዲያውም ሄሮድስ የትንቢት መጽሐፍ አዋቂ የሆኑትን ካህናትንና የሕዝቡንም ጻፎች ሰብስቦ ክርስቶስ የሚወለድበትን ጠየቃቸው፡፡ እነርሱም በትንቢተ ሚክያስ 5፡2 በተነገረው ትንቢት መሠረት በቤተልሔም መሆኑን ነገሩት፡፡ ሰብአ ሰገልን በስውር ጠርቶም ያዩበትን ዘመን ጠይቆ በቤተልሔም መሆኑንም አስረዱትና ሸኛቸው፡፡

**ጉዞ ወደ ቤተልሔም፡-**

እነርሱም ንጉሡን ሰምተው /ወደ ቤተልሔም/ ሄዱ፣ ኮከቡም ይመራቸው ነበር፡፡ ጌታችን ባለበት ሲደርሱም ኮከቡ ቆመ፡፡ እነርሱም ብዙ የተጓዙበትን ቦታ ሲያገኙ በታላቅ ደስታ እጅግ ደስ አላቸው፡፡ ወደ ቤት ሲገቡም ሕፃኑን ከእናቱ ከድንግል ማርያም ጋር አዩት፡፡

www.zeorthodox.org

**ስግደት እና ስጦታ፡-**

ሰብአ ሰገል፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እና ጻድቃን / እነ ቅዱስ ዮሴፍ/ ባሉበት ቤት ተገኝተዋል፡፡ ያቺ ቤት የዛሬዋ ቤተክርስቲያን ናት፡፡ ጌታችንና እናቱ ባሉባት ቤት የሚፈጸመው ምንድን ነው?

**ስግደት፡-** መጽሐፍ ሰብአ ሰገል *"ወድቀውም ሰገዱለት"* ማቴ. 2፡11 ይለናል፡፡ ከላይ ያየናቸው የመጻሕፍት አዋቂዎች ያልተረዱትን ከተስፋይቱ ምድር ውጪ የነበሩት ፈለጉት፣ አገኙት፣

የሚገባውንም ስግደት ሰገዱለት፣ምን ዓይነት ጥበብ ነው ? እነዚህ ሀብታም፣ ጥበበኞች እና ባለሥልጣን የነበሩ ሰዎች በሰው ዘንድ ካላቸው ክብር በላይ፣ ኢየሩሳሌም እና ንጉሥ ሄሮድስን ካስደነገጠ ዕውቀታቸው እና ክብራቸው በላይ እግዚአብሔርን ያከበሩ ናቸውና ***"ወድቀው ሰገዱለት"*** ። እኛም በእግዚአብሔር ቤት ስንገባ ጉልበት ሁሉ ለሚሰግድለት ለጌታችን ወድቀን እንሰግድለታለን።

*ስጦታ ፡- ነቢዩ ዳዊት* ***" ስጦታን ያቀርባሉ . . . እጅ መንሻ ያመጣሉ"*** *መዝ*.71/72/፡ 9-10 *ብሎ እንደተነበየው ሣጥኖቻቸውን ከፍተው* ***"ወርቅ ዕጣን ከርቤን"*** *እጅ መንሻ አቀረቡለት*።*ማቴ* 2፡11

*ክርስቶስ የሰማይ እና የምድር ንጉሥ ነውና - ወርቅ*

*የካህናት አለቃ /ሰያሜ ካህናት/ ነውና - ዕጣን*

*መራራ ሞትን ለሰው ልጆች ይቀምሳልና - ከርቤን አቀረቡለት። እኛም ያለንን ምስጋና፣ ምጽዋት፣ ጊዜ፣ ጉልበት፣ መልካም ንግግር ልናቀርብለት ይገባል ። እርሱም ትንሽ የሚለው ሳይኖር ይቀበላል /ሉቃ* 21፡2-4/ *ያበረክተዋልም። ዮሐ* 6፡9-11

***መልስ ፡-***

ሰብአ ሰገል የመጡበትን ከፈጸሙ በኋላ ሄሮድስ ***" እኔ ደግሞ መጥቼ እንድሰግድለት ንገሩኝ "*** *ማቴ*.2፡8 *ያላቸው ሥልጣኑን የሚቀማው የተወለደ መስሎት ሊገድለው ነበር*። ሰብአ ሰገል ይህንኑ በህልማቸው ተረድተው ወደ ሄሮድስ እንዳይመለሱ በሌላ *መንገድ* ወደ አገራቸው ሄዱ።

## ምን ተማርን ?

ሰብአ ሰገል እንደ ስያሜያቸው እውነተኛ ጥበበኞች ስለነበሩ ጌታቸውን አግኝተዉ ሰገዱለት ፤ ለአምላክ የሚቀርበውን ስጦታም አበረከቱለት።

*ከተለያየ ቦታ ቢመጡም አንድ ዓላማ ነበራቸው። እርሱም፤ ለክርስቶስ መስገድ እና ስጦታ ማቅረብ ። እኛም ከየትኛውም ቤተሰብ እና የኑሮ ደረጃ ብንመጣም በቤተ ክርስቲያን ያለን ዓላማ አንድ ነው።*

www.zeorthodox.org

## ተግባር፡-

እንደ ሰብአ ሰገል ስለ እግዚአብሔር ለማወቅ የእግዚአብሔርን ቃል እናንብብ።

ይህን ስናደርግም እንደ ሰብአ ሰገል ጌታችንን በቤቱ ውስጥ ከእናቱ ጋር እናየዋለን።

ራሳችንን በእግዚአብሔር ፊት በማዋረድ በፊቱ ወድቀን መስገድ አለብን።

ለእግዚአብሔር ቃል ታዛዦች እንሁን፡፡

**መዝሙር - 1**

**የጥበብ ሰዎች**

ሰማይና መሬት የማይወስኑት

ተወስኖ አየነው በጠባብ ደረት

ዘጠና ዘጠኙን መላእክትን ትቶ

አገኘነው ዛሬ በበረት ተኝቶ

የጥበብ ሰዎች መጡ (2) ሰምተውት በዜና

እያበራላቸው ኮከብ እንደፋና

ድንግል እመቤቴ ሰላምታ ይድረስሽ

ለአምላክ ወገኖች መመኪያቸው የሆንሽ

ከአንቺ ተወለደ የዓለም መድኅን

ኵነኔን አጥፍቶ ጽድቅን ሊያወርሰን

ጌታችን ሲወለድ በቤተልሔም

ሐዘን ተደምስሶ ሰፈነ ሰላም

እንጨቶች አፈሩ ፍሬ በረከት

ወንዞች ሁሉ ሆኑ ማርና ወተት፡፡

ሰብአ ሰገል መጡ ሊሰግዱ በሙሉ

የእሥራኤል ንጉሥ ወዴት ነው እያሉ

www.zeorthodox.org

እጅ መንሻውን ሰጡ እንደ የሥርዓቱ

ዕጣኑን ለክህነት ወርቁን ለመንግሥቱ፡፡

# ከተራ እና ገሀድ

## ሃያኛ ሳምንት

**የትምህርት ዓላማ፡-** በየዓመቱ ጥር 10 ቀን ስለምናከብረው በዓል እና ስለ ጾመ ገሃድ በቂ ዕውቀት እንዲያገኙ ማድረግ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ ፡-** ***"ሳይሻገሩም በዚያ አደሩ፡፡"*** ኢያ.3፡1

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ኢያሱ 3፡1-17

**መግቢያ፡-** በየዓመቱ ጥር 10 ቀን በጥምቀት በዓል ዋዜማ ታቦት አጅበን ታቦታት በሚያድሩበትና በዓሉ በሚከበርበት ጥምቀተ ባሕር በሚባለው ቦታ እንሄዳለን፤ በዕለቱም ጾም እንጾማለን ፡፡ ይህ በዓል ከተራ ሲባል ጾሙንም ጾመ ገሃድ እንለዋለን፡፡ በዛሬው ትምህርታችን በዚህ ዕለት ስለሚከበረው በዓል እና ስለ ጾመ ገሃድ እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

የጥምቀት በዓል እስራኤል የዳስ በዓል ብለው በኦሪት በሚያከብሩት በዓል እና ሥርዓት የተተካ ነው ፡፡ የጌታችንን በዮሐንስ እጅ መጠመቅ ፣ ያጣነውን የልጅነት ሥልጣን ጌታችን የመለሰበት እና የዕዳ ጽሕፈታችንን ለመደምሰስ በዮርዳኖስ የቀመበትን እናከብርበታለን፡፡ ከዚህም ጋር የእግዚአብሔር ሦስትነት /ምስጢረ ሥላሴ/ የተገለጸበትን የምናስብበት ታላቅ በዓላችን ነው፡፡ ዋዜማውም ከተራ ተብሎ እንደ በዓል ሲከበር፣ ገሃድ ተብሎ ይጾማል፡፡

ከተራ፡- ከተራ አቆመ አገደ ከለከለ የሚሉ ትርጉሞች የሚሰጥ ቃል ነው ፡፡ ይህ በዓል አከባበሩ በመጽሐፍ ቅዱስ በተፈጸመ ታሪክ መሠረት የሚከበር ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን ኢያሱ ምድረ ርስትን ለማውረስ ሕዝበ እስራኤልን እየመራ በጉዞ ላይ እንዳሉ ያጋጠማቸው የመጀመሪያው መሰናከል የዮርዳኖስ ወንዝ ነበር፣ ***"እንደ መከር ወራት ሁሉ የዮርዳኖስ ወንዝ እጅግ ሞልቶ ነበርና፡፡"*** (ኢያ. 3፡15) ዮርዳኖስን ካልተሻገሩ ደግሞ ሕዝበ እስራኤል ምድረ ርስትን ሊወርሱ አይችሉም፡፡ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ሦስት ቀን እግዚአብሔርን ጠየቁ፡፡

www.zeorthodox.org

በሰጢም የነበረው ኢያሱም ማልዶ ተነሣ፤ እርሱና የእስራኤልም ልጆች ሁሉ ከሰጢም ተነሥተው ወደ ዮርዳኖስ መጡ ፣ ሳይሻገሩም በዚያ አደሩ ፡፡ ከሦስት ቀንም በኋላ አለቆች በሰፈሩ እየዞሩ የሚከተለውን ዓወጁ፡- ***"የአምላካችን የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ታቦት ሌዋውያን ካህናት***

*ተሸክመውት ባያችሁ ጊዜ ÷ ከሰፈራችሁ ተነሥታችሁ ተከተሉት። "* ( ኢያ.3፡3)

ኢያሱም ሕዝቡን *"ተቀደሱ"* አለ። ካህናቱንም የቃል ኪዳኑን ታቦት ተሸክማችሁ በሕዝቡ ፊት እለፉ አለ፤ ካህናቱም አለፉ።

እግዚአብሔር ኢያሱን ‹‹በእስራኤል ሁሉ ዓይን ከፍ ከፍ አደርግህ ዘንድ እጀምራለሁ›› አለው። ካህናቱ ወንዙን ሲረግጡት እንደሚቆምም ነገረው።

‹‹ታቦቱንም የተሸከሙት የካህናቱ እግሮች በውኃው ዳር ሲጠልቁ ከላይ የሚወርደው ውኃ ቆመ፤ በጻርታን አጠገብ ባለችው አዳም በምትባል ከተማ በሩቅ ቆሞ በአንድ ክምር ተነሣ ወደ ዓረባ ባሕር ወደ ጨው ባሕር የሚወርደው ውኃ ፈጽሞ ተቋረጠ፤ ሕዝቡም በኢያሪኮ ፊት ለፊት ተሻገሩ።›› (ኢያ. 3፡15) በዮርዳኖስ በሕዝቡ ፊት ከፍ ከፍ የተደረገው ኢያሱ፣ በዮርዳኖስ ባሕር በአምላክነቱ የተገለጠው የጌታችን ምሳሌ ነው። ወንዙ እንደ ቆመ ጌታችን አበሳችንንና የኃጢአትን አስፈሪነት አቆመ ፤ ድል ማድረግን በልጅነት አድሎናል ። ይህንንም ለማሰብ በጥምቀት ዋዜማ ወንዝ ተከትሮ ፣ ግድብ ተሞልቶ ፣ ዳስ ተጥሎ ታቦታቱ በወንዝ ዳርቻ በዳስ ያድራሉና በዓሉ ከተራ ተባለ።

ገሃድ፡- በዘይቤ ግልጥ ማለት ሲሆን ፣ በዚህ ያለው ትርጉም ግን ልዋጭ ማለት ነው። ጥምቀት ታላቅ በዓል ስለሆነ በጾም ቀን ቢውል /ዓርብ እና ረቡዕ/ አይጾምም። በለውጥ እንዲጾሙ ተጀምሮ፣ በኋላ ከበዓል ጾምን ለማስቀደም ከጥምቀት በፊት ያለው ቀን /ከተራ/ እንዲጾም ሆኗል። ጥምቀት እሑድ ወይም ሰኞ ቢውል፣ ከጥምቀት በዓል ዕለት በፊት ያለው ቀን ቅዳሜ ወይም እሑድ የፍስክ ሳይበላ በጾም ምግቦች ይዋላል። ገሃድ በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ከሰባቱ አጽዋማት አንዱ ነው። ገሃድ የምስጢረ ሥላሴ፤ የክርስቶስ ለዓለም መገለጥ በሚከበርበት ዋዜማ ስለሚጾምም ገሃድ (በግልጥ) ሲባል፣ በምትክነቱም ለውጥ ተብሎ ይጾማል።

## ምን ተማርን ?

www.zeorthodox.org

ከተራ እግዚአብሔር የዮርዳኖስን ወንዝ ያቆመበትን ከሐዲስ ኪዳን መንፈሳዊ ትርጉም አንጻር የምናስበው እና የምናከብረው በዓል ነው። በዚህ በከተራ ቀን ከሰባቱ አጽዋማት አንዱ የሆነው ጾመ ገሃድ ይጾማል።

## ተግባር፡-

በከተራ ጌታችንን የምናከብርበት፣ ቃሉን ሰምተን የምንከተልበትን ሕይወት የምናስታውስበት ነውና ራሳችንን መፈተሽ ይገባል። አስፈሪው የኃጢአት ሸክምና ሞት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ

ተደምስሷል፡፡"*እኛ ደግሞ ሸክሙን ሁሉ ቶሎም የሚከበንን ኃጢአት አስወግደን ፣ የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ* " ዕብ.12፡2፡፡

**መዝሙር**

አክሊሎሙ አንተ ለሰማዕት

ወአስተርአየ ገሃደ ከመ ሰብእ

www.zeorthodox.org

# ጌታ ይወደው የነበረ ደቀ መዝሙር

## ሃያአንደኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ከወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ ፍቅርን፣ ጥልቅ መንፈሳዊነትና ጽናትን መማር፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *" ትእዛዚቱም ይህች ናት በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናምን ዘንድ ትእዛዝንም እንደ ሰጠን እርስ በእርሳችን እንዋደድ ዘንድ፡፡"* 1ኛ ዮሐ. 3፡23

**ምንባባት፡-** የዮሐንስ ወንጌል ፤ የወንጌል እና ሠለስቱ ሐዲሳት ትርጓሜ መግቢያ፣ ስንክሳር ጥር 4 ፡፡

**የትምህርቱ መግቢያ፡-** ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ የሆነውና በመጽሐፍ ቅዱስ ጌታ ይወደው የነበረ ደቀ መዝሙር የተባለው ዮሐንስ በመጽሐፍ ቅዱስ አምስት መጻሕፍትን ጽፎልናል፡፡በዛሬው ትምህርታችን የሐዋርያውን ሕይወት መሠረት በማድረግ እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

### ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ፡-

ስያሜው ዮሐንስ *" እግዚአብሔር ጸጋ ነው"* ማለት ነው፡፡ ይህ በቤተሰቡ የተሰጠው ስያሜ ሲሆን፣ ሌሎች ስያሜዎችም አሉት ፡-

**ወልደ ነጎድጓድ፡-** በሉቃ 9፣54 እና ማር 3፣17 እንደተጠቀሰው የሰማርያ ሰዎች ብዙ ተአምራት ተደርጎላቸው ፤ በጌታችን ባለማመናቸው እርሱና ወንድሙ ለጌታ ቀንተው፤ *እሳት ከሰማይ ወርዶ ያጥፋቸው፤* በማለታቸው የነጎድጓድ ልጆች ተባሉ፡፡

www.zeorthodox.org

**ፍቁረ እግዚእ፡-** የጌታ ወዳጅ /ጌታ ይወደው የነበረ/ ይሄም በወንጌል እንደተገለጠው ፣ ጌታ የምስጢር ሐዋርያት አድርጎ ከሚጠራቸው ከሦስቱ/ያዕቆብ፣ ጴጥሮስ እና ዮሐንስ/ አንዱ ከመሆኑም በተጨማሪ፤ ጌታችን አሳልፎ ስለሚሰጠው ይሁዳ ሲናገር፣ ዮሐንስ ከወዳጅነቱ የተነሳ ወደ ደረቱ ተጠግቶ መልስ አግኝቶአል፤ ይሄም በወንጌል *"ኢየሱስም ይወደው የነበረ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ በኢየሱስ ደረት ላይ ተጠጋ . . ."* ዮሐ. 13፡23 ተብሎዋል፡፡ ዮሐንስም ለፍቅሩ እውነተኛ ምላሽ

ስለነበረው ጌታ ሲሰቀል ከሁሉም ሐዋርያት ተለይቶ እስከ መጨረሻው በእግረ መስቀሉ ተገኝቷል፤ (ዮሐ. 13፡23 ፣ 19፡26) በዚህም ይህ ስም ተሰጥቶታል።

**ቊጹረ ገጽ** (ፊቱ በሐዘን የጠቆረ)፡- በነቢዩ ኢሳያስ ***" መልክና ውበት የለውም ባየነው ጊዜ እንወደው ዘንድ ደም ግባት የለውም። የተናቀ ከሰውም የተጠላ፣ የሕመም ሰው ደዌንም የሚያውቅ ነው፣ ሰውም ፊቱን እንደሚሰውርበት የተናቀ ነው፣ እኛም አላከበርነውም"*** (ኢሳ 53፣2-3) ተብሎ ስለ ጌታችን የመስቀል መከራ የተገለጠው ሲፈጸም ሐዋርያው ጌታችን ተሰቅሎ በዓይኑ አይቷል ፣ ከመስቀል በፊት ***"ውበትህ ከሰው ልጆች ይልቅ ያምራል"*** መዝ 44/45/፡3 የተባለለትን የጌታችንን ተወዳጅ ደም ግባትም ያውቃል። በመስቀል ላይ ያን ሁሉ መከራን ተቀብሎ የሚታይ አካል እስከማይቀርለት ድረስ ጌታችን የተቀበለውን መከራ ካየ በኂላ ፊቱ በሐዘን እንደተቋጠረ ስለኖረ ***"ፊቱ የተቋጠረ -ቊጽረ ገጽ"*** ተብሏል።

**ነባቤ መለኮት /*ታዎሎጎስ*/፡-** የክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት ከሁሉም በተለየ ሁኔታ ስለዘገበ፤ የመለኮትን ነገር የተናገረ፤ ለማለት ይህ ስያሜ ተሰጥቶታል። በአጠቃላይ በእነዚህ እና በሌሎች ስሞች የሚጠራውን ዮሐንስን ከትውልድ እና እድገቱ ጀምረን እንማራለን።

**2.ትውልዱ እና እድገቱ፡-**

ዮሐንስ አባቱ ዘብዴዎስ እናቱ ማርያም ባውፍልያ /ሰሎሜ/ ይባላሉ። (ማቴ 4፡1፣ 27፡26) አባቱ ዓሣ አጥማጅ ስለነበረ በዚሁ ሥራ አብሮ አድጓል። /ማር 1፣20/ በተጨማሪም በሊቀ ካህናቱ የታወቀ ነበር። እናቱ ሰሎሜም ጻድቅና በፍቅር ጌታን ትከተለው ነበር፤ (ማር 15፣40፤) የጌታን መቃብር ሽቱ ለመቀባት ከተባበሩት አንዱዋ ናት። /ዮሐ. 19፣25/ ዮሐንስ ዓሣ እያጠመደ፣ በእናቱ ሃይማኖት እየተጓዘና በሊቀ ካህናቱ በታወቀበት መቅደስ ለአገልግሎት የቀረበ ሰብእና ነበረው።

**3.ጥሪ እና ጌታን መከተል ፡-**

ከወንድሙ ከያዕቆብ ጋር በዓሣ አጥማጅነት እየሠሩ አባታቸውን ሲረዱ ጌታችን ***"ተከተሉኝ"*** አላቸው፤ ወዲያውም አባታቸውን ትተው ተከተሉት። ሄሮድስ አግሪጳ ያዕቆብን በ44 ዓ.ም ገደማ በሰይፍ አስገደለው። (የሐዋ. ሥራ 12፣1) ያዕቆብ፣ ጴጥሮስ፣ እንድርያስ እና ዮሐንስ ጌታችንን በመጀመሪያ የተከተሉት ደቀመዛሙርት ናቸው።

www.zeorthodox.org

ቅዱስ ሄሬንዮስ ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ ጌታችንን ሲከተል የሃያ አምስት ዓመት ወጣት ነበር ይላል።ከቅዱስ ጴጥሮስ እና ያዕቆብ ጋር በመሆን የምስጢር ሐዋርያት ሆነው በተለያዩ ቦታዎች ተገኝተዋል። **ለምሳሌ** በደብረ ታቦር /ግርማ መለኮቱን ሲገልጥ /ማቴ 17፣1/ የኢያኢሮስን ልጅ ሲያድን /ማር 5፣37/ በጌቴ ሲማኒ የአትክልት ስፍራ ሲጸልይ፣ /ማር 13፣3/

ጌታችን የፋሲካን ራት እንዲያዘጋጁ የላካቸው ጴጥሮስ እና ዮሐንስን ነበር። /ሉቃ. 22፡8/ በጌታችን ደረት ተጠግቷል / ዮሐ.13፡23 / እስከ መስቀል ጌታችንን ተከትሎም እመቤታችን ተቀብሎአል።/ዮሐ.19፡20-27/

ጌታችን ትንሣኤውን በጥብርያዶስ ባሕር ሲገልጥ ጌታን ቀድሞ ያወቀው ዮሐንስ ነበር።ዮሐ 21፡4-8። እስከ ጌታችን ዳግሞ ምጽአት እንደማይሞት የተነገረለትም ያን ጊዜ ነው። ዮሐ. 21፡20-23

መልካም በሚሏት መመላለሻ የነበረውን በሽተኛ ሲያድን /የሐዋ 3፡1-6/ በሰማርያም ለአሕዛብ መንፈስ ቅዱስን ሲያሳድር /የሐዋ 8፣14-17/ ከጴጥሮስ ጋር ነበር። ቅዱስ ጳውሎስ ***አዕማድ*** ብሎ ከጠራቸው ሐዋርያት አንዱ ይህ ዮሐንስ ነው።/የሐዋ 15፡6; ገላ 2፡6-9/

ዮሐንስ በታናሽ እስያዋ በኤፌሶን አስተምሮአል። በንጉሥ ድምጥያኖስ ተገርፎአል፣ መከራን ተቀብሎአል፣ በፍጥሞ ደሴትም ተግዞ ፣ በስደት ኑሮአል፤ በዚያም ***በጌታ ቀን በመንፈስ ሆኖ*** ያየውን ራእይ ጽፎአል።

ዮሐንስ በስተ እርጅናውም ከግዞት መልስ በኤፌሶን አባቶችን ለመሾም እና አሕዛብንም ለማስተማር ሄዷል። በአንድ ወቅት ብርቱ የነበረን አንድ ወጣት ክርስቲያን ከቤተ ክርስቲያን አጥቶት ሊቀጳጳሱን ሲጠይቅ፤ ክርስትናን ትቶ የሽፍቶች አለቃ መሆኑን ሰማ፤ ቅዱስ ዮሐንስ በእርጅናው በበቅሎ ወደ በረሐ ሄዶ ያንን ሰው ከጥፋት መንገዱ በፍቅር መልሶታል።

የኑፋቄን ትምህርት አጥብቆ በመቃወም የጻፈልን ዮሐንስ በሕይወቱም እንዲሁ ነበር። ዮሐንስ በስሙ የሚጠራውን ወንጌል፣ ሦስቱን መልእክታት እና ራእዩን ጽፎልናል።

በሚፈላ ዘይት ውስጥ ተጥሎ ጌታ አድኖታል። በመጨረሻም በፍጥሞ ደሴት ደቀ መዛሙርቱን አቅርቦ እና እርሱም ቆርቦ በዋሻ በተቆፈረ ጉድጓድ አጠገብ በዘጠና ዘጠኝ ወይም በአንድ መቶ ዓመቱ ከ98/98/ ዓ.ም እስከ 102 /102/ ዓ.ም ባለው ጊዜ ተሰውሮአል።

### ምን ተማርን ?

www.zeorthodox.org

1. ከዮሐንስ ፍቅር ፣ በእውነት እና በጽናት መንዝን እንማራለን።

2. የቅዱሳን ታሪክ በሃይማኖት እንድንጸና ያግዘናል።

## ተግባር፡-

የዮሐንስን ወንጌል አንብቡ

እግዚአብሔር በልባችሁ የጌታችንን ፍቅር እና የሃይማኖት ጽናትን እንዲሰጣችሁ ለምኑ።

# ሁለተኛዪቱ የዮሐንስ መልእክት

## ሃያ ሁለተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** በፍቅር እና በእውነት በመኖር ከአሳቾች መጠበቅን ማሳወቅ

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"እንደ ትእዛዛቱም እንሄድ ዘንድ ይህ ፍቅር ነው፤"*** 2ኛ ዮሐ ቁ. 6

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** 2ኛ ዮሐንስ ከቁጥር 1-13፡፡

**መግቢያ፡-** ሁለተኛይቱ የዮሐንስ መልእክት 03 ቍጥር ያላት መጽሐፍ ናት ፣ ጸሐፊው በመጽሐፍ ቅዱስ ካሉት መጻሕፍት አምስቱን የጻፈልን ቅዱስ ዮሐንስ ነው፡፡ በዚህች መልእክቱም ራሱን ***"ቀሲስ"*** ብሎ በመጥራት በእውነት ስለመሄድ፣በፍቅር ስለመኖር እና ከአሳቾች ትምህርትም ተጠንቀቁ ሲል ይመክራል ፡፡

በዛሬው ትምህርታችንም መልእክቲቱን በዳሰሳ ጥናት እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

### ምክንያተ ጽሒፍ

ዮሐንስ አስተምሮ ከሄደ በኂላ በእውነት የሚሄዱ፣ የነበሩትን ያህል በመካከል የገቡ የክርስቶስን በሥጋ መምጣት የማያምኑ ነበሩ፡፡ በእነዚህ አሳቾች ምክንያት በቤተ ክርስቲያኒቱ አለመስማማት ነበር፤ ዮሐንስም፡-

በእውነት የሚሄዱትን ሊያበረታ፣

ከጌታችን የተቀበልናት የኖረችን ትእዛዝ እርስ በእርስ መዋደድን ለማስተማር፣

ስለ አሳቾች በመግለጥ ፣ ምእመናን እንዲጠነቀቁ ለመምከር፣ የተጻፈች መልእክት ናት ፡፡

### የት እና ለማን ተጻፈ?፡-

ወንጌላዊ ዮሐንስ ሮምና ለተባለች እመቤት በኦፌሶን የጻፈው መልእክት ነው፡፡ ሮምና የመኳንንትን ልጆች የምታሳድግ የተከበረች እመቤት ናት፡፡ ዮሐንስ አስተምሮ ካሳመናት በቤት ውስጥም የተጀመረው አገልግሎት ሰፋ፡፡ በዚህም ብዙ ክርስቲያኖች በቤተ ክርስቲያን እንዲሰባሰቡ

www.zeorthodox.org

ምክንያት የሆነች ሴት ናት ። ዮሐንስም በመልእክቱ ***"እመቤቴ ሆይ"*** እያለ በአክብሮት ይጠራታል።

**አከፋፈሉ**

*መግቢያ*፤ ከቍጥር 1-3፣

ስለ እውነት እና ፍቅር፤ ከቍጥር 4-6፣

ከአሳቾች ተጠንቀቁ ፤ ከቍጥር 7-11፣

*ማጠቃለያ*፤ ከቍጥር 8-13፣

## ዋና መልእክት፡-

በዚህ መልእክት የጌታ ወዳጅ የዮሐንስ ሕይወት ተልእኮ የሆነውን ***"እውነት"*** ን በ***"ፍቅር"*** መግለጥ እንማራለን። ከፍቅር የተለየ እውነት የለም፣እውነት ከሆነ ከኢየሱስ ክርስቶስ የተለየ ፍቅርም የለም፤ ከቍጥር 2-5። አሳቾቹ የተባሉት ይህን እውነት ስተዋል።

**የመጽሐፉ ይዘት።**

## 5.1 መግቢያ

በክርስቲያኖች ያለው እውነት ዘላለማዊ ነው።(ቍ. 1 -2)

እመቤት ሮምና እና በቤተ ክርስቲያን የተሰባሰቡት ልጆችዋ እውነት እና ፍቅርን ስለያዙ እና ከእግዚአብሔር የሆኑት ጸጋ ፣ ምሕረትና ሰላም ስለሆነላቸው ፤ በሐዋርያው እና ዘላለማዊ ***"እውነትን"*** በሚያውቁ ሁሉ የተወደዱ ናቸው ።

ቅዱስ ዮሐንስ ሮምና እመቤት ሲላት የሚገባትን ክብር ከመሰጠት የዘለለ እውነት የለውም። ይሄም ቅዱስ ጳውሎስ ***"ክብር ለሚገባው ሁሉ ክብርን ስጡ "*** ሮሜ 13፡ 7 ያለውን ያስታውሰናል።

እውነተኛ ክርስቲያኖች በምድርና በሰማይ የመላ ፍቅር እና እውነት ስላላቸው እውነትን በሚያውቁት በቤተ ክርስቲያን አካላት ሁሉ ዘንድ የተወደዱ ናቸው ። እኛም በቤተ ክርስቲያን በእውነት ከኖርን እና በፍቅር ከተመላለስን በቅዱሳን የተወደድን እንሆናለን።

www.zeorthodox.org

እነ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፣ ቅዱስ ዮሐንስ፣ ቅዱስ ጳውሎስ ፣ ቅዱስ ጊዮርጊስ ፣ ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሌሎቹም ቅዱሳን ከእኛ ቀድመው በእኛ ዘንድ ያለውን እውነት ስለሚያውቁ ይወዱናል።

እግዚአብሔር ጸጋ ሰላም እና ምሕረት እንዲያበዛልን በእውነተኛ ፍቅር እንመላለስ።

**እውነት እና ፍቅር** (ከቍ. 4-6)

***"ጌታ ፤ ይወደው የነበረ"*** (ዮሐ 13፡23) ሐዋርያው ዮሐንስ በዚህ ክፍል እውነትን ፣ ፍቅርን እና አንድነታቸውን ያስተምራል ።

**እውነት**፡- በእውነት የሚሄዱ የቤተክርስቲያን ልጆችን ስላየ እጅግ ተደስቶአል። ቍ . 4

**ፍቅር**፡- በእውነት የሚኀዙ ሁሉ እርስ በእርስ በመዋደድ ፍቅርን እንዲይዙ ይመክራል። ይህችም ከመጀመሪያ የነበረች ትእዛዝ ናት። ወንጌላዊው ዮሐንስ ይህን ያስታውሳል ***"በፍቅር እንሄድ ዘንድ ትእዛዚቱ ይህች ናት"*** ቁ.5 ብሎ ይመክራል ።

**ከአሳቾች ተጠንቀቁ።** (ከቍ. 7-11)

የእውነት ጠላት ፣ እግዚብሔር የሰጠንን ፍቅር ሊያበላሽ የሐሰት ዘር ዘርቶአል። ጌታችን በማቴ 13፡24-30 " እንክርዳድ ያላቸውን እነዚህ የክፉው ዘሮችን ፣ በዮሐንስ ***"አሳቾች"*** ተብለዋል ፤ ደግሞም "ብዙ" ናቸው።

ስሕተታቸውም እግዚአብሔር ወልድ በ*ሥጋ መምጣቱን መካዳቸው ነው* ፤ (ቁጥር. 7 ) አብ እና ወልድን እንደተለያዩ አማልክት ይቆጥራሉ። (ቁ.9) ዮሐንስም ምእመናን በጥርጥር ከእግዚአብሔር *የሚያገኙትን ሙሉ ዋጋ* እንዳያጡ ያስጠነቅቃል።(ቁ.8) ቃል *ሥጋ* መሆኑን ***"እኔ እና አብ አንድ ነን"*** (ዮሐ. 1፡1 እና 14፣ ዮሐ. 10፡ 30) ባለው በክርስቶስ ትምህርት የማያምን እና ከዚህ ትምህርት የሚወጣ አምናለሁ ቢልም አምላክ የለውም። ይህን ትምህርት ሳይዝ የተሳሳተ ትምህርት የሚያመጡትን መቀበል የለብንም።(ቁ. 10-11)

## 5.4 ማጠቃለያ (ከቍ. 12 እና 13)

ቅዱስ ዮሐንስ በመልእክቱ ለማስተላለፍ የፈለገው ብዙ ትምህርቶች ነበሩት፤ነገር ግን በቀለም እና በወረቀት እንዲሆን አልፈለገም ። ቁ 12 ***" አፍ ለአፍም እንነጋገራለን"*** ቁ.13 ይላል። ቤተ ክርስቲያን ከጌታችን እና ከሐዋርያት በቃል የተላለፈላትን ትምህርት ጠብቃ አቆይታለች። ይህም ትውፊት ይባላል ። ከተጻፈው በቃልና በተግባር የተላለፈው ይበዛል። የመልእክቱ መጨረሻም ለሌሎች ሰላምታ አቅርቦ ይፈጸማል።

www.zeorthodox.org

***ምን ተማርን*** ?

1ኛ. መንፈሳዊ ሕይወት በእውነትና በፍቅር የምንኖርበት ሕይወት ነው።

2ኛ. በማንኛውም ደረጃ ብንገኝ ለሁሉም የሚገባ ፍቅር መስጠት ይገባናል፡፡

3ኛ. ከሐሰተኛ ትምህርት ተጠንቀቁ ተብለናልና፤ ከተለያዩ ክህደቶች ለመጠበቅ መንፈሳዊ እውቀት ያስፈልጋል፡፡

## ተግባር፡-

1ኛ. ከአንደበታችን የሐሰት ቃል ሊወጣ አይገባም፡፡ ቤተሰብ ለሚጠይቃችሁ እውነት መመለስ አሁኑኑ ተለማመዱ፡፡

2ኛ. በቤተ ክርስቲያን ላሉት እና በውጪ ላሉት ወገኖቻችን እውነተኛ አመለካከት በመያዝ በፍቅር እንግለጸው፡፡

***መዝሙር***

*ቃልህን ሰምቼ ሕይወትን እንዳገኝ*

*ማስተዋልና ጥበብን ስጠኝ፡፡*

www.zeorthodox.org

# ሰሙነ ሕማማት

## ሃያ ሦስተኛ ሣምንት

**የትምህርቱ ዓላማ:-** በሰሙነ ሕማማት እና በዓርብ ቀን ያሉትን ዋና መታሰቢያዎች፣ የትንሣኤውን ዝግጅትና በዓል አከባበር ምን እንደሚመስል መግለጥ፣ በሕማማት መስቀሉ የተቀበልነውን ጸጋ ማሳወቅ።

**የሚጠና ጥቅስ:-** ***"አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው።"*** ሉቃ 24፣34

**መግቢያ:-** ከፋሲካ በፊት ከሆሳዕና በኋላ ያሉት ቀናት በቤተ ክርስቲያናችን አጠራር ***"ሰሙነ ሕማማት"*** ተብለው ይጠራሉ። በእነዚህ ቀናትም የክርስቶስን መከራ፣ በዘመነ ብሉይ የነቢያትን ትንቢት እና ተስፋ እየታሰበ ይቆያል። ሰሙነ ሕማማት ታላቁ እና የመጨረሻው መንፈሳዊ አገልግሎት በቤተ ክርስቲያናችን የሚሰጥበት ሳምንት ነው። በዚህ ሳምንት ጌታችን ከትንሣኤው በፊት ባለው ሳምንት የፈጸመውን ሁሉ ዕለት በዕለት በቤተ ክርስቲያን ይታሰባል።

የሳምንቱ ቀናት እግዚአብሔርን በፍጹም ልብ ለማምለክ እና ለማሰብ ይውላሉ። ምእመናንም ያላቸውን ጊዜ ተጠቅመው በሐዘን እና በተመስጦ ያሳልፉታል። በቤተ ክርስቲያን የሐዘን ምልክቶች እና ድባብ ይታይባታል። ቤተ መቅደሱ በጥቁር ጨርቅ ይሸፈናል፣ ንዋያተ ቅድሳት ይሰቀላሉ፤ መጻሕፍት በጥቁር ሉቲዎች ይጠቀለላሉ። ካህናት ጠቆር ያለ ልብሰ ተክህኖ ይለብሳሉ። ዜማዎች በአራራይ ዜማ በሚያሳዝን ቅላጼ ይዜማሉ። ምንባባቱ ሁሉ ጌታችን ስለ እኛ የተቀበለውን መከራ እና የዘመነ ብሉይን ፍዳ የነቢያቱንም ጩኸት ያመለክታሉ ። የተቀረው የቤተ ክርስቲያን መንጋ ሁሉ /ምእምናን/ በቤተ ክርስቲያን መገኘት ያልቻለውም ከተድላ ከደስታ ተጠብቆ ይሰነብታል። ቤተ ክርስቲያን መከራውን በማሰብ ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ትሳተፋለች።

www.zoorthodox.org

የላመ፣ የጣመ፣ ሳይበላ የተዋርዶ ልብስ በመልበስ ይታሰባል፣ የጾም ሰዓት ይራዘማል።

ቅዳሴ አይኖርም፤ በእርሱ ፈንታ ስግደት እና የሕማማት መታሰቢያዎች ይነበባሉ።

ይህ ሳምንት በሆሣዕና ***"ቅዳሜ"*** ሠርክ ጸሎት ይጀመራል። በዚህ ጊዜም መዝሙራት/እምርት ዕለት በዓልነ ምልጣን / እስመ ይቤ ዛቲ ዕለት በዓለ እግዚአብሔር ሆሣዕና በአርያም / ወዘተ … በግብረ ሕማማት ከተሠሩት ምንባባት እና ጸሎታት ጋር ይደረሳል። ወንጌልና መልእክታት

ይነበባል። በዚህ ሁኔታ ይጀመራል።

ሆሣዕና ጌታችን ድል የነሳ የሰላም ንጉሥ ነውና በክብር ታጅቦ ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱ ይታሰብበታል። /ማቴ. 21፣ ማር. 11 ሉቃ 19 ፣ እና ዮሐ. 12/። በዚህ ዕለትም ከቅዳሜ ሌሊት ለእሑድ አጥቢያ ጀምሮ በዓሉን የሚመለከቱ ምንባባት እየተነበቡ መዝሙራት እየተዘመሩ የታደራል።

ሲነጋ ካህናቱ ቅዳሴ ከመግባታቸው በፊት ኅብስት እና ወይኑን የያዙት ካህናት በቤተመቅደሱ በር ቆመው፤ መኳንንት **ደጁን ክፈቱ የክብር ንጉሥ ይግባ** ሲሉ ከውስጥ " **ይህ የክብር ንጉሥ ማነው?**" ሲሉ ይመልሳሉ ። እየተቀባበሉ ይህን ካደረሱ በኋላ ***የክብር ንጉሥ ይግባ*** ይላሉ። ከዚያም መዘምራኑ የክብር ንጉሥ ይግባ - ይባዕ ንጉሠ ስብሐት ይባዕ አምላክ ምሕረት፤ ብለው እያሸበሸቡ ያስገቡታል።

አበምኔቱ ወይም በዕድሜ እና በማዓርገ ክህነት የሚበልጠው በቤተ መቅደስ የተዘጋጀውን ዘንባባ ባርኮ ለካህናት ይሰጣል፣ ካህናቱም ለምእመናን ይሰጣሉ። ሁሉም በመስቀል ቅርፅ እየሠሩ በራሳቸው እና በጣታቸው ያደርጋሉ። ጸሎተ ቅዳሴው ተጠናቆ በአራቱም መዓዘን የዕለቱ ወንጌል ተነቦ ይዘመራል።

**ጸሎተ ፍትሐት፡-** ይህ ጸሎት የሆሣዕና በዓል እና ጸሎት ማጠናቀቂያ ነው። የቤተ ክርስቲያን መጋረጃ ተዘግቶ ምእመናን በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ አጎንብሰው በመስገድ የሙታን ጸሎት ይደገምላቸዋል። ምክንያቱም በቀጣዩ ሳምንት መደበኛ የቤተ ክርስቲያን የጸሎት ሥርዓታት ሁሉ በጸሎተ ሕማማት ስለሚተኩ ነው።

**ሰሙነ ሕማማት፡-**

**ጸሎተ ሐሙስ፡-**

www.zoorthodox.org

የዕለቱ ምንባብ እና ስግደት ከተፈጸመ በኋላ ዲያቆኑ በሁለት ጎድጓዳ ሳህኖች ውኃ ያዘጋጃል፤ በውስጡም የወይራ፣የሎሚ ወይም የወይን ቅጠል ይደረጋል። ጸሎተ ቅዳሴው ተደርጎ በወንጌል ጌታ የደቀ መዛሙርቱን እግር ያጠበበት ክፍል /ዮሐ 13÷1-20/ ይነበባል። ውኃውን የባረከው ካህን ወገቡን ታጥቆ ውኃ ውስጥ የነበረውን ቅጠል እና ማበሻ ጨርቅ በመያዝ ካህናትንና ሕዝበ ክርስቲያኑን እግራቸውን ያጥባል። መዘምራኑም በመዝ.150 ጀምረው ***"ሐዋርያቲሁ ከበበ እግረ አርዳኢሁ ሐፀበ ኮኖሙ አበ ወእመ ወመሐሮሙ ጥበበ ሃሌ ሉያ "*** ትርጉም ፡- ***" በሐዋርያት መሐል ሆኖ የአገልጋዮቹን እግር አጠበ፤ አባት እናት ሆኖም ጥበብን አስተማራቸው ሃሌ ሉያ"***

ማለት ነው፡፡

ሥርዓተ ቅዳሴው ተፈጽሞ ምእመናን ቅዱስ ቊርባን ይቀበላሉ፡፡ ካህናት ጥቁር ልብስ ለብሰው ይቀድሳሉ፡፡ በቃጭል ፋንታ ጸናጽል ይሆናል፡፡ መስቀል ማሳለምና ቡራኬ የለም፡፡

**ዓርብ ስቅለት፡-**

ከሌሊት ስምንት ሰዓት ጀምሮ ተሰብስበው በቤተ መቅደስ የሥነ ስቅለት ሥዕል ተሰቅሎ ጽንዓዎችን ሰቅለው ገመድ ያስሩባቸዋል፡፡ ንዋያት እና ሌሎች በቦታቸው ከተቀመጡ በኊላ ጠዋት ጌታችን በካህናት አለቆች ፊት መቆሙን፣ በሦስት ሰዓት በጲላጦስ አደባባይ እንደተፈረደበት፣ በስድስት ሰዓት መሰቀሉን፣ በዘጠኝ ሰዓት ሞቱን፣ በሰርክ መገነዙን የሚያመለክቱ ምንባባት እየተነበቡ እየተዜሙ እና እየተሰገደ ይዋላል፡፡ በመጨረሻም ጥብጣብ ተደርጎ ሕዝቡ በሕማማት ለሠራው ሥራ /ኃጢአት/ ቀኖና ይቀበላል ይሰግዳል፡፡ በዘፀ 15፥1-18 ላይ የተዘመረው ***"እናመስግነው - ንሴብሖ"*** ይዘመራል፡፡ ይሄም ክርስቶስ በሲዖል ለነበሩ ነፍሳት ነጻነትን መስበኩን እና ዲያቢሎስና ጭፍሮቹ በሲዖል መዋጣቸውን ያሳያል ፡፡ በዐሥራ ሁለት ሰዓት እግዚኦታ ተደርሶ ጸሎተ ፍትሐት ይሰጣል፡፡

**ቀዳም ስዑር፡-**

ጌታችን በመቃብር መዋሉ ታስቦ በጾም ትዘከራለች፡፡ ኖኅ የጥፋት ውኃ መቀነሱን ርግብ የወይራ ዝንጣፊ በመያዝዋ እንዳወቀም ካህናት ***"ገብረ ሰላመ" "በምድር እና በሰማይ ሰላምን አደረገ*** " እያሉ በየቤታችን ቅጠል ያመጣሉ፡፡

**ምን ተማረን ?**

ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን ሕማም በማሰብ ውለታውን እንድናውቅ ታደርጋለች፡፡

ሰሙነ ሕማማት ጌታችን በሆሣዕና ወደ ኢየሩሳሌም ከገባበት እስከ መቃብር መውረዱ ይታሰብበታል፡፡

www.zeorthodox.org

## ተግባር

በሕማማት ሳምንት በቤተ ክርስቲያን የሚታሰበው የጌታችን ውለታ ሁሌም በልባችን ሊሳል ይገባል፡፡

የሕማማት ሰሞን መጻሕፍትን አግኝታችሁ ለሕማማት ተጠቀሙ፡፡

# በኩረ ትንሣኤ

## ሃያ አራተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** *የጌታችን ትንሣኤ በቤተ ክርስቲያን እና በእያንዳንዳችን ሕይወት ስለአለው በጎ ተፅዕኖ ማሳወቅ፡፡*

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኵራት ሆኖ ከሙታን ተነሥቶአል ፡፡"*** 1ኛ ቆሮ.15፡20

**መግቢያ፡-** ሰሙነ ትንሣኤ በቤተ ክርስቲያን በድምቀት የሚከበር የደስታ በዓል ነው፡፡ የትንሣኤ መልእክታት በዜማና በንባብ ከቤተ ክርስቲያን ይተላለፋሉ፡፡ ለሃምሳ ቀናት ስግደት እና ጾም አይኖርም፡፡

## የትምህርቱ ዋና ይዘት፡-

በኵረ ትንሣኤ፡-የትንሣኤያችን በኵር (መጀመሪያ) ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ዳዊት በመዝሙሩ ***‹‹ ስለ ድሆች መከራ፣ ስለ ችግረኞች ጩኸት እግዚአብሔር፡- አሁን እነሣለሁ ይላል፡፡ መድኃኒትን አደርጋለሁ በላዩም እገልጣለሁ››*** (መዝ. 11፣5) በማለት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ጽፎአል፡፡ በተጨማሪም ***‹‹ እኔ ተኛሁ አንቀላፋሁም እግዚአብሔርም ደግፎኛልና ነቃሁ››*** (መዝ. 11፣5) በማለት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ጽፎአል፡፡ እንዲሁም ***‹‹እግዚአብሔር ይነሣ ጠላቶቹም ይበተኑ የሚጠሉትም ከፊቱ ይሸሹ››*** (መዝ. 66፣1) በማለት ተናግሮአል፡፡ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሙስና መቃብርን ድል አድርጎ እንደሚነሣ በትምህርት ከገለጸ በኋላ በተግባር አሳይቶናል፡፡

www.zeorthodox.org

በትምህርት፡- ***‹‹ነፍሴን ደግሞ አነሣት ዘንድ እኖራለሁና ስለዚህ አብ ይወደኛል .. እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም፡፡ ላኖራት ሥልጣን አለኝ ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ*** (ዮሐ. 10፣18) ብሎ አስተምሮ ትንሣኤውን ነግሮን ነበር፡፡

በተግባር፡- ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ትንሣኤው በቃል አስተምሮን አልቀረም፡፡ የትንሣኤያችን በኵር ሆኖ በተግባር ገለጠልን እንጂ፤ ***‹‹ መልአኩም መልሶ ሴቶቹን አላቸው፡- እናንተስ አትፍሩ የተሰቀለውን ኢየሱስ እንድትሹ አውቃለሁና እንደተናገረ ተነሥቶአልና በዚህ የለም የተኛበትን***

*ሥፍራ ኑና እዩ›› (ማቴ 28፡5)* ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ ተነሥቶአል፡፡(ማር. 16፡6 ፤ ሉቃ.24፡7)

በዚህም የትንሣኤያችን በኵር ሆነ፤ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ስለክርስቶስ ትንሣኤ ብኵርና ሲያስተምር ***"አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኵራት ሆኖ ከሙታን ተነሥቶአል ፡፡"*** 1ኛ ቆሮ.15፡20 አለ፡፡ በሌላም *ሥፍራ* ***‹‹ ኢየሱስ እንደሞተና እንደተነሣ ካመንን እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉትን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና››*** (1ኛ ተሰ. 4፣14) ተብሎ ተጽፎአል፡፡

## የትንሣኤ ኃይል፡-

ከትንሣኤ በፊት ዲያቢሎስ በዙሪያው ያለውን ሁሉ አሸንፎ የማይነካ የመሰለበት ወቅት ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ኃጢአተኛ እና ክፉ አድራጊ ሞት ሊያስፈርድበትም ችሎ ነበር፡፡ ጌታችንም በክፉ አልመለሰም አልተቃወመምም፡፡ ዲያቢሎስ የቻለውን ጉዳት ሁሉ አድርሷል ፤ አስገረፈው ፤ በጥፊ አስመታው፣ አስቸነከረው፣ በመጨረሻም አሰቅሎታል፡፡ ክርስቶስ እነዚህን ሁሉ መከራዎች በትዕግሥት ሲቀበል ዲያብሎስ ደካማ ነው ብሎ አስቦ ሌሎች ነፍሳትን እንደለመደው ለመግዛት መጣ፡፡

ክርስቶስ በዕለተ ዓርብ ተሰቅሎ ከሞተ በኂላ ዮሴፍ እና ኒቆዲሞስ በአዲስ መቃብር ቀበሩት፡፡ ሐዋርያትም በታላቅ ፍርሐትና ድንጋጤ ተሞልተው ተደበቁ፡፡ የደቀ መዛሙርቱ ልብ በሐዘን እና በቀቢጸ ተስፋ ተሞላ፡፡ ሁለቱ የኤማሁስ መንገደኞች ጌታችን በመካከላቸው ሆኖ አብሯቸው እያወራ እንኳን ተስፋ እንደቆረጡ ነበር፡፡ ***"በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ሁሉ ፊት በሥራና በቃል ብርቱ ነቢይ ስለነበረው ስለ ናዝሬቱ ኢየሱስ እርሱንም የካህናት አለቆችና መኳንንቶች ለሞት ፍርድ እንዴት አሳልፈው እንደሰጡና እንደሰቀሉት፡፡"*** /ሉቃ 24÷19-21/

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እና ሌሎች ሴቶች የጌታችንን ሥጋ ሽቱ ለመቀባት በመቃብሩ ሥፍራ ከመንፈቀ ሌሊት ጀምሮ ነበሩ፡፡ ከሐዋርያትም ጴጥሮስ እና ዮሐንስ ሲነጋ ሄዱ ፡፡

www.zeorthodox.org

የትንሣኤው እውነት ግን ሐዘኑን ወደ ደስታ ፣ ተስፋ መቍረጥን ወደ ብርታት እና ጽናት ፍርሃትን ወደ ስብከት ቀየረው፡፡ ቤተ ክርስቲያናችንን በደስታና በኃይል የሞላት የጌታችን ትንሣኤ ነው ፡፡ ጌታችን በራሱ ኃይል ተነሥቷል፡፡ አዎን ተነሥቷል ፤ ድንጋዩ በመቃብር አፍ አልነበረም፡፡ ተነሥቷል ቁስሎቹ ነበሩ የጎድኑም ክፍተት ነበር፡፡ ግን ተነሥቶል፡፡

በትንሣኤው ***"ሞት ሆይ መውጊያህ የታል ? . . . ሲኦል ሆይ ድል መንሳትህ የታል"***

የተባለለትን አረጋገጠ፡፡ እነሣለሁ እንዳለ ተነሣ፤ መግነዙን እና ማበሻውን በዚያ ትቶ ተነሣ፡፡

## የትንሣኤው ደስታዎች፡-

ቤተ ክርስቲያን የትንሣኤውን ደስታ የሚያውጁ መዝሙራትን ትዘምራለች፡፡ ***"ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን ሞተ ወኬዶ ለሞት ለእለ ውስተ መቃብር ወሀበ ሕይወተ ዘለዓለም ዕረፍተ - ክርስቶስ ሞቶ ሞትን ድል አደረገው ፤ በትንሣኤውም ሕይወትንና የዘለዓለም ዕረፍትን በመቃብር ውስጥ ላሉት ሰጠ"***

## የዚህ ደስታ ምስጢር ምን ነበር?

የእባብን ራስ ቀጠቀጠው የሞትን መውጊያ ሰበረው' የገነትን መንገድ ከፈተልን፡፡ ትንሣኤ በሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ተጽእኖ ነበረው የሐዋርያትን ሥራ የጻፈልን ሉቃስ ***"ሐዋርያትም የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ በታላቅ ኃይል ይመሰክሩ ነበር በሁሉም ላይ ታላቅ ጸጋ ነበረባቸው፡፡"*** (የሐዋ. 4÷33)፤ቅዱስ ጳውሎስም በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ሲጽፍ ትንሣኤ የስብከት መሠረት መሆኑን ገልጦ፤ ትንሣኤ ከሌለ ስብከታችን ከንቱ ነው ይላል፡፡ ( 1ኛ ቆሮ 15÷14-17)

## ትንሣኤ በሕይወታችን ውስጥ፡-

ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ በፍጥሞ ደሴት ጌታችን ተገልጦለት ሲያየው እንደ ሞተ ሰው ሆኖ በፊቱ ተደፍቶ ወደቀ፡፡ ጌታችንም ቀኝ እጁን ጭኖበት፤ ***"አትፍራ ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ ሞቼም ነበርሁ እነሆም ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ የሞትና የሲኦልም መክፈቻ አለኝ፡፡"*** (*ራዕ* 1÷17-18)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰማይ ሕያው ነው፤ በአማንያንም ልብ ሕያው ሆኖ ይኖራል፡፡ በመንፈስ ቅዱስም ልባቸውን በትንሣኤ ኃይል ይሞላዋል፡፡ ለዚህም ቅዱስ ጳውሎስ ፡- ***"እርሱንና የትንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ በመከራውም እንድካፈል ወደ ሙታንም ትንሣኤ ልደርስ ቢሆንልኝ በሞቱ እንድመስለው እመኛለሁ"*** (ፊልጵ. 3÷10-11) ያለው፡፡ ትንሣኤ በክርስቶስ በገሀድ እንደታየ እና እንደተፈጸመ ኃይሉን በታጠቁ ምእመናን ልብ ኃይሉ ክብሩ እና ደስታው ለዘላለም ይኖራል፡፡

www.zeorthodox.org

ልባችን በመለኮታዊው ፍቅር ሲሞላ ትእዛዙን ለመፈጸም ይበረታል፡፡ የትንሣኤው ብርሃን ልባችንን ሞልቶት አስከፊው ኃጢአት ይሸነፋል፡፡ ቁጣችንን፣ ክፉ ምኞታችንን እና መጥፎ ተግባራችንን ትተን በተመለስንበት ጊዜ ክርስቶስን ከሙታን ያስነሣው የእርሱ መንፈስ ከመንፈሳዊው

ሞት ያስነሣል፡፡ ***"ነገር ግን ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው የእርሱ መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር ክርስቶስ ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው እርሱ በእናንተ በሚኖረው በመንፈሱ ለሚሞተው ሰውነታችሁ ደግሞ ሕይወትን ይሰጠዋል፡፡"*** (ሮሜ 8÷11)

## ማጠቃለያ፡-

ከክርስቶስ ጋር ከተነሣ በአብ ቀኝ በዙፋኑ ከተቀመጠው ከክርስቶስ የሚመጣውን እንፈልግ፡፡ በእውነት ከተነሣንም ሞቶ ለተነሣው ቅዱስ ጴጥሮስ፣ ***"ከወደድከኝ በጎቼን ጠብቅ"*** ያለውን እያሰብን የጠፉትን በጎች እንፈልግ፡፡

ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ እንዳለው ዛሬም ***"ከወደድከኝ ግልገሎቼን አሰማራ"***

## ተግባር

ስለትንሣኤ በወንጌል የተጻፉትን ምዕራፎች አንብቧቸው፡፡

"***ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን. ."*** የሚለውን መዝሙር በቃላችሁ ለመያዝ አጥኑ፡፡

በበዓለ ትንሣኤ ወላጅ ለሌላቸው ልጆች ስጦታ ላኩ፡፡

www.zeorthodox.org

# የመጽሐፍ ቅዱስ ዝግጅት

# /መሰባሰብ መዘጋጀት እና አሰያየም/

# ሃያ አምስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** *የመጽሐፍ ቅዱስን መሰባሰብ፣ዝግጅት እና ስያሜ ታሪክ ማሳወቅ፡፡*

**የሚጠና ጥቅስ ፡-** *" እግዚአብሔርንም ለሚፈሩ ስሙንም ለሚያስቡ የመታሰቢያ መጽሐፍ በፊቱ ተጻፈ፡፡"ሚልክ.3፡16*

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ኢሳ.34፡16

## *መግቢያ፡-*

በተለያየ ቦታና ዘመን በቅዱሳን ሰዎች የተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ አሁን በምናገኘው መልኩ ያለቀ ዝግጅት ላይ ለመድረስ የዘመናት ሒደቶችን አሳልፏል፡፡

ከአደጋ ለመከላከል፣ ለትርጉም እና በቀኖና ለመወሰን ሲባል በተነጣጠለ ሁኔታና አቀማመጥ ተለያይተው ይገኙ የነበሩ ቅዱሳት መጻሕፍት በአንድ ላይ በመጽሐፍ ቅዱስ እንዲሰባሰቡ ተደርጓል፡፡ በዛሬው ትምህርታችን መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት እንደተሰባሰበ እና እንደተዘጋጀ ከስያሜው ጋር እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡፡

www.zeorthodox.org

የቅዱሳት መጻሕፍት መሰባሰብ፣ ዝግጅት እና ስያሜን ቀጥለን እናያለን፡-

**መሰባሰብ፡፡**

ቅዱሳት መጻሕፍትን ያሰባሰበው መንፈስ ቅዱስ ነው ፡፡ ***"በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም አሬ አዝዞአልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም "*** (ኢሳ 34፡16) በነቢይ እና ካህኑ ዕዝራ የተጀመረው ቅዱሳት መጻሕፍትን በተለይም የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ማሰባሰብ *ሥራ* የአይሁድ ጸሐፍያን በሆኑት ማሶራውያን እና በተርጓሚዎቹ ሰብአ ሊቃናት ተጠናክሮአል፡፡

የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትም ለቀኖና፣ ከመናፍቃን ለመጠበቅ እና ለትርጉም እንዲያመች ተሰባስበዋል፡፡ ለምሳሌ፡- የእስክንድርያ ኮዴክስ በ822 የብራና ቅጠል ሙሉ ብሉይና ሐዲስ ኪዳንን / የቀሌምንጦስ መጽሐፍን ጨምሮ/ ያሰባሰበ ነው፡፡

**ዝግጅት፡-**

*መጻሕፍተ ብሉያት የተጻፉበትን ዕብራይስጥ ቋንቋ አናባቢ እና የቋንቋ ምልክት በመጨመር ለንባብና ትርጉም ያመቻቹት ማሶራውያን ሲሆኑ አሞንዮስ እና አውሳብዮስ መጽሐፍ ቅዱስን በክፍል አዘጋጅተዋል ፡፡*

በ1228/1228/ *ዓ.ም* ስቴፈን ላንግቶን በምዕራፍ ሲያዘጋጀው በ1551/1551/ *ዓ.ም* በሮበርት እስቲን /ስቲፋነስ/ በቁጥር ተከፋፍሎ ተዘጋጅቷል፡፡ በመጨረሻም በ*ዐሥራ* ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የግርጌ ማጣቀሻ /foot note /ተዘጅቶለታል፡፡

**ስያሜ**

ለቅዱሳት መጻሕፍት ስያሜ የሰጡ ራሳቸው ጸሐፊያኑ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ግን በኋላ በተነሡ አበው አማካኝነት፡- በጸሐፊው፣ በይዘታቸው እና በመግቢያቸው መሠረት ተሰይመዋል ***"...ሠለስቱ ምእት ለመጻሕፍት ስያሜ ሲሰጡ . . . ብለውታል፤"*** ፡፡

***ሀ.*** **በጸሐፊው ስም የሚጠሩ መጻሕፍት፡፡** *መጽሐፈ ኢያሱ፣ መጽሐፈ ሔኖክ፣መጽሐፈ ሳሙኤል፣. . .*

**ለ.በይዞታቸው የተሰየሙ መጻሕፍት፡፡** *ኦሪት ዘፍጥረት፣ዘጸአት፣ ዘኁልቍ፣ ዘሌዋውያን፣ ዘዳግም፣ መጽሐፈ ኩፋሌ ፣ መጽሐፈ ነገሥት .......፣*

**ሐ.በጸሐፊውና በይዞታቸው የሚጠሩ፡፡** *መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን ፣ ትንቢተ ኢሳይያስ ፣*

**መ.በሀገር /በከተማ/ ስም የሚጠሩ፡፡** የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎች፣ወደቆሮንቶስ፣ኤፌሶን. . .

www.zeorthodox.org

**ሠ.በተላከላቸው ሰዎች ስም የሚጠሩ፡፡** 1ኛ እና 2ኛ ጢሞቴዎስ፣ ፊልሞና ፣

**ምን ተማርን ?**

በተለያየ ቦታና ዘመን የተጻፉት ቅዱሳት መጻሕፍት ***" መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም "*** (ኢሳ 34፡16) ባለው *መሠረት* በእግዚአብሔር *ፈቃድና ርዳታ* ተሰባስበው ተዘጋጅተዋል፡፡

ቅዱሳት መጻሕፍት ***"እግዚአብሔርንም ለሚፈሩ ስሙንም ለሚያስቡ የመታሰቢያ መጽሐፍ በፊቱ ተጻፈ።"*** (ሚልክ.3፡16) እንደተባለ በራሳቸው እና በቤተ ክርስቲያን አበው ተሰይመዋል።

## ተግባር፡-

በቤታችሁ ያሉትን ቅዱሳት መጻሕፍት በክብር ሰብስባችሁ በአንድ ቦታ አስቀምጡ። የተሰባሰቡትንም በክብር አንብቡ ተጠቀሙበትም።

www.zeorthodox.org

# መጽሐፈ ምሳሌ

## ሃያ ስድስተኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** የመጽሐፈ ምሳሌን ይዘት እና ዓላማ ማሳወቅ፡፡ ልጆችን በዘመናቸው ሁሉ ወደ የሚያስፈልጋቸው ጥበብ መምራት ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** **"የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው ፤ ሰነፎች ግን ጥበብንና ተግሳጽን ይንቃሉ ፡፡ "** ምሳሌ 1፡ 7

**ምንባብ፡-** መጽሐፈ ምሳሌን በየቀኑ ሁለት ምዕራፎች አንብቡ፡፡

**መግቢያ፡-**የጥበብ መጽሐፍ በተደጋጋሚ ስንፍናን እያወገዘ ታማኝነትን እያሞገሰ የጥበብን ቃል ለሚሹ ሁሉ በጎ ሕይወትን እንደሚመሩና እንደሚወርሱ ቃል በመግባት ትምህርት ይለግሳል፡፡በአንዳንድ የመጽሐፉ ክፍሎች የተጻፉት ትምህርቶች በድራማ መልክ ጭምር የቀረቡ ናቸው ፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ በቀላሉ በቃል ለመያዝ እንዲያመቹ ሆነው የተጻፉ ገላጭ አባባሎች ይገኙበታል፡፡ ለምሳሌ፡- ***"ከጠበኛ ሴት ጋር በአንድ ቤት ከመቀመጥ በሰገነት ማዕዘን መቀመጥ ይሻላል ፡፡ "*** ምሳሌ 25፡24 ፡፡ ***" አንተ ታካች ወደ ገብረ ጉንዳን ሂድ መንገድዋንም ተመልክተህ ጠቢብ ሁን ፡፡ "*** (ምሳሌ 6፡ 6) ይህም በትጋትና በጥንካሬ የመሥራትን ምሳሌ በምድር ከምትገኝ ታናሽ ፍጥረት የምናገኝ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡

ይኸን የመሰሉ ምሳሌዎችና ታሪኮች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተካተው የምሳሌ ወይም የጥበብ መጻሕፍት ተብለው ይታወቃሉ፡፡ ከነዚህም መካከል መጽሐፈ ምሳሌ፤ መጽሐፈ መክብብ ፤ መጽሐፈ ሲራክ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ጠቢቡ ሰሎሞን በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 4፡32 እንደተጻፈው ሦስት ሺሕ ያህል ምሳሌዎችን ጽፏል፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንዶቹ እንደ ምሳሌ 30 እና 31 ደግሞ በአጉር እና ልሙኤል የተጻፉ ናቸው ፡፡

www.zeorthodox.org

## የትምህርቱ ዝርዝር ይዘት፡-

የጥበብ የማዕዘን ድንጋዮች በመጽሐፈ ምሳሌ በዝርዝር ተገልጸው ይገኛሉ ፡፡

ይልቁኑ ማስተዋል የሌላቸው ያልተማሩ ወጣቶች የጥበብን መንገድ በአግባቡ መማር ይገባቸዋል፡፡

አስቀድመው የጥበበን መንገድ የተማሩትም ጥበባቸውን ***" የተሸሸገውን ነገር ለማስተዋል "***

ምሳሌ 1፡6 እንዲሆናቸው የበለጠ መተርጎም ወደ ሚያስችላቸው ደረጃ ጥበባቸውን ያሳድጋሉ፡፡

*"የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው ፤ ሰነፎች ግን ጥበብንና ተግሣጽን ይንቃሉ፡፡"* 1፡7 *"በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን ፡ እግዚአብሔርን ከሀብትህ አክብር ፡፡ የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው ፤ ሰነፎች ግን ጥበብንና ተግሣጽን ይንቃሉ፡፡"* ምሳሌ 3 ፡5 ና 9፡፡

ወላጆችን ወይም ሽማግሌዎችን መስማት፡፡ *"ልጅ ሆይ ሕጌን አትርሳ ልብህም ትእዛዛቴን ይጠብቅ፡፡"* (3፡1)በእነዚህ ምክሮች መደገፍ ዕድሜያችንን በሙሉ ፍሬያማ ሕይወት እንድንመራ የሚያደርገን ሲሆን አንዴ ጥበብን የራሳችን ካደረግን ክፋትንና የኃጢአትን መንገድ ሁሉ የምንቃወምበት መሣሪያችን ይሆናል ፡፡ ራስን መቆጣጠር ከጥበብ ትምህርቶች ትልቁን ሥፍራ የሚይዝ ነው ፡፡ *"ባለ አእምሮ ልጅ የአባቱን ተግሣጽ ይሰማል ፡፡ ፌዘኛ ግን ተግሣጽን አይሰማም "* ምሳሌ 13፡1፡፡ ፌዘኞች ውስጣዊ ቅንዓት እና ትጋት የሌላቸው በማስተዋል የማይመሩ ችኩሎች ሲሆኑ ጥበበኞች ግን ጸጥተኞችና ነገርን ሁሉ በርጋታ የሚመለከቱ ናቸው ፡፡ ፈጥኖ የሚናደድ ነገሮችን ሁሉ ያለማስተዋል በሞኝነት በመመልከት የሞኝነትን መልስ ይሰጣል፡፡ ይኸም በሰው ሁሉ ዘንድ የተጠላ ይሆናል ፡፡

*ጻድቅ መሆንንም ያስተምራል፡፡"የሰው መንፈስ የእግዚአብሔር መብራት ነው"* ምሳሌ 20፡27፡፡ እንዳለ ጥበብ አእምሮን ሁሉ በመፈተሽ የበጎ ምግባር መንገዶችን ሁሉ ብሩህ ያደርጋል ፡፡ " የጻድቃን መንገድ እንደ ንጋት ብርሃን ነው ፡፡ የኃጥአን መንገድ ግን እንደ ጨለማ ነው ፡፡ " (ምሳሌ. 4፡18-19) ጻድቅ ከመከራ በሥራው የተጠበቀ ይሆናል ፡፡ *"የኀጥእ ሰው ሞያ ሐሰተኛ ነው ፡፡ ጽድቅን የሚዘራ ግን የታመነ ዋጋ አለው ፡፡ "* (ምሳሌ 11፡18 )

የጋብቻ ጤናማ ገጽታና በሥጋ የመተዋወቅ መልክና መጠን የጥበብ ትምህርት አንዱ አካል ነው ፡፡ *"ከጋለሞታ ሴት ከንፈር ማር ይንጠባጠባል ... ፍጻሜዋ ግን እንደ ሬት የመረረ ነው ፡፡ "* (5፡3- 4) መልካም ሚስት ግን *"እንደ ተወደደች ዋላ እንደ ተዋበችም ሚዳቋ ናት ፡፡ "* (5፡19) ሰነፍ ልክ *" በሬ ለመታረድ እንደሚነዳ ... ወፍ ወደ ወጥመድ እንደሚቸኩል"* ነው፡፡ (7፡22-23) አመንዝሮችን ይከተላል ፡፡ ሰነፎች በወጣቶች የዋህ አኗኗር እንደሚጫወቱ አካላቸውን ሸጠው እንደሚያድሩ ሴቶች ዓይነት አለባበስ ይለብሳሉ ፡፡ እርስዋ በከንፈርዋ በመሳም በመኝታዋ ሽቶውን በማርከፍከፍ ፤ ባለቤቴ ወደ ሩቅ መንገድ ሄዷል በቤቱም የለም በማለት ወደ ቤቷ ትጋብዛለች ፡፡ ምሳሌ 7

www.zeorthodox.org

ምዕራፍ ስድስት እግዚአብሔር የሚጠላቸውን ስድስት ነገሮች ይዘረዝርና ሰባተኛውንም ነፍሱ

እንደምትጸየፈው ይገልጻል ፡፡እነርሱም ፡-*"ትዕቢተኛ ዓይን ፤ ሐሰተኛ ምላስ ፤ ንጹሕ ደም የምታፈስ እጅ ፤ ክፉ ሐሳብን የሚያበቅል ልብ ፤ ወደ ክፉ የምትሮጥ እግር ፤ በሐሰት የሚናገር ሐሰተኛ ምስክር ፤እና በወንድማማች መካከል ጠብን የሚዘራ ናቸው ፡፡ "* ምሳሌ 6፡16-19

ጥበበኛ ዙሪያውን አካባቢውን አስተውሎ እንዲመለከትና ከጥቃቅን ፍጥረታት ትምህርት እንዲወስድ ይመከራል፡፡ *"በምድር ላይ አራት ጥቃቅን ፍጥረቶች አሉ፡፡ እነርሱ ግን እጅግ ጠቢባን ናቸው ፤ ገብረ ጉንዳን ኃይል የሌላቸው ሕዝቦች ናቸው ፤ ነገር ግን በበጋ መኖዎቻቸውን ይሰበስባሉ ፡፡ ሽኮኮዎች ያልበረቱ ሕዝቦች ናቸው ፤ ቤታቸውን ግን በቋጥኝ ድንጋይ ውስጥ ያደርጋሉ ፡፡ አንበጣዎች ንጉሥ የላቸውም ፤ ሁላቸው ግን በመልካም ሥርዓት ይሄዳሉ ፡፡ እንሽላሊት በእጅ ይያዛል፤ በነገሥታት ግቢ ግን ይኖራል ፡፡ "* (ምሳሌ 30፡24-28)

ለሌሎች የምናደርጋቸው ነገሮችም በምዕራፍ 31 ተዘርዝረዋል፡፡*"አፍህን ስለ ዲዳው ክፈት * ተስፋ ስለ ሌላቸውም ሁሉ ተፋረድ ፡፡ አፍህን ክፈት በእውነትም ፍረድ ለድሃና ለምስኪን ፍረድ ፡፡ "* (ምሳሌ 31፡8-9)

## ማጠቃለያ፡-

መጽሐፈ ምሳሌ ወጣቶችን በትክክለኛው የሕይወት መንገዳቸው ለመምራት የሚችል ታላቅ መጽሐፍ ነው ፡፡ መጽሓፉ ፈጣን ምክር ሲያስፈልገን የምንጠቀምበት በማንኛውም ጊዜ ሁሉ ማስተዋልን የሚሰጠን በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ የምናገኘው ታላቅ ቋሚ ሀብትም ጭምር ነው ፡፡

## ተግባር፡-

በየቀኑ ከመጽሐፈ ምሳሌ ሁለት ምዕራፎችን በማንበብ የወደዳችሁትን በደብተራችሁ ጻፉ፡፡

*መዝሙር ፡-*

ቃልህን ሰምቼ ሕይወትን እንዳገኝ፤

www.zeorthodox.org

ማስተዋል እና ጥበብን ስጠኝ፡፡

# የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ፍሬ በዘመነ ሐዋርያት

## ሃያሰባተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች በቤተ ክርስቲያን ስለሚኖራቸው አገልግሎት ከአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ትምህርት እንዲቀስሙ ማድረግ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *"ደቀ መዛሙርት መጀመሪያ በአንጾኪያ ክርስቲያን ተባሉ፡፡"* የሐዋ.ሥ 11÷26

**ተጨማሪ ምንባባት፡-**የሐዋ.ሥ 11÷19-26 ፣ 13፡1-3 ፣ 14፡26 ፣ 15፡35-41 ፣ 18÷23

**መግቢያ፡-** በአባቶቻችን በሐዋርያት የአገልግሎት ዘመን ከነበሩት አብያተ ክርስቲያናት አንድዋ እና አይሁድ እና የአሕዛብ ክርስቲያኖች ማዕከል የነበረችው አንጾኪያ ናት፡፡ በአንጾኪያ ባለችው ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያት አስተምረዋል፡፡

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች የሆኑ የተለያዩ ጸጋዎች ያሉዋቸዉ አባቶችና ምእመናንም ነበሩባት፡፡ ሁሉም በተሰጠው መሰማራቱ እና ማገልገሉም የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ፍሬ ነበር፡፡

በዛሬው ትምህርታችን ስለ የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ስናጠና÷ በዘመነ ሐዋርያት ምን እንደምትመስል እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

**አንጾኪያ፡-**

በመጽሐፍ ቅዱስ ዐሥራ አምስት ጊዜ የተጠቀሰች ከተማ ናት፡፡ ታላቁ ባሕር ብሎ ከሚጠራው ከሜዲትራንያን ባሕር በስተ ምሥራቅ ሃያ አራት ኪሎ ሜትር ገባ ብላ የምትገኝ ከተማ ናት፡፡

www.zeorthodox.org

በ301/301/ ዓ.ዓ (ከክርስቶስ ልደት በፊት) ኦሬንቴስ በተባለ የሜዲትራንያን ባሕር ገባር ወንዝ አጠገብ ተቋቋመች፡፡ ከታላቁ እስክንድር በኋላ የግሪክን ግዛት ተካፍለው ከመሩት የጦር መሪዎች አንዱ ሴሉከስ በአባቱ በአንጥያኮስ ስም አንጾኪያ ብሎ ሰየማት፡፡

በ65/65/ ዓ.ም በሮም መንግሥት ሥር ስትሆን፤ ከሮማ እና እስክንድርያ ቀጥሎ ሦስተኛዋ

ዋና ከተማ አደረጓት፤ በሶሪያ የነበረው የሮም ጦር ማዘዣም ሆነች፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮም የሶሪያ ዋና ማዕከል ሆነች።

## የደቀ መዛሙርት ስደት፡-

ቅዱስ እስጢፋኖስ በድንጋይ ተወግሮ በሰማዕትነት ካረፈ በኋላ ወደ ተለያየ የዓለም ክፍሎች የተበተኑት ክርስቲያኖች በፊንቄ(የዛሬዋ ሊባኖስ) እና ቆጵሮስ አድርገው አንጾኪያ ደረሱ።

በሄዱበት ሁሉ ቃሉን ይሰብኩ ነበር። በትውልድ አይሁዳዊ ስለሆኑና ከአሕዛብ ጋር ስለማይቀላቀሉም መጀመሪያ ያስተምሩ የነበሩት ለአይሁድ ብቻ ነበር። (የሐዋ.ሥ 11÷19)

ከተሰደዱት ክርስቲያኖች መካከል የቆጵሮስና የቀሬና ሰዎች ነበሩ። እነርሱም ለግሪክ ሰዎች ወንጌልን ተናገሩ። የእግዚአብሔር ኃይል ከእነዚህ ሰዎች ጋር ሆኖ ብዙ አሕዛብ አመኑ። ካመኑት ሰዎች ብዛትና ከተገለጠው የእግዚአብሔር ኃይል የተነሣ ዝናው እስከ ኢየሩሳሌም ተሰማ። አባቶች ሐዋርያትም ይሄን ሰምተው በርናባስን ላኩት።(የሐዋ.ሥ 11፡21-23)

## የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን መመሥረት

በርናባስ የኦሪት መጻሕፍት ሊቅ ነበር። የቀድሞ ስሙ ዮሴፍ ሲሆን ሐዋርያት በርናባስ አሉት፤ ***"የመጽናናት ልጅ"*** ማለት ነው። ወደ ክርስትና የተመለሰ ሌዋዊ ሲሆን ፡- እምነት ፣ ዕውቀት እና ጸጋ የነበረው ደግ ሰው ነበር። መሬቱን ሸጦ ለቤተ ክርስቲያን ሰጥቶአል። የሐ.ሥ4፡36 -37 መንፈስ ቅዱስ የወረደበት የማርቆስ እናት የማርያም ቤት ነበር። ይህች ማርያም እኅቱ ናት። ለማርቆስም አጎቱ ነበር። እንግዲህ ይህ በርናባስ ነው ፣ ወደ አንጾኪያ የተላከው።

***ሀ. በርናባስ እና ሳውል*** በርናባስ ወደ አንጾኪያ ወረደ እርሱም መጥቶ የእግዚአብሔርን ጸጋ ባየ ጊዜ ደስ አለው። ***"ሁሉንም በልባቸው ፈቃድ በጌታ ጸንተው ይኖሩ ዘንድ መከራቸው"*** የሐ.ሥ. 11፡23 ዕለት ዕለት ማስተማሩን አጽንቶ በመቀጠሉም።"***ብዙ ሕዝብ ወደ ጌታ ተጨመሩ*** " ይህ የአማንያን መብዛት እና የአገልግሎቱን መስፋት ያስተዋለው በርናባስ ሳውልን ከጠርሴስ አመጣው። ሳውል እና በርናባስ አንድ ዓመት አስተማሩ፤ ጉባኤውም ለአንድ ዓመት ቀጠለ፤ ክርስቲያኖችም በዙ።

www.zeorthodox.org

እነዚህም ከአይሁድ እና ከአሕዛብ ሆነው በእውነት እግዚአብሔርን የሚያመልኩ የክርስቶስ ተከታዮች ***ደቀመዛሙርት*** ሲባሉ ኖረው በአንጾኪያ ክርስቲያኖች ተባሉ። ይህ ስያሜም በዓለም ያሉ ክርስቲያኖች ሁሉ መጠሪያ ሆነ።

ለ.ነቢያት ወደ አንጾኪያ ወረዱ *"በዚያም ወራት ነቢያት ከኢየሩሳሌም ወደ አንጾኪያ ወረዱ"* (የሐዋ.ሥ.11፡27) ሲል ቅዱስ ሉቃስ ይተርክልናል፡፡ ከእነዚህ አንዱም አጋቦስ ነበር፡፡ እርሱም በምድር ራብ እንዲሆን ተንብዮ ተፈጽሞለታል፡፡

**ጸጋ፤ ጾም እና ጸሎት የነበሩባት ቤተ ክርስቲያን፡-**

የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ከላይ ያየናቸው የማስተማር እና ትንቢት የመናገር ጸጋ የተሰጣቸው አበው ነበሩባት፡፡ በጾም እና በጸሎት የተጉም ነበሩ፡፡ የሐዋ.ሥ 13፡1-3

በእግዚአብሔር ፈቃድ የሚመሩ ክርስቲያኖች ስብስብ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር የሆነ ጸጋ የሚሰጣት ምእመናንን ለማነጽ ጥቅም ነው፡፡ ጸጋ በዛልን ማለትም ጾም ጸሎት አያስፈልግም ማለት አይደለም፡፡ ለዚህም ነው፤ የአንጾኪያ መምህራን እና ነቢያት ከተሰጣቸው ጸጋ ጋር ***እግዚአብሔርን በማምለክ በጾም በጸሎት ይተጉ የነበረው፡፡***

## የአገልግሎት ጥሪ በቤተ ክርስቲያን፡-

ከላይ እንዳየነው የአንጾኪያ ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ጸጋ እና በጾም በጸሎትም ሲበረቱ፤ "***መንፈስ ቅዱስ በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ አለ፡፡"*** (የሐዋ.ሥ.13፡3) እነርሱም ጾመው ጸልየው ላኩዋቸው፡፡ ከዚህ በኋላ የቅዱስ ጳውሎስ አስገራሚዎቹ እና ለብዙ አብያተ ክርስቲያናት መመሥረት ምክንያት የሆኑት ጉዞዎች መነሻ አንጾኪያ ሆነች፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ አንጾኪያን መነሻና መድረሻ በማድረግ ሦስት ሐዋርያዊ ጉዞ አድርጎአል፡፡ (የሐዋ. 13፡4 14፡26 ፤ 15፡35-41 ፤ 18፡22-23)

## ልግስና ያለባት የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን፡-

ሌላው በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን የምናየው መንፈሳዊ ፍሬ ልግስና ነው፡፡ በኢየሩሳሌም የነበሩት ክርስቲያኖች በአይሁድ ግፍ እና በአካባቢው በነበረው ድህነት ተጠቂዎች ነበሩ፡፡ በምድር የሆነው ራብም ኢየሩሳሌምን ጎድቷታል፡፡ በዚህ መሠረትም በአንጾኪያ ያሉት ክርስቲያኖች ሁሉም እንደ አቅማቸው ገንዘብ አዋጥተው ርዳታን በይሁዳ ለሚኖሩ ክርስቲያኖች ለመላክ ወሰኑ፡፡ ይህንንም ርዳታ በሳውል እና በርናባስ እጅ ሰደዱት፡፡ (የሐዋ. 11፡29-30)

www.zeorthodox.org

## የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ፈተናዎች እና መፍትሔ ፍለጋ ፡-

የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን እና መምህራን አለመግባባቶች ሲፈጠሩ የቤተ

ክርስቲያንን ውሳኔ ይጠብቁ ነበር። ከፈሪሳውያን ወገን የሆኑ አንዳንዶች ከይሁዳ ወደ አንጾኪያ ወርደው የሙሴን ሕግ የረበናተ አይሁድን ወግ ካልጠበቃችሁ አትድኑም እናም ተገረዙ ብለው አስተምረው። ጳውሎስ እና በርናባስ ይህ ትክክል እንዳልሆነና መሥዋዕተ ኦሪት በጌታችን ሥጋና ደም ግርዛት በጥምቀት መተካቱን አስተማሩ። ነገር ግን ፈሪሳውያኑ ክርክር ስላበዙ ከአሕዛብ ወገን ካመኑት ጋር ተጣሉ። በዚህም ምክንያት ጳውሎስ በርናባስ እና ተከራካሪዎቹም ወደ ኢየሩሳሌም ሄደው በቅዱስ ሲኖዶስ እንዲያስወስኑ ወደ ሐዋርያት ተላኩ። ሐዋርያትም የቤተ ክርቲያንን ውሳኔ አሳወቁ። የዚህን ክፍል ዝርዝር በሚቀጥለው ሳምንት ትምህርታችን እናየዋለን።

## ማጠቃለያ ፡-

የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን በዕውቀት በትምህርት እና በጸጋ የበረቱ ምእመናን ነበሩባት።

**ተግባር፡-** በተሰጠን ጸጋ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንስማራ።

www.zeorthodox.org

# የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ

## ሃያ ስምንተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ስለ መጀመሪያው የሐዋርያት ጉባኤ እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *"ከሚያስፈልገው በቀር ሌላ ሸክም እንዳንጭንባችሁ እኛና መንፈስ ቅዱስ ፈቅደናል "* የሐዋ. 15፡29

**ተጨማሪ ምንባብ፡-**የሐዋ. 15፡1-35

### መግቢያ፡-

ቤተ ክርስቲያን የምትመራው በመንፈስ ቅዱስ በሚመራው ጉባኤ ነው፡፡ ይህም ጉባኤ ቅዱስ ሲኖዶስ ይባላል፡፡ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ሐዋርያት እና ተከታዮቻቸው ጳጳሳት ተሰብስበው በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ስለ ቤተ ክርስቲያን የሚነጋገሩበት እና የሚወስኑበት ጉባኤ ነው፡፡ በዛሬው ትምህርታችን ከእነዚህ ጉባኤያት የመጀመሪያውን እንማራለን፡፡

### የሳምንቱ ትምህርት፡-

1.የጉባኤው ስያሜ

የመጀመሪያው ጉባኤ፣ ጉባኤ ሐዋርያት (በአንዳንድ የአገራችን ቦታዎች ይህን መጠሪያ አሳጥረው ጉሓርያ ይሉታል፡፡) እነዚህ ስያሜዎች የጉባኤውን ዘመንና አባቶች ያመለክታሉ፡፡ ጉባኤው የተካሄደውም በ50 ዓ.ም ነበር፡፡

2. ጉባኤው የተጠራበት ምክንያት

www.zeorthodox.org

ቅዱስ እስጢፋኖስ በሰማዕትነት ካረፈ በኋላ ፤ ክርስትና ከኢየሩሳሌም ወደ አሕዛብ ከተሞች ተስፋፋ ፤ ከአሕዛብ ወገን ያመኑት እና ከአይሁድ ያመኑት መካከል አለመግባባት ተፈጠረ፡፡ እነ ቅዱስ ጳውሎስ በክርስትና ማመን ማለት የአይሁድን ወግ የመጠበቅ ግዴታ የለበትም ብለው አስተምረው ነበር፡፡ እንደ ግርዛት ያሉት የሙሴ ሕጎችም በጥምቀት መተካታቸውንም አስተማሩ፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስ ከእግዚአብሔር የተማረውም ይሄንኑ ነበር፡፡ (የሐዋ. 10፡9-23)

ከፈሪሳውያን ያመኑት፤ *"አንዳንዶች ከይሁዳ ወረዱና፡-እንደ ሙሴ ሥርዓት ካልተገረዛችሁ*

*ትድኑ ዘንድ አትችሉም ብለው ወንድሞችን አስተማሩ”* የሐዋ.*ሥ* 15፡1፡፡

ከይሁዳ በወረዱት እና በቅዱስ ጳውሎስና በርናባስ መካከል ክርክር ተፈጠረ፡፡ አንዳንዶችም ተጣሉ፡፡ በዚህ ክርክር የተነሣ ሰዎች ተመርጠው ከአንጾኪያ ወደ ኢየሩሳሌም ጥቄያቸውን ይዘው ተላኩ፡፡ ጳውሎስና በርናባስም ወንጌልን እየሰበኩ ኢየሩሳሌም ደረሱ፡፡ ከቤተ ክርስቲያን የተላኩበትንም ጉዳይ አቀረቡ፡፡

3. ጉባኤው ተጠራ

ሐዋርያት እና ሌሎች አባቶች ተሰባሰቡ፡፡ ሁለቱም ወገን ሐሳባቸውን አቅርበው ክርክር ተካሄደ፡፡ ከላይ የተጠቀሰውንም ሓሳብ አቀረቡ፡፡ ከብዙ ክርክር በኋላ፤ ቅዱስ ጴጥሮስ እግዚአብሔር አሕዛብን እንደመረጠ ይህንንም መንፈስ ቅዱስ ለአሕዛብ በመስጠት እንደመሰከረላቸው ተናገረ፡፡ እግዚአብሔር በአይሁድ እና በአሕዛብ መካከልም ልዩነት እንዳላደረገ ገለጠ፡፡ እኛ እና አባቶች ልንሸከመው ያልቻልነውን ቀንበር  ሌሎች ላይ መጫን እግዚአብሔርን መፈታተን ነው፤ በማለት አስተማረ፡፡ በጌታችን ጸጋ እንደምንድን እናምናለን፤ አለ፡፡

ጳውሎስ እና በርናባስም እግዚአብሔር ለአሕዛብ ያደረገውን ምልክት እና ድንቅ መሰከሩ፡፡ በመጨረሻም የዮሐንስ ወንድም ቅዱስ ያዕቆብ፡- የስምዖን ጴጥሮስን ምስክርነት አረጋግጦ፤ ከዚህ ጋር የነቢያት ቃል ይስማማል ብሎ የአሞጽን ትንቢት ጠቅሶ አስተማረ፡፡ (አሞ. 9፡11-12) በመጨረሻም ከመንፈስ ቅዱስ የሆነውን ሐሳብ አቀረበላቸው፡፡ እንዲህም አለ ፡- *“ከአሕዛብ ወደ እግዚአብሔር የዞሩትን እንዳናስቸግራቸው ÷ ነገር ግን ከጣዖት ርኩሰትና ከዝሙት ከታነቀም ከደምም ይርቁ ዘንድ እንድንጽፍላችሁ እቈርጣለሁ”* (የሐዋ.15፡20) ጉባኤውም በዚህ ተስማማ፡፡ በርስያን የተባለው ይሁዳ እና ሲላስ ተመርጠው ከጳውሎስ እና ከበርናባስ ጋር ወደ አንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ከሐዋርያት ጉባኤ የሚከተለውን ደብዳቤ ይዘው ተላኩ፡፡

4. የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ውሳኔ

*ከ፡ሐዋርያትና ሽማግሌዎች ወንድሞችም ፣*

www.zeorthodox.org

*ለ፡በአንጾኪያና በሶሪያ በኪልቅያም ለሚኖሩ ከአሕዛብ ወገን ለሆኑ ፣*

*ወንድሞች ሰላምታ ያቀርባሉ፡፡*

*ያላዘዝናቸው ሰዎች ከእኛ ወጥተው፡- ትገረዙ ዘንድና ሕግን ትጠብቁ ዘንድ ይገባችኋል ብለው ልባችሁን እያወኩ በቃል እናዳናወጡአችሁ ስለ ሰማን ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነፍሳቸውን ከሰጡት ከምንወዳቸው ከበርናባስና ከጳውሎስ ጋር የተመረጡትን ሰዎች ወደ እናንተ*

*እንልክ ዘንድ በአንድ ልብ ሆነን ፈቀድን። ራሳቸውም ደግሞ በቃላቸው ያንኑ ይነግሩአቸው ዘንድ ይሁዳንና ሲላስን ልከናል።*

*ለጣዖት ከተሠዋ*

*ከደምም÷ከታነቀም(በክት)*

*ከዝሙትም ትርቁ ዘንድ*

*ከዚህ ከሚያስፈልገው በቀር ሌላ ሸክም እንዳንጭንባችሁ ÷ እኛና መንፈስ ቅዱስ ፈቅደናልና ከዚህም ሁሉ ራሳችሁን ብትጠብቁ በመልካም ትኖራላችሁ ፣ ጤና ይስጣችሁ።*

የተላኩትም ወደ አንጾኪያ ወረዱ ሕዝቡንም ሰብስበው ደብዳቤውን ሰጡአቸው። ባነበቡትም ጊዜ ከምክሩ የተነሣ ደስ አላቸው።

## ማጠቃለያ፡-

ፈሪሳውያን በቤተ ክርስቲያን ያስተማሩትን የተሳሳተ ትምህርት እነ ቅዱስ ጳውሎስ ተቃውመው ቢያርሙም ክርክር እና ጥል ስለተፈጠረ በሐዋርያት ጉባኤ አስወስነዋል።

ይህ ጉባኤም የመጀመሪያው የሐዋርያት ጉባኤ ይባላል። በውሳኔውም ትክክለኛውን ከሐሰት ትምህርት ለይተውበታል።

**ተግባር፡-** በማንኛውም መንፈሳዊ ጉዳዮች የቤተ ክርስቲያንን ድምፅ ጠብቁ።ሰዎች ሲሳሳቱም በፍቅር እና በእውነት ለማረም ጣሩ።

*መዝሙር፡-*

ቤተ ክርስቲያን ባሕረ ጥበባት፣

አትመረመርም እጅግ ድንቅ ናት።

www.zeorthodox.org

# ቅዱስ አግናጥዮስ (1)

## ሃያ ዘጠነኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ከቅዱስ አግናጥዩስ ሕይወት መማር፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"ዕለት ዕለት የሚከብድብኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አሳብ ነው፡፡"*** 2ኛ ቆሮ.11፡28

**ምንባብ** ፡-ስንክሳር

**መግቢያ ፡-** ቅዱስ አግናጥዮስ በሶሪያ የተወለደ እና በሮም ከ98-117 ዓ.ም በሰማዕትነት ያረፈ አባት ነው፡፡ ብዙ ጥንታውያን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፍያን ቅዱስ አግናጥዮስን፤ ***"ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእጆቹ አቅፎ እንደዚህ ካሉ ሕፃናት . . ."*** ማር 9፡35 ብሎ ትሕትና ያስተማረበት ልጅ እርሱ ነው ይላሉ፡፡ የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ሦስተኛው ሊቀ ጳጳስ ነበር፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ከሐዋርያት ክህነትን የተቀበለ መሆኑን ጽፎዋል፡፡

ቅዱስ አግናጥዮስ በእግዚአብሔር ፍቅር እና በጽኑዕ እምነት ለመንጋው ምሳሌ የሆነ፣ በምእመናንም ዘንድ ተወዳጅ የነበረ ለአርባ ዓመታት ቤተ ክርስቲያንን ያገለገለ አባት ነው፡፡ አግናጥዮስ በቤተ ክርስቲያናችን ለባሴ እግዚአብሔር (The bearer of God) በግሪክ ቴዎፎሮስ (theophoros - እግዚአብሔርን የተሸከመ፤) Christo Phoros (ክርስቶስን የተሸከመ) ተብሎ ይጠራል፡፡

በዛሬው ትምህርታችን የዚህን ቅዱስ ታሪክ እንማራለን፣ በረከቱ ይደርብን፣ ጸሎቱ ይርዳን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

www.zeorthodox.org

አንጾኪያ በሶሪያ የምትገኝ እና የመጀመሪያዋ የአሕዛብ ክርስቲያኖች ከተማና መናኸሪያ ነበረች፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስ እና ቅዱስ ጳውሎስ አገልግለውባታል፡፡ቅዱስ አግናጥዮስም በቅዱስ ጴጥሮስ እጅ ተሹሞባታል፣፡ በአገልግሎቱም ብርሃን ሆኖ አልፏል፡፡

የአንድ ፍጹም አገልጋይ /አባት/ ጠንካራ ጎኖች እና እውነተኛ የክርስቶስ ወታደሮች ሰብእናዎች የተገለጡበት የአንጾኪያው ሊቀጳጳስ አግናጥዮስ ነበር፡፡

በዚህ መሠረት የሮማው ንጉሥ ድምጥያኖስ የቁጣ ማዕበል ተነሥቶ፤ ነበልባሉ የሶሪያ ክርስቲያኖችን ሲያቃጥል፤ ባለምሉዕ እምነቱን የቤተ ክርስቲያን መሪ ተዘጋጅቶ እና በንቃት ቆሞ አገኘው፡፡

በትምህርቱ እያጽናና ከውጭው መከራ በላይ የውስጥ ደስታ እንዲኖራቸው ሲያደርግ፤ በጾም እና በጸሎት ቤተ ክርስቲያንን በመጠበቅ የመንጋው መምህር እና ምሳሌ ሆኖ የመከራውን ዘመን አሻገራቸው፡፡ ድምጥያኖስ በ96/96/ ዓ.ም ሲሞት የተተካው ኔርቫ ለዐሥራ አምስት ወራት ሲገዛ ቤተ ክርስቲያን ከደረሰባት መከራ ለጥቂት ጊዜያት ዐረፈች፡፡

ሁልጊዜም ንቁ የሆነው ቅዱስ አግናጥዮስ ድካም የማያውቀው በመከራ ያዘኑትንና የደከሙትን ምእመናን እያጽናና በተስፋ የሚያነቃቃ እና እንዲጠነክሩ ሳይታክት የሚተጋ አባት ነበር፡፡ ለጥቂት ጊዜ የተገኘውን ሰላም የምቾች ጊዜ አድርጎ ለራሱ ደስታ እና ዕረፍት አላዋለውም፡፡ ይልቁንም የዝግጅት ወቅት አድርጎ ለሰማዕትነት ተዘጋጀበት፡፡

ትራጃን 98-117 (98-117) ሮማን ሲመራ በዘመነ መንግሥቱ በዘጠነኛው ዓመት ስኪቲያን እና ዶቅያን አሸንፎ በድል የዓለም አቀፋዊቱ ሮም ንጉሥ ሆነ፡፡ ግዛቱን ሁሉ በአንድ ሃይማኖት ሥር ማስተዳደር ዋነኛው የሮም መንግሥት መርሕና ዓላማ አድርጎ መተግበር ፈለገ፡፡ ***‹‹ክርስቶያኖች ከአረማውያን ጎረቤቶቻቸው ጋር በአምልኮ አንድ ሆነው እንዲተባበሩ››*** አዘዘ፣ ይህን የማያደርጉት በሞት እንዲቀጡ አዘዘ፡፡

በዚህ ወቅት ነው አግናጥዮስ የንጉሡን ትምህርት የተቃወመው ጣዖታት አማልክት እንዳልሆኑና መሥዋዕት ሊሠዋላቸው እንደማይገባ እንደ ኤልያስ ለእግዚአብሔር ቀንቶ አስተማረ፤ ክርስቲያኖችም በትምህርቱ ጸንተው በክርስቶስ ሃይማኖት ቆሙ፡፡ ይህ መንፈሳዊ ቅንዓት ግን በቤተ ክርስቲያን አሳዳጆች ጆሮ ለመድረስ አልዘገየም፡፡

ቅዱስ አግናጥዮስ አንጾኪያን እያጎበኘ በነበረው በትራጃን ፊት ታስሮ ቀረበ፡፡ በራሱ በንጉሡ የመንግሥትን ሕግ በመጣስ እና ሌሎችም እንዲተላለፉ በማነሣሣት ወንጀል ተከሰሰ፡፡ ቅዱስ አግናጥዮስም በግልጽ የክርስቶስን አዳኝነት እና የክርስትናን ሃይማኖት በመመስከር ከጣዖታት ጋር ያለውን ልዩነት በጽናት መሰከረ፡፡

በዚህ ወቅት ንጉሡ በቁጣ ለትእዛዜ የማትገዛ እና ሌሎችንም በማሳደም ወደ ጥፋት የምትማግድ አንተ ክፉ ማን ነህ ? አለው፡፡

ቅዱሱም ***‹‹ማንም ቴኦፎሮስን (እግዚአብሔርን የተሸከመውን) - ክፉው መንፈስ ብሎ***

www.zeorthodox.org

***አልጠራውም›› ሲል መለሰ፡፡***

**ቴኦፎሮስ** ማነው ? ንጉሡ ጠየቀ፡፡

ክርስቶስን በውስጡ የያዘው እርሱ ነው፡፡

በጠላቶቻችን ላይ ድል የሚሰጡን አማልክትስ እኛን አልተሸከሙንም ማለት ነው ?

ከአጋንንት የማይሻሉትን አማልክት በማለትህ ተሳስተሃል፡፡ ነገር ግን አንድ እግዚአብሔር ነው ያለው ፤ እርሱም ሰማይንና ምድርን በውስጣቸው ካሉት ጋር ፈጥሮአል፡፡ እኔም የአንድያ ልጁን የኢየሱስ ክርስቶስን /ንጉሥ የሆነ/ መንግሥት ልወርሳት እናፍቃለሁ - አለ፡፡

***" ጲላጦስ የሰቀለውን የናዝሬቱን ኢየሱስን ማለትህ ነው ? "*** አለው ንጉሡ በፌዝ፡፡

***" አዎ እርሱ ነው ፤በሞቱ ኃጢአትን እና ሥልጣኑን የሰቀለ እና እርሱን በልባቸው የተሸከሙትን ሁሉ ዲያብሎስና ሸንገላውን ከእግራቸው በታች እንዲረግጡ ያደረገው፤ አዎ እርሱ ነው፡፡"***

እናስ አንተ ክርስቶስን ተሸክመሃል ?

አዎን *‹‹በእነርሱ እኖራለሁ በመካከላቸው እመላለሳለሁ››* 2ኛ ቆሮ 6፣16፣ ዘሌ 26፣12 ተብሎ እንደተጻፈ በእኛ ውስጥ አለ አለው፡፡

በትራጃን ፊት የተገለጸው የቅዱስ አግናጥዮስ መንፈሳዊ አቋም በመንፈስ እግዚአብሔር የተቃኘ እና የተከናወነ ንግግር፣ ግርማ እና ጀግንነትን የተላበሰ የእምነት ጽንዓት ነበር፡፡ ቅዱስ አግናጥዮስ በትራጃን ፊት መንፈሳዊ አቋሙን ሲገልጽ፡- አስደናቂውን አቀራረብ ለማስተዋል እና ለማድነቅ ያልቻለው ንጉሥ በንዴት፤ አስረው ወደ ሮም እንዲወስዱት እና የአናብስቱ ቀለብ እና የሕዝቡ መዝናኛ እንዲሆን አዘዘ፡፡

**ተግባር፡-** በሰላም ጊዜ እና በሚመች ሁኔታ በአግባቡ ተጠቀሙ እና ሥሩ፡፡

www.zeorthodox.org

**ማጠቃለያ፡-** ቅዱስ አግናጥዮስ እውነተኛ የቤተ ክርስቲያን አባት ነበር፡፡

# ቅዱስ አግናጥዮስ (2)

## ሠላሳኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ከቅዱስ አግናጥዮስ ሕይወት መማር፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *"እርሱንና የትንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ፣ በመከራውም እንድካፈል ወደ ሙታንም ትንሣኤ ልደርስ ቢሆንልኝ፣ በሞቱ እንድመስለው እመኛለሁ"፡፡* ፊልጵ. 3፣11

**ምንባብ ፡-** መጽሐፈ ስንክሳር

***መግቢያ፡-*** ስለ ቅዱስ አግናጥዮስ የጀመርነውን ትምህርት ለማጠቃለል እንዲረዳ መምህር ያለፈውን ሳምንት ትምህርት አስታውሱአቸው፡፡

### የሳምንቱ ትምህርት፡-

ቅዱስ አግናጥዮስ በንጉሡ የታዘዘበትን እስራት በደስታ ተቀብሎ ሲጓዝ ደቀ መዛሙርቱ ቢያዝኑም አጽናንቷቸው ከወታደሮቹ ጋር እየፈጠነ ሲጓዝ ፤ ለሞት ሳይሆን ለሽልማት የሚሄድ ይመስል ነበር ፡፡ ከረጅም ጉዞ በኋላ ዕረፍት ሲያደርጉ ቅዱስ አግናጥዮስ፡-

ለአብያተ ክርስቲያናት መልእክት ይጽፍ ነበር፡፡ ለመጀመሪያ ባረፈባት በሰርምኔስ ሆኖ ወደ ኤፌሶን፣ ወደሮም እና ወደ ማኔዝያ እና ወደ አውሊያ መልእክት ጽፏል፡፡ በጉዞው ወቅት የነበረውን የወታደሮቹን ጭካኔ፤ ***‹‹ከሶርያ ወደ ሮም በቀንና በሌሊት በባሕር እና በየብስ በአስር አናብርት መሐል ታስሬ በርኅራኄ ፋንታ ጭካኔ በሚጨምሩ ወታደሮች ጋር እየተፋለምኩ ተጓዝኩ››*** በማለት ጽፎታል፡፡

www.zeorthodox.org

በአካባቢው ያሉትን ክርስቲያኖች ያጽናና እና ይመክር ነበር፡፡ በሰርምኔስ በቅዱስ ዮሐንስ ደቀ መዝሙርነቱ ጊዜ ጓደኛው ከነበረው ከቅዱስ ፓሊካርፐስ የሰርምኔስ ቤተ ክርስቲያን ሊቀጳጳስ ጋር ተገናኙ፡፡ አግናጥዮስ ወደ ወዳጁ ፓሊካርፐ ሲሄድ፣ ፓሊካርፐም እግሩ ሥር ወድቆ ሳመው፡፡ በዚያ የተሰባሰቡ ክርስቲያኖችንም አጽናንቶ በየመጡበት ቤተ ክርስቲያንም ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር እንዲስማሙ፣ ከመናፍቃን እንዲጠበቁ እየመከረ የአንዲት ቤተ ክርስቲያንን ፍቅር እንዲያጸኑ

አስተምሮአል፡፡ መጥተው ለጠየቁትም ምስጋና አቅርቧል፡፡

ለሮም ክርስቲያኖችም በተለይ ከሰማዕትነቱ እንዳያስቀሩት በመልእክቱ ይለምናቸዋል፡፡ ከሰርምኔስ አሳሪዎቹ ተነሥተው ጉዞአቸውን በመቀጠል ጢሮስ ሲደርሱም ለቅዱስ ፓሊካርፕስ፣ ለፊልድልፊያ እና ለሰርምኔስ አብያተ ክርስቲያናት የተላኩትን መልእክታት ጻፈ፡፡

ቅዱስ አግናጥዮስ በታናሽ እስያ እና በአንጾኪያ በሮም እንደ አባት ፖሊካርፐርስን ‹‹የእስያ አብያተ ክርስትያናት›› አደራ ሰጠው፡፡

ከዚህ ጎን በአንጾኪያ ያሉት ክርስቲያኖች መከራ ስለጸናባቸው በታናሽ እስያ ያሉ ክርስቲያኖች ወንድማዊ ቸርነት እንዲያደርጉላቸው ለማሳሰብ ፈልጎ ነበር፡፡ ነገር ግን ጠባቂዎቹ የጉዞ እቅዳቸው ይለዋወጥ ስለነበረ መልእክቱን ቅዱስ ፓሊካርፐስ እንዲጽፍላቸው አሳስቦት ተጓዘ፡፡ ከጢሮስ ወደ ኒያፓሊስ (Neopolis) በመርከብ ሄዱ፡፡ ከኒያ ፖሊስ በመቄዶንያ እና ኢላሪያ አድርገው በየብስ ተጓዙ፡፡ በየቦታው ክርስቲያኖች እያገኙት በጽናቱ እየተደነቁ፣ በቃሉ እየተማሩና እየተባረኩም በፍቅር ይሸኙት ነበር፡፡ በአድርያቲክ ባሕረ ሰላጤ ቴሬን እና ሌሎች ደሴቶችንም አቋርጠው ከብዙ የእንግልት ጉዞ በኋላ ሮም ደረሱ፡፡

የትሮጃን አምፊ ቴአትር ትዕይንት ለቀናት ቀጥሎዋል፡፡ ነገር ግን ሳይደርሱ ትዕይንቱ ሊበተን ነውና ወታደሮቹ ተበሳጭተዋል፡፡ ***‹‹በጣም ዘግይተናል ሊዘጋ ነው››*** ይላሉ በተደጋጋሚ፣ ቅዱሱም ***‹‹እንዳይዘጋብን››*** ብሎ መፍጠን ጀመረ፡፡ እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 20 ቀን ትዕይንቱ በሚዘጋጅበት ዕለት ሮም ደረሱ፡፡ ወታደሮቹ በማስቃየት ሐሳቡን ለማስቀየር በአስቸጋሪ እና ረጅም መንገድ በሰሜን በኩል ሲወስዱት፤ በአጭሩ የምሥራቅ መንገድ የተጓዙት የቅዱሱ ወዳጆችና ደቀመዛሙርት ቀድመው ሮም ደርሰው እየጠበቁት ነበር፡፡ ወታደሮቹ ለፓሊስ ሓላፊው ከንጉሡ የሞት ትእዛዝ ደብዳቤ ጋር አስረከቡት፡፡ በንጉሡ ትእዛዝ መሠረት የወታደሮቹ አዛዥ ቅዱስ አግናጥዮስን ትዕይንቱ ወደሚታይበት ቦታ ወይም ስታዲዮም /ኮሎሲየም ይባላል/ እንዲወሰድ አደረገ፡፡

www.zeorthodox.org

ክርስቲያኖች ቅዱሱን የእግዚአብሔር ሰው በማየት ደስታ ቢሰማቸውም በመሞቱ ሐዘን ሲቃ ይዟቸው ያነባሉ፡፡ ክርስቶፎሮስ ቅዱስ አግናጥዮስ በወታደሮች እየተገፈተረ፤ ክርስቲያኖች ልቡን እንዳያደክሙበት መምከሩን ቀጥሎ፤ ለሮም ሕዝብ እይታ ቀረበ፡፡ ዝናው የተናኘውን ቅዱስ ሮማውያንና ክርስቲያኖች እያዩት ለሁሉም የስንብት ሰላምታውን ሰጥቶ ለሚያለቅሱት ***‹‹ወደ ጌታ የምጓዘውን ጉዞ አታደናቅፉኝ ብሎ ለመነ፡፡››*** እነርሱም ከፊቱ በመሆን ሰገዱለት፡፡ ባለሥልጣናቱ ቅዱስ አግናጥዮስን እየገረፉ ክርስቶስን በክህደት ሰድቦ ጣዖት እንዲያመልክ ጠየቁት፡፡ እሱ ግን በታላቅ ድምፅ ክርስቶስን ሰበከ፡፡

ወደ አናብስቱ መውጫ ሲወስዱት የጌታችንን ስም እየጠራ ገባ፤ እንዲያቆም በመከራ አስጨነቁት፡፡*‹‹የክርስቶስ ስም በአንደበቴ ሳይሆን በልቤም ተጽፏል . ... ለመተው አልችልም››* አላቸው፤ የሥቃዩን መብዛት አይተው ዝም እንዲል ለጠየቁት ክርስቲያኖች *‹‹በአናብስት በሚቆራረጠው የልቤ ቁራጭ ሁሉ ክርስቶስ ተጽፏል››* በማለት እየደጋገመ ነገራቸው፡፡

ወታደሮቹ ቅዱስ አግናጥዮስን አናብስቱ በሚወጡበት አጥር በር በኩል በስታድየሙ መካከል አቆሙት፡፡ ከውስጥ የሚያገሱት አናብስት ድምፅ በኃይል እያስተጋባ ይሰማል፡፡ ቅዱሱ ሊቀ ጳጳሳት ከአናብስቱ ድምፅ ይልቅ በሚያስገመግም ድምፅ፤ *‹‹እናንተ ሮማውያን ከዚህ የተሰበሰባችሁት ይህን ውጊያ ልታዩ ነው፡፡ ማወቅ ያለባችሁ ይህ የሞት ቅጣት ወንጀል ሠርቼ የመጣብኝ ሳይሆን ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሰኝ መንገድ ነው፤ በዚህም የጌታን ፍቅርና የልቤን ምኞት የምፈጽምበት ነው፡፡ እኔ የእግዚአብሔር መገበሪያ ስንዴ ነኝ፣ እርሱ ለእኔ ኅብስት እንደሆነ እኔም በአናብስት ጥርስ በመፈጨት የክርስቶስ ኅብስት እሆናለሁ፡፡››* አለ፡፡

ይህን ተናግሮ ሲጨርስ ሁለት የተራቡ አናብስት እየዘለሉ ወደ እሱ መጡ፡፡ አጥንቱን ብቻ ከቁራጭ ሥጋ ጋር አስረው ወደቦታቸው ተመለሱ፡፡ የቅዱሱም የሰማዕትነት ጸሎት በዚህ ሁኔታ ምላሽ አገኘ፡፡ በ/111/ ዓ.ም ገደማ ያረፈው ሰማዕት፣ ሊቀጳጳስ፣ ሐዋርያው፣ ጸሐፊ እና ሰባኪው ቅዱስ አግናጥዮስን ቤተ ክርስቲያናችን ታኅሣሥ 24 ታከብረዋለች፡፡

## ምን ተማርን ?

ክርስትና በእውነት፣ በፍቅር እና በሰማዕትነት ጸንቶ ካለንበት ዘመን ድረስ የተላለፈ ሃይማኖት ነው፡፡

ክርስቲያኖች በመከራ የሚጸኑ፤ ስቃይ የማያሸንፋቸው ናቸው፡፡ እኛም በእግዚአብሔር አምነን ፈተናዎችን በመጋፈጥ ማሸነፍን ተምረናል፡፡ ቅዱስ አግናጥዮስ ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ ፍቅር ነበረው፡፡

www.zeorthodox.org

ክርስቶስን መውደዳችን በጥልቀት ከሆነ የሚገለጠውም በሚመችም በማይመችም ጊዜ መሆኑን ከአባታችን ሕይወት ተምረናል፡፡

## ተግባር፡-

ሰማዕታትን እንደ ቤተ ክርስቲያን ማሰብ እና ማክበር አለብን፡፡

# ቅዱስ አትናቴዎስ

## ሠላሳ አንደኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የቅዱስ አትናቴዎስን ሕይወት እና ታሪክ መሠረት በማድረግ ለክርስትና እምነት እና ለቤተ ክርስቲያን እውነት የተከፈለውን መሥዋዕትነት ማጥናት ነው፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"እንግዲህ አትፍሯቸው ፤ የማይገለጥ የተከደነ ፣ የማይታወቅም የተሰወረ ምንም የለምና፡፡"*** ማቴ 10፡24-26

## መግቢያ፡-

በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የቤተ ክርስቲያን የስደት ዘመን ያበቃበት እና ክርስቲያኖች የአምልኮ ነጻነታቸውን በዓዋጅ ያገኙበት ወቅት ነው፡፡ቤተ ክርስቲያን ይህን ነጻነት ያገኘችው እግዚብሔርን አምነው በጽንዓት በመቆም፤ እውነትን በመስበክ፣ በፍቅር በመኖር እና ሰማዕትነትን በመክፈል በአባቶች እና እናቶች እውነተኛ ሕይወት ዓለም ስለተማረከ ነው፡፡ እንዲሁም የክርስትና ጠላቶች አረማውያን እና አይሁድ ትምህርቱን ተቋቁመው መዝለቅ ስላልቻሉ በወንጌል ትምህርት ስለተሸነፉ ነው፡፡

ይህን ድል ተከትሎም የተለያየ እምነት እና ሐሳብ ያላቸው ቡድኖች ወደ ክርስትና ገቡ፡፡ በእውነት አምነው የገቡ እንዳሉ ሁሉ ካሸነፈው ጋር ለመኖር ሲሉ ብቻም በማስመሰል ክርስቲያን የሆኑ ነበሩ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ የክርስትና ትክክለኛ ትምህርት ያልገባቸው እና ከበፊቱ ዕውቀት እና እምነታቸው ጋር የሚቀላቅሉ ነበሩ፡፡

የማስመሰል እና የተቀላቀለ እምነት የያዙትም አዲስ ፈተና ለቤተ ክርስቲያን አመጡ ፡፡ ከነዚህም አንዱ እና ዋነኛው አርዮስ ነው፡፡ እርሱም ከግሪካውያን ፍልስፍና የተቀየጠ እና የክርስቶስን አምላክነት የሚክድ አዲስ ትምህርት አስተማረ ፤ ብዙ ተከታዮች እና ደጋፊዎችም ነበሩት ፡፡ በዛሬው ትምህርታችን ይህንን የተሳሳተ ትምህርት ለማረም ከተነሡት አባቶች መካከል የቅዱስ አትናቴዎስን ታሪክ እንማራለን፡፡

www.zeorthodox.org

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

**የቅዱስ አትናቴዎስ ልደት እና እድገት፡-**

ቅዱስ አትናቴዎስ ከአረማውያን ቤተሰቦች በ296/296/ ዓ.ም ገደማ በግብጽ አሌክሳንድርያ ከተማ ተወለደ፡፡ አባቱ ባዕለ ጸጋ የነበረ ቢሆንም በልጅነቱ ሞተ፡፡ እናቱም በክርስቲያኖች ትምህርት ቤት እንዲማር አደረገች፡፡ በኋላም አትናቴዎስ ክርስቲያን ሆኖ ተጠመቀ እናቱም ተጠምቃ ሞተች፡፡ በዚያም ክርስትናን በጥልቀት ተማረ፡፡ በኋላም በወቅቱ የእስክንድርያ ፖትርያርክ አለእስክንድሮስ ተመርጦ ዲያቆን እና ጸሐፊ ሆኖ ያገለግል ጀመር፡፡ በበረሐ ውስጥ ምንኵስና የጀመረው የታላቁ ቅዱስ እንጦንስ ደቀመዝሙር ሆኖም በበረሐ ኖሯል፡፡

የመንፈስ አባቱን እለ እስክንደሮስን እያገለገለም በኒቂያ ጉባኤ ላይ ተገኝቶ ከአርዮስ ጋር ተከራክሮ አሸንፎአል፡፡ በኋላም እለእስክንድሮስ ሲሞት ተተኪው ፖትርያርክ እርሱ ሆነ፤ ***"ሐዋርያዊው "*** የሚል ቅጽል ስያሜ የተሰጠውም ለቤተ ክርስቲያን እና ለእምነትዋ ጠበቃ ሆኖ በፈጸመው ተጋድሎ ነው፡፡

ይህን ተጋድሎ እንዴት ፈጸመ? ስንልም÷ በጽኑዕ ልብ የቆመ ስለነበረ ነው፡፡

ግብጻዊው "ካህን" አርዮስ አንደበተ ርቱዕ፣ የግጥም እና የዜማ ሰው፣ በዕድሜ ሽማግሌ እና ታዋቂም ነበር፡፡ ሲያስተምርም ‹‹ክርስቶስ ከአብ ያነሰ እና በአብ የተፈጠረ ሁለተኛ አምላክ ነው›› አለ፡፡ በዚህም መጽሐፍ ቅዱሳዊ እና ሐዋርያዊ ትምህርቶችን ተቃወመ፡፡ ፖትርያርኩ እለ እስክንድሮስ ይህን የተሳሳተ ትምህርቱን እንዳያስፋፋ ሊያቆመው ቢሞክርም፣ አልተሳካም፡፡

በመጨረሻም እለእስክንድሮስ አውግዞ ከቤተ ክርስቲያን ለየው፡፡ አርዮስ ግን የእለእስክንድሮስን ስም እያጠፋ የሐሰት ትምህርቱን ገፋበት፡፡ አርዮስ የሚያስፋፋውን የስሕተት ትምህርትና ኑፋቄ ለማረምና ለማቆም ሲባል፤ ጉባኤ ማካሄድ እና ውሳኔ ማሳለፍም ወቅታዊ ጉዳይ እና ግዴታ ሆነ፡፡ በታላቁ ቆስጠንጢኖስ ዘመነ መንግሥት በ/325/ ዓ.ም በተጠራው የኒቂያ ጉባዔ /318/ ጳጳሳት ከመላው ዓለም ተሰባሰቡ፡፡ ዲያቆኑ አትናቴዎስም፤ ‹‹ክርስቶስ በባሕርይ እና በመለኮት ከአባቱ ከአብ ጋር እኩል ነው፤›› ብሎ አሳመነ፡፡ ጉባኤውም የአርዮስን ስሕተት የቅዱስ አትናቴዎስን የጠራ ትምህርት አዳምጦ ወሰነ፡፡

www.zeorthodox.org

ከጉባኤውም በኋላ በሁለተኛው ዓመት እለእስክንድሮስ ዐረፈ፡፡ ቅዱስ አትናቴዎስም ሃያኛው ፖትርያርክ ሆኖ በእስክንድርያ ተሾመ፡፡ ቅዱስ አትናቴዎስ የቤተ ክርስቲያን መሠረተ እምነት ጠበቃ ከሚባሉት አንዱ ነው፡፡ የሥነ መለኮት ሊቅ እና ጸሐፊ የነበረው ቅዱስ አትናቴዎስ ከታወቁት መጻሐፍቱ የሚከተሉት ይገኙበታል፡-

አረማዊነትን የተቃወመበት /Against the pagance/

የቃል ሥጋ መሆን /The Incarnation of the word/

የቅዱስ እንጦንስ ሕይወት /The Life of Saint Antony/

አርዮሳዊነትን የተቃወመባቸው መጽሕፍት

እምነት /The Faith/

ስለ መንፈስ ቅዱስ የተላከ መልእክት (Letters on the Holy Spirit)

ስለ ኒቂያ ጉባኤ እና ውሳኔዎች የተጻፈ መልእክት፡፡

የትንሣኤ መልእክታት /Paschal letters/ ናቸው፡፡

ቅዱሱ የቤተ ክርስቲያን ጠበቃ አትናቴዎስ አምስት ጊዜ ከመንበሩ የተሰደደ ሲሆን በሁሉም ስደቶች አስደናቂና የበለጠ ውጤታማ አገልግሎቶችን ፈጽሟል ፡፡ ዛሬ ለነገረ መለኮት (Theology) ትምህርት የሚያገለግሉ ትምህርቶቹ በመልእክታት መልክ የተጻፉት በዚህ ወቅት ነበር፡፡ በእምነት ከመለዘብ እና ከመመሳሰል መሰደድን መርጦ በጽናት የቆመ አባት ነው፡፡

ቤተ ክርስቲያንም በየዓመቱ ትዘክረዋለች፣ በጸሎቶቿም ታስበዋለች፡፡

## ምን ተማረን?

ያደግንበት አስተዳደግ እና መሠረታዊ ዕውቀታችን በነገው ሕይወታችን ውስጥ ወሳኝ ነው፡፡ ቅዱስ አትናቴዎስ በክርስቶስ ፍቅር ያደገና እርሱንም በሚገባ ያወቀ ነው፡፡ እኛም በሕይወታችን ለእግዚአብሔር ፍቅር ትኩረት ሰጥተን ማደግ አለብን፡፡

ቅዱስ አትናቴዎስ አርዮሳውያንን በጽናት ተቃውሞ እውነተኛውን ትምህርት አስተምሮ፣ በሃይማኖት አሸንፏቸዋል፡፡ እኛም ሃይማኖታችንን በመጠበቅ፣ የተሳሳቱ ትምህርቶችን እና የዓለምን ኑፋቄ በማሸነፍ መጽናት አለብን፡፡

www.zeorthodox.org

# ቅዱስ ላሊበላ

## ሠላሳ ሁለተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ ፦** ከደጋግ አባቶቻችን ታሪክ ጽናትን እና ሀገርን መውደድ መማር።

### መግቢያ፦

ንጉሥ ላሊበላ ቤተ ክርስትያን የቅድስና መዓርግ ከሰጠቻቸው ኢትዮጵያውያን ነገሥታት አንዱ ነው።

ከዓለማችን ድንቅ ቅርሶች መካከል አንዱን ያነጸውና በቅድስና ኑሮው የሚታወቀውን የቅዱስ ላሊበላ ታሪክ በዛሬው ትምህርታችን እንማራለን። የቅዱሳን አምላክ ከሁላችንም ጋር ይሁን አሜን!!

### የሚጠና ጥቅስ፦

"***በቤቱና በቅጥሬ ውስጥ ከወንዶችና ከሴቶች ልጆች ይልቅ የሚበልጥ መታሰቢያና ስም እሰጣቸዋለሁ፤ የማይጠፋም የዘለዓለም ስም እሰጣቸዋለሁ።...በጸሎቴም ቤት ደስ አሰኛቸዋለሁ።***" ኢሳ.56፡4-7

## የትምህርቱ ይዘት፦

### ከልደት እስከ ንግሥና

በጥንቷ ሮሐ በዛሬዋ ቡግና የሚገኙትን ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ያነጸው ንጉሥ ላሊበላ አባቱ ሥዩም እናቱ ኪረወይና ይባላሉ።

www.zeorthodox.org

ከሁለቱ የተገኘው ሕፃን ታኅሣሥ 29 ቀን ሲወለድ ንብ ከቦት ነበር። በዚህ የተነሣ እናቱ በአገውኛ ላል ይበላ/ላሊበላ/ ብላ ጠራችው። ***"ላሊበላ ብሂል ንህብ አእመረ ጸጋሁ - ላሊበላ ማለት ንብ ጸጋውን አወቀ ማለት ነው"*** ይላል ገድሉ። ይህም ወደፊትም ንጉሥ  ይሆናል ተብሎ ተተረጐመ። ይህ ስያሜና ትርጓሜ ለመንገሥ ያስብ የነበረውን ወንድሙን ሐርቤን ቅር አሰኝቶታል።

ከዚያ በኋላ ሐርቤ ነገሠ፤ ላሊበላም በሞገስ አደገ። ከሕፃንነቱ ጀምሮ ተወዳጅ የነበረው የሮሐው ልዑል - ላሊበላ በመልካም ሰብእናው፣ በመንፈሳዊ ሕይወቱ እና በበጎ ተግባሩ የሚከበርና

እና ለንግሥና የሚናፈቅ ልዑል ሆነ፡፡

ላሊበላ የመጀመሪያውን ትምህርት በቤተሰቡ አካባቢ ከተማረ በኋላ ወደ ጎጃም መርጡለ ማርያም ቤተ ክርስቲያን በመጓዝ ትምህርቱን አስፋፍቷል፡፡ በነበረው ቀለም የመቀበል ችሎታ የቀኑበት ሌሎች ተማሪዎች ችግር ስለፈጠሩበት ትምህርቱን አቋርጦ ወደ ላስታ ተመልሶ፤ መስቀል ክብራን አገባ፡፡

ከወንድሙ የሚያጣሉት ነገረ ሠሪዎች እና በአባት ብቻ የምትወለደው እኅቱ/ዮዲት/ ‹‹በንጉሡ ላይ ይነግሣል›› ብለው በክፋት ተነሡበት፡፡ በአንድ ወቅትም እኅቱ በአባት እና በእናት ለሚወለዳት ወንድም የተቆረቆረች መስሎአት መርዝ ቀላቅላ ሰጠችው፡፡ ጌታችን ‹‹***በእኔ የሚያምኑ...... የሚገድልም ነገር ቢጠጡ አይጎዳቸውም*** ....›› /ማር. 16፥18/ እንዳለ ለሦስት ቀናት ራሱን ከሳተ በኋላ ተነሣ፡፡ አብያተ ክርስትያናቱን ያነጸበትንም ራእይ በዚህ ጊዜ እንዳየም ገድሉ ይገልጣል፡፡

በዚህ ያልበቃቸው ክፉ አሳቢዎች በድጋሚ ነገር ሠርተው ከወንድሙ ጋር አጣሉት፡፡ በዚህ ምክንያትም ታስሮ ተገረፈ፡፡ ከዚያም ከክፉ ሰዎች ጋር ከመኖር ከአራዊት ጋር መኖር ይሻላል ብሎ ትግራይ ውስጥ መደባይ ታቦር በተባለ ቦታ ሚስቱን አስቀምጧት፤ ወደ በረሐ ተሰዶ በምሥራቅ ኢትዮጵያ ለዓመታት ኖረ፤ በዚያም ከእግዚአብሔር በተሰጠው ጥበብ ውቅር አብያተ ክርስቲያን ሠራ፡፡ አንዳንድ ምንጮች በስደቱ ወቅት ኢየሩሳሌም እንደሄደ ያትታሉ፡፡ ከዚያም ወንድሙ ተጸጽቶ ስላስጠራው ወደ ቤተ መንግሥት ተመለሰ፡፡ ንጉሥ የነበረው ወንድሙም ሥልጣኑን ለላሊበላ አስረከበው፡፡

በቅድስና ኑሮው በአስተዳደር ብቃቱ እና በሕንጻ ጥበቡ ቅዱስ ላሊበላ የነበረውን ክርስቲያናዊ ዝና በመስማት ከአምስተ ሺሕ በላይ ግብጻውያን ክርስቲያኖች ወደ ሮሐ መጥተው ነበር፡፡

## የዓለት ላይ አብያተ ክርስቲያናት ሥራ

የዛጉዌ ነገሥታት ከሚታወቁባቸው ነገሮች አንዱና ዋነኛው የዋሻ ውስጥ አብያተ ክርስቲያናትን በመገንባትና ከዓለት ላይ በመፈልፈል አብያተ ክርስቲያናትን ማነጻቸው ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ሥራ የተጀመረው በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በዐፄ ካሌብ ዘመነ መንግሥት ቢሆንም ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት የላቀ ደረጃ የደረሰው ግን በዛጉዌ ነገሥታት ነው፡፡ ይህም በዘፈቀደ ሳይሆን ራሱን ያቻለ ሃይማኖታዊ ትርጒምና መጽሐፍ ቅዱሳዊ አንድምታ አለው፡፡

www.zeorthodox.org

የላሊበላን ዘመነ መንግሥት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በክብር እየታሰበ እንዲኖር ከሚያደርጉት የሚያስታውስበት ምክንያቶች ውስጥ ጻድቁ ንጉሥ ከአንድ ቋጥኝ አስፈልፍሎ

የሠራቸው አብያተ ክርስቲያናት ናቸው፡፡ ከእነዚህም ዛሬ በላሊበላ የሚገኙት ዐሥራ አንድ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ፡-

| | |
|---|---|
| ቤተ ደናግል | 7. ቤተ ገብርኤል |
| ቤተ ማርያም | 8. ቤተ አባ ሊባኖስ |
| ቤተ መድኃኔዓለም | 9. ቤተ መርቆርዮስ |
| ቤተ መስቀል | 10. ቤተ አማኑኤል |
| ቤተ ጎልጎታ | 11. ቤተ ጊዮርጊስ ናቸው |
| ቤተ ቅዱስ ሚካኤል | |
| ናግ | 7. ቤተ ገብርኤል |

የታሪክ ተመራማሪው አል ቫሬስ ስለ ቅዱስ ላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት በዐሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የሚከተለውን ብሎ ነበር፡፡ ‹‹***ስለ እነዚህ ሕንጻዎች መጻፍ ደከመኝ፡፡ ምክንያቱም የማየውን ማመን አቃተኝ፡፡ ከዚህ ተጨማሪ ብጽፍ ማንም አያምነኝም፤ ሐሰተኛ እባላለሁና፡፡ ስለዚህ በእግዚአብሔር ስም እምላለሁ የጻፍኩት ሁሉ እውነት ነው፡፡ ምንም ከራሴ የጨመርኩት የለም፡፡ እንዲያውም ያልጻፍኩት እና የተውኩት ብዙ ነው፤ ውሸታም ተብዬ እንዳልወቀስ፡፡ ዓለም ይህን ድንቅ ሥራ እንዲያውቅልኝ እመኛለሁ፡፡***`` (The Sign and the Seal)

ቅዱስ ላሊበላ በሮሐ ካነጻቸው በተጨማሪ በተለያዩ ቦታዎች እስከ ሰባ (ሃያ ሦስት የሚሉም አሉ) አብያተ ክርስቲያናትን አንጾአል፡፡

## የሰላማዊና መልካም ግንኙነት ፍሬዎች፡-

www.zeorthodox.org

ቅዱስ ላሊበላ በዘመኑ ከግብጻውያን ጋር የነበረው ግንኙነት በመልካም ጎኑ የሚጠቀስና በአብዛኛው በወዳጅነት ላይ የተመሠረተ ነበር፡፡ ንጉሡ መልእክተኞቹን ከብዙ ገጸ በረከት ጋር ልኮ አባ ሚካኤል የሚባሉ ጳጳስ ከእስክንድርያ አስመጥቶ የደመቀ አቀባበል እንደተደረገላቸው ተዘግቧል፡፡

ቅዱስ ላሊበላ በሦስተኛው የመስቀል ጦርነት ወቅት ድል ከቀናው ሳላህዲን ከተባለ ግብጻዊ ሡልጣን ትልቅ ግምት የሚሰጣቸው በኢየሩሳሌም የሚገኙ ቅዱሳት መካናት በስጦታ ተበርክቶለታል፡፡ ከእነዚህም መካናት መካከል በጎልጎታ የጌታ መቃብር አጠገብ ያለው፣ እሌኒ ንግሥት መስቀሉን ያስወጣችበት ዋሻና በቤተልሔም ጌታ የተወለደበት በረት ይገኙበታል፡፡

በመካከለኛው ዘመን የዓለም ታሪክ ውስጥ ምዕራባውያኑ (የሮም) ካቶሊኮች ቅድስት አገር ኢየሩሳሌምን ነጻ ለማውጣት በሚል ሰበብ ከሙስሊሞች ጋር ያደረጉት ስምንት የመስቀል ጦርነቶች ነበሩ፡፡(ጦርነቱ ፍትሐዊ አለመሆኑና በካቶሊካውያኑ ብቻ የተያዘ ስለነበር አርቶዶክሳውያኑ አልተሳተፉበትም ውጤቱም መልካም አልነበረም፡፡)

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ቅዱስ ላሊበላ ከሳላህዲን (ከሙስሊሞቹ መሪ) በኢየሩሳሌም ያሉ ቦታዎችን በስጦታ ያገኘው ኢትዮጵያ በመስቀል ጦርነት ጊዜ ገለልተኛ ሆና በሰላማዊነት በመቆየቷ ነው፡፡ ይህም ከኢትዮጵያውያን በተጨማሪ ግብጻውያን እና ካቶሊካውያን መነኮሳት በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት መጠጊያ እንዲያገኙ አስችሎአል፡፡

## ቅዱሱ እና ቅዱሳኑ፡-

በቅዱስ ላሊበላ ዘመነ መንግሥት ታላቁ አባት ጻድቁ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ከግብጽ ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል፡፡ ንጉሡ ቤተ ክርስትያኑን ሠርቶ እንደፈጸመ በጸሎት ቦታው ሆኖ ሲጸልይ በእግዚአብሔር ጸጋ ፊታቸው የሚያበራ፤በጣም ረጅምና የሚያምር ጢም ያላቸው አባት በአናብርት እና አናብስት ተከበው መጡ፡፡ ቤተ ክርስቲያኑንም በመደነቅ ይመለከቱ ነበር፡፡ እኚህ አባት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ናቸው፡፡ ንጉሡ ጸሎቱን ጨርሶ ወደ እርሳቸው ቀርቦ ‹‹***ሰማያዊ ነዎት ወይስ ምድራዊ?***›› ሲላቸው፤ እርሳቸውም ፤ ‹‹***ይህ ሕንጻ የምድር ነው የሰማይ?***›› አሉት፡፡ ከዚያም እግዚአብሔር ያደረገላቸውን ተነጋገሩ፡፡

ወደ ቤቱ ወስዶ ለተወሰኑ ቀናት አስተናገዳቸው፤ በጻድቁ ገድል እንደተመለከተው ቅዱስ ላሊበላ የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስን መንፈሳዊነት ወዶ የተለየ የክብር ቦታ ሰጣቸው፡፡ እርሳቸውም ጥቂት ቀናት እያስተማሩ በሮሐ ቤተ መንግሥት ሰነበቱ፡፡

በመቀጠልም ቅዱስ ላሊበላ ቦታ ልስጥዎትና በዚህ እየጸለዩ እየባረኩ ፣ ወንጌልንም እያስተማሩ ይቀመጡ አላቸው፡፡ እሳቸው ግን፤ ‹‹እኔ እንዳስተምር እና እንድጸልይ የታዘዝኩት በዚህ አይደለም፡፡ በደብረ ታቦር አምሳል በሆነች በዝቋላ ተራራ ስለሆነ ወደዚያው እሔዳለሁ፡፡ የአንተ ግን ከተማህ የተባረከ ነው፤ አንተም የተባረክ ነህ፤›› ብለው ወደ ዝቋላ ለመሔድ ሲነሡ ዝቋላ ድረስ ሸኝቷቸው እንደተመለስ ተጽፏል፡፡ ሸኝቶ ሲመለስም የአዳዲ ማርያምን ቤተ ክርስቲያን አነጻት፡፡

www.zeorthodox.org

ላሊበላ ከሚታወስባቸው ነገሮች መካከል ሌላው የግል ኑሮውን እንደ መንግሥት በሚሰበስበው ግብር ላይ ሳይመሠርት ለመንግሥት ሥራ ብቻ ማዋሉ ሲሆን፤ለኑሮው የሚሆነውን ገንዘብ ያገኝ የነበረው በእጁ ተግባረ እድ እየሠራና ያንን እየሸጠ ነበር፡፡

ከዚህም በላይ ራሱ እየሠራ የሚያሠራ ንጉሥም ነበር፡፡ እንዲያውም ብዙ ጊዜ ልብሰ መንግሥቱን አውልቆ ተራ ልብስ በመልበስ ለሥራ ይሰለፍ ነበር፡፡

የንጉሥ ላሊበላ ሚስት አባ ሊባኖስ የተባሉትን ቅዱስ ታከብር እና ትወዳቸው ነበር፡፡ ንጉሡም እንዲሁ ያከብራቸው ነበር፡፡(አባ ሊባኖስ /አባ መጣዕ/ በአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ የነበሩ ብዙ ተአምራት የፈጸሙ ጻድቅ አባት ናቸው፡፡) ለዚህም ነው ከዐሥራ አንዱ ውቅር አብያተ ክርስትያናት አንዱ ቤተሊባኖስ የሆነው፡፡ ከአዲግራት በስተ ምዕራብ የሚገኘውን ደብረ ሊባኖስ ዘሺምዛና ገዳምም በጣም ይወድ ነበር፡፡ ላሊበላ ለዚህ ገዳም ብዙ ርስት ሰጥቶ ነበር፡፡ በኋላም በሚስቱ በቅድስት መስቀል ክብራ ስም እንደገና ጉልት ሰጥቶል፡፡ ዐፄ ላሊበላ ኢትዮጵያን ለዐርባ ዓመታት ከገዛ በኋላ በ/1220/ ዓ.ም / በ/1173/ ዓ.ም ነው የሚሉም አሉ፡፡/ ሰኔ 02 ቀን ዐርፎ በቤተ ጎልጎታ ተቀበረ፡፡ ቤተ ክርስቲያን ቅድስናውን አረጋግጣ ‹‹ቅዱስ›› ብላ ታቦት በስሙ ቀርፃ ገድሉን ጽፋ ታከብረዋለች፡፡

የተወለደበት ቀን ታኅሣስ 29 እና ያረፈበት ሰኔ 12 መታሰቢያ በዓሉ በየዓመቱ ይከበራል፡፡

አምላካችን እና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአባቶቻችን የሰጠውን ማስተዋል ያድለን ከቅዱሱ በረከት ያካፍለን፡፡ አሜን!!!

www.zeorthodox.org

# ኢያሱ ሕዝቡ የሚያመልኩትን አስመረጠ

## ሠላሳ ሦስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-**እግዚአብሔርን በነጻነት ስለ መምረጥ፣ከኢያሱ እና ከሕዝቡ ታሪክ መማር

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *"የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ። "* ኢያ.24፡15

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** መጽሐፈ ኢያሱ ምዕ 24፡1-28

**መግቢያ፡-** ኢያሱ ማለት አዳኝ ማለት ነው። በሙሴ ተተክቶ ሕዝበ እስራኤልን የመራ እና ከእግዚአብሔር በተሰጣቸው ቃል ኪዳን መሠረት የተስፋይቱን ምድር ያወረሰ፣ ሙሴን በተከተለበት ዘመን ሁሉ አባቱን ሙሴን አክባሪ፣ አምላኩን እግዚአብሔርን በፍጹም ልቡ የሚያምን ነበር።

በዛሬው ትምህርታችን ኢያሱ በሕይወቱ ዘመን መጨረሻ የሠራውን እንማራለን። በዙሪያቸው ያሉትን የአሕዛብን አማልክት እና እግዚአብሔርን በማምለክ መካከል ለሚያመነቱት ለእስራኤል ዘሥጋ ያቀረበላቸውን ምርጫ እና ውጤቱን እናያለን።

### የሳምንቱ ትምህርት፡-

በኢያሱ የመጨረሻ ዘመን የተፈጸመው ይህ ታሪክ የሚከተሉት ሂደቶች ነበሩት።

**ሕዝቡን ወደ ሴኬም ሰበሰበ፡-** ሴኬም አብርሃም ከካራን ሲወጣ መጀመሪያ መሠዊያውን የሠራባት ቦታ ናት። (ዘፍ.12፡6-8) ኢያሱም ሕዝቡን በዚህ ቦታ ሰበሰበ። ኢያሱ እግዚአብሔርን በፍጹም ልባቸው እንዲያመልኩ ለሕዝበ እስራኤል እና ለልጆቻቸው ያስተማረ ነው። የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ፍቅር ገልጦ ነገሮአቸዋል፤ ለፍቅሩ ፍቅር እንዲመልሱም ይመክራል። ይህ የእግዚአብሔር ፍቅር እና በጎ ዓላማ ሲጀመር አብርሃም ለመጀመሪያ ጊዜ ለእግዚአብሔር የሠዋበትን ቦታ ሴኬምን ኢያሱ መረጠ።

www.zeorthodox.org

**የእግዚአብሔርን ውለታ አስታወሰ** ኢያ.24፣3-13 እግዚአብሔር ለርስቱ ለመረጣቸው ሕዝበ እስራኤል ከቀደሙት አባቶቻቸው ከአብርሃም አባት ከታራ ጀምሮ ምድረ ከነዓንን እስኪወርሱ ድረስ መልካም አድርጎአል። ኢያሱ የሚከተሉትን እንዲያስታውሱ በስብከት ደገመላቸው፡-

አብርሃምን ከዑር አውጥቶ ወደ ከነዓን የመራው እና የወረሱዋትን ምድር ቃል የገባለት

እግዚአብሔር ነው፡፡ በእርግናው ወራት ልጆችንም ሰጠው፡፡ በያዕቆብ ወደ ግብጽ ወርደው ያበዛቸው ጌታ፣ ከፈርዖን ቀንበር አላቆ ባሕረ ኤርትራን አሻግሮ ጠላቶቻቸውን አሸንፎ በጸናች እጅ ያወጣቸውም እርሱ ነው፡፡ ያልደከሙበትን ርስት ከነዓንንም አወረሳቸው፡፡ የግብጽ ጣዖታት እና ጠንቋዮች ነበሩ፡፡ በከነዓንም የአሕዛብ አማልክት ነበሩ፡፡ የበለዓም መርገምም ክፉ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ግን እነዚህን ሁሉ ከልክሎ ፤ ሁሉንም ድል አድርጎ ምድረ ርስትን አወረሳቸው፡፡ ኢያሱ ይሄን ያደረገላቸውን ***"እግዚአብሔርንም አምልኩ"*** ኢያ. 24፡14 ሲል መለኮታዊውን እውነት ሰበከ፡፡

**በፈቃድ እግዚአብሔርን መምረጥ፡-** እግዚአብሔር የነጻነት አምላክ ነውና፤ የሰዎችን ነጻ ፈቃድ ይፈልጋል፡፡ ሕያው የእግዚአብሔር ሥዕሎች፣ የጽድቁ ዓዋጆች እንድንሆን እና ተግባራዊ ፍቅርን እንድንገልጥ ይሻል፡፡ እንደ ባርያ ሳይሆን በነጻነት እንዳለና የአባቱን ደስታና ክብር እንደሚጋራ ልጅ እንድንሆን ይፈልጋል፡፡ ኢያሱም፡-***" እግዚአብሔርንም ማምለክ ክፉ መስሎ ቢታያችሁ....የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ፡፡ "*** 24፡15 ካለ በኋላ አርአያ በመሆንም የእርሱን ምርጫ ***" እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን"*** ብሎ አሳወቀ፡፡ በምላሹም ሕዝቡ፤ ***" እግዚአብሔርን ትተን ሌሎች አማልክትን ማምለክ ከእኛ ይራቅ ..እርሱ አምላካችን ነውና እግዚአብሔርን እናመልካለን"*** ኢያ.24፡16-18 በማለት ምርጫቸውን አሳወቁ፡፡

ዛሬም ቤተ ክርስቲያን አምላኬ ጌታዬ ይህ ነው እናንተም እርሱን ምረጡ ትለናለች፡፡ እግዚአብሔርን ወይም ዓለምን መምረጥ መብታችን ነው፡፡ ሞት እና ሕይወት በነጻ ፈቃዳችን ይመሠረታል፡፡

4. **በመቀደስ ማረጋገጥ፡-** በንግግር እና በተለምዶ ሥርዓት ብቻ ሳይሆን ከልብ የሚወጣ ፍቅራቸውን በፍጹም ፈቃዳቸው እንዲሰጡት ይጠይቃል፡፡ ሕዝቡ በቃል ተናገሩ፣ ኢያሱ ግን ***‹‹ልባችሁን አዘንብሉ››*** ብሎ የልባቸውን ዝንባሌ ጠየቃቸው፡፡ ኢያሱ እግዚአብሔር አምላካችን ነው ያሉትን ከልባቸው ፈቃድ እንደወጣ በስሜት እና በፍርሀት እንዳያዳሉ ለማረጋገጥ፤ ***" እርሱ ቅዱስ አምላክ ነውና፤እርሱም ቀናተኛ አምላክ ነውና እግዚአብሔርን ማምለክ አትችሉም፤..እግዚአብሔርን ማምለክ ትታችሁ ሌሎችን አማልክት ብታመልኩ፤መልካም ካደረገላችሁ በኋላ ተመልሶ ክፉ ክፉ ነገር ያደርግባችኋል ያጠፋችኋልም "*** ኢያ.24፡19 ብሎ እግዚአብሔርን ማመን በቅድስና ኑሮ ከጣዖታት በመለየት እንጂ ሁለቱንም ቀላቅሎ እንዳይደለ አስረዳ፡፡ ሕዝቡም፤ ***‹‹እንዲህ አይሁን፣ ነገር ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን››*** አሉት፡፡

www.zeorthodox.org

እግዚአብሔር ይሻለናል ካልን፣ እግዚአብሔር ቅዱስ ነውና ቅድስና ይፈልጋል፡፡ ***" ቅዱስ ነኝና***

***ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ"*** 1ኛ.ጴጥ.1፡15-16 ዘሌ.19፡2፣ በዳዊት መዝሙርም ***" እርሱ ጻድቅ ነውና ጽድቅን ይወዳል ቅንነት ግን ፊቱን ታየዋለች"*** እንደተባለ መዝ.10(11)፡7 ለመረጥነው እግዚአብጤር የሚመች የቅድስና ኑሮ ያስፈልገናል፡፡

**ምርጫው በቃል ኪዳን ጸና፡-** በሙሉ ልባቸው ፣ በፍጹም ፈቃዳቸው ሊያመልኩት እና ሊያገለግሉት የመረጡትን እግዚአብሔርን ብቻ እንዲከተሉ ምርጫቸውን በቃል ኪዳን አጸኑ፡፡ ***"አምላካችንን እግዚአብሔርን ብቻ እናመልካለን ድምፁንም እንሰማለን "*** ኢያ.24፡24 ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ***ለሐዲስ ኪዳን የሚሆን*** ብሎ የሰጠንን ቅዱስ ***ሥጋውን*** ክቡር ደሙንም በመቀበል ቃል ኪዳናችንን እናጸናለን፡፡ ዕለት ዕለትም ሕይወት የሆነውን የእግዚሐብሔርን ድምፅ ከቅዱሳት መጻሕፍትና ከቤተ ክርስቲያን መስማት እና ማንበብ ይኖርብናል፡፡

**የምስክር ሐውልት፡-** ***"ኢያሱም ይህን ቃል ሁሉ በእግዚአብሔር ሕግ መጽሐፍ ጻፈ፤ታላቁንም ድንጋይ ወስዶ በእግዚአብሔር መቅደስ አጠገብ ከነበረችው ከአድባሩ ዛፍ በታች አቆመው፡፡"*** (ኢያ.24፡26) ይህም እስራኤል ድንጋዩን እያዩ ቃል ኪዳናቸውን እንዲያስታውሱ እና ከአመፃ እንዲመለሱ ነበር፡፡

ያ ድንጋይ በመስቀል የተሰቀለው የክርስቶስ ምሳሌ ነው፡፡ መስቀሉን ስናይ ውለታውን እና የሰጠንን ነጻነት እናስባለን፡፡ያ ድንጋይ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የተገለጡበት ምስጢር የተፈጸመባት የባሕርያችን መመኪያ የድንግል ማርያም ምሳሌ ነው፡፡ በእርሷ ምልጃና ጸሎት በክርስቶስ ቤዛነት ባገኘነው ድኅነት እንጸናለን፡፡

**ወደ ርስት መሄድ፡-** እግዚአብሔርን መርጦ በመቀደስ በመሐላ ከተደረገ ኪዳን በኋላ፡- ***" ኢያሱም እያንዳንዱን ወደ ርስቱ ሰደደ"*** ኢያ.24፡26፡፡ ይህም በወንጌል ጌታችን የገባልንን ቃል ያስታውሰናል፡፡ ***" በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፡፡ ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና ....እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ፡፡"*** (ዮሐ.14፡3) ባለን መሠረት ወደ ርስታችን ሊያገባን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ ይመጣል ፡፡ ያን ጊዜም ***እናንተ የአባቴ ብሩካን፤ኑ፤ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ፡፡*** ማቴ.25፡34 የሚለውን ቃል ለመስማትና ርስታችንን መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ፤ በምድራዊቷ ርስታችን እርሱን ብቻ ማመን ፣ በቅድስና መኖር ፣ በቃል ኪዳኑም መጽናት ይገባናል፡፡

www.zeorthodox.org

## ተግባር፡-

1) የሁል ጊዜ ምርጫችን እግዚአብሔር እና ፈቃዱን መፈጸም ይሁን
2) የቅድስናን ሕይወት ከዝሙት፣ ከስርቆት፣ ከስድብ የተለየ . . . የንጽሕና፣ የደግነት እና የምስጋና ሕይወት በመኖር ጀምሩት፡፡

www.zeorthodox.org

# ቤተ ክርስቲያን በዘመነ ሐዋርያት(፩)

# የቤተ ክርስቲያን ልደት

## ሠላሳ አራተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-**ይህ በተከታታይ የምንማረው *"ቤተ ክርስቲያን በሐዋርያት ዘመን ክፍል አንድ(1) ነው።*

" በዛሬው ትምህርታችንም የቤተ ክርስቲያንን ታሪክን በማጥናት በተለይም ዘመነ ሐዋርያትን እንማራለን።

**የሚጠና ጥቅስ**"*መንግሥተ ሰማያት ሰው ወስዶ በእርሻው የዘራትን የሰናፍጭ ቅንጣት ትመስላለች...*" ማቴ.13፡31

**ትምህርቱ የሚያተኩርባቸው ነጥቦች፡-**

**መግቢያ፡-** የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ለምን እናጠናለን?

ስለ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ስናጠና በምድር ስላለው የእግዚአብሔር መንግሥት ማጥናታችን ነው። የመንግሥቱ አጀማመር መስፋፋቱና የሰው ልጆች ድኅነትም የታሪኩ አካላት ናቸው።

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ***"የሰናፍጭ ቅንጣት"*** ወይም ***"ዳቦን ሁሉ የሚያቦካ እርሾ"*** ተብሎ በጌታችን የተመሰለው ምሳሌ ቀጣይ ክፍልና ማብራሪያ ነው። ***"መንግሥተ ሰማያት ሰው ወስዶ በእርሻው የዘራትን የሰናፈጭ ቅንጣት ትመስላለች። እሷም ከዘር ሁሉ ታንሳለች፤ ባደገች ጊዜ ግን ከአትክልቶች ትበልጣለች የሰማይም ወፎች መጥተው በቅርንጫፏ እስኪሰፍሩ ዛፍ ትሆናለች። ሌላ ምሳሌ ነገራቸው እንዲህም አለ፡- መንግሥተ ሰማያት ሁሉ እስኪቦካ ድረስ ሴት ወስዳ በሦስት መስፈሪያ ዱቄት የሸሸገችውን እርሾ ትመስላለች።"*** ማቴ. 13፣31-33

www.zeorthodox.org

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ የእግዚአብሔርን ኃይል በዲያብሎስና በጭፍሮቹ ላይ ያለውን ድል እንዲሁም የብርሃን መንግሥት ከጨለማው መንግሥት በላይ ያለውን ጥንካሬ የምናይበት ነው። የቤተ ክርስቲያን ታሪክ የተሻለው የክርስትና መገለጫ ነው። የሰው ዘር ሃይማኖታዊ እድገትና የእግዚአብሔርን የማዳን ዕቅድ ያሳየናል።

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ የክርስቲያኖች ብርታትና ጽናት ነው፡፡ ***"እንግዲህ እነዚህን የሚያህሉ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን ካሉልን እኛ ደግሞ ሸክምን ሁሉ ቶሎም የሚከበንን ኃጢአት አስወገድን የእምነታችንንም ራስና ፍጻሜውን ኢየሱስን ተመልክተን በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ"*** ዕብ. 12፡1

## የዘመነ ሐዋርያትን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ የማጥናት ጥቅም፡-

ዘመነ ሐዋርያት ዋናው የቤተ ክርስቲያን ምንጭ እና መሠረት ነው፡፡ ይህ ዘመንም መንፈስ ቅዱስ የሐዋርያትን ሥራ በሙሉ ይመራበት የነበረ ዘመንና ሐዋርያት ከዛ በኋላ ላለው ዘመን ሁሉ የሚሆነውን ሁሉ የሠሩበት ዘመን ነው፡፡

ዘመነ ሐዋርያት የክርስትናን ውጤታማነትና ንጽሕና የሚያሳይ የእምነት ሥዕል ነው፡፡ ይሄም ክርስትና እንደ ሃይማኖት ከሰው ልጆች ሥራ ሁሉ የሚበልጠውን የእግዚአብሔርን ሥራ የሚያረጋግጥልን ነው፡፡

መልካም ምሳሌ የሚሆኑን እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ፣ ቅዱስ ጳውሎስ፣ ቅዱስ ማርቆስና ቅዱስ ዮሐንስ ዓይነት አርኣያዎቻችንን የሚያሳየን ዘመን ነው፡፡

### የዘመነ ሐዋርያት ታሪካዊ ምንጮቻችን

የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በተለይም የሐዋርያት ሥራ ፡፡ የሐዋርያት የትምህርትና የሕግ መጻሕፍት ለምሳሌ፡- መጽሐፈ ዲድስቅልያ

የሐዋርያውያን አበው (የሐዋርያት ተከታይ የነበሩ ናቸው፡፡) ጽሑፎች፡- ለምሳሌ የሮማው ቀሌምንጦስ፣ አግናጥዮስና ፖሊካርፐርስ... የመሳሰሉት

አይሁዳዊ ምንጮች ለምሳሌ፡- የፊሎና ዮሲፉስ ጽሑፎች፣

www.zeorthodox.org

በሁለተኛው ክፍለ ዘመን የነበሩ አበው መጻሕፍት፡፡ ማለትም ሁለተኛው የሐዋርያት ትውልድ የዚህ ምንጭ ምሳሌዎቻችንን ዮስጢኖስ ፣ኢራያዎስ እና ሄጂሲፐስ ናቸው፡፡

**ዘመነ ሐዋርያት ማለት ምን ማለት ነው?** ይህ ዘመን ከ/33/ ዓ.ም እስከ /100/ ዓ.ም ያለው ዘመን ነው፡፡ ይህም መንፈስ ቅዱስ ከወረደበት የጰንጠቆስጤ ዕለት ዮሐንስ እስከ ተሰወረበት ዓመት ማለት ነው፡፡ ዮሐንስ ወንጌላዊ ከሐዋርያት ረጅም ዕድሜ የኖረ ሐዋርያ ነው፡፡

**ቤተ ክርስቲያን በተወለደችበት ዘመን የነበረው ዓለም ፡-**

ይህን ጉዳይ ለመመልከት በሦስት ከፍለን ማየት ይጠበቅብናል:-

**አይሁድ**: በውስጣቸው የነበሩ ክፍሎችን፣ ልማዳቸውን ወ.ዘ.ተ

**አሕዛብ**: ጣዖት ያመልክ የነበረው ዓለም፣

በወቅቱ የነበረው የፖለቲካ ሁኔታ።

## በዚህ ትምህርት ምን አጠናን?

ውድ የሆነችውን የቤተ ክርስቲያናችንን ታሪክ ማጥናት በሚገባ አውቀናት በአግባቡ እንድንኖርባትና እንድንከተላት ይረዳናል። እንዲሁም አዳዲስ የሐሰት ትምህርቶችን እና አሳሳቾችን እንዲሁም ሌሎች የዓለም ፍልፍናዎችንና እምነቶችን እንድንቋቋም ያስችለናል።

ቤተ ክርስቲያናችን ታሪካዊት ናት። በጣም ብዙ ዓመታት ዘልቆ በጽናት የኖረ መሠረት አለን። ወደፊትም በቤተ ክርስቲያን ልጅነታችን ጠንክረን እንድንቀጥል ከቀደመው እውነተኛና ጽኑ መሠረታችን ጋር መገናኘት አለብን።

በዚህች ድንቅና ውድ ቤተ ክርስቲያን እንኮራለን ማለት ብቻ በቂ አይደለም። ዋናው መስመር በእውነት እና በፍቅር ውስጥ ነን? ይህንስ በድርጊቶቻችን ለሌላው እንገልጻለን? ብሎ ራስን መጠየቅና መመርመር ይገባል።

www.zeorthodox.org

# ቤተ ክርስቲያን በዘመነ ሐዋርያት (፪) -

# ልደተ ቤተክርስቲያን (፪)

## ሠላሳ አምስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ** ፡-ክርስቶስ በዚህ ምድር በተመላለሰበት እና ሐዋርያት ባስተማሩበት ዘመን የነበረውን የአይሁድ ክፍሎች ማመላከት፡፡

**የሚጠና ጥቅስ** ፡- ***"ወዮላችሁ እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን"*** *ሉቃ*.11፡43-44

**መግቢያ፡-** ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን ስለ ቤተ ክርስቲያን የልደት ዘመን ስናጠና ስለ አይሁድ አሕዛብ እና የሮም መንግሥት ማወቅ እንደሚያስፈልገን ተምረን ነበር፡፡

ቀጣዩን እንደሚከተለው እናያለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

*ሀ. አይሁድ*

1.**ፖለቲካዊ ሁኔታቸው** በሮማውያን በ/63/ ዓ.ዓ (ቅ.ል.ክ) በቅኝ ግዛት ከተያዙ በኋላ ፤ ፓለቲካዊ አመራሩ በሮማውያን በሚሾምላቸው አስተዳዳሪዎች አገዛዝ ሥር ነበር፡፡

2.**ኢኮኖሚያዊ ሁኔታቸው**፡፡ አብዛኛዎቹ አይሁድ በአስከፊ ድህነት ሥር ሲሆኑ የተሻሉ የሚባሉት ሰዱቃውያን ነበሩ፡፡

www.zeorthodox.org

3.**ሃይማኖታዊ ሁኔታቸው** በሙሴ ሕግ የተጣበቁ ቢመስሉም መንፈሱን አልተረዱትም፡፡

4.**ምኩራብ** አይሁድ የአይሁድ ማኅበራዊ እና ሃይማኖታዊ ማዕከላት ነበሩ፡፡ እያንዳንዱ ከተማ የራሱ ምኩራብ ነበረው፡፡ ምኩራቡ በከፍተኛ ቦታዎች ሲቀመጥ፣ የመንጻትን ሥርዓት ለመፈጸም በወንዝ አጠገብ ወይም በባሕር ዳርቻ ይሠራ ነበር፡፡ በኢየሩሳሌም ብቻ ለተለያዩ የአይሁድ ክፍሎች የተዘጋጁ አራት መቶ የሚደርሱ ምኩራባት ነበሩ፡፡ እያንዳንዱ ምኩራብ አለቃ ነበረው፡፡ ***"ለምኩራቡ አለቃ እመን እንጂ አትፍራ አለው"*** (ማር.5፡36) ብዙ ሽማግሌዎች፣ አንባቢዎች እና መተርጉማነ

አይሁድም ነበሩ። ከእነርሱም ውጪ የእጅ ሥራ የሚሠሩ፣ገንዘብ የሚሰበስቡና ድሆችን የሚረዱም ነበሩ። የምኵራብ ሥርዓተ አምልኮ በጣም ረጅም ነበር። መዝሙራት ፣ ብሉይ ኪዳን ምንባባት እና ማብራርያዎችን ያካትታል። የደም መሥዋዕት ግን በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ብቻ ይቀርብ ነበር።ይህም ከክርስቶስ ስቅለት በኋላ በሐዲስ መሥዋዕት የተተካ ሲሆን ፤ ቤተ መቅደሱ በሮማውያን ሲፈርስ ሙሉ በሙሉ ቀርቶአል።

5. **የተለያዩ የአይሁድ ቡድኖች** ክርስትና በምድረ እስራኤል ሲወለድ አይሁድ በተለያዩ ቡድኖች ተከፋፍለው ተቀብለውታል። በዋናነትም ሦስት ዋና ዋና ቡድኖች ነበሩ። እነርሱም ፈሪሳውያን፣ ሰዱቃውያን እና ኤስያውያን ነበሩ።

**ፈሪሳውያን፦**

ምርጦች ወይም የተለዩ ማለት ነው። የሙሴን ሕግ እንጠብቃለን የሚሉና በወጋቸውም ተይዘው አጥባቂ ሆነው የሚኖሩ ናቸው። ከዚህ ውጪ የሆኑትን ሁሉ ይንቁ ነበር። (ሉቃ.18፡9-14) መሲሕ በጦር ኃይል ከሮም አገዛዝ ያድነናል፤ብለው ይጠብቁ ነበር።

ጸሐፍትም ብዙ ጊዜ ከፈሪሳውያን ጋር አብረው ይጠራሉ ። (ማቴ.23፡2 ሉቃ.11፡44) ጸሐፍት ለብቻቸው እንደ አንድ ቡድን አይቆጠሩም፤ የፈሪሳውያን ንኡስ ክፍሎች ሆነው መጻሕፍትን የሚተረጉሙ ናቸው። ጸሐፍት እንደ ቡድን የሚቆጠሩት ከዕዝራ ዘመን ጀምሮ ነው ፤(1ኛዜና መዋዕል 2፡55) በሕዝቡም ዘንድ በጣም የተከበሩ ነበሩ።

**ሰዱቃውያን ፦**

ክርስቶስ በሥጋ በተመላለሰበት ዘመን በነበረው የአይሁድ ማኅበረሰብ ውስጥ በበላይነት ሆነው፤ ከምክራቦች ግብር የሚቀበሉና የባለጠጎች ቡድን ነበሩ። ለእስራኤላዊ ወግ እና ባሕል ግድየለሾች ሲሆኑ ከፈሪሳውያን ጋር የማይግባቡ ከሮማውያን ጋር የጠበቀ ግንኙነትም ያላቸው ነበሩ። ለዓለማዊ ክብር እና ብልጥግና ትኩረት የሚሰጡ ሲሆኑ ትንሣኤ ሙታን ፤ መናፍስት እና መላእክትም የሉም ብለው ያምኑ ነበር።የሐዋ.23፡1-9

www.zeorthodox.org

**ኤስያውያን፦**

በመጽሐፍ ቅዱስ አልተገለጡም፤ ክርስቶስ በሥጋ በተመላለሰበት ዘመን ነበሩ፤ በታሪክም በስፋት እናገኛቸዋለን። በቁምራን ዋሻ የተባሕትዎ ኑሮ ያዘወትሩ ነበር። የሙሴን ሕግ ቢቀበሉም

እንደ ሰዱቃውያን ቃል በቃል ሳይሆን በመንፈሳዊ ትርጓሜ ያምኑ ነበር፡፡ ራሳቸውን ***"የእግዚአብሔር ጉባኤ"*** *ወይም* ***"የቋሚው ኪዳን ቡድኖች"*** ብለው ይጠሩ ነበር፡፡ መሲሕ በተአምራት ከሮም አገዛዝ ያድነናል፤ ብለው ተስፋ ያደርጉም ነበር፡፡

**የአይሁድ ጉባኤ (ሰን ሀድሪን)፡-**

የአይሁድ ከፍተኛው ጉባኤ ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እና ሐዋርያት በዚህ ጉባኤ ፊት ተፈርደባቸዋል፡፡ ከሰባ እስከ ሰባሁለት የሚደርሱ አክራሪ አባላት ያሉት ጉባኤ ነበር፡፡ ከሦስት ቡድን የተውጣጡም ነበሩ፡፡ እነርሱም፡-

1. ካህናት፤ ሃያ አራት ሲሆኑ መሥዋዕቱን የሚመሩ ናቸው፡፡
2. ሽማግሌዎች (የነገድ አባቶች)፡፡
3. ጸሐፍት የፈሪሳውያን መሪዎች ናቸው፡፡ ይህ ጉባኤ በመሠዊያው ይደረግ ነበር፡፡

## ተግባር

አይሁድ በጌታችን ማመን አልቻሉም፡፡ ምክንያቱም ከልብ የሆነ አምልኮተ እግዚአብሔር ስላልነበራቸው ነው፡፡ እኛም አምልኮታችን ከልብ መሆን አለበት፡፡

አይሁድ የተሳሳተ ተስፋ ይዘው ነበር፡፡ እኛ ከክርስቶስ እውነተኛ ተስፋ ጋር እንኑር፡፡

www.zeorthodox.org

# ቤተ ክርስቲያን በዘመነ ሐዋርያት (፫) -

# ልደተ ቤተ ክርስቲያን (፫)

## ሠላሳ ስድስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓለማ** ይህ ትምህርት ስለ ዘመነ ሐዋርያት የቤተ ክርስቲያን ታሪክ የምንማረው ተከታታይ ትምህርት አካል ነው፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም ቤተ ክርስቲያን ስትወለድ የነበረውን የዓለም ሁኔታ እናያለን፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፦** ***"ይህ ለፍላፊ ምን ሊናገር ይወዳል……"*** የሐዋ. 17፡18

***መግቢያ፦*** ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን ክርስቶስ በሥጋ በተገለጠበት ዘመን ስለ ነበረው የአይሁድ ሁኔታ ተምረናል፡፡ በዚህ ትምህርት ስለ አሕዛብ የሮም መንግሥት እንነጋገራለን፡፡

### የሳምንቱ ትምህርት፦

**አሕዛብ፦**

እነዚህ ጣዖታትን የማያመልኩ እና ስለ እግዚአብሔር፣ ስለ ኃጢአት ወይም ስለ ቅድስና ትኩረት የሌላቸው የዓለም ክፍሎች ነበሩ፡፡

**የአሕዛብ ፍልስፍና** በክርስትና የመጀመሪያ ዘመን ከነበሩት ታዋቂ የፍልስፍና ትምህርት ቤቶች አፊቆሮስና አስጢኢኮች ነበሩ፡፡ ***"ከኤፊቆሮስ ወገንና ኢስጦኢኮችም ከተባሉት ፈላስፎች አንዳንዶች ከእርሱ ጋር ተገናኙ "*** (የሐዋ. 17፡18)

www.zeorthodox.org

**የኤፊቆሮሶች ፍልስፍና፦** ሁሉንም ሃይማኖቶች የሚቃወሙና በማንኛውም ሃይማኖት ያለ እምነት ኃጢአት ነው ብለው ያስባሉ፡፡

በሰማይ፣ መለኮታዊ ኃይልና መሪ የለም ባዮች ሲሆኑ አምላካቸው በአንድ በማይታወቅ ቦታ ራሱን አግልሎ የሚኖርና ስለ እነርሱም ሕይወት የማያስብ እንደሆነ ያምናሉ፡፡ ብዙ ሮማውያን በኢፊቆሮስ ፍልስፍና ያምኑ ነበር፡፡

**የኢስጦኢኮች ፍልስፍና፦** በአንድ እግዚአብሔር ያምናሉ፤ሁሉም ነገሮች ከአንድ መንፈስ

ይወጣሉ እናም እያንዳንዱ ሰው ከእግዚአብሔር የሚወጣና የባሕርዩ ክፋይ የሆነ ጨረር ነው ይላሉ። ሰው ይህን ጨረር ሊጠብቀውና ለመልካም ነገሮችም ሊያውለው ይችላል ብለው ያምናሉ። ከዚህም የተነሣ የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር የተሰጠው ልዩ ስጦታ አእምሮ ነው ብለው ያምናሉ። የአሕዛብ ጠባይ አሕዛብ የነበሩበትን የተመሰቃቀለ ኑሮ በጥሩ ሁኔታ የሚያስረዳን በሮሜ.1፣18-32 የተጻፈው ነው። *እውነትን በዓመፃ በሚከለክሉ ሰዎች በኃጢአታቸውና በዓመፃቸው ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ከሰማይ ይገለጣልና እግዚአብሔር ስለ ገለጠላቸው ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው በእነርሱ ዘንድ ግልጥ ነውና ። የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና ፤ስለዚህም እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩትና ስላላመሰገኑት የሚያመካኙት አጡ ፤ ነገር ግን በአሳባቸው ከንቱ ሆኑ የማያስተውለውም ልባቸው ጨለመ። ጥበበኞች ነን ሲሉ ደንቆሮ ሆኑ፣ የማይጠፋውንም የእግዚአብሔርን ክብር በሚጠፋ ሰውና በወፎች አራት እግር ባላቸውም በሚንቀሳቀሱትም መልክ መስለው ለወጡ።*

*ስለዚህ እርስ በርሳቸው ሥጋቸውን ሊያዋርዱ እግዚአብሔር በልባቸው ፍትወት ወደ ርኩስነት አሳልፎ ሰጣቸው። ይህም የእግዚአብሔርን እውነት በውሸት ስለ ለወጡ በፈጣሪም ፈንታ የተፈጠረውን ስላመለኩና ስላገለገሉ ነው፣ እርሱም ለዘላለም የተባረከ ነው አሜን።*

*ስለዚህ እግዚአብሔር ለሚያስነውር ምኞት አሳልፎ ሰጣቸው። ሴቶቻቸውም ለባሕርያቸው የሚገባውን ሥራ ለባሕርያቸው በማይገባው ለወጡ። እንዲሁም ወንዶች ደግሞ ለባሕርያቸው የሚገባውን ሴቶችን መገናኘት ትተው እርስ በርሳቸው በፍትወታቸው ተቃጠሉ። ወንዶችም በወንዶች ነውር አድርገው በስሕተታቸው የሚገባውን ብድራት በራሳቸው ተቀበሉ።*

*እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን እግዚአብሔር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይገባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው፤ ዓመፃ ሁሉ፣ ግፍ፣ መመኘት፣ ክፋት፣ ምላባቸው፤ ቅናትን ፣ ነፍስ መግደልን ፣ ክርክርን ፣ ተንኮልን ፣ ክፉ ጠባይን ተሞሉ። የሚያሾከሹኩ፣ ሐሜተኞች፣ አምላክን የሚጠሉ፣ የሚያንገላቱ፣ ትዕቢተኞች፣ ትምክሕተኞች፣ ክፋትን የሚፈላለጉ፣ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፣ የማያስተውሉ፣ ውል የሚያፈርሱ፣ ፍቅር የሌላቸው፣ ምሕረት ያጡ ናቸው። እንደዚህ ለሚያደርጉት ሞት ይገባቸዋል የሚለውን የእግዚአብሔርን ሕግ እያወቁ እነዚህን ከሚያደርጉ ጋር ይስማማሉ እንጂ አድራጊዎች ብቻ አይደሉም።*

www.zeorthodox.org

**ሐ.የሮም መንግሥት**፡- የአይሁድ ከተሞችና ሀገር ጠንካራና የተደራጀ በነበረው በሮማውያን አገዛዝ ሥልጣን ሥር ነበር፡፡

**ስፋቱ**፡- የአውሮፓ፣ የእስያ እና የተወሰነ የአፍሪካ ምድርንም ያጠቃልል ነበር፡፡

**የሮም መንግሥት አወቃቀር**፡- በተለያዩ ግዛቶች የተዋቀረ፣ለሁሉም ግዛቶች ከዋናው የመገናኛ ከተማ ከሮም የተወከለ ሀገረ ገዥ ነበረው፡፡ እነዚህም ግዛቶች በሮም ሕግና የግብር ሥርዓት ይመሩ ነበር፡፡

ይህ የዚያን ዘመን ሕግ ሲሆን፣ በቅኝ ግዛት የተያዘና የተሸነፈ ሀገር ነዋሪዎች በቋሚነት ለሮም መንግሥት ግብር እየገበሩ ይኖሩ ነበር፡፡ ለዚህም ነው ሮማውያን ሕዝቡን በቋሚነት የሚቆጥሩት፡፡ **‹‹በዚያም ወራት ዓለሙ ሁሉ እንዲጻፍ ከአውግስጦስ ቄሣር ትእዛዝ ወጣች፤ ቄሬኔዎስ በሶርያ አገረ ገዥ በነበረ ጊዜ ይህ የመጀመሪያ ጽሕፈት ሆነ፡፡››** ሉቃ. 2፡1

**የሮም ዜግነት ያላቸው ሰዎች መብቶች** ፡- በሮም ግዛት የሮም ዜግነት ያላቸው ልዩ ክብር ነበራቸው፡፡

**"የሮም ዜግነት"** መብቶች የሚሰጣቸው ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ ነበር፡፡ ዜግነቱን የሚያገኙት በመግዛት፣ በሮም ሠራዊት ውስጥ ወታደራዊ አገልግሎት በመስጠት ወይም በሮም ግዛት በመወለድ ነበር፡፡

**የሚያገኙት ጥቅምም**፤ የሕግ ጥበቃ፣ ሳይከሰሱ አለመታሰር፣በሮም ከተማ የመዳኘት መብት ናቸው፡፡ ***" ስለዚህም ሊመረምሩት ያሰቡት ከእርሱ ወዲያው ተለዩ፤ የሻለቃውም ደግሞ ሮማዊ መሆኑን ባወቀ ጊዜ ፈራ አሳስሮት ነበርና፡፡"*** (የሐዋ. 22፡29) ***" ጳውሎስ ግን እኛ የሮሜ ሰዎች ስንሆን ያለ ፍርድ በሕዝብ ፊት ደብድበው በወኅኒ ጣሉን አሁንም በስውር ይጥሉናልን? አሁንም ራሳቸው ግን መጥተው ያውጡን አላቸው ፡፡*** " (የሐዋ. 16፡37)

***" እንግዲህ በድዬ ወይም ሞት የሚገባውን ነገር አድርጌ እንደ ሆነ ከሞት ልዳን አልልም፤ እነዚህ የሚከሱኝ ክስ ከንቱ እንደ ሆነ ለእነርሱ አሳልፎ ይሰጠኝ ዘንድ ማንም አይችልም፤ ወደ ቄሣር ይግባኝ ብዬአለሁ አለ፡፡*** " (የሐዋ. 25፡17)

www.zeorthodox.org

**ከዚህ ምን እንማራለን ?**

ክርስትና በመጀመሪያ የገጠመው ፈተና ከሦስት ክፍሎች ነበር፡፡ ከአይሁድ፣ ከአሕዛብና ከሮም መንግሥት፤ ይህን ማወቅም መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት ያግዘናል፡፡

ክርስትና በጣም ጠንካራና የተደራጀ የተቃውሞ ኃይል አጋጥሞታል፡፡ ነገር ግን

የእግዚአብሔር ኃይል ከዚህ ይልቅ ጠንካራ ነውና እነዚህን አሸንፎ በፍጥነት ተስፋፍቶአል።

ክርስትና እነዚህን ኃይሎች ያሸነፈው በጸብና በዓመጽ አልነበረም። የሕዝቡን እምነትና የእግዚአብሔርን መንግሥት እየገነባ እንጂ። ስለዚህ ክፉን በመቃወም፣ ጨለማን ከመርገም ሻማ ማብራት፤ የሚለውን አባባል ያስታውሰናል።

በዛሬው ማኅበረሰብም በርካታ የተዛቡ ነገሮች አሉ። የክርስትናው መንገድም እነዚህን መድገም ሳይሆን በማረም መልካም አስተሳሰቦችን ማስፋፋት ነው።

www.zeorthodox.org

**ቤተ ክርስቲያን በዘመነ ሐዋርያት (፬) - የአይሁድ ተቃውሞ**

**ሠላሳ ሰባተኛ ሳምንት**

**የትምህርቱ ዓላማ፡** ስለ ዘመነ ሐዋርያት የምንማረው ተከታታይ ትምህርት ቀጣይ ክፍል ነው፡፡

***መግቢያ፡-*** በዛሬው ትምህርት ቤተ ክርስቲያን ከአይሁድ ስለገጠማት ተቃውሞ እንማራለን፡፡ ክርስትና በሰማዕትነት ፣ በፍቅርና በተአምራት ተስፋፍቶል፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-*" የሚያምኑትም ከፊት ይልቅ ለጌታ ይጨምሩለት ነበር፡፡"*** የሐዋ. 5፡14

**የትምህርቱ ትኩረት ባለፉት ሁለት ሳምንታት የተማራችሁትን ከልሱ፡፡**

**(ሀ)በኢየሩሳሌም የነበረችው ቤተ ክርስቲያን፡-**

ቤተ ክርስቲያን የተወለደችው በበዓለ ሃምሳ በኢየሩሳሌም ነው:: ከበዓለ ሃምሳ በኋላም በክርስቶስ ያመኑት ወደየሀገራቸው ተመልሰው ክርስትናን አስፋፉ፡፡

የእግዚአብሔር መንፈስ በሐዋርያት አድሮ ይሠራ ነበርና የአማኞች ቁጥር በየቀኑ ይጨምር ነበር፡፡ በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ብቻ የአማኞች ብዛት እስከ አምስት ሺሕ ደረሰ፡፡ ***"ነገር ግን ቃሉን ከሰሙት ብዙዎች አመኑ፡፡ የወንዶችም ቁጥር አምስት ሺሕ ያህል ሆነ፡፡"*** (የሐዋ.4፡4)

**በየጊዜው የአማንያን ብዛት እየጨመረ የመምጣቱ ምክንያት፡-** በሚፈጸሙት ተአምራት እንዲሁም በፍቅርና በጽድቅ የተሞላውን የክርስቲያኖችን ሕይወት በማየት ነበር፡፡***"ሕዝቡ ግን ያከብሩዋቸው ነበር፡፡ የሚያምኑትም ከፊት ይልቅ ለጌታ ይጨመሩለት ነበር፡፡"*** (የሐዋ. 5፡14) (የሐዋ. 6 እና 7) ***"እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ በሕዝቡ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው፡፡ ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር፡፡"*** (የሐዋ.2፡47) በዚህ ምክንያትም አይሁድ በቅናት በክርስቲያኖች ላይ ተነሡ፡፡

www.zeorthodox.org

**ክርስቲያኖች ከአይሁድ የደረሰባቸው እንግልት፡-**

አይሁድ በክርስቶስ በተከታዮቹ በሐዋርያት እና በክርስቲያኖች ላይ የነበራቸውን ተቃውሞ ወንጌል በግልጥ አሳይቶናል፡፡ አይሁድ ሰዎች ክርስቶስን ሲከተሉ ሲያዩ በቅናት ተነሣሥተው ***"ግደለው፣ ስቀለው"*** ይሉ ነበር፡፡***"የካህናት አለቆችና ሽማግሎች ግን በርባንን እንዲለምኑ ኢየሱሱን ግን እንዲያጠፉ ሕዝቡን አባባሉ፡፡"*** (ማቴ. 27፡20)

ቅዱስ እስጢፋኖስን ጠልተው በድንጋይ ሲወግሩትም፤ "የነጻ ወጪዎች ከተባለችው ምኵራብም ከቀሬናና ከእስክንድርያም ሰዎች ከኪልቅያና ከእስያም ከነበሩት አንዳንዶቹ ተነሥተው እስጢፋኖስን ይከራከሩት ነበር፤ ይናገርበት የነበረውንም ጥበብና መንፈስ ይቃወሙ ዘንድ አልቻሉም። በዚያን ጊዜ፦ በሙሴ ላይ በእግዚአብሔርም ላይ የስድብን ነገር ሲናገር ሰምተነዋል የሚሉ ሰዎችን አስነሡ። ሕዝቡንና ሽማግሌዎችንም ጻፎችንም አናደዱ፤ ቀርበውም ያዙት፤ ወደ ሸንጎም አመጡትና፦ ይህ ሰው በዚህ በተቀደሰው ሥፍራ በሕግም ላይ የስድብን ነገር ለመናገር አይተውም፤ ይህ የናዝሬቱ ኢየሱስ ይህን ሥፍራ ያፈርሰዋል፤ ሙሴም ያስተላለፈልንን ሥርዓት ይለውጣል ሲል ሰምተነዋልና የሚሉ የሐሰት ምስክሮችን አቆሙ።›› (የሐዋ.6፡9-14)

በቅዱስ ጳውሎስ ላይ ያደረጉትንም ተቃውሞ በሐዋርያት ሥራ ላይ በተለያዩ ክፍሎች እናነባለን።‹‹ብዙ ቀንም ሲሞላ አይሁድ ሊገድሉት ተማከሩ፤ ሳውል ግን አሳባቸውን አወቀ። ይገድሉትም ዘንድ በሌሊትና በቀን የከተማይቱን በር ሁሉ ይጠብቁ ነበር›› /የሐዋ.ሥ.9 23-25/ ‹‹አይሁድ ግን የሚያመልኩትን የከበሩትንም ሴቶችና የከተማውን መኳንንት አወኩ፤ በጳውሎስና በበርናባስም ላይ ስደትን አስነሥተው ከአገራቸው አወጡአቸው።›› /የሐዋ.ሥ.13 50/፤ ‹‹ከወደ ኢያሶን ቤት ቀረቡ፤ ባላገኙአቸውም ጊዜ ኢያሶንንና ከወንድሞች አንዳንዶችን ወደ ከተማው አለቆች ጎትተው፦ ዓለሙን ያወኩ እነዚህ ወደዚህ ደግሞ መጥተዋል። ኢያሶንም ተቀብሏቸዋል፤ እነዚህም ሁሉ፦ ኢየሱስ የሚሉት ሌላ ንጉሥ አለ እያሉ የቄሣርን ትእዛዝ ይቃወማሉ ብለው ጮኹ። ሕዝቡና የከተማውም አለቆች ይህን ነገር በሰሙ ጊዜ ታወኩ።›› /የሐዋ.ሥ.17 6-8/፤‹‹የከተማውም ሕዝብ ተከፍለው እኩሌቶቹ ከአይሁድ እኩሌቶቹም ከሐዋርያት ጋር ሆኑ። አሕዛብና አይሁድ ግን ከአለቆቻቸው ጋር ሊያንገላቱአቸውና ሊወግሩአቸው ባሰቡ ጊዜ፤ አውቀው ልስጥራንና ደርቤን ወደሚባሉት ወደ ሊቃኦንያ ከተማዎች በእነርሱም ዙሪያ ወዳለው አገር ሸሹ›› /የሐዋ.ሥ.14 4-6/፤ ‹‹ይህንም ብለው እንዳይሠውላቸው ሕዝቡን በጭንቅ አስተውአቸው። አይሁድ ግን ከአንጾኪያና ከኢቆንዮን መጡ፤ ሕዝቡንም አባብለው ጳውሎስን ወገሩ የሞተም መስሎአቸው ከከተማ ወደ ውጭ ጎተቱት›› /የሐዋ.ሥ.14 18-19/።

www.zeorthodox.org

ቅዱስ ጳውሎስም ከአይሁድ ብዙ መከራ እንደተቀበለ እንዲህ ሲል ገልጾልናል፦‹‹*እነዚያም ጌታ ኢየሱስን ደግሞ ገደሉ፤ ነቢያትንም እኛንም አሳደዱ፤ እግዚአብሔርንም ደስ አያሰኙም፤ ሰዎችንም ሁሉ ይቃወማሉ፤ ሁልጊዜም ኃጢአታቸውን ይፈጽሙ ዘንድ አሕዛብ እንዲድኑና እንዳንናገራቸው ይከለክሉናልና። ነገር ግን ቁጣው ወደ እነርሱ ፈጽሞ ደርሶአል።››/1ኛ ተሰሎ.2 15-16/*

ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብም ከሐዋርያት ቀድሞ በሰማዕትነት አርፎአል።‹‹በዚያን ዘመን ንጉሡ

ሄሮድስ መከራ ያጸናባቸው ዘንድ ከቤተ ክርስቲያኑ በአንዳንዶቹ ላይ እጁን ጫነባቸው፡፡ የዮሐንስንም ወንድም ያዕቆብን በሰይፍ ገደለው፡፡›› /የሐዋ.ሥ. 12 1-2/ ከዚያም ቅዱስ ጴጥሮስ ታሠረ፡፡

በሐዋ.ሥ.12 የቤተ ክርስቲያንን መንፈስና አዲስ ልደት ስናነብ መንፈሳዊ እሴቶችንም እናገኛለን፡፡

### የመከራ ፍሬዎች:-

ስደቱ እስከተነሣበት ጊዜ ሐዋርያት በሙሉ ኃይላቸው ተሰባስበው ያስተማሩት በኢየሩሳሌም ነበር፡፡ ከዚያም ከኢየሩሳሌም የተሰደዱ ክርስቲያኖች በተለያዩ ከተሞች የእግዚአብሔርን ቃል አደረሱ፡፡ ‹‹የተበተኑትም ቃሉን እየሰበኩ ዞሩ፡፡›› /የሐዋ. 8፡4/

ቅዱስ ጳውሎስም፤ ‹‹ ይህንም ደግሞ በኢየሩሳሌም አደረግሁት፤ ከካህናት አለቆችም ሥልጣን ተቀብዬ እኔ ከቅዱሳን ብዙዎችን በወኅኒ አሳሰርኋቸው፤ ሲገድሉአቸውም አብሬ ተቸሁ፡፡ በምኩራብም ሁሉ ብዙ ጊዜ እየቀጣሁ ይሰድቡት ዘንድ ግድ አልኋቸው ያለልክ ስቆጣባቸውም እስከ ውጭ አገር ከተማዎች ድረስ እንኳ አሳድድ ነበር፡፡›› (የሐዋ.26፡10-11) ብሎአል፡፡ መከራና ስደቱም ቃለ ወንጌል በተለያዩ ከተሞች እንዲዳረስና ክርስትና ከጥንካሬ ጋር እንዲስፋፋ አደረገ ፡፡

### ስብከተ ወንጌል በሰማርያ:-

ሰማርያ ሙሉ በሙሉ ጣዖት የሚመለክባት አልነበረችም፡፡ ስለ ሰማርያ (በ2ኛ.ነገሥ.17፡24-34) አንብቡ

ክርስትና በሰማርያ ከተሞች መሰበክ ነበረበት፡፡ ይህም በሐዋርያት እና ሰማርያውያንን ይጠሉ በነበሩት አይሁድ ዘንድ ጠላትነትን ለረጅም ጊዜ እንዲሰፍን አደረገ፡፡

መጀመሪያ ወንጌልን በሰማርያ ከተሞች የሰበከው ከሰባቱ ዲቆናት አንዱ የሆነው ፊልጶስ ነው:: ጌታችንም በብዙ ተአምራት አገልግሎታቸውን ያጸና ነበር፡፡ ‹‹ ***ፊልጶስም ወደ ሰማርያ ከተማ ወርዶ ክርስቶስን ሰበከላቸው፡፡ ሕዝቡም የፊልጶስን ቃል በሰሙ ጊዜ ያደርጉት የነበረውንም ምልክት ባዩ ጊዜ፤ የተናገረውን በአንድ ልብ አደመጡ፡፡ ርኩሳን መናፍስት በታላቅ ድምፅ እየጮኹ ከብዙ ሰዎች ይወጡ ነበርና ብዙም ሽባዎችና አንካሶች ተፈወሱ፤ በዚያችም ከተማ ታላቅ ደስታ ሆነ፡፡››*** (የሐዋ.8፡5-8)

www.zeorthodox.org

ከዚያም ቅዱስ ጴጥሮስ እና ቅዱስ ዮሐንስ በሰማርያ አስተማሩ፤ ***"በኢየሩሳሌም የነበሩት ሐዋርያት የሰማርያ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንደተቀበሉ ሰምተው ጴጥሮስንና ዮሐንስን ሰደዱላቸው፡፡ እነርሱም በወረዱ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ ጸለዩላቸው፤ በጌታ በኢየሱስ***

*ስም ብቻ ተጠምቀው ነበር እንጂ ከእነርሱ በአንዱ ላይ ስንኳ ገና አልወረደም ነበርና፡፡ በዚያን ጊዜ እጃቸውን ጫኑባቸው መንፈስ ቅዱስንም ተቀበሉ፡፡›› (የሐዋ. 8፡15-17) ‹‹እነርሱም መሰከሩና የጌታን ቃል ከተናገሩ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፤ በሳምራውያን በብዙ መንደሮችም ወንጌልን ሰበኩ፡፡›› (የሐዋ.8፡25) በሐዋርያው ፊልጶስ ለኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የተሰበከለትን ታሪክ፤ ከሐዋ. 8፡26-40 አንብቡ፡፡

## ክርስቶስ በባሕር ዳርቻዎች ባሉ ከተሞችም ተሰበከ

ፊልጶስ ወደ ፍልስጤም ከተሞችና በባሕር ዳርቻዎች ሄዶ አስተማረ፡፡ ‹‹ ከውኃውም ከወጡ በኋላ የጌታ መንፈስ ፊልጶስን ነጠቀው፤ ጃንደረባውም ሁለተኛ አላየውም፤ ደስ ብሎት መንገዱን ይሄድ ነበርና፡፡ ፊልጶስ ግን በአዛጦን ተገኘ፤ ወደ ቂሣርያም እስኪመጣ ድረስ እየዞረ በከተማዎች ሁሉ ወንጌልን ይሰብክ ነበር፡፡›› (የሐዋ.8፡39-40)

## ስብከተ ወንጌል በገሊላ

ክርስትና በገሊላ ቀድሞ ተሰብኮ ነበር፡፡‹‹በይሁዳም ሁሉና በገሊላ በሰማርያም የነበሩት አብያተ ክርስቲያናት በሰላም ኖሩ ታነጹም፤ በእግዚብሔርም ፍርሃትና በመንፈስ ቅዱስ መጽናናት እየሄዱ ይበዙ ነበር፡፡ (የሐዋ.ሥ. 9፡31)

ቅዱስ ጳውሎስ በ37 ዓ.ም ክርስቲያን ሆነ:: (የሐዋ. 9፡1-6) አንብቡ::

## ምን ተማርን?

የክርስቶስ ብርሃን የዲያበሎስን ጨለማ አጥፍቶአል፡፡ ለዚህም ነው ክርስትና የሚቃወሙትን ኃይሎች በሙሉ አሸንፎ በዓለም የተሠራጨው፡፡

በተመሳሳይም የኃጢአትን ጨለማ ለማጥፋት ከፈለግን የክርስቶስ ብርሃን በልባችን አንጸባርቆ የኃጢአት ጨለማ ሊርቅ ይገባል፡፡

www.zeorthodox.org

# ቤተ ክርስቲያን በዘመነ ሐዋርያት (፯) -

# ሥርዓተ አምልኮ በሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን

## ሠላሳ ስምንተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ይህ በተከታታይ የምንማረው የዘመነ ሐዋርያት የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሰባተኛና የመጨረሻ ክፍል ሲሆን፤ ዓላማውም በዚያን ዘመን ስለነበረው ሥርዓተ አምልኮ ማስገንዘብ ነው፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-**

***"በእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት መኖር እንዴት እንደሚገባ ታውቅ ዘንድ እጽፍልሃለሁ፤ "***
1ኛ ጢሞ 3፣ 15

**የትምህርቱ ትኩረት፡-**

### መግቢያ ፡-

በተከታታይ የተማርነውን ከልሱ፡፡ ስለ ሥርዓተ አምልኮ ከመነጋገራችን በፊት ቤተ ክርስቲያን ለአማንያን ለምን እንደሚጠቅማቸው እናያለን፡፡

ቤተ ክርስቲያን በሐዋርያት ትምህርትና ሐሳብ የእግዚአብሔር ቤት ናት፡፡ ***"ነገር ግን ብዘገይ በእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት መኖር እንዴት እንደሚገባ ታውቅ ዘንድ እጽፍልሃለሁ፤ቤቱም የእውነት ዓምድና መሠረት የሕያው እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ነው፡፡"*** (1ኛ ጢሞ. 3፣15) ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ሙሽራ ናት፡፡

www.zeorthodox.org

በቤተ ክርስቲያን በሚፈጸሙ ምስጢራት በረከትና ጸጋ እናገኛለን፤ በዘመነ ሐዋርያት የነበረችው ቤተ ክስቲያንም ለምስጢራት ጥቅም ትኩረት ነበራት፡፡ በሐዋርያት ሥራ ምዕ. 9 እና 10 የተጠቀሰውን የሳውልንና የቆርኔሌዎስን ጥምቀት ታሪክ አንብቡ፡፡

### የጌታ ዕለት - እሑድ

ጌታችን ከሙታን ተለይቶ የተነሣባት ስለሆነች የጌታ ቀን ትባላለች፡፡ እሑድ አይሁድ

የሚያከብርዋትን ቅዳሜ ተክታለች።

በመጽሐፍ ቅዱስ እሑድ ክርስቲያኖች ተሰባስበው ቅዱስ ቍርባን የሚቀበሉባት መሆኑ ተገልጾዋል። "ከስምንት ቀን በኋላም ደቀ መዛሙርቱ ደግመው በውስጥ ነበሩ፤ ቶማስም ከእነርሱ ጋር ነበረ። ደጆች ተዘግተው ሳሉ ኢየሱስ መጣ፣ በመካከላቸውም ቆሞ፡- ‹‹ሰላም ለእናንተ ይሁን›› አላቸው። (ዮሐ 20፣26) "ከሳምንቱም በመጀመሪያ ቀን እንጀራ ለመቁረስ ተሰብስበን ሳለን÷ ጳውሎስ በነገው ሊሄድ ስላሰበ ከእነርሱ ጋር ይነጋገር ነበር÷እስከ መንፈቀ ሌሊትም ነገሩን አስረዘመ።"(ሐዋ.ሥራ 20÷7) "እኔ ስመጣ ይህ የገንዘብ ማዋጣት ያን ጊዜ እንዳይሆን፣ ከእናንተ እያንዳንዱ በየሳምንቱ በፊተኛው ቀን እንደ ቀናው መጠን እያስቀረ በቤቱ ያስቀምጥ።" (1ኛቆሮ16÷2)

## ለአምልኮ መሰባሰብ

### ቦታዎች

ሥርዓተ አምልኮ ለመፈጸም የሚሰበሰቡት ቤቶች ውስጥ ነበር። ለምሳሌ በበዓለ ሀምሳ የተሰባሰቡበት በማርቆስ እናት በማርያም ቤት ነበር።

**ሥርዓቱ** በቅዱስ ቍርባን ጊዜ ወንጌል በማንበብ ይጀመራል፣ የነቢያት ትንቢት ይነበባል፣ ስብከት ከተሰጠ በኋላ ጸሎት ይደረጋል። ጸሎቱም ስለ ቤተክርስቲያን ጉዳዮች፣ ስለ ሰላም እና የምስጢራት አፈጻጸም ጸሎት ናቸው።

### አጋፔ "የምእመናን ስብስብ-አንድነት"

አጋፔ በሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን የታወቀ ነው። ክርስቲያኖች በአንድነት ተሰባስበው መዝሙር የሚዘምሩበት የሚማሩበትና የሚመገቡበት ነበር። በመጀመሪያ አጋፔ ከቅዱስ ቍርባን ጋር የሚፈጽሙ ነበሩ። በኋላ ግን ሁለቱን ሙሉ በሙሉ ለይተዋል።

www.zeorthodox.org

### ጸሎት፡-

ወንዶችና ሴቶች ለሁለት ተከፍለው ይጸልዩ ነበር። ጸሎቱም የጌታችንን ጸሎት ነበር። "እንግዲህ እናንተስ እንዲህ ጸልዩ፡- በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ ስምህ ይቀደስ መንግሥትህ ትምጣ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን፤ የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን፤ እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን፤ ከክፉም አድነን እንጂ ወደ ፈተና

አታግባን፤ መንግሥት ያንተ ናትና ኃይልም ክብርም ለዘለዓለሙ አሜን።" (ማቴ. 6÷9-13)

መዝሙረ ዳዊትም የጸሎቱ ክፍል ነበር። "እንግዲህ፣ወንድሞች ሆይ፣ምንድር ነው? በምትሰበሰቡበት ጊዜ ለእያንዳንዱ መዝሙር አለው፣ትምህርት አለው፣መግለጥ አለው፣በልሳን መናገር አለው፤ መተርጎም አለው፣ሁሉ ለማነጽ ይሁን።" (1ኛ ቆሮ.14÷26) እንዲሁም "ይህ ማባከን ነውና በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ፤ ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ" (ኤፌ. 5÷19)

**መዝሙራት፦** በዘመነ ሐዋርያትም መዝሙር ይዘመር ነበር። (ኤፌ. 5÷19 ፤ ቆላ.3÷16)

**የመስቀል ምልክት፦** የክርስቶስ መስቀል ከመጀመሪያ ጀምሮ ለክርስቲያኖች የክብርና የቅድስና ምልክት ነበር። በደረታቸው እና በክንዳቸው ይነቀሱትም ነበር። የመስቀል ምልክት ያደርጉ የነበሩትም የመስቀልን ኃይል ለማግኘት፣ ዲያብሎስን ለማሸነፍ እና በመስቀል የተገለጠውን የጌታችንን ፍቅር ለማስታወስም ነበር። "የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት፣ ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና;; " (1ኛ ቆሮ. 1÷18)

**ጾም** ፦የረቡዕ እና የዓርብ ጾም፤ እነዚህ ሁለት ቀናት አይሁድ ይጾሟቸው በነበሩት ሁለት ቀናት ሐሙስና ዓርብ የተተኩ ናቸው።

የአርባ ቀናት ጾም፦ ይህ የፋሲካን በዓል ለማሰብ የሚጾም ነው።

ሰሙነ ሕማማት /የተቀደሰው ሳምንት/ ከመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጀምሮ የሚፈጸም ነው።

## የክርስቲያኖች በዓላት፦

በሐዋርያት ዘመን ቢያንስ ሁለት በዓላት ይከበሩ እንደነበር ተረጋግጦአል። ፋሲካ (የጌታችን ትንሣኤ ስለሆነ) እና በዓለ ጰራቅሊጦስ (መንፈስ ቅዱስ በቤተ ክስቲያን የወረደበት ዕለት)

www.zeorthodox.org

**የሙታን ጸሎት፦**

በዘመነ ሐዋርያት የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ለሙታን ትጸልይ ነበር። ቤተ ክርስቲያን ለሙታን በሚደረግ ጸሎት ሙታንና የሚጸልዩት ሕያዋንም እንደሚጠቀሙበት ታምናለች። ቅዱስ ዮሐንስ ይሄንን ሲያጸና "ማንም ወንድሙን ሞት የማይገባውን ኃጢአት ሲያደርግ ቢያየው ይለምን፣ሞትም የማይገባውን ኃጢአት ላደረጉት ሕይወት ይሰጥለታል። ሞት የሚገባው ኃጢአት

አለ፤ስለዚያ እንዲጠይቅ አልልም።" (1ኛ ዮሐ. 5÷16) "እንግዲህ እግዚአብሔርን በመምሰልና በጭምትነትም ሁሉ ጸጥና ዝግ ብለን እንድንኖር፣ልመናና ጸሎት ምልጃም ምስጋናም ስለ ሰዎች ሁሉ ስለ ነገሥታትና ስለ መኳንንትም እንዲደረጉ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ። ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው።" (1ኛ ጢሞ. 2፣1-3) "በዚያን ቀን ከጌታ ምሕረትን እንዲያገኝ ጌታ ይስጠው፤በኤፌሶንም እንዴት እንዳገለገለኝ አንተ በደኅና ታውቃለህ።" (2ኛ ጢሞ.1፣18)

ይህም ማለት በሃይማኖት በቅድስና ኖረው ያላወቁት ቀላል ኃጢአት (ስሕተት) ለሠሩ የሚደረግ ጸሎት ነው።

## ምን ተማርን?

(1)በሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን እንኑር። በዓለም ብዙ የሐሰት ሃይማኖቶች እንሰማለን። በነዚህ የሐሰት ትምህርቶች ልንሳብባቸው ግን አይገባም። ቤተ ክርስቲያናችን በታሪክና በመንፈስ ከዘመነ ሐዋርያት ጋር አንድ ናት።

(2)ሥርዓተ አምልኮታችንን መቀየር ምን ያመጣል? ሥርዓተ አምልኮታችንን ከቀየርን ሐዋርያዊ ሥርዓተ አምልኮትን አናጸናም ። በመለወጥ የሚገኝ ትርፍም የለም ። ቤተ ክርስቲያንና ሰዎችን ከሙጉዳት በስተቀር ሌሎች በክርስትና ስም የሚንቀሳቀሱ ክፍልፋዮች በዚህ የለውጥ እንቅስቃሴ በአስከፊ ይዤን በረከት አጥተዋል ። ለዚህም ነው የጭፈራ ቤት ትዕይንትን አምልኮ የሚሉት።***"ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንት ዛሬ ለዘላለምም ያው ነው ። ልዩ ልዩ ዓይነት በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትውሰዱ ።"*** (ዕብ. 1÷8-9)

www.zeorthodox.org

www.zeorthodox.org

# የዜማ ምልክቶች

## ሠላሳ ዘጠነኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ ፡-** የቤተ ክርስቲያን የዜማ ምልክቶች ማሳወቅ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ ፡-** *“ በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ እርስ በእሳችሁ ተነጋገሩ፤ ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ፤”* (ኤፌ. 5÷19)

**ተጨማሪ ምንባብ ፡-**ቅዱስ ያሬድ እና ዜማው፡፡

**መግቢያ፡-** ቤተ ክርስቲያንን እግዚአብሔርን የምታመሰግንበት ዜማ ያሬዳዊ ዜማ ይባላል፡፡ ይህም ዜማ መንፈሳዊ ትርጉም ያላቸው ምልክቶች አሉት፡፡በዛሬው ትምህርታችንም እነዚህን ምልክቶች እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

### ዜማ ማለት ምን ማለት ነው?

ዜማ ስልት ያለው ድምፅ ወይም ደስ የሚያሰኝ መልካም ቃና ያለው በስልት የተቀነባበረ ጩኸት ማለት ነው፡፡ዜማ ዓለማዊ ዜማ እና መንፈሳዊ ዜማ ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡፡

1. **ዓለማዊ ዜማ፡-** እንደ ኅብረተሰቡ ቋንቋ እና ባህል በኅብረት እና በተናጠል የሚቀርብ ሕዝባዊ ዜማ ነው፡፡ ዓለማዊ ዜማ ሰውን ለማስደሰት የተዘጋጀ ሲሆን መንፈሳዊ ዜማ ግን እግዚአብሔርን ለማገልገል የተዘጋጀ ነው፡፡

www.zeorthodox.org

2.**መንፈሳዊ ዜማ፡-** በቤተ ክርስቲያን ወይም በሌላ ቦታ በበዓላት እና በአጽዋማት ሥርዓት በአለው ሁኔታ በመዓልትም ሆነ በሌሊት እግዚአብሔር የሚገለገልበት መንፈሳዊ ምስጋና ነው፡፡

መንፈሳዊ ዜማ የምንልበት ምክንያትም የዜማው አደራረስ ከቅዱሳት መጻሕፍት የተውጣጣ እና ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ስለሆነ ነው፡፡ ያሬዳዊ ዜማም ከሁለተኛው ወገን ከመንፈሳዊ ዜማ የሚቆጠር ነው፡፡ ምክንያቱም በያሬዳዊ ዜማ የሚመሰገነው እግዚአብሔር ነው፡፡ የተገኘውም ከቅዱሳን መላእክት በመሆኑ ነው፡፡

የዓለማዊ ዜማ እና የመንፈሳዊ ዜማ ድምፃቸውን ብቻ ስንመለከት ሁለቱም በርቀት ይሰማሉ። ሁለቱም ሰሚዎችን ደስ ያሰኛሉ። በሚሰጡት መልእክት ግን ልዩነት አላቸው። የቤተ ክርስቲያን ዜማ ሰማያዊ ሲሆን፤ሌላው ዜማ የምድር ነው። ይህም ከእግዚአብሔር በተቀበለው እና ባዘጋጀው በቅዱስ ያሬድ ተሰይሞአል።

ይህም ያሬዳዊ ዜማ ከስድስተኛው ክፍለ ዘመን እስከ አለንበት ጊዜ ድረስ በቤተ ክርስቲያን በአለው መንፈሳዊ አግልግሎት ልዩ ሥፍራ ይዞ ይገኛል። ያሬዳዊ ዜማ ግእዝ፣ ዕዝል እና አራራይ ተብሎ በሦስት ዓይነት ይከፈላል።

ግእዝ ማለት አንደኛ (መጀመሪያ) ማለት ነው።

ዕዝል ማለት ከግእዝ ጋር ተደርቦ (ታዝሎ) የሚዜም ማለት ነው።

አራራይ ማለት የሚያሳዝን (የሚያራራ) ማለት ነው።

ከላይ የተገለጹትን የዜማ ዓይነቶች ለማዜም የሚረዱ ዐሥር ረዳት ምልክቶች (ቅርፆች) አሉ። እነርሱም፡-

1.ይዘት ( ) 3. ሂደት ( ) 5.ቅናት ( ) 7. ርክርክ ( ) 9. አንብር ( )

2.ድፋት( ) 4.ቁርጥ ( ) 6. ጭረት ( ) 8. ደረት ( ) 10.ድርስ(ርስ) ናቸው።

**ማጠቃለያ፡-** የቤተ ክርስቲያን ዜማ ዓይነቶች ሦስት ሲሆኑ፤ዐስር ፊደል አልባ ምልክቶች አሉዋቸው።

**ተግባር፡-** የቤተ ክርስቲያንን ዜማ ምልክቶች በድምፅ ከዜማ መምህራን ጠይቁ።

www.zeorthodox.org

# ወንጌል(አንድ)

## አርባኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለ ወንጌል እና ወንጌላውያን አውቀው፤ የሚሰጣቸውን ጥያቄዎች ያበራራሉ።

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***" ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ።"*** ማር.16፡16

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ‹‹ወንጌል ትርጓሜ መቅድም››፤ ‹‹የሐዲስ ኪዳን መግቢያ›› ያልታተመ ለሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ የተዘጋጀ መማሪያ ጽሑፍ በመጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ፤ ኪዳነ ጽድቅ ማኅበረ ቅዱሳን ፤ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ፤ Bible dictionary (Mathew henry)

**መግቢያ፡-** መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ወንጌል እና ወንጌላዊነት ያስተምረናል ፤ በመጽሐፍ ቅዱሳችንም ወንጌል የሚባሉ አራት መጻሕፍት አሉ። በዛሬው ትምህርታችን ስለ ወንጌል እንማራለን።

### የሳምንቱ ትምህርት፡-

**ወንጌል፡-**

***" ዩ አንጌሊዎን "*** ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣው ‹‹ወንጌል›› በግእዝ ‹‹ብሥራት›› በአማርኛ ‹‹የምሥራች›› ማለት ነው። የምሥራቹም በኃጢአት፣ በፍዳ እና በዲያብሎስ አገዛዝ ባርነት ለሚኖረው የሰው ልጅ ፤ የነጻነት የጽድቅ እና የምሕረት ደጅ መከፈቱን ድኅነት መፈጸሙን ስለሚያበስር የተሰጠ ስያሜ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ***"ወንጌል"*** የተባለው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስና ሐዋርያቱ ያስተማሩት ትምህርት ነው።

www.zeorthodox.org

ይህን ቃል በሐዲስ ኪዳን ለመጀመሪያ ጊዜ የተናገረው ***የጌታ መልአክ*** እና ***መልአኩ*** ብሎ ሉቃስ የገለጠው ቅዱስ ገብርኤል ነው።***" እነሆም የጌታ መልአክ ወደ እነርሱ ቀረበ የጌታ ክብርም በዙርያቸው አበራ ታላቅ ፍርሀትም ፈሩ ። መልአኩም እንዲህ አላቸው፡- እነሆ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች(ወንጌል)እነግራችኋለሁና አትፍሩ፣ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት***

***እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና።"*** (ሉቃ.2÷10) ይህ የምሥራች ቀድሞ ተነግሮአል።

***የምሥራቹ ትንቢት ሲነገር ነበር፡-***

በአባብ አድሮ አዳምና ሔዋንን ላሳተው ሰይጣን ከሴቲቱ የሚወለደው ***"እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል"*** (ዘፍ.3÷15) ሲለው፤ለሰው ልጅ የምሥራች ደወል ነበር።አብርሃምን ***" የምድር ነገዶች ሁሉ በአንተ ይባረካሉ"*** ዘፍ.12፡ሲል ከአብርሃም ዘር ስለሚወለደው መድኅን ቀድሞ አየሰበከው ነበር።ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ሲያብራራልን***"መጽሐፍም እግዚአብሔር አሕዛብን በእምነት እንዲያጸድቅ አስቀድሞ አይቶ፡- በአንተ አሕዛብ ሁሉ ይባረካሉ ብሎ ወንጌልን ለአብርሃም አስቀድሞ ሰበከ ይላል።"*** ( ገላ.3÷8) ሌሎችም ነቢያት የምሥራቹን ቀድመው በመንፈስ ቅዱስ ተንብየዋል። ለምሳሌ ኢሳይያስን የቤተ ክርስቲያን መምህራን ***"ደረቅ ሐዲስ(ወንጌል)"*** ይሉታል ፤ ምክንያቱም የጌታችንን መወለድ እና ማዳን ቀድሞ በማብሠሩ ነው።***"የምሥራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው"*** (ሮሜ.10÷15 ኢሳ.5÷27)

ወንጌል የዓለም መዳን ዓዋጅ ነው።ይህም ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተማርነው ነው። ***"ኢየሱስም በምኵራቦቻቸው እያስተማረ የመንግሥትንም ወንጌል እየሰበከ በሕዝብም ያለውን ደዌና ሕማም ሁሉ እየፈወሰ በገሊላ ሁሉ ይዞር ነበር።"*** (ማቴ.4÷23)

ለሐዋርያቱም ***" ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ። ያመነ የተጠመቀ ይድናል፤ያላመነ ያልተጠመቀ ግን ይፈረድበታል"*** ብሎ ባዘዛቸው መሠረት የእነርሱ ትምህርት ወንጌል ናት። (ማር.16÷16)።ከዚሁም ጋር አምነን የምንድናባት ናት።***" መልካሙን የምሥራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው"*** (ሮሜ.10÷15፣ኢሳ.52÷7) እንደተባለ የሐዋርያት ***"ድምፃቸው በምድር ሁሉ ላይ ቃላቸውም እስከ ዓለም ዳርቻ "***(*መዝ*.18፡4 ፣ሮሜ 10፡18) ወጥቷል።ይህም በእነርሱ እና በተከታዮቻቸው የተደረገውን አገልግሎት ያመለክተናል።

ክርስትና ለወንጌል መታዘዝ ነው። ይህም ማመን ፣ መጠመቅ ፣ መልካም መሥራትን ያካትታል(ማር.16፡16) ከዚሁም ጋር የምሥራቹን መመስከር አለ ፤***" በአፍህ በልብህም ሆኖ ቃሉ ቀርቦልሃል፤ ይህም የምንሰብከው የእምነት ቃል ነው። ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ በአፍህ ብትመሰክር …በልብህም ብታምን ትድናለህና ፤ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፉም መስክሮ ይድናልና።"*** (ሮሜ 10፡8-10) ምስክርነቱም ለአንድ ሰው ፣ ለቤተሰብ እና ለወዳጆቻችን ከመመስከር በጉባኤ እስከ ማስተማር ያለውን ያካትታል።

www.zoorthodox.org

ወንጌል ልዩነቶችን ያጠፋች የአንድነት ቤት ናት። ሰውና መላእክት በአንድነት ያመሰገኑት ወንጌል ስትነገር ነው /ሉቃ.2፡14/። አንጥያኮስ አራተኛ ከሚባለው የግሪክ ንጉሥ ዘመን ጀምሮ (170

ዓ.ዓ ) የነበረውን የአይሁድ እና ግሪካውያን ልዩነት አጥብባ ወንጌል ፍቅር እና ሰላምን ሰብካለች። ምክንያቱም ወንጌል ለሰዎች ሁሉ የሚያስፈልግ ፤ አምነው እንዲድኑም የተገለጠ የእግዚአብሔር ኃይል ነው ። ***"በወንጌል አላፍርምና፤ አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው፣ ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና።"*** (ሮሜ.1፡16) በዚህም መሠረት ያመኑት አይሁድ ከግሪካውያን ጋር ተባብረው በአንዲት ቤተ ክርስቲያን በአንድ ልብ እንዲኖሩ ያደረገች ወንጌል ናት ። (የሐዋ.ሥ.11፡20-21 )።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የአምላክ ሰው መሆን ፤ በሥጋ ተገልጦ በምድር ሲመላለስ የሠራቸው የማዳን ሥራዎች ፤ ትምህርቱንም የሚተርኩ አራቱ መጻሕፍተ ወንጌል ይባላሉ ። እነዚህም የማቴዎስ ወንጌል ፣ የማርቆስ ወንጌል ፣ የሉቃስ ወንጌል እና የዮሐንስ ወንጌል ናቸው።

2. **ወንጌላውያን፡-**

የምሥራቹን የሚሰብኩ ሁሉ ወንጌላውያን ይባላሉ። (ሐዋ.ሥ21፡8) ***" ሌሎችም ወንጌልን ሰባኪዎች፣ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ"*** (ኤፌ.4፡11) ተብሎ እንደተጻፈ ወንጌላዊነት ተሰጥዖ ነው። ወንጌላዊነት ለቤተ ክርስቲያን መምህራን እና አባቶች የተሰጠ ሥራ ነው ።(2ኛ ጢሞ.4፡5)

ከዚህ በተለየም ወንጌላውያን የምንላቸው አራቱን ወንጌላት የጻፉልንን ነው። ብዙ ወንጌላት የነበሩና የተጻፉ ቢሆንም በመጽሐፍ ቅዱስ እና በቤተ ክርስቲያን የምንቀበላቸው ወንጌላት አራት ብቻ ናቸው ።ጸሐፊዎቹ ሁለቱ ሐዋርያት ሲሆኑ ሁለቱ ከሰባ ሁለቱ አርድዕት ናቸው።

## ማጠቃለያ፡-

ወንጌል የመዳናችን እና እግዚአብሔር እኛን የወደደበት ጥልቅ ፍቅሩ የተገለጠበት የአምላክ ሰው መሆንን (ሥጋዌ) ታበሥራለች ።

www.zeorthodox.org

ይህች ወንጌል በነቢያት የተነገረችና በሐዋርትያም የተሰበከች ናት። በአራቱ ወንጌላውያንም ተጽፋለች።

ክርስቲያኖች ወንጌልን መስበክ ሃይማኖታዊ ግዴታቸው ነው። ተሰጥዖ ያላቸውም በአደባባይ ይሰብካሉ።

## ተግባር፡-

በቤተ ክርስቲያን የሚሰጠውን ቃለ ወንጌል ተማሩ።

በሕይወታችሁ ወንጌልን ስበኩ፣ በቃላችሁም ተናገሩት።

**ጥያቄዎች፡-**

‹‹ወንጌል›› የሚለው ቃል አመጣጥና ትርጉም ምንድ ነው? ስያሜው እንዴት ተሰጠ?

ወንጌልን/የምሥራችን/ በሐዲስ ኪዳን ለመጀመሪያ ጊዜ የተናገረው ማነው?

መጻሕፍተ ወንጌል ስንት ናቸው? ዝርዝራቸውን እና ጸሐፊዎቹን ጥቀሱ፡

የምሥራቹን የሚሰብኩ ማን ይባላሉ?

www.zeorthodox.org

# ወንጌል(ሁለት)

# አርባ አንደኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ወንጌላውያን ለምን አራት እንደሆኑ መማር፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***“ ሌሎችም ወንጌልን ሰባኪዎች፣ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ”*** ኤፌ.4፡11

**ተጨማሪ ምንባባት፡-**ወንጌል ትርጓሜ መቅድም ፤ ‹‹የሐዲስ ኪዳን መግቢያ›› ያልታተመ ለሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት መማሪያ የተዘጋጀ ጽሑፍ በመጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ፤ ‹‹ኪዳነ ጽድቅ›› ማኅበረ ቅዱሳን ፤ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ፤ Bible dictionary (Mathew henry) ፤

**መግቢያ፡-** ባለፈው ሳምንት ስለ ወንጌላውያን ስንማር ፤ በመጽሐፍ ቅዱሳችንም ‹‹ወንጌል›› የሚባሉ ኣራት መጻሐፍት አሉ ብለናል፡፡ በዛሬው ትምህርታችን ወንጌል ለምን አራት እንደሆነች እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

### ወንጌላውያን ለምን አራት ብቻ ሆኑ ?

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአገልግሎት ከጠራቸው ከመረጣቸው ዐሥራ ሁለት ሐዋርያትና ሰባ ሁለት አርድእት መካከል ወንጌላት በአራቱ ብቻ እንዲጻፉ ለምን አደረገ ? የመጻሕፍትን ቊጥር በቀኖና ከወሰኑ ሊቃውንትስ ወንጌልን እንዲጽፉ የተመደቡ ሐዋርያትና አርድእት አራቱ ወንጌላውያን ብቻ ለምን ሆኑ ? የሚሉ ጥያቄዎችን ልናነሣ እንችላለን፡፡

www.zeorthodox.org

ከዚህ በፊት እንደተማርነው ቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፉት በተለያየ ዘመን እና ቦታ በነበሩ ከአርባ በሚበልጡ ቅዱሳን፤ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት እና ገላጭነት ነው፡፡ መጻሕፍት የተሰባሰቡት እና በቊጥር የተወሰኑት በኋላ ነው፡፡ በዚህ መሠረትም መንፈሳዊውን ነገር ከመንፈሳዊው ነገር ጋር አስተያይተው፣ የጠራ ትምህርት የያዙትን በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተጻፉትንም ለይተው፤ በመጀመሪያ የሊዮኑ ሊቀ ጳጳስ ሄሬኔዎስ እና ሌሎች አባቶች በሰጡት ቀኖና መነሻ ወንጌላት በአራት

ተወሰነዋል፡፡ ይህም የተደረገው በእግዚአብሔር ጥበብ መሆኑን እናስተውላለን፡፡

ለወንጌል አራት መሆን መሠረት የሆነውን ትምህርት ያመጣው የሊዮኑ ሊቀ ጳጳስ ሄሬኔዎስ /Irenaeus/ ነው፡፡ ሄሬኔዎስ የወንጌላት ቊጥር ከአራት ሊያንስም ሊጨምርም አይችልም፣ ምክንያቱም አራት ዐቢይ የዓለም መዓዝናት ፣ አራት ዋና ዋና ነፋሳት፣ሕዝቅኤል እና ዮሐንስ ያዩዋቸው አራቱ እንስሶችም የወንጌል ቊጥር አራት መሆን እንደሚገባው ያመለክታሉ፡፡ (ሕዝ 1፡5-10 ፣ ራእ 4፡7) ቤተ ክርስቲያንም ሊኖራት የሚገባው አራት ዐምዶች፤ አራት ወንጌላት ናቸው ሲል አጽንቶ አስተማረ፡፡ እንደ ሄሬኔዎስ አራት ቁጥር ራሱም ፍጹም ስለሆነ ወንጌል በዚሁ ፍጹም ቊጥር የተወሰነች ናት ብሎአል፡፡ ለአራቱ ወንጌላት ምሳሌ የሆኑትን ቀጥለን ስንመለከት በእግዚአብሔር ምግብና እንጀምራለን፤ ፍጥረታት የሚመገቡት በባለቤታቸዉ በእግዚአብሔር ነው፡፡ የሚመግብበትም መንገድ የተለያየ ነው፡፡ ከእነዚህም የወንጌላትን አራት መሆን የሚያመለክቱትን ብቻ እንመልከት፡፡

**አራቱ አፍላጋት (ወንዞች)፡-**እግዚአብሔር መሬትን የሚመግቡ አራት አፍላጋትን ፈጥሯል፡፡ (ዘፍጥ.2፡8-17)፡፡ እነርሱም ኤፌሶን፣ግዮን፣ ጤግሮስና ኤፍራጥስ ናቸው፡፡ አራቱም ከዔደን ገነት እየወጡ ዕፀዋትን ከመድረቅ ወደ ልምላሜ፣ ከልምላሜ ወደ አበባ ፣ ከአበባም ወደ ፍሬ ያደርሳሉ፡፡ ዕፀዋቱን በአራቱ ወንዞች እንደሚያረሰርስ ሁሉ ፤ በአራቱ ወንጌላት የሰው ልጆችን ከኃጢአት ወደ ንስሓ ፤ ከንስሓ ወደ መልካም ምግባር ከምግባርም ወደ ክብር የሚያበቁ ናቸው፡፡ በዚህም መሠረትም ኤፌሶን የማቴዎስ፣ ግዮን የማርቆስ፣ ጤግሮስ የሉቃስ፣ ኤፍራጥስ የዮሐንስ ምሳሌዎች ናቸው፡፡

**አራቱ ነፋሳት፡-**እግዚአሔር ፍጥረቱን በአራቱ ነፋሳተ ምሕረት ይመግባል፡፡እነዚህ አራት ነፋሳት ሲነፍሱ ለሰው አምስት ነገሮች ይደረጉለታል፡፡ እነዚህም ጠል፣ ዝናም፣ ሕይወት፣ በረከት እና ፈውስ ናቸው፡፡ በአራቱ ወንጌላትም እንደ ጠል ትምህርት፣ እንደ ዝናም ሥጋ ወደሙ፣ እንደ ፈውስ ፈውስ መንፈሳዊ እንደ በረከትም በረከት መንፈሳዊ ይገኛሉ፡፡

www.zeorthodox.org

**አራት ዘመናት፡-** አራቱ ክፍለ ዘመናትም ሌሎች የመመገቢያው መንገዶች ናቸው፡፡በአራቱ ክፍለ ዘመናት መፈራረቅ ምግበ ሥጋ እንደሚሰጠን፤ በአራቱ ወንጌላውያን ትምህርትም ምግበ ነፍስ ይደረግልናል፡፡ በተጨማሪም አራቱ ዘመናት በአራቱ ወንጌላውያን ተሰይመዋል፡፡ እነርሱም ዘመነ ማቴዎስ፣ ዘመነ ማርቆስ፣ ዘመነ ሉቃስ እና ዘመነ ዮሐንስ ይባላሉ፡፡

**አራቱ የዓለም መዓዝናት፡-**ዓለም አራት መዓዝናት አሉዋት፤ ወንጌላውያንም በመዓዝናቱ

ይመሰላሉ፡፡ በአራቱ መዓዝናት ዓለም እንደተያዘች እና እንድትታወቅ ፤ በአራቱ ወንጌላትም የክርስቶስ አምላክነት እና አዳኝነት ታውቋል፡፡ የቅዱሳት መጻሕፍት ማዕዘንም የክርስቶስ ሥጋዌ እና ማዳን ነው፡፡ የነቢያቱ ትንቢት የሐዋርያት ስብከትም ይህንኑ ያመለክታል፡፡

**አራቱ እንስሳት፡-** አራቱ ወንጌላውያን መንበሩን በሚሸከሙ በአራቱ እንስሶች ይመሰላሉ፡፡ እነዚህ አርባዕቱ እንስሳ እግዚአብሔር እነርሱን ይሸከማቸዋል እንጂ እነርሱ አይሸከሙትም፡፡ ነገር ግን ለወዳጆቹ ሲገለጥ በእነርሱ ነው፡፡(ኢሳይ. 6፡1 ራእ. 5)

እግዚአብሔር በእነዚህ እንስሳት ተገልጦ እንደሚታየው ሁሉ የኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት ፣የእግዚአብሔር አንድነቱ ሦስትነቱ፣ሰጪ ነሺ፣ ገዳይ አዳኝ፣ የዓለሙ መድኃኒት፣ የቅዱሳን ክብር /አዳኛቸው፣ቀዳሻቸው፣አክባሪያቸው/ እርሱ መሆኑ የተገለጠው በእነዚህ አራት ወንጌላት ነውና ወንጌላውያን በአርባዕቱ እንስሳት ይመሰላሉ፡፡አራቱ እንስሳት የየራሳቸው መልክ አላቸው፡፡ፊተኛው አንበሳ ፤ ሁለተኛው ጥጃን(ላምን) ፤ ሦስተኛው ሰውን ፤ አራተኛው ንስርን ይመስላሉ፡፡ (ራእ.5፡7-8)

ቅዱስ ማቴዎስ በገጸ ብእሲ /በባለ ሰው መልክ/ ይመሰላል፡፡ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ምድራዊ ልደቱን በማስቀደም ***"የዳዊት ልጅ፣ የአብርሃም ልጅ፣ የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ መጽሐፍ"*** ሲል ጽሑፉን ይጀምራል፡፡ (ማቴ1፡1)

ቅዱስ ማርቆስ ደግሞ በገጸ አንበሳ ይመሰላል፡፡ አንበሳ የሚኖረው ሰዎች ከሚኖሩበት አካባቢ ሩቅ በሆነ ምድረ በዳና በረሓ ነው፡፡ ባለበት ሆኖ ድምፁን ባሰማ ጊዜ አራዊቱ ሁሉ ይደነግጣሉ፤እንስሳትም ይገሠጻሉ፡፡ ቅዱስ ማርቆስም ከነቢያት ትንቢት፣ ከወንጌል ብሥራትና ከሐዋርያት ትምህርት ምድረ በዳ በነበረች በግብጽ ተገኝቶ ወንጌልን ሲያስተምር አጋንንትና መናፍቃን /እውነትን የሚጠራጠሩ/ ደንግጠዋል ምእመናንም ተገሥጸዋል፡፡ ከዚህም በላይ አንበሳ ላምን እንደሚሰብር በግብጽ የነበረውን አምልኮ ጣዖት /የላም ምስል ሠርቶ ማምለክን/ አጥፍቷል፡፡

www.zeorthodox.org

ቅዱስ ሉቃስም በገጸ ላሕም /በላም ገጽ/ ይመሰላል፡፡ጌታ ስለመንግሥተ ሰማያት በምሳሌ ካስተማራቸው ትምህርቶች የጠፋውን ልጅ ታሪክ ሲጽፍ ፡፡ የጠፋው ልጅ በተገኘ ጊዜ አባትየው / ጌታችን / ***"ወአምጽኡ ላሕመ መግዝዓ ወጥብሁ፤ ንብላዕ ወንትፈሣሕ፡- የሰባ ፍሪዳ አምጥታችሁ እረዱ፤ ከእርሱም ጋር በልተን ደስ ይበለን "*** ማለቱን ስለጻፈ እና በበረት በከብቶች ግርግም መወለዱን ስለጻፈ በላም ተመስሏል፡፡ሉቃ.14፡23 1፡7

ቅዱስ ዮሐንስ ደግሞ በገጸ ንስር ይመሰላል፡፡ ንስር የጠራ ዓይን አለው ጥቃቅኗን ሁሉ ማየት ይችላል፡፡ ቅዱስ ዮሐንስም ከሌሎቹ ሐዋርያት ይልቅ ረቂቅ ነገረ መለኮትን ይጽፋል፡፡ወንጌሉን ሲጀምርም ረቂቁን ምስጢር ***"መጀመሪያ ቃል ነበረ፤........"*** ብሎ በመተረክ ነው፡፡ ንስር በእግሩም የሚሽከረከር በክንፋም የሚበርር ነው ፤ ቅዱስ ዮሐንስም ነገረ መለኮቱንና በምድር ተመላልሶ የሠራውን ለሰው በሚረዳ መንገድ አብራርቶ ጽፏል፡፡

ወንጌላውያን በአራቱ ገጻተ ኪሩቤል ስለሚመሰሉና እግዚአብሔር በሰማያት ለእነ ኢሳይያስ እንደ ተገለጸ ሥጋዌውንም በእነዚህ በአራቱ ወንጌላውያን ለመግለጽ እርሱ ባወቀ ቍጥራቸውን በአራት ወስኖታል፡፡

**ሲኖፕቲክስ፡-** ከዚህ በተጨማሪም ሦስቱ ወንጌላት ሲኖፕቲክስ(ተመሳሳይ ማለት ነው)የሚል ስያሜ ተሰጥቶአቸዋል፡፡ እነርሱም፡- ማቴዎስ፣ማርቆስ እና ሉቃስ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ተመሳሳይ ታሪኮችን ስለሚተርኩ ነው፡፡ ዮሐንስ ግን ከሌሎቹ ተለይቶ የቃልን ቅድምናና የሥጋዌን ጥልቅ ትምህርት ትኩረት ሰጥቶአል፡፡ እና ከሦስቱ ይለያል፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ወንጌላት አራት የሆኑት እግዚአብሔር በጥበቡ በሠራው የፍጥረት ሥርዓት እና በሰማይ መላእክት (ኪሩቤል)ምሳሌ ነው፡፡

ይህን ምስጢር ከተናገሩ አበው የመጀመሪያው ሄሬኔዎስ ይባላል፡፡ሌሎችም ቅዱሳን የወንጌልን አራት መሆን አብራርተዋል፡፡

ሦስቱ(የማቴዎስ ፣ የማርቆስ እና የሉቃስ) ወንጌላት ሲኖፕቲክስ(ተመሳሳይ) ወንጌላት ይባላሉ፡፡

www.zeorthodox.org

## ተግባር፡-

የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት በጥልቀት ለማወቅ ጣሩ ጠይቁም፡፡

ከሥነ ፍጥረት ስለእግዚአብሔር እንድታስተውሉ የሚያደርጋችሁን ለመምህር አስረዱ፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. ለወንጌል አራት መሆን መሠት የሆነውን ትምህርት ያመጣው ማን ይባላል? ምክንያቱ

ምንድነው? አብራሩ፡፡

2. አራቱ ወንጌላውያን መንበሩን በሚሸከሙ በአራቱ እንስሶች ይመሰላሉ፡፡ የየራሳቸው መልክ አላቸው፡፡ ማን ይባላሉ?

3. ቅዱስ ዮሐንስ በገጸ ንስር ይመስላል፡፡ ምክንያቱን አብራሩ፡፡

4. ሦስቱ ተመሳሳይ ወንጌላት የሚባሉት እነማን ናቸው? ለምን ተባሉ?

www.zeorthodox.org

# ቅዱስ ማቴዎስ ወንጌላዊ(አንድ)

## አርባ ሁለተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች የወንጌላዊውን የማቴዎስን ታሪክ እና የወንጌሉን መግቢያ አውቀው፤ ያብራራሉ፤ በመምህሩ የሚሰጧቸውነ ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***" መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሓ ግቡ"*** ማቴ.4፡17

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ወንጌል ቅዱስ ትርጓሜ መቅድም እና የሐዲስ ኪዳን መግቢያ ( በመጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ የተዘጋጀ )

### መግቢያ፡-

ይህ በተከታታይ ሁለት ክፍል የምንማረው የማቴዎስ ወንጌል የመጀመሪያው ክፍል ነው፡፡ ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ የሆነው ማቴዎስ ከአራቱ ወንጌላት አንዱን ጽፎልናል፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም የቅዱስ ማቴዎስን ሕይወት እና ስለወንጌሉ እንማራለን፡፡

### የሳምንቱ ትምህርት ፡-

ቅዱስ ማቴዎስ ከዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት እና ከአራቱ ወንጌላውያን አንዱ ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያናችን ትውፊት የማቴዎስ አባት ዲቁ ሲሆን እናቱ ደግሞ ካሩትያስ ትባላለች፡፡ በማርቆስ ወንጌል ግን የአባቱ ስም እልፍዮስ ተብሎ ተጠርቷል፡፡ ይኸም የዲቁ ሌላ ስሙ ነው፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ በትውልድ አይሁዳዊ ሲሆን የቀድሞ ሥራው ቀራጭነት ወይም ግብር ሰብሳቢነት ነበር፡፡ ለሐዋርያነት ከመመረጡ በፊት ስሙ ሌዊ የነበረ ሲሆን ማቴዎስ የሚለውን ስም ያወጣለት ጌታ ነው፡፡ ትርጕሙም ***"የተመረጠ"*** ወይም ***"የእግዚአብሔር ስጦታ"*** ማለት ነው፡፡

www.zeorthodox.org

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ማቴዎስን ለሐዋርያነት የጠራው በገሊላ አጠገብ በምትገኘው የቅፍርናሆም ከተማ ቀረጥ ይሰበስብ ከነበረበት ቦታ ነው፡፡ ማቴዎስ ጌታችንን ደግሶ በመጋበዝ በቤቱ አስተናግዶታል፡፡

የቅዱስ ማቴዎስ ሐዋርያዊ አገልግሎቱ መጀመሪያ በፍልስጥኤም አካባቢ የተወሰነ ነበር፡፡

በኋላ ግን በፋርስ ፣ በባቢሎን ፣ በዐረቢያ እና በኢትዮጵያም ወንጌልን እንደ ሰበከ ይነገራል፡፡ ቅዱስ ማቴዎስ በኢትዮጵያ ስለማስተማሩ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ ሩፊኖስ አረጋግጧል፡፡ የሀገራችንን ሊቃውንት ያስተማረው በትግራይ በስተምዕራብ በአድዋ ልዩ ስሙ ናዕዌር በተባለ ቦታ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ በመጨረሻም ጥቅምት 12 ቀን በሰማዕትነት ዐርፎአል፡፡

**የማቴዎስ ወንጌል መጻፍ፡-**በ58 ዓ.ም  አካባቢ በዕብራይስጥ ቋንቋ ተጽፎአል፡፡ ቅዱስ ማቴዎስ የነቢያትን ትንቢት ለሚያውቁት አይሁድ ትንቢት የተነገረለት ሱባኤ የተቆጠረለት መሲሕ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ለማስረዳት ወንጌሉን ጽፎአል፡፡ በመሆኑም ከአንድ መቶ ሃምሳ በላይ የብሉይ ኪዳን ጥቅሶችን አቅርቦአል፡፡

**የወንጌሉ አከፋፈል**

| | |
|---|---|
| ከልደት እስከ ጥምቀተ ክርስቶስ | ከምዕራፍ 1-4 |
| የተራራው ስብከት | ከምዕራፍ 5-7 |
| የጌታችን ትምህርቶችና ተአምራት | ከምዕራፍ 8-20 |
| የመጨረሻው ሳምንት | ከምዕራፍ 21-28 |

ወደ ኢየሩሳሌም ገባ ቤተመቅደሱን አጸዳ (ከምዕ. 21፡1-22)

የፈታኞቹ ጥያቄዎች እና የጌታ ትምህርታዊ መልሶች (ከምዕ.21፡23-22፡46)

ተግሣጽ  (ምዕ.23)

የዳግም ምጽአት እና የትንሣኤ ሙታን ትምህርት (ከምዕ. 24-25)

ከሞት ምክር እስከ ዕርገት (ከምዕ.26-28)

www.zeorthodox.org

**የመጽሐፉ ይዘት፡-**ይህ ወንጌል ሃያ ስምንት ምዕራፎችን በመያዝ ትልቁ ወንጌል ሲሆን ፤ በ 1068 ቍጥሮች ሁለተኛው ወንጌል ነው፡፡ ከእነዚህ ቍጥሮች 744ቱ የጌታችን ትምህርቶች ናቸው ፡፡

ከልደት እስከ ጥምቀተ ክርስቶስ (ከምዕራፍ 1-4) በዚህ ክፍል ሰባት (7) ዓበይት ነገሮች ተጠቅሰዋል፡፡እነርሱም፡-

**የጌታችን ሐረገ ትውልድ፡፡ (ምዕ.1፡1-17)** ማቴዎስ በነቢያት ትንቢት ተመሥርቶ ለዕብራውያን እንደመጻፉ፤ አይሁድ አብርሃም አባታችን፣ ዳዊት ንጉሣችን ብለው በሚመኩባቸው

ጀምሮ ጌታችን በምድር የተወለደበትን የዘር ሐረግ ይቆጥራል፡፡ በዚህ ሐረገ ትውልድ ውስጥ ክርስቶስ ከሕዝብ እና ከአሕዛብ የተወለደ መሆኑን ለማስረዳት፤ ከአሕዛብ በጌታ የዘር ሐረግ የተቆጠሩ ሦስት (ትዕማር ፣ራኬብ እና ሩት የተባሉ) እናቶች በስም ሲጠሩ ፤ በአይሁድ ልማድ ለማስተማር ሌሎቹን የእስራኤል እናቶች ግን በስም አልጠራቸውም ፡፡ ከአብርሃም እስከ ክርስቶስ ያለው ትውልድም አርባ ሁለት ነው ፡፡ ከዚህም ለአዳም ተስፋ የተሰጠው ለአብረሃም አሕዛብ በዘርህ ይባረካሉ፤ለዳዊትም የተነገረው መሲሕ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ማቴዎስ አስረግጦልናል፡፡

**የጌታችን ልደት** (ምዕ.1፡18-2፡1) ***" የኢየሱስ ክርስቶስም ልደት እንዲህ ነበር፡፡..."*** ማቴ.1፡18 በማለት የሚጀምረው ይህ ክፍል ሦስት ዓበይት ነገሮች ይዞአል፡፡

1)ጌታችን ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በመንፈስ ቅዱስ መፀነሱንና መወለዱን ያበሥራል፡፡

2)የጠባቂዋን የዮሴፍን ጽድቅ ያስተምረናል ፡፡ ዮሴፍ መፅነስዋን ሲያውቅ ጻድቅ ስለነበር ሊገልጣት አልወደደም፤ ከባቴ አበሳ ነውና በስውር ሊተዋት አሰበ፡፡ይህም የወንጌል ጽድቅ ነው፡፡በዚህ ሲጨነቅ መልአክ ተገልጦለት በመንፈስ ቅዱስ መፅነስዋን ስሙን ኢየሱስ እንደሚለውና የነቢዩ ኢሳይያስ ትንቢት መፈጸሙንም አበሠረው፡፡

3)ጌታችን በይሁዳ ቤተልሔም ተወለደ፡፡ ዮሴፍ የተሾመበትን የጠባቂነት አገልግሎት በሚገባ ፈጸመ፡፡

**የሰብአ ሰገል ታሪክ** (2፡2 -12)ከምሥራቅ ኮከቡን አይተው ለክርስቶስ ሊሰግዱ የመጡት ሰብአ ሰገል ፤ ወርቅ፣ እጣን፣ ከረቤን በስጦታ የማቅረባቸውን ታሪክም ከሌሎቹ ወንጌላውያን ተለይቶ በማቴዎስ ወንጌል ተጽፎልናል፡፡ የሰብአ ሰገል መምጣት እና የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው ማለታቸው፤ ከዚያም ሳይነግሩት በሌላ መንገድ መሄዳቸው፤ ሄሮድስ ክፋቱን እንዲገልጥ ምክንያት ሲሆነው እናያለን፡፡

www.zeorthodox.org

**የግብጽ ስደት**(2፡13 - 23) ሄሮድስ በሰብአ ሰገል መምጣት ተደናግጦ የአይሁድ ንጉሥ የሚወለድበትን ቦታ ከካህናት ዘመኑንም ከሰብአ ሰገል ተረድቶ በእሰግድለታለሁ ሰበብ ሊያስገድለው ፈለገ፡፡ ሆኖም ሰብአ ሰገል በሕልም ተረድተው በሌላ መንገድ መሄዳቸውን እንደተሳለቁበት ቆጠረው፣ እጅግ ተቆጥቶም ሁለት ዓመት የሆናቸውን ሕፃናት አስገደለ፡፡

ጻድቁ ዮሴፍም ከመልአክ በተረዳው መሠረት ሕፃኑንና እናቱን ይዞ ወደ ግብጽ ሸሸ ፡፡ ሄሮድስ ከሞተ በኋላም ወደ ናዝሬት መጥቶ ኖረ፡፡ ናዝሬት የተናቀች ከተማ ብትሆንም ጌታችን አደገባት፡፡

የነቢያትም ትንቢት ተፈጸመ፡፡ ይህ ትንቢትም በመጽሐፍ ያልተጻፈ በትውፊት ሲነገር የኖረ ትንቢት ነው፡፡

***የጌታችን ጥምቀት*** (3፡1 - 17) መጥምቁ ዮሐንስ የንስሓን ጥምቀት እያጠመቀ(3፡3-6) ፣ ስለ ክርስቶስ እየመሰከረ (3፡11-12)እና ሕዝቡን እያዘጋጀ (3፡2-3) ልበ ደንዳኖችን እየወቀሰ (3፡7-10) ከዮርዳኖስ በረሐ መጣ፡፡ ጌታችንም በሠላሳ ዓመቱ ለመጠመቅ ወደ ዮሐንስ ሄዶ በትሕትና ተጠመቀ፡፡ በዚህ ጊዜም አብ የምወደው ልጄ ብሎ መሰከረ፤ መንፈስ ቅዱስም እንደ ርግብ በእርሱ ላይ መጣ፡፡(ማቴ.3፡13-17)

***ጾመ ክርስቶስ***(4፡1-11) ጌታችን አርባ ቀንና ሌሊትም ጾሞ ፤ በፈታኙ ተፈትኖ፣ ምኞትን ትዕቢትን እና ገንዘብን መውደድን ድል አድርጎ ድል ማድርገን ሰጠን፡፡ ከዚያም መላእክት ቀርበው አገለገሉት ፡፡ ይህም ድል ብናደርግ የምናገኘውን ክብር ያስተምረናል፡፡

***የጌታችን የመጀመሪያ ትምህርቶች እና ደቀ መዛሙርት*** (4፡12-25) ይህ ክፍል ጌታችን ዮሐንስ ስለተያዘ ወደ ገሊላ ፈቀቅ አለ ፤ በማለት ይጀምራል፡፡ በቅፍርናሆምም ኖረ ፡፡ የመጀመሪያውን ትምህርት ***"መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሓ ግቡ"*** ብሎ የሰበከውም በዚያ ነው ፡፡ በገሊላ ባሕርም አራቱን ደቀ መዛሙርት ጠራ፡፡ይህ ክፍል የሚዘጋው ***ኢየሱስ በምኩራቦቻቸው ..እየሰበከ በሕዝቡ ያለውን ደዌና ሕማም ሁሉ እየፈወሰ ይዞር ነበር፡፡ዝናውም ወደ ሶርያ ሁሉ ወጣ ብሎ ነው፡፡*** በዚህ ምክንያትም ከየከተማው ብዙ ሕዝብ ተከተሉት፡፡

*ማጠቃለያ፡-*ማቴዎስ ጌታችንን ፈቅዶ የተከተለ ሐዋርያ ነው፡፡ ሃያ ስምንት ምዕራፎች ባሉትና በስሙ በተሰየመው ወንጌል የመጀመሪያዎቹን አራት ምዕራፋት በዛሬው ትምህርት አይተናል፡፡ቀሪውን ለሚቀጥለው ክፍል ያድርሰን፡፡

## ተግባር፡-

እግዚአብሔርን ለመከተል የምናስቀረው ነገር መኖር እንደ ሌለበት ከማቴዎስ ተምረናል፡፡

www.zeorthodox.org

ጌታችን ከሕዝብ ከአሕዛብም ሲወለድ አልተጸየፈም፤ እኛም ሁሉንም ማክበር አለበን፡፡

ጌታችን የሥራውን መጀመሪያ በትሕትና እና በጾም ጀመሮአል፡፡ እኛም ከዚህ ትሕትናን እንማራለን፡፡

የማቴዎስ ወንጌልን ከምዕ.5-7 አንብቡ፡፡(መምህር የወንጌሉን ክፍል ተከፋፍለው እና ተዘጋጅተው እንዲመጡ ያድርጉ፡፡)

# የተራራው ስብከት

## አርባ ሦስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ከተራራው ስብከት የወንጌልን ሕግ እና የጌታችንን ትእዛዛት አውቀው፤ በመምህሩ የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ያብራራሉ፡፡

**የዕለቱ ጥቅስ፡-*" እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም "*** ማቴ.5፡17

**ተጨማሪ ምንባባት፡-**ማቴ.5-7 ፤

***መግቢያ፡-*** ባለፈው ሳምንት ስለ ወንጌላዊው ማቴዎስ እና የማቴዎስን ወንጌል የመጀመሪያ ክፍል ተምረናል፡፡ የማቴዎስ ወንጌል ከምዕራፍ 5-7 ጌታችን በተራራ ላይ ስላስተማረው ***የተራራው ስብከት*** ይባላል፤ የእኛ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትም በመግቢያው ትምህርት ***አንቀጸ ብፁዓን*** ይሉታል፡፡ ይህንን የማቴዎስ ወንጌል ክፍል በዛሬው ትምህርታችን እናያለን ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ጌታችን መሠረታዊ ትምህርቶችን ያስተላለፈበት ይህ የወንጌል ክፍል ሦስት ምዕራፎች አሉት፡፡ ከይዘቱ በመነሣትም በአምስት ክፍለን እናየዋለን፡፡

### አንቀጸ ብፁዓን (ማቴ.5÷1-12)

ጌታችን በእግዚአብሔር ፊት ብፁዓን ስለሚያደርጉን ፍጹም ተግባራት ሲያስተምረን ዘጠኝ የብፅዕና ትምህርቶችን አስምሮዋል፡፡ በሰንጠረዡ ያሉትን በቃላችሁ አጥኑ፡፡

www.zeorthodox.org

| | | |
|---|---|---|
| 1.በመንፈስ ድኆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው፡፡ | 4.ስለጽድቅ የሚራቡ እና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው፡፡ | 7. የሚያስታርቁ ብፁዓን ናቸው፡፡ |
| 2.የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው፡፡ | 5.የሚምሩ ብፁዓን ናቸው | 8.ስለጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው፡፡ |
| 3. የዋሆች ብፁዓን ናቸው፡፡ | 6. ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው | 9.ሲነቅፉአችሁና ሲያሳድዷችሁ በእኔ ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናቸው፡፡ |

## አርአያነት (ማቴ.5፡13-16)

እነኚህን የመልካም ምግባር ትእዛዛት የሚልዋቸውም አሉ፡፡ ጌታችን የሌሎችን ሕይወት መቀየርንና ለሌሎች መኖርን *“ የምድር ጨው ናቸሁ”* ብሎ የተሰጠንን ኃላፊነት ሲነግረን ፤ ለሌሎች አርአያ መሆንንም *“የዓለም ብርሃን ናችሁ ”* በማለት አስተምሮናል፡፡

## ሕግጋተ ወንጌል(ማቴ.5፡17-48)

እነዚህ ሕግጋት ኦሪትን ፍጹም ያደረገባቸው ናቸው ፡፡ *“ እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም”* (ማቴ.5፡17) ይህን ማድረግ ያስፈለገበትም አይሁድ በተሳሳተ መንገድ ኦሪትን ተረድተው ወደ ማስመሰል ስለሄዱ ነው ፡፡ የጌታችን ደቀ መዛሙርት የሆኑት ክርስቲያኖች ግን ጽድቃቸው ከጻፎች እና ከፈሪሳውያን እንዲበልጥ አዘዛቸው፡፡ (ማቴ.5÷20) ሕገ ኦሪትን እንዴት ፍጽምት እንዳደረጋትም ከሰንጠረዡ አነጻጽሩ፡-

| | ኦሪት | ወንጌል |
|---|---|---|
| 1. | አትግደል | ስድብ ቂም እና ቁጣ አይገቡም |
| 2. | አታመንዝር | አትመኙ |
| 3. | የሚፈታ የፍች ጽሕፈት ይስጥ | ካለዝሙት አትፋቱ |
| 4. | በሐሰት አትማል | ፈጽማችሁ አትማሉ |
| 5. | ዓይን ስለ ዓይን | ክፉውን በበጎ መመለስ |
| 6. | ባልንጀራህን ውደድ ጠላትህን ጥላ | ጠላትህን ውደድ |

የሕጉ ፍጻሜም *“የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ እናንተም ፍጹማን ሁኑ፡፡”* ማቴ5÷48 የሚል ነው፡፡

www.zeorthodox.org

## አንቀጸ ምጽዋት ጸሎት እና ጦም (ማቴ.6፡1-ፍጻሜ)

ጾም ፣ ጸሎት እና ምጽዋታችን እንደ ግብዞች እና አሕዛብ ለታይታ እንዳይሆን ጌታችን ሲያስተምረን *“በስውር የሚያይ አባትህ በግልጥ ይከፍልሃል”* ማቴ.6÷4፣6፣18 ብሎናል፡፡ ይህን ማድረግም በማይወሰድብን ቦታ ማስቀመጥ ነው፡፡ ከግብዝነት መራቅም በጤናማ ዓይን ተመስሎአል፡፡ የምጽዋት እንቅፋት የሚሆነው ገንዘብን መውደድም እግዚአብሔርን የሚገዳደር ጌታ

ነውና ለአንዱ ተገዙ ብሎናል ፡፡ ከዚህ በቀረው ጥያቄያችንን በእምነት በጸሎት ከማቅረብ ውጪ መጨነቅ አይገባም፡፡

**ጥንቃቄና ምርጫ(ማቴ.7÷1-ፍጻሜ ምዕራፍ)**

የተራራው ስብከት ማጠቃለያ ሲሆን በዚህ ምዕራፍ የሚከተሉት ነጥቦች ተነሥተዋል፡፡

**ሀ. አለመፍረድ እና ጥንቃቄ፡-**

ከመንፈሳዊ ውድቀት ምክንያቶች አንዱ በሌሎች መፍረድ ነው፡፡ ስለሆነም "አትፍረዱ" ብሎ ለሌሎች በምናስተላልፈው እንድንጠነቀቅም ***"ከውሾች ተጠበቁ"፣ "እንቁዎቻችሁን በእርያዎች ፊት አትጣሉ"*** ብሎ ፍሬያማ ትእዛዝ ሰጥቶናል፡፡

**ለ.የሕይወት መንገድ፡-**

ወደ ሕይወት የሚያደርሰው መንገድ የጠበበ ደጅ ቀጭን መንገድ ነው ፡፡ ለመሄድ የሚፈልጉትም ጥቂቶች ናቸው፡፡ እኛም ግቡ ተብለናል፡፡ (ማቴ.7፡13-14) ነገር ግን በዚህ የሕይወት መንገድ የማንሄደው በቀጭንዋ መንገድ ለመሄድ ባለመፈለጋችን ብቻ ሳይሆን እውነተኛ የሚመስሉ ሐሰተኖች ስላሉም ነው፡፡ በትዕግሥትና በማስተዋል የሚመራ ሐሰተኞችን በፍሬያቸው መለየት ይችላል፡፡(ማቴ.7፡15-20)

እውነተኛ የክርስቶስ ተከታዮች ስንሆንም የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንፈጽማለን እንጂ በአንደበት ብቻ ‹‹ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ›› አንልም፤ ይህም ከፍርድ አያድንም ፡፡ (ማቴ.7፡21-23) ስለዚህ ቃሉን ሰምቶ መፈጸም በመልካም አለት ላይ እንደታነጸ ቤት በመከራ ጊዜ ያጸናናል፡፡ (ማቴ.7፡24-27)

**ሐ. ተገረሙ፡-**

www.zeorthodox.org

ይህ የጌታችን ትምህርት ሲያልቅ**"ሕዝቡ በትምህርቱ ተገረሙ እንደ ጻፎቻቸው ሳይሆን እንደ ባለ ሥልጣን ያስተምራቸው ነበርና"**፡፡(ማቴ.7፡28) አዎን በመለኮታዊው ሥልጣኑ ኦሪትን የሰጠ ወንጌልንም በሥልጣኑ ሠርቶልናል፡፡

**ማጠቃለያ ፡-** የማቴዎስ ወንጌል ከምዕራፍ 5-7 ጌታችን ሕገ ወንጌልን የሰጠበትን ትምህርት የያዘ ነው፡፡

**ተግባር ፡-** የመጽሐፉን ሙሉ ቃል አንብቡ።

***ጥያቄዎች፡-***

1. ጌታችን በተራራ ላይ ስለአስተማረው ‹‹የተራራው ስብከት›› በመባል የሚታወቀው የማቴዎስ ወንጌል ክፍል ስንት ምዕራፎች ይዟል? ምዕራፎቹን ጥቀሱ።
2. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሊቃውንት መምህራን ‹‹የተራራው ስብከት››ን ምን ብለው ይጠሩታል?
3. ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የገለጸልን የብፅዕና ትምህርቶች ስንት ናቸው? በዝርዝር ግለጽ።
4. ጌታችን ሕገ ኦሪትን ፍጽምት ያደረገበትን የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 5፡20፤ በሕገ ኦሪት እና በወንጌል እያነጻጸራችሁ በሰንጠረዥ ሠርታችሁ፤ ለመምህራችሁ አቅርቡ።

www.zeorthodox.org

# መላእክት

## አርባ አራተኛ ሳምንት

***ዓላማ፡-*** ተማሪዎች ስለ መላእክት ተፈጥሮ እና ተልእኮ አውቀው፤ በመምህሩ ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች ማብራሪያ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠናጥቅስ፡-*“ የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል ያድናቸውማል፡፡”*** መዝ. 34፥7

***ተጨማሪ ምንባብ፡-*** መጽሐፈ ሥነ ፍጥረት እና አምስቱ አዕማደ ምሥጢራት፡፡

**መግቢያ፡-** መላእክት በመጀመሪያው ቀን የተፈጠሩ ረቂቃን ፍጥረታት ናቸው፡፡ በዚህ ትምህርታችንም ስለ መላእክት አፈጣጠር ፣ ተልእኮ እና በሕይወታችን ስላላቸው ሚና እንማራለን፡፡

**ትምህርቱ፡-** መልአክ የግእዝ ቃል ሲሆን መልእክተኛ ማለት ነው፡፡ የተፈጠሩት እሑድ ሌሊት በመጀመሪያ የፍጥረት ቀን ነው፡፡ እግዚአብሔር መላእክቱን በሰማይ ፈጥሮ ተሰወረባቸው፡፡ ማን እንደፈጠራቸው መጠየቅ ጀመሩ፡፡ ከመላእክት መካከል ሳጥናኤል በማዕርግ ከሁሉ ይበልጥ ስለነበረም እኔ ነኝ የፈጠርኳችሁ ብሎ ዋሸ፡፡ ይህም በመላእክት መካከል ልዩነትን ፈጠረ፡፡ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ‹‹***የፈጠረንን እስክናውቅ በየአለንበት እንጽና***›› ብሎ አረጋጋቸው፡፡ ነገር ግን አንዳንዶቹ ሳጥናኤልን ሲከተሉ በመላእክት መካከል ጦርነት ተፈጠረ፡፡ ይሄን ጦርነት ወንጌላዊው ዮሐንስ እንዲህ ብሎ ገልጾታል፡-***“ በሰማይ ሰልፍ ሆነ፤ሚካኤል እና መላእክቱ ዘንዶውን ተዋጉ፡፡ ዘንዶውም ከመላእክቱ ጋር ተዋጋ አልቻላቸውምም፤ ከዚያም ወዲያ በሰማይ ስፍራ አልተገኘላቸውም፡፡ ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው፣ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀድሞው እባብ ተጣለ፤ ወደ ምድር ተጣለ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ፡፡”*** ራእ. 12፥7-9

www.zeorthodox.org

በሰማይ ዘጠኝ የመላእክት ማዓርጋት አሉ፡፡እነርሱም፡-

1.ኪሩቤል 3. መናብርት 5. ኃይላት 7. ሊቃናት

2. ሱራፌል 4. ሥልጣናት 6. መኳንንት 8. አርባብ 9. መላእክት ናቸው፡፡

የመላእክት ማዓርጋት እና ስሞች እነዚህ ሲሆኑ በተለምዶ /በአብዛኛው/ መላእክት ተብለው ይጠራሉ፡፡ እነርሱም የሚከተሉት ሓላፊነት እና ተልእኮ አላቸው፡፡

1. መላእክት እግዚአብሔርን በሰማይ ያመልካሉ፤የመጀመሪያው የመላእክት ሥራ እግዚአብሔርን ማመስገን/ማምለክ/ ነው። ካለ ዕረፍት ያለማቋረጥ ያመሰግኑታል ፤ ከሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ይሄን መረዳት እንችላለን።" *አራቱም እንስሶች እያንዳንዳቸው ስድስት ክንፎች አሏቸው፤ በዙሪያቸውና በውስጣቸው ዓይኖች ሞልተውባቸዋል፣ ቅዱስ፣ቅዱስ፣ቅዱስ የነበረውና ያለው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ፤ እያሉ ቀንና ሌሊት አያርፉም። እንስሶቹም በዙፋን ላይ ለተቀመጠው ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም በሕይወት ለሚኖረው ለእርሱ ክብርና ውዳሴ ምስጋናም. . . እየሰገዱ፦ ጌታችንና አምላካችን ሆይ አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና ስለፈቃድህም ሆነዋልና ተፈጥረውማልና ክብር ውዳሴ ኃይልም ልትቀበል ይገባሃል፤ እያሉ አክሊላቸውን በዙፋኑ ፊት ያኖራሉ።"* (ራእ.4÷8-11)

*መላእክት የሰው ልጆችን ይረዳሉ፤* መላእክት ረዳቶቻችንም ናቸው። ቅዱስ ጳውሎስ "*መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው፣ ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት አይደሉምን* " ዕብ.1÷14 ብሎ አስተምሮናል።በተጨማሪም ቅዱስ ጴጥሮስን ከእስር ቤቱ እንዳወጡት /የሐዋ.ሥ.12÷6-17/ ሎጥን ከሰዶም ጥፋት እንዳተረፉት (ዘፍ.19÷12-22 ተጽፏል።

*በመንፈሳዊ ሕይወታችን መከራ ሲያጋጥመን ያድኑናል፤* ይህንን መዝሙረኛው ዳዊት *"የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል ያድናቸውማል"* (መዝ.34÷7) ሲል ገልጾታል።

*መላእክት ይጠብቁናል ይንከባከቡናልም፤* እግዚአብሔር ለሙሴ " *በመንገድህ ይጠብቅህ ዘንድ እኔ ወደ አዘጋጀሁትም ሥፍራ ያገባህ ዘንድ፣እነሆ እኔ መልአኩን በፊትህ እሰዳለሁ* " ዘጸ.23÷20 ብሎት ነበር። በመልአኩ መሪነትና ጠባቂነትም አርባ ዓመት በበረሐው ተጉዘዋል። እያንዳንዳችንም ጠባቂ መላእክት አሉን፣ ስለኛ ይጸልዩልናል። *"ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን እንዳትንቁ ተጠንቀቁ፤መላእክቶቻቸው ዘወትር በሰማያት ያለውን የአባቴን ፊት ያያሉ እላችኋለሁና።"* ማቴ. 18÷10

www.zeorthodox.org

*መላእክት የእግዚአብሔር ትእዛዝ የሚክዱትን /የማይፈጽሙትን/ ይቀጣሉ።* እግዚአብሔር ሙሴን *"በፊቱ ተጠንቀቁ፣ቃሉንም አድምጡ ፣ ስሜም በእርሱ ስለሆነ ኃጢአትን ብትሠሩ ይቅር አይልምና አታስመርሩት።"* (ዘጸ.23÷21)እግዚአብሔር ሰዶምና ገሞራን እንዲያጠፉ መላእክትን ልኮ ነበር። /ዘፍጥ19/ ካህኑ ዘካርያስን ዲዳ አድርጎ ቀጥቶት ነበር።/ሉቃ1÷20-22፣/

*መላእክት ከእግዚአብሔር የምሥራች ቃልን ያመጡልናል።*የጌታችንን መፀነስና መወለድ ለእመቤታችን ያበሠራት ቅዱስ ገብርኤል ነው።(ሉቃ.1÷26-38) እረኞችን የጌታን መወለድ

ያበሠራቸው የጌታ መልአክ ነበር፡፡ሉቃ2÷8-14

***መላእክት ጸሎታችንን ወደ እግዚአብሔር ያሳርጋሉ፡፡*** የሚከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ መላእክት ጸሎታችንን እንዳሚያሳርጉ ያስተምረናል፡፡“ ***የዕጣኑም ጢስ ከቅዱሳን ጸሎት ጋር ከመልአኩ እጅ በእግዚሐብሔር ፊት ወጣ፡፡”*** ራእ.8÷4

***ያስተምሩናል፤*** "***ዳንኤል ሆይ ጥበብና ማስተዋልን ልሰጥህ አሁን መጥቻለሁ ፤ አይቼው የነበረው ገብርኤል….አስተማረኝ ተናገረኝም እንዲህም አለኝ”*** (ዳን.9÷21-22)

***ያማልዱናል፤ “ የእግዚአብሔር መልአክ መልሶ፣ አቤቱ የሠራዊት ጌታ ሆይ፣ እነዚህ ሰባ ዓመት የተቆጣሃቸውን ኢየሩሳሌምንና የይሁዳን ከተሞች የማትምራቸው እስከ መቼ ነው? አለ፡፡ እግዚአብሔርም መልሶ ከእኔ ጋር ይነጋገር ለነበረው መልአክ በመልካምና በሚያጽናና ቃል ተናገረው፡፡”*** ዘካ.1÷12

**ማጠቃለያ** መላእክት በመጀመሪያው የፍጥረት ቀን የተፈጠሩ ረቂቃን ፍጥረታት ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ በሳጥናኤል ሐሰት ምክንያት ሐሰተኛውን ሳጥናኤልን ተከትለው ከክብራቸው ተዋርደዋል፡፡ በዚህም በሰማይ ሰልፍ ሆኗል፡፡ በቅዱሳን መላእክት ዘጠኝ ማዓርጋት አሉ፡፡ እነዚህ መላእክት እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ /ያመልካሉ፡፡/ እኛን ይጠብቃሉ፤ ይረዱናልም፡፡ ከእግዚአብሔርም መልእክት ያመጡልናል ፣ ያበሥሩናል ፡፡ ስለ እኛም ይጸልያሉ ያማልዳሉም፡፡

**ጥያቄዎች፡-**

1. በመጀመሪያው ቀን የተፈጠሩተ እነማን ናቸው?
2. በመላእክት መካከል ልዩነት የተፈጠረው ለምንድን ነው?
3. ‹‹የፈጠረንን እስክናውቅ በየአለንበት እንጽና›› ብሎ መላእክትን ያረጋጋቸው መልአክ ማን ነው?
4. ዘጠኙን የመላእክት መዓርጋት ዘርዝሩ፡፡
5. የመላእክትን ሓላፊነት እና ተልእኮ በአጭሩ አብራሩ፡፡

www.zeorthodox.org

# እግዚአብሔርን ወደ መውደድ የሚመሩን ተግባራዊ መንገዶች

## አርባ አምስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** *ተማሪዎች ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር የሚያሳድጉ እና የሚያጸኑ መንገዶችን አውቀው፤ በክፍል ውስጥ ያብራራሉ።*

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***" ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን ባርኪ፣ አጥንቶቼም ሁሉ፣ የተቀደሰ ስሙን።"*** *መዝ.* 102(3)፡1

**የትምህርቱ ትኩረት፡-**ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር በዚህ ምድርም ሆነ በዘላለማዊ ሕይወታችን በደስታ ለመኖር ጠቃሚ ነው።

በዚህ ትምህርታችንም እግዚአብሔርን የበለጠ እንድንወደው ስለሚረዱን መንገዶች ትኩረት ሰጥተን እንማራለን። እግዚአብሔርን የበለጠ ለመውደድ የሚረዱን መንገዶች፡-

**ሁሌም የእግዚአብሔርን በረከቶችና የሰጣችሁን ሁሉ አስታውሱ !**

እግዚአብሔር በሚያስፈልጋችሁ ሁሉ የረዳችሁን አስቡ። አሁን ላላችሁበት እንድትደርሱ ያገዛችሁ እርሱ እግዚአብሔር ነው። ባላችሁ ነገር ሁሉ (ቤተሰብ ፣ ትምህርት ፣ ጤና ) የባረካችሁም እርሱ ነው።ወደ ቤቱ እንድትመጡ ጠራችሁ ፣ ቅዱስ ቊርባንን እንድትቀበሉና ሌሎች በረከቶችን እንድታገኙም ፈቀደላችሁ። እንደ ነቢዩ ዳዊትም ***"ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን ባርኪ፣ አጥንቶቼም ሁሉ ፣ የተቀደሰ ስሙን "*** የሚለውን አንብቡ። እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ሰጥቶናል፤ ጤና ፣ ቤተሰብ ፣ የሚመራን መንፈስ ቅዱስ እና ምቾት...

**ስትጸልዩ ፣ በሙሉ ልባችሁ ጸልዩ እንዲሁም የፍቅር ቃላትን ተጠቀሙ!**

በጸሎታችሁ የምትናገሩትን መልካም ነገር አስቡት። ሐሳባችሁ ሁሉ ሳይበታተን በተረጋጋ መንፈስ ከልባችሁ ጸልዩ። ስተጸልዩም እግዚአብሔር እንደሚወዳችሁ፣ በልባችሁ እንዲያድርና በመንፈስ ቅዱስ እንድትሞሉ ለምኑ፣ በፍጹም ልባችሁ እንድትወዱትም እንዲረዳችሁ አጥብቃችሁ ጸልዩ።

www.zeorthodox.org

**ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር በመታዘዝ እንጀምር።**

ለእግዚአብሔር ስንታዘዝ፣ የተናገረንን እንፈጽማለን፤ በዚህም ሰላምን፣ ደስታን እና በሕይወታችን ትርጉም እናገኛለን። ይህም የበለጠ እግዚአብሔርን እንድናውቀውና እንድንወደው

ያደርገናል፡፡

**እግዚአብሔርን ለመውደድ ከፈለጋችሁ ስለርሱ አንብቡ፤ ራሳችሁንም ለእግዚአብሔር ስጡ፡፡**

ስለእግዚአብሔር ለማወቅና ለማሰብ ስለ እርሱ ቅዱስ ቃሉን ከቅዱሳት መጻሕፍት የበለጠ አንብቡ ፡፡ ለእርሱ ስታነቡና ስታስቡም አእምሮኣችሁ እና ልባችሁ ቀስ በቀስ ከእግዚአብሔር ጋር ይሆናል ፤ ትወዱትማላችሁ፡፡ ***" የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፣ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው፤ በዚያን ጊዜም መንገድህ ይቃናልሃል ይከናወንልሃልም፡፡*** " (ኢያ.1፡8)

**እግዚአብሔርን የበለጠ ለመውደድ እግዚአብሔርን የሚቃወሙትን ነገሮች አስወግዱ፡፡**

ከቁሳዊና ክፉ ነገሮች ራቁ ፣ ኃጢአትና ስድብም ተው፣ ወደ ሕይወታችሁ እንዳይገባም ተጠንቀቁ፡፡***"ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለ ሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ፣ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም፡፡"*** (ዮሐ. 2፡15-16)

***ያጋጠማችሁ ችግር ምንጭ እግዚአብሔር እንደሆነ አታስቡ፡፡***

***"ማንም ሲፈተን በእግዚአብሔር እፈተናለሁ አይበል ፤ እግዚአብሔር በክፉ አይፈትንምና እርሱ ራሱስ ማንንም አይፈትንም፡፡ ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል፡፡ "*** *ያዕ.* 1፣13 እግዚአብሔር ክፉ ነገር አይሰጠንም፡፡ ያጋጠሙን አሳዛኝ ነገሮች ሁሉ ምንጫቸው እግዚአብሔር አይደለም፡፡ እግዚአብሔር መልካም ነው የሚሰጠንም መልካም ነገሮችን ነው፡፡ ክፉ ነገር ሲያጋጥማችሁም እግዚአብሔርን አትውቀሱ፡፡ ይህ የኃጢአታችንና የስሕተታችን ውጤት ሊሆን ይችላል፡፡ ወይም የሌሎች ስሕተት ችግሩን ፈጥሮብን ይሆናል፡፡

***መስቀሉን ካለማቋረጥ ተመልከቱ፤ እግዚአብሔር ለሁሉም ያለውን ያልተገደበ ፍቅር አስቡ***

***"እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛ እንወደዋለን፡፡"*** 1ኛ ዮሐ. 4፣19

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ ፡-

ክርስትና በፍቅር ላይ የተመሠረተ ነው፡፡***"እግዚአብሔር ፍቅር ነው፣በፍቅርም የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል፤ እግዚአብሔርም በእርሱ ይኖራል"*** (1ኛ ዮሐ. 4፡16)

ከላይ የተጠቀሱትን የምንፈጽመው ከእግዚአብሔር ጋር እውነተኛ ግንኙነት እንዲኖረን ነው፡፡

እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ያለው ዓላማ ፍቅር ነው፡፡ እግዚአብሔር ትእዛዛትን የሰጠን ለማዘዝ

ብቻ አይደለም ወይም መንግሥተ ሰማያትን መውረስ አስቸጋሪ እንዲሆንብን አይደለም፡፡

በዙሪያችን ላሉ ሰዎች መልካም መሆንንና መውደድን መለማመድ አለብን፡፡ ይህም ወደ ፍቅረ እግዚአብሔር የሚያደርስን መንገድ ነው፡፡

## *ተግባራዊ ጥያቄ*

*መምህር ተማሪዎችን በቡድን ይከፋፍሏቸው፡፡*

እግዚአብሔርን የበለጠ እንድንወደው የሚረዱንን መንገዶች በዝርዝር እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡

በዝርዝር ከጻፏቸው እግዚአብሔርን እንድንወደው ከሚረዱን መንገዶች በየቡድኑ አንድ አንድን በማከፋፈል በክፍል ውስጥ እንዲያብራሩ ያድርጓቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ቅዱስ ኒቆላዎስ - ሊቀ ጳጳስ - (Santa claus)

## አርባ ስድስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ** ፡- ተማሪዎች ከቅዱስ ኒቆላዎስ ታሪክ፤ ቅዱሳንን በሚገባ አውቀን እንድናከብራቸው እና እኛም እግዚኣብሔርን እንዴት ደስ እንደምናሰኘው ተገንዝበው፤በመምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ያብራራሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ**፡-"የታመንህ ሁን የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ፡፡"(ራእ. 2፡10-11)

**ተጨማሪ ምንባብ** መጽሐፍ ቅዱስ (የተሰጡትን ጥቅሶች በሚገባ አንብብዋቸው)፤ የታኅሣሥ 10 መጽሐፈ ስንክሳር

**መግቢያ፡-** በዛሬው ትምህርታችን እግዚአብሔርን በፍጹም ልቡ በተከተለው ቅዱስ ኒቆላዎስ መንፈሳዊ ሕይወት ተመሥርተን እንማራለን፡፡ ወደ ዋናው ትምህርት ከመግባታችን በፊት ስለ ቅዱስ ኒቆላዎስ /ሳንታ ክላውስ/ (Santa claus) የምታውቁትን ለመምህር አስረዱ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

**ልደትና እድገቱ፡-** ኒቆላዎስ - የሕዝብ አሸናፊ ማለት ነው፡፡ ሀገሩ ሜራ ሲባል በጥንትዋ ሊቅያ (lycia)በዛሬዋ ቱርክ የምትገኝ ታሪካዊት ከተማ ናት፡፡ ኒቆላዎስ አባቱ ኤጲፋንዮስ እናቱ ዮና ይባላሉ፡፡ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ባዕለጸጎች ነበሩ፡፡ ልጅ ግን አልነበራቸውም፡፡ እግዚአብሔር ልጅ እንዲሰጣቸው ሲለምኑ ኖረው መውለጃቸው ሲያልፍ ልመናቸውን ተዉ፡፡ ሥራው ድንቅ የሆነ ፈጣሪያችን ልዑል እግዚአብሔር ግን ጊዜውን ጠብቆ ልጅ ሰጣቸው፡፡ ስሙንም ኒቆላዎስ አሉት፡፡ ሲወለድ በታየው በሕጻንነቱ በነበረው መንፈሳዊ ሥራ ሁሉም ይደነቁ ነበር፡፡ ትኩረቱም የሕይወት ምንጭ የሆነው መንፈሳዊው ምግብ ቃለ እግዚኣብሔርን መመገብ ነበር፡፡ ኒቆላዎስ ዕድሜው ሲደርስ ወላጆቹ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት እንዲማር ላኩት፡፡

www.zeorthodox.org

**መንፈሳዊ አገልግሎት፡-** ትምህርቱን በሚገባ አጠናቆ መንፈሳዊ ሥራን በየቀኑ የሚጨምር

ሆነ። የአጎቱ ልጅ በአበምኔትነት እያገለገለ ወዳለበት ቦታም ሄዶ በድንግልና መኖር ጀመረ። ኒቆላዎስ በፍጹም ተጋድሎ እየኖረም በ19ዓመቱ ቅስና ተቀበለ። እግዚአብሔርም ድንቅ ተአምራትን መፈጸምን ድውያንንም የመፈወስ ጸጋ ሰጠው፤ በተሰጠው ጸጋም፡- ከሰዎችና ከሚያመልኳቸው ዛፎች አጋንንት አወጣ፤ በርካታ በሽተኞችንም ፈወሰ፤ ትንሽ እንጀራ ባርኮም ብዙ ሕዝብ መገበ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ‹‹***የተጨነቁትንም ራሳችሁ ደግሞ በሥጋ እንዳለ ሆናችሁ አስቡ።***›› (ዕብ.13፡3) ተብሎ እንደተጻፈም ፤ አራት ሴት ልጆች የነበሩትንና ከሀብታምነት ወደ ፍጹም ድህነት የተሸጋገረን ሰው ረድቶታል።

***ታሪኩም እንዲህ ነው፡-*** ይህ ሰው ሴቶች ልጆችን መዳርና መመገብ ስላቃተው በዝሙት እንዲኖሩ ቤቱን የዝሙት ቤት ሊያደርግ ሲዘጋጅ አባ ኒቆላዎስ በእግዚአብሔር ጸጋ አውቆ ወደዚህ ሰው ቤት በሌሊት ሄደ። ወንጌል ‹‹***ስጡ ይሰጣችሁማል፤በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ተመልሶ ይሰፈርላችኋልና***›› (ሉቃ.6፡38) እንዳለ በመጀመሪያ 100 ወርቅ ዲናር በበሩ ሥር አስቀምጦለት ተሰወረ። በዚህም ጌታችን ‹‹***አንተ ግን ምጽዋት ስታደርግ ምጽዋትህ በስውር እንዲሆን ቀኝህ የምትሠራውን ግራህ አትወቅ ፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል***›› (ማቴ. 6፡3-4) ያለውን ቃል ፈጸመ። ሰውየው ጠዋት ሲነሣ የወርቅ ዲናሩን አገኘና ፈጣሪውን አመስግኖ የመጀመሪያይቱን ልጅ ዳራት።

ለሁለተኛ እና ሦስተኛዋም አባ ኒቆላዎስ ተደብቆ ሰውየዉን ረዳው ፤ ሰውየዉም እግዚኣብሔርን አመስግኖ ልጆቹን ዳረ። በመጨረሻም ሰውየዉ ገንዘቡን የሚሰጠው ማን መሆኑን ለማወቅ ነቅቶ ሲጠብቅ ቅዱሱ እንደተለመደው ወርቁን አስገብቶ ሲሄድ ደረሰበት። አባ ኒቆላዎስ መሆኑን ሲያውቅም እግሩ ላይ ወድቀው ከልጁ ጋር አመሰገኑት።ወንጌል በዚህ ምድር ብቻ ከሰው የሚመሰገኑ ‹‹***ዋጋቸውን ተቀብለዋል***›› እንዳለ ሰማያዊውን ዋጋ እንዳያስቀሩበት እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ ነግሮአቸው ሄደ።

www.zeorthodox.org

***ጽጽስና ፡- "ማንም ኤጲስ ቆጶስነትን ቢፈልግ መልካምን ሥራ ይመኛል የሚለው ቃል የታመነ ነው።" 1ኛ .ጢሞ.3፡1***

ኒቆላዎስ በሕልሙ ዙፋንና የከበረ የክህነት ልብስ ሲሰጠውና ልብሱን ለብሶ በዙፋኑ እንዲቀመጥ ሲያዘውም አየ።***ዳግመኛም*** እመቤታችን የክህነት ልብስ ጌታችንም ወንጌል ሲሰጡት አየ። የሚራ ኤጲስ ቆጶስ ሲያርፍም፣ የእግዚአብሔር መልአክ ለሮሙ ሊቀጳጳሳት ተገልጦ በሚራ

መንበር የሚተካው አባ ኒቆላዎስ መሆኑን ነገረው፡፡ ያም ሊቀጳጳሳት ለሕዝቡ ነገራቸው ፤ አምነውም አባ ኒቆላዎስን በሀገራቸው ኤጳስ ቆጶስነት ሾሙት፡፡ምእመናንን በታማኝነት እያገለገለም ሰይጣን በቤተ ክርስቲያን ላይ ተነሣ፡፡

ፈተና፡-በዘመነ ዲዮቅልጥያኖስ ክርስቲያኖችን የሚያሳድድ እና ጣዖት እንዲያመልኩ የሚያስገድድ ዓዋጅ ወጣ፤ቅዱስ ኒቆላዎስም ምእመናን እግዚኣብሔርን በማመን እንዲጸኑ ያስተምር ነበር፡፡ በራእየ ዮሐንስ "**ልትቀበለው ያለህን መከራ አትፍራ፡፡እነሆ እንድትፈተኑ ዲያብሎስ ከእናንተ አንዳንዶቻችሁን በወኅኒ ሊያገባችሁ አለው፡፡………እስከሞት ድረስ የታመንህ ሁን የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ፡፡መንፈስ ለአብያተ ክርስትያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ፡፡ድል የነሣው በሁለተኛው ሞት አይጎዳም**" ራእ.2፡10-11 ተብሎ እንደተነገረ፤ ዲዮቅልጥያኖስ ምንም ጥፋት ሳያገኝበት አቡነ ኒቆላዎስን በብዙ መከራ አሰቃየው ፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን እንደ ቅዱስ ቃሉ አጸናው፤ ስቃዩም አልጎዳውም፡፡

ማሰቃየቱ ያልጠቀመው እና የሰለቸው ዲዮቅልጥያኖስም ቅዱሱን አሰረው፡፡ አቡነ ኒቆላዎስ በእስር እያለ፣ ለወዳጆቹ የሚፈርድላቸው እግዚአብሔር የቅዱሳኑን ትዕግሥት ተመልክቶ ዲዮቅልጥያኖስ ተሸነፈ፡፡ ታላቁ ቆስጠንጢኖስ በሮም መንበረ መንግሥት ተተካ፡፡

***‹‹ሥራህን አውቃለሁ፤ እነሆ በአንተ ፊት የተከፈተ በር ሰጥቼአለሁ ማንምም ሊዘጋው አይችልም፤ ኃይልህ ምንም ትንሽ ቢሆን ቃሌን ጠብቀሃልና፣ስሜንም አልካድህምና›› ራእ. 3፡8*** ተብሎ እንደተጻፈም ቆስጠንጢኖስ ካስፈታቸው ቅዱሳን አንዱ ይህ ቅዱስ አባት አቡነ ኒቆላዎስ ነበር፡፡ከእስር ወጥቶ ወደ ሌላው የሕይወቱ ምዕራፍ፤ጌታችን ወደ ከፈተለት የአገልግሎት በር ተሰማራ፡፡

ወደ መንበረ ጵጵስናው ተመልሶ ምእመናንን እና አምላኩን በብርቱ አገለገለ፡፡ አርዮስ ሲነሣ በኒቅያ ጉባዔ ከነበሩት ሦስት መቶ ዐሥራ ስምንቱ ሊቃውንት አንዱ ይህ ቅዱስ ነው፡፡ ከዚያም ያማረ ተጋድሎውን ፈጽሞ በጵጵስናው ብቻ ከአርባ ዓመት በላይ አገልግሎ ዐረፈ፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ፡-

መጽሐፍ ቅዱስ ‹‹***የጻድቅ መታሰቢያ ለዘላለም ይኖራል - ለበረከትም ነው*** ፡፡›› (መዝ.111 (112)፡6፤ምሳ.10፡7) እንዳለ፤ ቅዱስ ኒቆላዎስ - ሊቀጳጳስ በቤተ ክርስቲያናችንና በሌሎች አኃት

አብያተ ክርስቲያናትም በየዓመቱ ታኅሣስ ዐሥር ቀን ይታሰባል፡፡

የምዕራባውያኑ ሳንታ ክላውስ ትውፊትም ከዚህ ቅዱስ ታሪክ ይነሣል ፤ ነገር ግን ከታሪኩ እንዳየነው ቅዱስ ኒቆላዎስ ድሆችን አጽናኝ ትርፍ ሳይሻም ሰዎችን ያስደሰተ እንጂ በዘመናችን እንደሚታየው የንግድ እና ሥጋዊ ማታለያ የሠራ አልነበረም፡፡

### ምን ተማርን ?

የቅዱስ ኒቆላዎስ ቤተሰቦች እስከ መጨረሻው በመተማመን ኖሩ፤ በእነሱ ዕውቀት ተስፋ ቆርጠው አብቅቶለታል ያሉት የልባቸውን ፍላጎት የሚፈጸምበት ጊዜም በእግዚአብሔር የታሰበ ነበር፡፡በእውነትም እርሱ ስጦታውን የሚሰጥበት ጊዜ አለው ፤ ***ለሁሉም ዘመን አለው*** መክ.3፡1 ብሎናልና ተስፋ ባለመቁረጥ እንጠብቀው፡፡

ቅዱስ ኒቆላዎስ ፈጣሪዉን ከልጅነቱ ጀምሮ ተከተለው ፤ እግዚኣብሔርም በጸጋ ጎበኘው ፤ ከፍ ከፍም አደረገው፡፡‹‹***የጭንቀት ቀን ሳይመጣ በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ፤ደስ አያሰኙም የምትላቸውም ዓመታት ሳይደርሱ›› መክ.12፡1*** ተብለናልና፤ እኛም እግዚኣብሔርን የምናገለግልበት ዘመን አሁን ነው፡፡

ለሰዎች መልካም እናድርግ፤ በተለይም ለተቸገሩ፡፡ የልደት መልእክትም ይሄው ነው፡፡ሁሉም የእርሱ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በከብቶች በረት የተወለደው የተቸገረውን የሰው ልጅ ባለጸጋ ለማድረግ ነው፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹***የተጨነቁትንም ራሳችሁ ደግሞ በሥጋ እንዳለ ሆናችሁ አስቡ***›› ዕብ.13፡3 ብሎ እንዳስተማረን፤ አቡነ ኒቆላዎስ ከተቸገሩት እኩል ተጨንቆ የሚችለውን አደረገ፡፡እኛም የገና ስጦታን ከቅዱሱ አባት በተማርነው መሠረተ ማድረግን እንማራለን፡፡

"***በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው፤ ከተፈተነ በኋላ ለሚወዱት ተስፋ ስለ እርሱ የሰጣቸውን የሕይወት አክሊል ይቀበላልና*** " (ያዕ.1፡12) ቅዱስ ኒቆላዎስ ስለጸና እግዚኣብሔር አከበረው፡፡ እኛም እግዚኣብሔር እንደማይተወን አውቀን መጽናትን እንማራለን፡፡

የቅዱሳንን ታሪክና መልካም ተጋድሎ በተገቢው መንገድ ብናከብረው ከጻድቁ በረከት እናገኝበታለንና ምሳ.10፡7 የቅዱሳንን በዓላት በመንፈሳዊ መንገድ ማሰብ አለብን፡፡‹‹**እንግዲህ እነዚህን የሚያህሉ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን ካሉልን፤እኛ ደግሞ ሸክምን ሁሉ ቶሎም የሚከበንን**

www.zeorthodox.org

ኃጢአት አስወግደን፣የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን፣በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ›› ዕብ.12፡1-2 ።ቅዱሳን ክርስቶስን መስለውታልና 1ኛ.ቆሮ.11፡1 በተግባር ብንከተላቸው ክርስቶስን እናገኘዋለን፡፡

ቅዱስ ኒቆላዎስ (Santa Claus)የእምነት፤የልግስና፤የእውነት እና ለእግዚኣብሔር እና ለቤተሰብ የመታዘዝ ሕይወትን ያሳየ የመንፈሳዊው ተጋድሎ አርኣያችን ነው፡፡ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን ፤ እኛንም በቅዱስ ኒቆላዎስ ጸሎት ይጠብቀን ፣ በረከቱም ትደርብን አሜን!!

## ጥያቄዎች

1. ‹‹ኒቆላዎስ›› ማለት ትርጉሙ ምንድነው?
2. የቅዱስ ኒቆላዎሰ አባትና እናት ስማቸው ማን ይባሉ ነበር?
3. ቅዱስ ኒቆላዎስ የየት ሀገር ጳጳስ ነበር?
4. ክርስቲያኖችን የሚያሳድድ እና ጣዖት እንዲያመልኩ የሚያስገድድ ዓዋጅ የወጣው በማን የአገዛዝ ዘመን ነው?
5. ቅዱስ ኒቆላዎስ ያጋጠመው ፈተና ምን ነበር? በማን ዘመን?

www.zeorthodox.org

# የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ (፩) መግቢያ

## አርባ ሰባተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለ ኢትዮጵያውን የሃይማኖት ታሪክ አውቀው፤ ከክርስትና በፊት ስላለው የኢትዮጵያ የሃይማኖት ታሪክ ያብራራሉ።

**የሚጠናጥቅስ፡-** *" የእስራኤል ልጆች ሆይ እናንተ ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን ይላል እግዚአብሔር "* አሞ.9፡7

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ አቡነ ጎርጎርዮስ ፤ Ancient and Medieval Ethiopian history/ prof. .sirgew hableselase pp 89-113/

**መግቢያ፡-** በዛሬው ትምህርታችን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ስናጠና ፤ ቅድመ ክርስትና የነበራትን ሃይማኖታዊ ታሪክ አስቀድመን እናያለን።

### የሳምንቱ ትምህርት፡-

### ኢትዮጵያ ቅድመ ክርስትና፡-

የኢትዮጵያን ታሪክ ክፍል ስናጠና ሁለት ዓይነት የሃይማኖት መልክ እናገኛለን። በአንዱ እግዚአብሔር (ለአብርሃም በተገለጠው አምላክ) የሚያምኑ እና በጣዖታት የሚያምኑ ኢትዮጵያውያን ታሪክ።

www.zeorthodox.org

በአንድ አምላክ(monothestic)፡ ኢትዮጵያውያን አማኞች እንደ ነበሩ እና ለአብርሃም በተሰጠው ተስፋ በሙሴም ሕግ እና መሥዋዕት አቀራረብ እግዚአብሔርን ሲያመልኩ መኖራቸውን በሚከተሉት ምንጮች እንረዳለን።

#### መጽሐፍ ቅዱስ

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢትዮጵያውያን እና ስለ ኢትዮጵያ ከአርባ ጊዜ በላይ ጠቅሶአል።

***መልክአ ምድራዊ መገኛዋን፡-*** ከኤደን ገነት የሚፈልቁ አራት ወንዞች ከሚያጠጡዋቸው በአንዱ ከግዮን (ዓባይ) ነው፡፡ይህንንም ***"እርሱም የኢትዮጵያን ምድር ሁሉ ይከባል"*** ዘፍ 2÷13 ሲል ይገልጠዋል፡፡

እግዚአብሔር እስራኤል ከአሕዛብ ጋር እንዳይጋቡ ሲያዝ ምክንያቱ አሕዛብ እስራኤላውያንን ወደ ጣዖት አምልኮ እንዳይስብዋቸው ነበር፡፡ የሙሴ ሚስት ኢትዮጵያዊት ስለሆነች አሮንና ማርያም ሲቃወሙ ግን እግዚአብሔር ኢትዮጵያዊትዋን ለሙሴ ፈቅዶለታል፡፡ ምክንቱያም የሙሴ ሚስት እንደ ሩት እግዚአብሔርን ታመልክ ስለ ነበር ነው፡፡ ዘኍ 12÷1

እስራኤል አርባ ዓመታት በበረሐ ሲጓዙ የቃል ኪዳኑን ታቦት ማረፊያ ይመራቸው የነበረው የኢትዮጵያ ሰው ነበር፡፡ ዘኍል. 10÷29 — 34 ሲያጠፉም በነቢያት ተገሥጸዋል፡፡ሶፎ 2÷12 2ዜና 14÷9

ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች ተብሎ ተተንብዮላታል ይህም ተፈጽሞል፡፡ መዝ.67(68)÷31

የኢትዮጵያ ሕዝቦች ቀለም በነብር ዥንጉርጉርነት ተመስሎ በመጽሐፍ ቅዱስ ተነግሯል፡፡ኤር.13÷23፣

ብዙ ወንዞች ከሚፈልቁባት(The Water Tower of Africa) ምድር ከኢትዮጵያ ለእግዚአብሔር እጅ መነሻ የሚቀርብበት ዘመን እንደሚመጣ ኢሳይያስ ነቢይ ተናግሮ ነበር፡፡ኢሳ. 18፡1-7

በእግዚአብሔር የተወደዱ የሃይማኖት ሰዎች የነቢያት ወዳጆችም ነበሩ፡፡ኤር.38 እና 39

ኢትዮጵያውያን በዘመነ ብሉይ የእግዚአብሔር ሕዝብ ከሚባሉት ጋር የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው የተጠቀሱ ሕዝቦች ናቸው፡፡ አሞጽ 9÷7

www.zeorthodox.org

ኢትዮጵያውያን ለእግዚአብሔር ንጹሕ መሥዋዕት እንደሚያቀርቡ ተተንብዮአል፡፡ እስራኤል ወንጌልን ሲገፉዋት እና ሐዋርያት ወደ አሕዛብ ፊታቸውን ዘወር ሲያደርጉ ከአሕዛብ የመጀመሪያው አማኝ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ነበር (የሐዋ. 8፡26-40) ይህ የንግሥት ህንደኬ ባለ ሙሉ ሥልጣን ሹም ወደ ኢየሩሳሌም የሄደው ***ሊሰግድ*** ነበር፡፡ የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍም ያነብ ነበር ፡፡ ይህ ሁሉ ድርጊቱም በእስራኤል አምላክ በእግዚአብሔር እምነት እና ተስፋ እንደሚኖር ያመለክተናል፡፡

ይህም ወደ ቀጣዮቹ ማስረጃዎች ያሸጋግረናል፡፡

**ኦሪታዊ ምልክቶች**

እግዚአብሔር ለሙሴ በመገለጡ የተገኙ በሌላው ዓለም የሌሉ በቤተ እስራኤል ብቻ የሚገኙ ሃይማኖታዊ ትውፊቶች በኢትዮጵያ ይገኛሉ ፡፡ ይህም ኢትዮጵያ ቅድመ ክርስትና የነበራትን ሃይማኖታዊ ታሪክ ያመለክተናል፡፡

**የኦሪት መሠዊያዎች በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች መገኘት፡፡** በአክሱም ፣ በጣና ቂርቆስ ፣ ብርብር ማርያም …… ወ.ዘ.ተ ያሉት፤ ለኦሪት መሥዋዕት የሚያገለግሉ መሠዊያዎች ጥንታውያን ቅርሶች ለዚህ ማስረጃዎች ናቸው፡፡

**ኦሪታዊ ልማድና ሥርዓቶች በሕዝቡና በቤተ ክርስቲያን መኖሩ፡፡**

ግርዛት ፣ በለቅሶ ቤት መሰባሰብ ፣ የሚበሉና የማይበሉ እንስሳትን መለየት ፣ በአራስ ቤት መንጻትን መጠበቅ ወዘተ. . . ሕዝቡ ወደ ክርስትና ሲገባ ከኦሪታዊ ልማዱ የያዛቸው ናቸው፡፡

የመቅደስ ሥርዓት (የታቦት ሥርዓት ፣ ልብሰ ተክህኖ ፣ መጋረጃ ፣ የቤተ መቅደሱ ክፍሎች ) ፤ ሁለት ሰንበታት (ቅዳሜ እና እሑድ)ን ማክበር ፣ የሕንጻ ቤተ ክርስቲያን አሠራር ወ.ዘ.ተ…. ከሌላው ዓለም ክርስትና ተለይቶ በእኛ ቤተ ክርስቲያን ብቻ መኖራቸው ኢትዮጵያን ከኦሪት ወደ ወንጌል የተሸጋገረች ብቸኛ ቤተ ክርስቲያን ያደርጋታል፡፡

## ትውፊት

በቤተ ክርስቲያን ትውፊት መሠረት በኢትዮጵያ በዘመነ ብሉይ የኦሪት መጻሕፍት ፣ ታቦት እና መሥዋዕት እንደነበረና ሕያው እግዚአብሔር ይመለክ እንደ ነበር የሚገልጡ ትውፊቶች አሉ ፡፡ ከእነዚህም ፡-

www.zeorthodox.org

የኖኅ ልጆች ምድርን ሲካፈሉ ማዕከላዊው የዓለም ክፍል ለካም በደረሰው መሠረት ከካም ልጆች አንዱ ኩሽ ወደ አሁንዋ የኢትዮጵያ ምድር ሲመጣ የአያቱን የኖኅን እምነት ይዞ ገብቶአል፡፡ ለዚህም የዕብራይስጡ ብሉይ ኪዳን ኢትዮጵያን የኩሽ ምድር ብሎ መጥራቱ ዋና አብነት ተደርጎ ይቀርባል፡፡

ንግሥተ ሳባ /አዜብ/ ፡፡ እንደ ዜና መዋዕል አጠራር ንግሥተ ሳባ በወንጌል ንግሥተ አዜብ /የደቡብ ንግሥት/ ትባላለች፡፡ ሁለቱም ስያሜዎች የንግሥትነት ቦታዋን ያመለክታሉ፡፡ (የሳባውያን

ንግሥት እና የደቡብ ንግሥት) ክብረ ነገሥት የተባለው የኢትዮጵያ ታሪክ መጽሐፍም በቤተሰብ ስምዋ ማክዳ ይላታል፡፡ ይህች ንግሥት ወደ ንጉሥ ሰሎሞን ስለ መሄድዋ፡- በእግዚአብሔር ስም የወጣለትን ዝና ስለ ሰማች ፤ በእንቆቅልሽ ትፈትነው ዘንድ እና ከብዙ ውድ ስጦታዎች ጋር ሄዳ ነበር ፡፡ (1ኛነገሥት 10፡1-10) ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ ለፍርድ ሲመጣ የእምነት ምልክት አድርጐ የሚያቀርባት ንግሥተ ሳባን / አዜብን/ ነው፡፡ ማቴ 12÷42 ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ጥበብ ፈልጋ ከሩቅ አገር ወደ ኢየሩሳሌም ስትመጣ አይሁድ ግን ከሰሎሞን የሚበልጠውን ክርስቶስን በአካባቢያቸው ሲመላለስ ስለ አላመኑበት ነው፡፡ በዚህ መሠረት ወደ ንጉሥ ሰሎሞን ሄዳ ባየችው ***"እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን "*** 1ኛ ነገ.10፡9 ብላ እግዚአብሔርን ስታመሰግን፤ ለንጉሡ ያቀረበችለትን ጥያቄዎችም አንድም ሳይቀር መለሰላት፡፡ስጦታዎችዋንም መጽሐፍ ቅዱስ ***"የሳባም ንግሥት ለንጉሡ ለሰሎሞን እንደሰጠችው ያለ የሽቱ ብዛት ከዚያ ወዲያ አልመጣም ነበር፡፡"*** 1ኛነገ.10፡10 ካለን በኋላ በአጸፋው ንጉሡ ሰሎሞንም ***"በገዛ እጁ ከሰጣት ሌላ የወደደችውን ሁሉ ከእርሱም የለመነችውን ሁሉ ለሳባ ንግሥት ሰጣት "*** 1ኛ ነገሥ.10፡13 ሲል ይተርክልናል፡፡ ከእነዚህም አንዱ በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ያለው የዴር ሱልጣን ገዳም ነው፤ በማለት ታሪክ እና ትውፊተ ቤተ ክርስቲያን ያስረዳሉ፡፡ ይህም ኢትዮጵያን በኢየሩሳሌም የቦታ ይዞታ ያላት ብቸኛ የጥቁር አፍሪካ ሀገር አድርጎአታል ፡፡

**ቀዳማዊ ምኒልክ** ንግሥተ ሳባ ከንጉሥ ሰሎሞን ቀዳማዊ ምኒልክን ፀንሳ ወደ ሀገርዋ ተመለሰች ፤ ከሀገርዋ ስትደርስም ወለደችው፡፡ ስሙንም የብልሃተኛ ልጅ ስትል እብን አል ሐኪም / ምኒልክ/ አለችው፡፡ ምኑልክ ከእናቱ ጋር አድጐ ዐሥራ ሁለት ዓመት ሲሆነው አባቱን ንጉሥ ሰሎሞንን ለማየት ወደ ኢየሩሳሌም ወረደ፡፡ ሕገ ኦሪትን፣ ሕገ መንግሥት፣ የእብራይስጥን ቋንቋ እየተማረ ሦስት ዓመት ተቀመጠ፡፡ከዚያም ከብዙ የተማሩ እስራኤላውያን ጋር ወደ ሀገሩ ሰደደው፡፡ እነርሱም ሕገ ኦሪትንና መሥዋዕቱን ይዘው ወደ ኢትዮጵያ በ 950 ዓ.ዓ ገደማ / ከክርስቶስ ልደት በፊት/ ገቡ፡፡ የሊቀ ካህናቱ ሳዶቅ ልጅ አዛርያስ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር አብሮ ነበርና ፤ የቃል ኪዳኑ ታቦት ያን ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ገብቶአል፡፡

**ጣዖት አምልኮ (ልማዳዊ እምነቶች)፡፡**

ኢትዮጵያ ከላይ እንደ ተገለጠው በአንድ እግዚአብሔር የሚያምኑ ሕዝበ እንደ ነበሩባት በአፍ እና በመጽሐፍ ያየነውን ያህል፤ ጣዖት አምላኪያን እና አጋንንታዊ አሠራሮችን የሚከተሉም እንደ

www.zeorthodox.org

ነበሩ እና እንዳሉም ከታሪክ ከነባራዊ ክስተት እና ከትውፊት እንረዳለን፡፡ ከእነዚህም፡-

**ሀ.ባህላዊ እምነቶች**፡፡ ከቤተሰብ ተይዘው እንደ ባህል ከተፈጥሮ ጋር ተቆራኝተው የሚታመኑ ከወላጅ ወደ ልጅ የሚሸጋገሩ ባዕድ አምልኮቶች ናቸው ፡፡ ጨሌ ፣ ዛር …በሰሜን፣ ኢሬቻ የመሳሰሉት በደቡብ አሉ፡፡

**ለ.ጣዖት አምልኮ**፡፡ ከጥንቱ የየሃ ቤተ መቅደስ እና የአዱሊስ አብያተ ጣዖታት በኢዛና ሐውልት እስከ ተጠቀሰው ማሕረም ያሉት ጣዖታት ቅድመ ክርስትና በሀገሪቱ ከኦሪት ጎን አምልኮተ ባዕድ እንደ ነበር ማስረጃዎች ናቸው ፡፡

## ማጠቃለያ፡-

*ሀገራችን ኢትዮጵያ ቅድመ ክርስትና ከእስራኤል ጋር አንድ እግዚአብሔርን የሚያምኑ የእግዚአብሔር ወገኖች የነበሩባት ብቸኛ የአሕዛብ (ከእስራኤል ውጪ) ያለች ሀገር ናት፡፡ ከዚሁም ጋር ጣዖታትን የሚያመልኩ ሰዎችም ነበሩ፡፡*

## ተግባር፡-

ንግሥተ ሳባ የእግዚአብሔርን ጥበብ ሰምታ ወደ ኢየሩሳሌም እንደሄደች እኛም በእግረ ልቦና ጥበብ ሁሉ የእርሱ ሰለሆነ ጥበብ ወደ ተባለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእምነት እንጓዛለን፡፡

ስለ ሀገራችን ትክክለኛ እውቀት እንዲኖረን የአባቶችን ትውፊት እና መጻሕፍትን እንማር፡፡ ያልገባንን በመጠየቅም እውነቱን ከስሕተቱ እንለይ፡፡

***መዝሙር፡-***

ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር

እንዘ ትብል አምላኪየ አምላኪየ ነጽረኒ ወአድኀነኒ እም ኃይለ ጸላኢ ወጸር፡፡

www.zeorthodox.org

***ጥያቄዎች፡-***

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን ከተጠቀሱት ውስጥ የተወሰኑትን ጥቅሶች ግለጹ፡፡

ከእስራኤል ውጪ ወንጌልን የተቀበለው እና የመጀመሪያው በወንጌል አምኖ የተጠመቀው ሰው

ማን ነው? በዚህ ዘመን የኢትዮጵያ ንግሥት የነበረችው ማን ትባላለች?

ኢትዮጵያ ከክርስትና መምጣት /ከክርስቶስ ልደት በፊት/ በኦሪት እግዚአብሔርን ታመልክ እንደነበር የሚገልጡ /የሚያሳዩ/ ማስረጃዎችን ጥቀሱ።

የኦሪት መሠዊያዎች አሁን ድረስ በኢትዮጵያ የሚገኙባቸውን ቦታዎች ግለጹ።

በእግዚአብሔር ስም የወጣለትን ዝና ሰምታ በእንቆቅልሽ ትፈትነው ዘንድ ብዙ ውድ ስጦታዎችን ይዛ ወደ እስራኤል ንጉሥ ሰሎሞን ዘንድ የሄደችው የኢትዮጵያ ንግሥት ማን ትባላለች? ከንጉሥ ሰሎሞን የወለደችው ልጅስ ስም ማን ይባላል?

የቃል ኪዳኑ ታቦት፣ ታቦተ ጽዮንን ከሕገ ኦሪት እና ከካህናቱ ጋር ይዞ ወደ ኢትዮጵያ የገባው /የመጣው/ ማን ነው?

www.zeorthodox.org

# የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ (፪) የክርስትና አጀማመር

## አርባ ስምንተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ እንዴት እንደገባ እና እንደተስፋፋ ያውቃሉ፤ በመምህሩ ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ።

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። እነሆ ውኃ እጠመቅ ዘንድ የሚከለክለኝ ምንድ ነው ? "*** የሐዋ. 8፡36

***ተጨማሪ ምንባባት፡-***የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፤ አቡነ ጎርጎርዮስ ፤ Ancient & Medieval Ethiopian History /Sirgew Hableselase, pp 89-113/pr.

***መግቢያ፡-*** ባለፈው ትምህርታችን ኢትዮጵያ ቅድመ ክርስትና የነበራትን ሃይማኖት አይተናል። ዛሬ የክርስትናን መግባት እና መስፋፋት እንማራለን።

www.zeorthodox.org

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

### ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ እንዴት ገባ ?

**በዓለ ሃምሳ**

ለመቶ ሃያው ቤተሰብ መንፈስ ቅዱስ በወረደበት ዕለት ከኢትዮጵያ የሄዱ አይሁድ ወደ ይሁዲነትም የገቡ ኢትጵያውያን ነበሩ፡፡ በመጀመሪያው ቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት መጀመሪያ ካመኑት መካከል ኢትዮጵያውያን እንደነበሩ የገለጠው ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በጥምቀት ስብከቱ የሚከተለውን ብሏል፡-*“ ለሐዋርያት መንፈስ ቅዱስ በወረደበትና ሦስት ሺሕ ሕዝብ በተጠመቁበት ዕለት ኢትዮጵያውያንም በቦታው ነበሩ፡፡ ቅዱስ ሉቃስ ያልጠቀሳቸው ቍጥራቸው ጥቂት ስለሆነ ነው፡፡…”* (ዮሐንስ አፈወርቅ፤)

**ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ፡-**

በግብረ ሐዋርያት እንደ ተጻፈው፤ ለቅዱስ ጴጥሮስ አሕዛብን ማጥመቅ በራእይ ከመገለጡ በፊት ፤ ቅዱሳን ሐዋርያት ከእስራኤል ውጪ ባደረጉት ስብከት የመጀመሪያው ተጠማቂ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ነው፡፡ (በኢትዮጵያ ድርሳናት ባኮስ ወይም አቢላክ ይባላል ) ባኮስ የኢትዮጵያይትዋ ንግሥት ህንደኬ ግዛት ባለ ሙሉ ሥልጣን ነበር፡፡ የሮም እና የይሁዳ ነገሥታት እና ሹማምንት ክርስትናን ሲያሳድዱ*“ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው፡፡ …..እነሆ ውኃ እጠመቅ ዘንድ የሚከለክለኝ ምንድ ነው ? ”*ብሎ ያመነ የመጀመሪያውም ከፍተኛ ባለሥልጣን ነው፡፡ ለዚህም ነው የዓለም የቤተክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊው አውሳብዮስ *“ከእስራኤል ወገኖች ውጭ መጀመሪያ የተጠመቀው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ነው፡፡ እርሱም ሄዶ ለወገኖቹ ሰበከ፡፡ በዚህም በመዝሙረ ዳዊት ላይ ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች የሚለውን ትንቢት ፈጸመ ”* ያለው፡፡

www.zeorthodox.org

በቤተ ክርስቲያን ትውፊት መሠረትም ሥልጣኑን ትቶ በቤተ መንግሥት አካባቢ በተለያዩ የኢትዮጵያ ግዛቶች እና በውጭ እስከ ሕንድ አስተምሮ በሰማዕትነት ዐርፏል፡፡

ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ አስመልክቶ የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን አባቶች እና ታሪክ ጸሐፊዎች ጽፈዋል፡፡ *“ኢትዮጵያውያን የአይሁድ ቤተሰብነት ከሌላቸው የዓለም ክርስቲያኖች መካከል የመጀመሪያዎቹ የወንጌል ፍሬዎች ናቸው፡፡”* /አውሳብዮስ ዘቂሣርያ/

**አቡነ ሰላማ ፡-**

ሀገራችን ኢትዮጵያ ክርስትናን የተቀበለችው በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ ነው ሆኖም ቢሆንም በሲኖዶስ ሕግ የኤጲስ ቆጶስነት መንበር ያገኘችው ፤ በሶርያዊው በአቡነ ሰላማ / ፍሬምናጦስ / አማካኝነት በ350 ዓ.ም ነው። ፍሬምናጦስ ከ20ኛው የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ ከአትናቴዎስ ጵጵስና ከተቀበለ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሷል። ከዚያም ፡-

የወንጌልን ትምህርት ለሕዝቡ በስፋት የሚያዳርሱ፣ የሚያጠምቁና የሚያቆርቡ ካህናትና ዲያቆናትንም ሾመ ።

በአብርሃ ወ አጽብሐ አማካኝነት አያሌ አብያተ ክርስቲያናትን አሳነጸ።

በዘመኑ የኢትዮጵያ ግዛት ወደ ነበሩት ወደ ኑብያ ፣ አኑና እና ሜርዌ አምስት ቀሞሳትን በመላክ ትምህርተ ወንጌል እንዲሰበክ ቤተ ክርስቲያን እንዲስፋፋ አድርጓል።

ቅዱሳት መጻሕፍትን ከሱርስት፣ ከዕብራይስጥ እና ከግሪክ ወደ ግእዝ እንዲተረጐሙ አድርጓል። የቅዳሴ መጽሐፍ አዘጋጀ።

የሳባውያንን የፊደል አቀማመጥ በመለወጥ ከግራ ወደ ቀኝ የመጻፍንና የማንበብን ዘዴ ያስተማረው አቡነ ሰላማ /ፍሬምናጦስ/ እርሱ ነው ።

በአክሱም ማኅበረ ጽዮንን አቋቁሞ ክርስትና እንዲስፋፋ በማስተማሩ ***"ከሣቴ ብርሃን ሰላማ "*** የሚል ቅጽል አግኝቷል።

ክርስትና በኢትዮጵያ አስፋፍቶ ሐምሌ 26 ቀን 356 ዓ.ም ዐረፈ።

**ሊቀ ካህኑ እንበረም /ሕዝበ ቀድስ / እና የአክሱም ትምህርት ቤት፡-**

እንበረም በቀዳማዊ ምኒልክ ጊዜ ታቦተ ጽዮንን ይዘው ከመጡት የአዛርያስ የልጅ ልጆች አንዱ ነው። በኢትዮጵያ የነበሩትን ምኵራባት በአክሱም ሆኖ ያስተዳድር ነበር። የሁለት ልጆች አባት ሲሆን በዘመነ ሐዲስ ክርስትናን ተቀብሎ ኤጲስ ቆጶስ ሆኗል። የኤጲስ ቆጶስነቱ ስምም ***"ሕዝበ ቀድስ "*** ይባላል። በኢትዮጵያ ግዛቶች እና እስከ ሰሜን ምሥራቅ አፍሪካ ድረስ ወንጌልን ሰብኮ ዐርፎአል።

www.zeorthodox.org

በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያ ካህናት ተልእኮ እስከ ሰሜን አፍሪካ ደርሶ እንደ ነበር ሲነስየስ / 370 ዓ.ም / የተባለው ታሪክ ጸሐፊ በ 122ኛው ደብዳቤው ***"ኢትዮጵያውያን ካህናት***

*ከሰሜን አፍሪካዋ ቀሬና ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ነበራቸው "* በማለት ጽፏል፡፡

**አብርሃ ወ አጽብሃ**

ቅዱሳን ነገሥት ኢዛናና ሳይዛና / አብርሃ ወ አጽብሐ/ በኢትዮጵያ ታሪክለሁለት ኢትዮጵያን በፍቅር የመሩ ወንድማማቾች ነበሩ፡፡ ክርስትናን ከተቀበሉ ወዲህ አብርሃ ወ አጽብሐ ተባሉ ፤ በ350 ዓ.ም ክርስትናን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት አድርገው ዓወጁ ፡፡

አብርሃ እና አጽብሐ ካሠሯቸው አብያተ ክርስቲያናት ፡- አክሱም ጽዮን፣ መርጦ ለማርያም ፣ ተድባበ ማርያም ወዘተ… ከምኵራብነት ወደ ቤተ ክርስቲያንነት ተለውጠዋል፡፡ የቅድስት አርሴማ የአቡነ ሰላማና በስማቸው የተገደሙ ገዳማት አሉ፡፡ ከዚህም ሌላ ስብከተ ወንጌልን በሀገሪቱ ውስጥ አስፋፍተዋል፡፡ ለንጉሥ ቆስጠንጢኖስና ለንግሥት እሌኒ በጻፉት ደብዳቤ መሠረት በኢየሩሳሌም ያሉን ቅዱሳት መካናት እንዲመለስልን አድርገዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ከመጀመሪያዎቹ የክርስትና መነኮሳት መካከል የሆኑት መነኮሳት በዚያ ይኖሩ ነበር፡፡ በ386 ዓ.ም በቤተልሔም ከተማ የነበረው ሄሮኒመስ - ማርሴላ ለተባለች ወጣት በጻፈላት ደብዳቤ፤ ***"ከሕንድ ከፋርስ እና ከኢትዮጵያ በየጊዜው ብዙ መነኮሳት ይመጣሉ"*** በማለት ኢትዮጵያውያን በኢየሩሳሌም ያለንን ጥንታዊ ታሪክ መስክሯል፡፡

**የአርዮሳዊው ቴዎፍሎስ ተልእኮ ወደ ኢትዮጵያ ፡-**

ከታላቁ ቆስጠንጢኖስ በኋላ በቁስጥንጥንያ የነገሠው ኮንስታንቲዩስ በእምነቱ አርዩሳዊ በመሆኑ የአርዮስ ኑፋቄ ቀንደኛ ደጋፊ የነበረውን ጊዮርጊስ ዘቀጰዶቅያን የእስክንድርያ ፖትርያርክ አድርጐ ሹሞት ነበር፡፡ በመሆኑም ቀደም ሲል በቅዱስ አትናቴዎስ የተሾመው ፍሬምናጦስ ወደ አርዮሳዊው ፓትርያርክ መጥቶ ትምህርቱን እንዲያስመረምርና ሹመቱንም እንደገና እንዲያስባርክ ለኢትዮጵያውያን ነገሥታት ቴዎፍሎስ በተባለ ሕንዳዊ ቄስ እጅ ደብዳቤ ላከ፡፡ የኢትዮጵያ ነገሥታት ግን አልተቀበሉትም፡፡ ቅዱስ አትናቴዎስም በተጋዘበት ቦታ ይህንን ዜና ሲሰማ ለነገሥታቱ የምስጋና ደብዳቤ እንደጻፈ ይተረካል፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ፡-

ኢትዮጵያውያን ከመጀመሪያዎቹ አማንያነ ወንጌል ናቸው፡፡ በበዓለ ሃምሳ ስለነበሩት እና ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ተምረናል፡፡

በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የመጀመሪያው ጳጳስ አቡነ ሰላማ ተሹሞ ሲመጣ ምስጢራተ

ቤተ ክርስቲያን መፈጸም ጀመሩ ።

ቅዱሳኑ ነገሥታት አብርሃ እና አጽብሐ፤ ቅዱስ አትናቴዎስ እና አቡነ ሰላማ ክርስትና በሀገራችን እንዲዳረስ ያደረጉ ሦስቱ ማዕዘናት ናቸው።

## ምን ተማርን

ለእግዚአብሔር ጥሪ እና ቃል ዛሬውኑ መልስ መስጠትን ከኢትጵያዊው ጃንደረባ እና ከአቡነ ሰላማ ሕይወት እንማራለን።

በማንኛውም ደረጃ መንፈሳዊ አገልግሎት መፈጸምን። ከሁለቱ ነገሥታት እንማራለን።

**ተግባር፡-** በአካባቢያችሁ ያሉትን ያላመኑ ሰዎች አስተምሩ።

## ጥያቄዎች፡-

በሐዋርያት ሥራ እንደተጻፈው፤ ቅዱሳን ሐዋርያት ከእስራኤል ውጪ ባደረጉት ስብከት የመጀመሪያው ተጠማቂ ማነው?

ሀገራችን ኢትዮጵያ በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን መግቢያ በጃንደረባው አማካኝነት ክርስትናን ከተቀበለች በኋላ በሲኖዶስ ሕግ የኤጲስ ቆጶስነትን መንበር ስታገኝ የመጀመሪያው ጳጳስ ማን ነው?

አቡነ ሰላማ /ፍሬምናጦስ/ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ካከናወናቸው ተግባራት አምስቱን ዋና ዋና ተግባራት ግለጹ።

በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የቅድስና መዓርግ የተሰጣቸው፤ ኢትዮጵያን ለሁለት በፍቅር ያስተዳደሩ ቅዱሳን ወንድማማች ነገሥታት እነማን ናቸው?

www.zeorthodox.org

# አስተርእዮ

## አርባ ዘጠነኛ ሳምንት

ዓላማ፡- ተማሪዎች ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ እና የጥምቀትን ዓላማ መማር አውቀው፤ በመምህሩ የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ያብራራሉ፡፡

የሚጠና ጥቅስ፡-*"እኔስ ለንስሓ በውኃ አጠምቃችኋለሁ! ጫማውን እሸከም ዘንድ የማይገባኝ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታል! እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም ያጠምቃችኋል!"* ማቴ 3÷11

ምንባባት፡- ማቴ 3፣ ማር.1፣ ሊቃ. 3÷፣ ዮሐ 1÷29-34

**መግቢያ፡-** የመጨረሻው ነቢይ የካህኑ ዘካርያስ እና ኤልሳቤጥ ልጅ ዮሐንስ ስለ ንስሐ እየሰበከና እያጠመቀ በዮርዳኖስ ነበር፡፡

ሕዝቡ ስለራሱ ሲጠይቁትም *"እኔ ለንስሐ በውኃ አጠምቃችኋለሁ፡፡ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔ በፊት ነበር፡፡ የእግሩን ጫማ ልፈታ የማይገባኝ ነው ያልኳችሁ ይሄ ነው፡፡ እርሱም በውኃና በመንፈስ ያጠምቃችኋል፡፡ እኔ በበረሐ ለጌታ መንገድን አቅኑ ብሎ የሚጮኽ ድምፅ እኔ ነኝ"* አላቸው፡፡ ሕዝቡ ጌታችንን እንዲቀበሉና እንዲዘጋጁ መንፈቀ ዓመት ቀድሞ መንገድ ጠርጓል፡፡

ዛሬ በዚህ ላይ ተመሥርተን ስለ ጥምቀትና ዘመነ አስተርእዮ እንማራለን፡፡

## ትምህርቱ፡-

www.zeorthodox.org

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሠላሳ ዓመት ሲሞላው በዮሐንስ እጅ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ ሄደ፡፡

ዮሐንስ ግን እኔ ባንተ ልጠመቅ ይገባኛል ብሎ ከለከለው፡፡ ጌታችን *" አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና "* አለው፡፡ ማቴ.3÷15 ዮሐንስም አጠመቀው፡፡ ጌታችን ተጠምቆ ከውኃ ሲወጣም ÷ሰማያት ተከፈቱ፡- መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳያ ከሰማይ ወረደ፤ ‹‹ይህ

የምወደው ልጄ ነው፤ እርሱንም ስሙት›› የሚል ድምፅ ከሰማይ ተሰማ፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ በተጠመቀበት ዕለት እግዚአብሔር በአንድነት በሦስትነቱ ተገለጠ፡፡ እግዚአብሔር አብ ስለ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ በመመስከር ተገለጠ፡፡ ወልድ በዮርዳኖስ ባሕር በመጠመቅና በአባቱ እየተመሰከረለት በሥጋ ሲገለጥ፤ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በርግብ አምሳል በወልድ ላይ በማረፍ ተገለጠ፡፡

በዚህም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነቱን በመግለጥ የሰው ልጆችን በትሕትና ማገልገል ጀመረ፡፡ የተጠመቀበት አንዱ ምክንያትም የራሱን አባቱና የመንፈስ ቅዱስን መገለጥ ነበር፡፡ሌላው ምክንያት ደግሞ ምሳሌ ሊሆነንና ትንቢቶችን ለመፈጸም ነበር፡፡ በእኛ ቤተ ክርስቲያን በዓለ ጥምቀት ጥር 10ና 11 ቀን ሲከበር! ከልደት በኋላ ያለውን ወቅትም እስከ ጾመ ነነዌ ‹‹ዘመነ አስተርእዮ›› /የመገለጥ ዘመን/ ብለን እናከብረዋለን፡፡

በምዕራብውያን (Epiphany) መገለጥ ተብሎ ይከበራል፡፡ ይህም መገለጥ የአምላክ ሦስትነት ፣ የጌታ ማስተማር በገሀድ መውጣት የመሳሰሉትን የሚያካትት ነው፡፡

## መደምደሚያ /ማጠቃለያ/፡-

ከዚህ ትምህርት የሚከተሉትን ነጥቦች እንማራለን፡፡

**ንሰሓ፡-** መጥምቁ ዮሐንስ "***መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሓ ግቡ***" በማለት አስተምሮ ነበር፡፡ ንሰሓ ከልባችን በመጸጸት ኃጢአትን መተው፣ መናዘዝና ወደተውነው ኃጢአት ላለመመለስ መወሰንም ነው፡፡ በዚህም በክርስቶስ አዲስ ሕይወት እናገኛለን፡፡

**ትሕትና፡-**ዮሐንስ እንደገለጠው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእርሱ ይበልጣል÷ብቻም ሳይሆን ጌታውና አምላኩም ነበር፡፡ የሰማይና የምድርም ፈጣሪ ነው ፤ ነገር ግን እርሱ ወደ ዮሐንስ ሄዶ ሲጠመቅ ትሕትናን ሊያስተምር ነው፡፡ ለዚህም ነው "***ጽድቅን ሁሉ ልንፈጽም ይገባናል***" ያለው፡፡ ከጌታ ትሕትናን ከዮሐንስ መታዘዝን ተምረናል፡፡

www.zeorthodox.org

**በምሳሌ ማስተማር፡-** ጌታችን በቃል ብቻ አላስተማረንም በተግባርና በቃልም ምሳሌ በመሆን አስተማረን እንጂ፡፡ በዚህም በዕለታዊ ኑሮአችን መልካም ምሳሌ እንድንሆን አርአያ ሆኖ አስተምሮናል፡፡

**አስተርእዮ፡-** መገለጥ ማለት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ሦስትነት፣ የጽድቅን ሥራ ለማስተማር

መታየት በጌታችን የተፈጸሙበት ወቅትም ነው፡፡

***ጥያቄዎች፡-***

ስለ ንስሐ እየሰበከና እያጠመቀ በዮርዳኖስ የነበረው የመጨረሻው ነቢይ ማን ነው? እናትና አባቱስ ማን ይባላሉ?

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮርዳኖስ ወንዝ በመጥምቁ ዮሐንስ እጅ ሲጠመቅ የተፈጸመውን በዝርዝር አብራሩ፡፡ እግዚአብሔር በአንድነት በሦስትነቱ ተገለጠ ሲባል ምን ማለት ነው? አብራሩ፡፡

በቤተክርስቲያናችን ዘመነ አስተርእዮ ብለን የምናከብረው ከመቼ እስከመቼ ያለውን ጊዜ/ወቅት/ ነው?

‹‹አስተርእዮ›› ማለት ምን ማለት ነው?

ንስሐ ማለት ምን ማለት ነው? አብራሩ፡፡

www.zeorthodox.org

# ተስፋ

## ሃምሳኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለ ተስፋ ምንነት እና ክርስትና የጽኑ ተስፋ ሃይማኖት መሆኑን ያውቃሉ፤ በመምህሩ የሚሰጣቸውን ጥያቄዎች ያብራራሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለፈሰሰ ተስፋ አያሳፍርም፡፡"*** ሮሜ 5÷5

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ‹‹የተስፋ ሕይወት›› በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ

**መግቢያ፡-** ክርስትና የተስፋ ሕይወት ነው፡፡ ተስፋውም በምድር ስንኖር የምናምነው እና ጌታችን ይመጣል ብለን የምንጠብቀው የዘላለም ሕይወት ነው፡፡ ይህን ለማግኘትም የአሁኑ ዘመን መከራ እና አጋጣሚ አያታልለንም፡፡ በዛሬው ትምህርታችን ስለ ተስፋ እንማራለን፡፡

### የሳምንቱ ትምህርት፡-

#### ለምን ተፈጠርን ?

ስለ ተስፋ ስንማር ለምን ተፈጠርን? እና ወዴት እንሄዳለን? የሚሉትን ጥያቄዎች መመልከት አለብን፡፡ የብዙዎች የዘመናት ጥያቄ የሆኑት እነዚህ ጥያቄዎች አንዳንዴ በተዛባ መንገድ ሲመለሱና የተሳሳተ ድምዳሜ ሲሠጥባቸው ማየት የተለመደ ነው፡፡ በሥነ ፍጥረት ታሪክ ትምህርታችን የሰው ልጅና ዓለሙ ከውስጡ ጋር መፈጠሩን ተመልክተናል፡፡

www.zeorthodox.org

በዚህም መሠረት ለጋስ የሆነው እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ሲፈጥር በምድር የሚመላለሱትን "ግዙአቸው" ብሎ ያሠለጠናቸው ሲሆን ፍጻሜውም "ሕያው ሆኖ እንዲኖር" ነው፡፡ በመጨረሻም የመንግሥተ እግዚአብሔር ወራሾቹ የክብሩም ተካፋዮች እንድንሆን ነበር፡፡ ነገር ግን የሰው ልጅ ‹‹አታድርግ›› የተባለውን በማድረጉ ወደቀ፡፡ ውድቀቱም ሞተ ሥጋ እና ሞተ ነፍስ አመጣበት፡፡ ከዚህ ለመውጣት ያደረገው ጥረት ስለ አላዳነው በተስፋ አምላኩን ለመነ፤ እግዚአብሔርም የማዳን ተስፋ ሰጠው፡፡

እግዚአብሔር ለሰው ልጅ በሰጠው ተስፋ መሠረት ጌታችን ተወልዶ አዳነን÷ በኂላ መጥቶም ጽድቅ ያለበትን ምድር እንደሚያወርሰን ተስፋ ሰጥቶናል። ያንንም ተስፋ እንጠባበቃለን። ተስፋ በእግዚአብሔር ሕልውና ያለንን እምነት እና መታመን የሚያመጣልን ኃይል ነው÷ በእርሱ በእግዚአብሔር ያለንን ሕይወትም ያስረግጥልናል። መዝ 23÷4፣ ዕብራ 13÷8

የተፈጠርነው የእግዚአብሔር ክብር ወራሾች ሆነን በዘላለም ሕይወት ለመኖር ነው። ዓለም በኃጢአቶች በመያዙ ከመጣብን ፍዳም ነጻ ወጥተናል ፤ ጉዞአችንም ወደ ዘላለማዊቱ ኑሮ የመዘጋጀት ነው። ይህንን የሰው ልጆች ክብርም ፍጥረት ከነፍሳችን ጋር ይጠባበቃል፡-***"ለእኛም ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን የአሁኑ ዘመን ስቃይ ምንም እንዳይደለ አስባለሁ የፍጥረት ናፍቆት የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ ይጠባበቃልና። ፍጥረት ለከንቱነት ተገዝቶአልና በተስፋ ስላስገዛው ነው እንጂ በፈቃዱ አይደለም ተስፋውም ፍጥረት እራሱ ደግሞ ከጥፋት ባርነት ነፃነት ወጥቶ ለእግዚአብሔር ልጆች ወደ ሚሆን ክብር ነጻነት እንዲደርስ ነው። ፍጥረት ሁሉ እስካሁን ድረስ አብሮ በመቃተትና በምጥ አብሮ መኖሩን እናውቃለንና። እርሱም ብቻ አይደለም ነገር ግን የመንፈስ በኵራት ያለን ራሳችን ደግሞ የሰውነታችን ቤዛ የሆነው ልጅነት እየተጠባበቅን በውስጣችን እንቃትታለን። በተስፋ ድነናልና ነገር ግን በተስፋ የሚደረግበት ነገር ቢታይ ተስፋ አይደለም፤የሚያየውንማ ማን ተስፋ ያደርገዋል? የማናየውን ግን ተስፋ ብናደርገው በትዕግሥት እንጠባበቃለን።"*** ሮሜ.8÷18-25

**የተስፋ ውጤት ፡-**

***ሀ. ተስፋ አዳዲስ ሐሳብ እና ሥራ የማመንጨት ኃይል ነው።***

ተስፋ ትክክለኛ ግብ ይሰጣል ፤ ወደ ግብ ለመድረስ እና ፍጻሜውን ለማግኘትም ጥረት ይኖራል። ነገን በተስፋ የሚያይና የሚጥር ከሚያጋጥሙት ችግሮች አልፎ መፍትሔ ያስባል። ተስፋ በሥራችንና በሕይወታችን በጎ አመለካከት ይፈጥርልናል። ቅዱሳን ለሚያሰቃዩዋቸው ምሕረት እና ፍቅርን የመመኘት ኃይል ያገኙት ከተስፋቸው ከኢየሱስ ክርስቶስ ነበር። (የሐዋ.7) ተስፋ በመከራዎች በትዕግሥትና በጽናት እንድንቆም ያበረታናል።***"በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለፈሰሰ ተስፋ አያሳፍርም።"*** ሮሜ 5÷5

www.zeorthodox.org

***ለ. ተስፋ ለሥነ ልቦናዊ እድገት እና ብቃት ያደርሰናል።***

ግባችን ከፍ ያለና ሩቅ ሲሆን ተስፋ ፣ ትዕግሥት እና ጽናትን በውስጣችን ያመነጫል። ይህም በአጸፋው በአስተሳሰባችን እና በፍላጐታችን ብስለት እንዲኖረን ያስችለናል። ለእውነተኛው

እድገት እና ብቃት የደረሰም ጌታችን ***"ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል"*** ማቴ.6÷33 ብሎ እንዳስተማረን፤ ተጨማሪውን አያስቀድምም። ሙሴ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መሰደድን ሲመርጥ በግብጽ ያጣው ምስፍና ከመንፈሳዊው ሹመት ጋር ተጨመረለት፤ የበለጠውን የማየት እድገት እና ብቃት ያገኘውም ***"ከግብጽም ብዙ ገንዘብ ይልቅ ስለክርስቶስ መነቀፍ እጅግ የሚበልጥ ባለጠግነት እንዲሆን አስቦአልና ለጊዜው በኃጢአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበልን መረጠ ብድራቱን ትኩር ብሎ ተመልክቶአልና"*** ዕብ.11፡25-27

**ሐ. ተስፋ ሙሉ እይታ እና ሰፊ አመለካከትን ያመጣል።**

በአንድ አቅጣጫ ብቻ በማየት መሳሳት በጠባብ አመለካካት መወሰን ፤ ችግሩ ብቻ ፣ ምድራዊነት ብቻ ፣ የሰዎች ድካም እና ክፋት ብቻ እንዲታየን ያደርጉናል ። ይህ ግን ጎዶሎ እይታ ነው። ምክንያቱም ከችግሩ በኋላ መፍትሔ አለ ፣ ሰዎች ምድራውያን ብቻ ሳንሆን ሰማያውያንም ነን ። ማንኛውም ሰው ከድካሙ የሚበልጡ ጠንካራ ጎኖች አሉት። እነኚህን አለመረዳት ሙሉ እይታ እና ሰፊ አመለካካት ከማጣት ይመነጫሉ።

ተስፋ ግን የዛሬውን እና የወደፊቱን፤ ጊዜያዊውን እና ዘላለማዊውን ፤ ችግሩን እና መውጫውን ፤ ለራስ እና ለሌሎች ማሰብን ይሰጣል። ፍጹሙ ተስፋ በውስጣችሁ ሲኖር ያጋጠማችሁን ችግር ብቻ ሳይሆን ምክንያቱን መፍትሔውንና በአጋጣሚው የምታገኙትን ልምድ ማየት ትጀምራላችሁ።

ወደ ፍጹም ተስፋ መድረስም ፣ ምሉዕ እይታ እና ሰፊ አመለካከትን ያመጣል ። ተስፋ ለእኔ ከማለት፣ ብቻ ከስግብግብነት እና ስስት ወጥተን ለሌሎች ወደ ማሰብ እና ወደ መንከባከብ ያደርሰናል ። በተቃራኒው በፍጹም ተስፋ የሌለ ሰው እይታው ስለሚጠብ ***"ዛሬ"*** እና ***"እኔ ብቻ"*** ሲል ሕይወቱን ያሳልፋል። ቅዱሳን ወደ ፍጹም ተስፋ ስለደረሱ ለሌሎች መዳን ሕይወታቸውን ሰጥተው ኖሩ።

www.zeorthodox.org

አድካሚ ሥራን በጠራራ ፀሐይ ላቡ እየተንጠፈጠፈ የሚሠራው ውጤቱን ተስፋ አድርጎ ነው። እንቅልፉን አጥቶ የሚያጠናው ተማሪም በክፍሉ የሚያመጣውን ከፍተኛ ውጤቱን እና የነገውንም የተሻለ ሕይወት ተስፋ አድርጎ ነው። በክርስትና ትምህርት ዋናው ተስፋ ትንሣኤ ሙታን ነው። በክርስቶስ ዳግም ምጽአት የምናገኘውን ሕይወት ተስፋ ስለምናደርግ ከጊዜው መከራ፣ በምኞት ከመታለልም በላይ ዘለዓለማዊውን ሕይወት እና ክብር ተስፋ እናደርጋለን። ተስፋ ከዓለም ጌጥ እና ከሥጋ ክፉ ምኞት፣ ከጊዜያዊውም መከራ በላይ በሙሉ እይታ በሰፋ አመለካካት ያቆመናል።

ለዚህም ነው *" በተስፋ ደስ ይበላችሁ ደግሜ እላለሁ ደስ ይበላችሁ"* ብሎ ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ የጻፈልን፡፡

**መ. ተስፋ የድል ምንጭ ናት፡፡**

የክርስቶስ የማዳን ሥራ አንድ ጊዜ ለዘላለም ሲፈጸም ለኃጥአን እና ለደካሞች የተስፋን በር ከፍቶልናል፡፡ ምሳ 24÷16 ፡፡ ተሸናፊዎች አሸናፊ የሆኑበት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ይህን የሚያምን በጌታችን የተሰጠውን ተስፋ ለመቀበልም በጽናት ይጓዛል፤ በእምነትም ድል ያደርጋል፡፡ ተስፋውም ዘለዓለማዊ ሕይወት፣ ሰማያዊው ክብር ነው ፡፡ በዚህ ተስፋ ደካሞች ይበረታሉ፤ የሰለሉት እጆችም ይጠነክራሉ፡፡ (ዕብ.12÷12)በዚህ መሠረትም ተስፋ ለደከሙ እና ለወደቁ በእምነት ስለሚገኘው ድል የሚነግረን ዓዋጅ ነው፡፡

**ሠ. እውነተኛ ተስፋ በእምነት ተመሥርታ በፍቅር ትጸናለች፡፡**

ሕሙማን በእግዚአብሔር አምነው ይድናሉ፡፡ እውነተኛ ተስፋም በእምነት ይመሠረታል በፍቅር ይጸናል፡፡ አንድ ሰው በእግዚአብሔር አምኖ የሚኖረው ተስፋ በእውነተኛው ታማኝ ላይ ስለሆነ እንደማያፍር ተስፋውንም እንደሚያገኝ እርግጠኛ ነው ÷ ይህንኑ በጽኑ መሠረት የተጣለ ተስፋም ለአምላኩ እና ለሰዎች በሚሰጠው ፍቅር ይገልጠዋል፡፡ ለሌሎች ስናካፍል፣ ስናገለግል እና ለክፉዎችም ስንጸልይ ተስፋውን እንዲያገኙ ካለን ፍቅር ነው፡፡

**ዘላለማዊ ተስፋን መጠበቅ ፡-**

ከላይ እንደተገለጠው ክርስትና ዘላለማዊ ተስፋ ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ***"በዚች ሕይወት ብቻ ክርስቶስን ተስፋ ያደረግነው ከሆነ ከሰው ሁሉ ይልቅ ምስኪኖች ነን "*** (1ኛ ቆሮ.15÷19) እንዳለም፤ እውነተኛው የክርስትና ተስፋ የዘላለም ሕይወት ነው ፡፡ ይህ ደካማ ታማሚ እና መዋቲ ሥጋ ክቡር እና ሕያው ሆኖ ይነሣል፡፡ ከክርስቶስ ጋር በሰማያዊትዋ ሀገር እንኖራለን፡፡ያቺ ሀገር ፍትሕ አይጎድልባትም ፣ ሐዘን ፣ ሕመም እና ሞትም አይኖርባትም፡፡***"ነገር ግን ጽድቅ የሚኖርባትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደ ተስፋ ቃሉ እንጠብቃለን "***(2ኛ ጴጥ.3፡13) ***"ስለዚህ የማይናወጥን መንግሥት ስለምንቀበል በማክበርና በፍርሃት እግዚአብሔርን ደስ እያሰኘን የምናመልክበትን ጸጋ እንያዝ አምላካችን በእውነት የሚያጠፋ እሳት ነውና፡፡"*** *ዕብ.12፡29*

www.zeorthodox.org

ክርስትና በእግዚአብሔር ፍቅር እና ብርሃን እንኖራለን ብሎ በማመን ተስፋ ማድረግ ነው፡፡ ***"ስለዚህ የልቡናችሁን ወገብ ታጥቃችሁና በመጠን ኖራችሁ ÷ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ የምታገኙትን ጸጋ ፈጽማችሁ ተስፋ አድርጉ፡፡"*** 1ኛ ጴጥ.1፡13

## ማጠቃለያ፡-

ሰው የተፈጠረው ለዘላለማዊ ሕይወት እና ክብር ነው፡፡ ያንን በመጠበቅ መኖርም ተስፋ ይባላል፡፡

ክርስትና የዚህ የጸና ተስፋ ሃይማኖት ነው፡፡ ተስፋውም ፍጥረት በናፍቆት የሚጠብቀው የእግዚአብሔር ልጆች ክብር ነው፡፡

## ተግባር፡-

በማንኛውም ፈተና ተስፋ ይኑራችሁ፡፡ ለሕሙማን ለተጨነቁና ተስፋ ለሌላቸው በቃል በፈገግታ እና በመልእክት ተስፋ ስጡዋቸው፡፡

***መዝሙር፡-***

ተስፋችን ነህ አንተ እስከ ዘላለም የድንግል ማርያም ልጅ መድኃኔ ዓለም ፤

ደምህን አፍሰህ ሥጋህን ቆርሰህ ብሉ ጠጡ ብለህ ለዓለም ሰጠህ፡፡

**ተግባራዊ ጥያቄዎች**

መምህር ተማሪዎችዎን በቡድን ከፋፍለው መድቧቸው፡፡ ከዚያም ቀጥሎ በቀረበው ርእሰ ጉዳይ ላይ፤ በክፍል ውስጥ ከተማሩት፣ መጻሕፍትን አንብበውና ሌሎች መምህራንን ጠይቀው የተረዱትን/የተገነዘቡትን/ በጽሑፍ አቅርበው በክፍል ውስጥ ማብራሪያ ይስጡ፤ ወይም ገለጻ ያድርጉ፡፡

1. የሰው ልጅ ‹‹አታድርግ›› የተባለውን ትእዛዝ በመጣሱ ምን መጣበት?
2. በእግዚአብሔር የተሰጠው የመዳን ተስፋ ምንድነው? ግለጹ፡፡
3. ‹‹ተስፋ በመከራዎች ሁሉ በጽናትና በትዕግሥት እንድንቆም ያበረታናል፡፡›› የሚለውን አባባል በጥቅስ ጭምር እያብራራችሁ ግለጹ፡፡
4. ‹‹ክርስትና ዘለዓለማዊ ተስፋ ነው›› ይህን አባባል ከጥቅስ ጋር አብራሩ፡፡

www.zeorthodox.org

# መታመንና ከስህተት መማር

## ሃምሳ አንደኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** ተማሪዎች በመንፈሳዊ ሕይወት መታመንን እና ከስሕተት በመማር ራስን ስለማሳደግ ያውቃሉ፤መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄ ያብራራሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"የማይታየውን እንጂ የሚታየውን ባንመለከት ቀላል የሆነ የጊዜው መከራችን የክብርን የዘላለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅ ያደርግልናልና፤ የሚታየው የጊዜው ነውና የማይታየው ግን የዘላለም ነውና፡፡"*** 2ኛ ቆሮ 4፡18፡፡

**ምንባብ፡-** ዘፍ.31-33 ፣ ማቴ.25÷14-30 ፣ ራእ.21÷1-10

**መግቢያ፡-** ከዚህ በፊት መንገዳችንን ስለመፈተን ተምረናል፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም ጥቂት በጥቂት እየታመንን ጌታ ስለሚጨምርልንና ስለሚሰጠን ጸጋ፣ የሕይወት ጉዞአችንን መፈተሽና ለዘላለማዊው ሕይወታችን ስለሚኖረን ዝግጅትም እንማራለን፡፡

## ትምህርቱ፡-

**ሀ.በጥቂቱ መታመን ፡-**

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- ***"በጥቂቱ ታምነሃል፤በብዙ እሾምሃለሁ፤..."*** ማቴ 25፡21፡፡ ይህ ማለት ‹‹በምድራዊ ነገሮች ላይ ታማኝ ሆነህ ስትገኝ በሰማያዊ ነገሮች ላይ እሾምሃለሁ›› ማለት ነው፡፡ በዚህኛው ዓለም ውስጥ ታማኝ ሆነህ ከቆየህ በዘላለማዊነት ውስጥ እሾምሃለሁ ማለትም ነው፡፡ ይህ መመሪያ በብዙ መስኮች ላይ ተግባራዊ ሊሆን ይችላል፡፡

ዘመዶችህን በመውደድ ላይ ታማኝ ሆነህ ከተገኘህ እግዚአብሔር ጠላቶችህንም በመውደድ ላይ ይሾምሃል፡፡ ጠላትህን የምትወድበትን ጸጋ ያድልሃል ማለት ነው፡፡

www.zeorthodox.org

በትርፍ ጊዜህ እግዚአብሔርን የምታገለግል ከሆንክ በሕይወትህ ጊዜ ሙሉ በእርሱ ላይ ትኩረት የምታደርግበትን ፍቅር ያድልሃል፡፡ የፈቃድ ኃጢአቶችን ከአንተ በማስወገድ ላይ ታማኝ ሆነህ ከተገኘህ እግዚአብሔር ያለ ፈቃድ ከሚመጡ ኃጢአቶች ነጻ ያወጣሃል፡፡

ንቁ ኅሊናህን ከክፉ አሳቦች የምትጠብቅ ከሆንህ እግዚአብሔር ንቁ ያልሆነው ኅሊናህን ንጽሕና ያድልሃል፣ከዚህ በተጨማሪ የሕልሞችህን ንጽሕናም ያድልሃል፡፡

ልጅ እያለህ ታማኝ ከሆንህ እግዚአብሔር ውጊያዎች በሚበዙበት በወጣትነት ዘመንህ ውስጥም ታማኝነትን ያድልሃል፡፡

ሌሎች ሰዎች ላይ በቃላት ብቻ የማትፈርድባቸው ሆነህ ለመገኘት ታማኝ ከሆንህ ይበልጥ አስቸጋሪ በሆነው በአሳብ እንዳትፈርድባቸው ያስችልሃል፡፡

ልክ እንደዚሁ ራስህን ከውጪያዊ ንዴት በመጠበቅ ላይ ታማኝ ሆነህ ከተገኘህ እግዚአብሔር ከውስጣዊ ቁጣ፣ ንዴትና ቅናት ነጻ ያወጣሀል፡፡

በተለመዱ መንፈሳዊነቶች (በመንፈስ ፍሬዎች) ላይ ታማኝ ሆነህ ከተገኘህ እግዚአብሔር የመንፈስ ስጦታዎችን ያድልሃል፤ በመጀመሪያው ላይ ታማኝ ሆነህ ካልተገኘህ ሁለተኛውን ፈጽሞ ልታገኘው አትችልምና፡፡

እግዚአብሔር በመጀመሪያ የሚፈትሽህ በጥቂት ነገር ነው፡፡ በዚህች በጥቂቷ ነገር ላይ ታማኝ መሆንህን ካረጋገጥህ እርሱ በሚበልጠው ነገር ላይ ይሾምሃል፡፡

ውድቀትህንና አለመታመንህን በጥቂቱ ነገር ላይ ከገለጽህ ግን እግዚአብሔር በሚበልጠው ነገር ላይ አይሾምህም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላልና፡-***"ከእግረኞች ጋር በሮጥህ ጊዜ እነርሱ ቢያደክሙህ ከፈረሶች ጋር መታገል እንዴት ትችላለህ?"*** ኤር 12፡5፡፡

ብዙ ሰዎች ዝቅተኛውን ሓላፊነት መወጣት ሳይችሉ ከፍተኛውን ሓላፊነት ለመቀበል ማሰባቸው እጅግ አስደናቂ ነገር ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች በተሰጣቸው ጸጋ ሳይጠቀሙ ተጨማሪ ጸጋ እንዲሰጣቸው የሚጠይቁ ናቸው፡፡ይህን ሲያደርጉም ***"በጥቂቱ ታምነሃል፤ በብዙ እሾምሃለሁ፤..."*** የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል በመዘንጋት ነው፡፡ ይህ ቃል ለእነርሱ እንደ ሁኔታው የሚወሰንበት ነው የሚሆነው፡፡

በጥቂቱ ነገር ላይ የምትታመን ከሆንህ እግዚአብሔር በብዙ ነገር ላይ ይሾምሃል፡፡ ልታደርገው በምትችለው ነገር ላይ ታማኝ ከሆንህ እግዚአብሔር ልታደርገው በማትችለው ነገር ላይም ይሾምሃል፡፡

በአንድ ተሰጥኦህ ላይ ታማኝ ሆነህ ከተገኘህ እግዚአብሔር በዐሥር ተሰጥዎች ላይ ይሾምሃል፡፡

www.zeorthodox.org

ከውጭ በሚመጡ ውጊያዎች ላይ ታማኝ ሆነህ ከተገኘህ እግዚአብሔር ከውስጥ በአሳቦችህና በልብህ በሚፈሉ መንፈሳዊ የተመስጦ ምንጮች ላይ ይሾምሃል፡፡

ራስህን ከሲና በረሓ ካወጣህ እግዚአብሔር ወደ ምድረ ከነዓን እንድትገባ ያስችልሃል፡፡ በጲጥፋራ ቤት ላይ ታማኝ ሆነህ ከተገኘህ እግዚአብሔር በፈርዖን ቤተ መንግሥትና በግብጽ ሀብት ላይ ሁሉ ይሾምሃል፡፡ በአርጤክስስ ቤተ መንግሥት ውስጥ ታማኝ ስትሆን እግዚአብሔር እንደ

ነህምያ ቤተ መቅደሱን ኢየሩሳሌም ውስጥ እንድታንጽ ይሾምሃል፡፡

ለእግዚአብሔር በሚታዩ ነገሮች ላይ ታማኝ ሆነህ ከተገኘህ እግዚአብሔር በማይታዩ ነገሮች ላይ ይሾምሃል፡፡ በዚህም ዐይን ባለየው፣ጆሮ ባልሰማውና በሰው ልብ ባልታሰበ ከተማ ላይ ይሾምሃል፡፡

እግዚአብሔር ታማኝነትህን በማንኛውም ነገር ላይ ሊፈትን ይችላል፡፡ ፈተናው አንድ ቀላል ትእዛዝ መጠበቅ ወይም ከአንዲት ፍሬ መከልከል ሊሆን ይችላል፡፡ በዕውቀት ዛፍ ላይ ታማኝነትህ ከተረጋገጠ እግዚአብሔር በሕይወት ዛፍና ከሰማይ በወረደው መና ላይ ይሾምሃል፡፡

ያሉህን መክሊቶች አሳንሰህ አትመልከት፡፡ ይልቁንም ባሉህ መክሊቶችህ ላይ ታማኝ ሆነህ ተገኝ፡፡ እግዚአብሔር የሚመለከተው ያሉህን መክሊቶች ማነስ ወይም መብዛት አይደለም፤ባሉህ መክሊቶች ላይ ታማኝ ሆነህ መገኘትህን እንጂ፡፡

**ለ. ከስሕተቶች መጠቀም**

ማንኛውም ሰው ለስሕተት የተጋለጠ ቢሆንም ከስሕተቱ የሚጠቀም ሰው ግን ብልህ ነው፡፡ ይህ ሰው ዳግመኛ ኃጢአት እንዳይሠራ መንፈሳዊ ልምድን፤ ዕውቀትንና ጥንቃቄን ገንዘቡ ያደርጋል፡፡ ከአባቶች አንዱ ይህን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል፡፡ ***"ዲያብሎስ ለተመሳሳይ ኃጢአት ሁለቴ የቀሰቀሰኝን ጊዜ አላስታውስም፡፡"***

መንፈሳዊ ሰው በስሕተቶቹ ውስጥ ትሕትናን የራሱ ያደርጋል፡፡ ይህ ሰው ስሕተቱን በመለየትና እንደ ሌሎች ሰዎች እንዴት ለስሕተት እንደሚጋለጥ በማወቅ ከስሕተቱ ይማራል፡፡ በመሆኑም አይኮራም ወይም እብሪት አይሰማውም ወይም ራሱን ከሌሎች ልዩ አድርጎ አይመለከትም፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ***"ስለዚህ እንደ ቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ፡፡"*** (1ኛ ቆሮ 10፡12) ብሎ የተናገረው ቃል በእርሱ ሕይወት ውስጥ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

እብሪተኛ ሰው ሲወድቅ ስለሚደክም ለውድቀት የሚያበቁት ጥፋቶቹን በተደጋጋሚ መሥራቱን ይቀጥላል፡፡ በመጨረሻም ይሰላቻል፣ ተስፋ ይቆርጣል ፣ ላይነሣም ወድቆ ይቀራል፤

www.zeorthodox.org

ብልህ ሰው ግን በኃጢአቶቹ ውስጥ ያሉትን የዲያብሎስ ማታለያዎችና ውጊያዎች ይገነዘባል፡፡ እርሱ ዲያብሎስ ወደ ሰው ልጆች ነፍስ እንዴት እንደሚገባ እንዴት እርሱን መጠንቀቅ እንዳለበት? እንዴት ትክክለኛ ሰው መሆን እንደሚገባው? ይማራል፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፤ አመጣጡንና መንገዱን ይበልጥ እየተረዳ ሲመጣም ሌሎችን ለመርዳት የሚያስችለውን ሁኔታ ያዘጋጃል፤፤

መንፈሳዊ ሰው ቅዱስ ጳውሎስ እንደ ተናገረ፤ ከሌሎች ሰዎች ጋር በመሆን ስለ ሌሎች ሰዎች በሚሆን ሐዘኑ ውስጥ ከስሕተቱ ይማራል፡፡ ***"ከእነርሱ ጋር እንደ ታሰራችሁ ሆናችሁ እስሮችን አስቡ፣ የተጨነቁትንም ራሳችሁ ደግሞ በሥጋ እንዳለ ሆናችሁ አስቡ፡፡"*** ዕብ13፡3፡፡ ስለሆነም አንድ

መንፈሳዊ ሰው ሲወድቅ ለሌሎች ለወደቁ ሰዎች ይበልጥ ሐዘን ስለሚሰማው እነርሱን አይገሥጽም፤ በእነርሱም ላይ አይፈርድም፤ እርሱ ራሱ የዲያብሎስን ኃይልና የሰው ልጆችን ደካማ ተፈጥሮ ያውቃልና፡፡

መንፈሳዊው ሰው ለራሱና ለሌሎች በሚያደርገው የጸሎት ልምምድ ውስጥ ከስሕተቱ ይጠቀማል፡፡ እርሱ የሰው ልጆች ድል ነሺነት የሚመሠረተው በእነርሱ ኃይልና ብልሃት ላይ ሳይሆን ምንጊዜም ቢሆን ወደ ድል በሚመራን በእግዚአብሔር ርዳታ መሆኑን ጠንቅቆ ያውቃል፡፡ ይህ በመሆኑም ሰው ***"እርዳኝ እድናለሁም፤..."*** (መዝ 118፡117) እና ***"አምላካችን ስለ እኛ ይዋጋል፤..."*** (ነህ 4፡20) በማለት በጸሎቱ ከእግዚአብሔር ጋር ይጣበቃል፡፡

መጠቀምን የሚሻ ሰው ከራሱም ሆነ ከሌሎች ሰዎች ስሕተት በመማር ይጠቀማል፡፡ ይህ በመሆኑም እግዚአብሔር ባጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሌሎች ስሕተት እንዲጠቀስ አድርጓል፡፡ በዚህ መሠረት እኛ ትምህርት ሆኖን እንጠቀምባቸው ዘንድ የነቢያትና የጻድቃን ስሕተቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲጻፉ ፈቅዷል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ***"...ከብርቱም ውስጥ ጥፍጥ ወጣ...."*** (መሳ 14፡14) በማለት ያናገረ አምላካችን እግዚአብሔር ለድኅነታችን ይሆን ዘንድ ከእያንዳንዱ ኃጢአት ጠቃሚ ትምህርት ሊሰጠን ይችላል፡፡

በመሆኑም በሕይወታችን ዘመናት ከምናገኛቸው ሰዎቸ ሁሉ እንጠቀማለን ማለት ነው፡፡ ከጻድቅ ሰው ምሳሌ ስንወስድ ከእኛና ከሌሎች ሰዎች ኃጢአት ደግሞ ልምድና ንቃትን ገንዘብ እናደርጋለን፡፡

***መዝሙር፡-***

እግዚአብሔር ኀበነ ልሳነ ጥበብ ፤

ከመ ናዕምር ሕጋ ለቤተ ክርስቲያን፡፡

***ትርጉም***

www.zeorthodox.org

እግዚአብሔር ሆይ የቤተ ክርስቲያንን ሕግ

የምናውቅበት ጥበብ ስጠን፡፡

***ጥያቄ***

1.‹‹በጥቂቱ ታምነሃል፤በብዙ እሾምሃለሁ፤. . .›› ማቴ. 25፡21 የሚለው ጥቅስ ምን ማለት ነው? ከተማራችሁት የተገነዘባችሁትን መሠረተ በማድረግ አብራሩ፡፡

# ሰው በክርስትና እይታ

## ሃምሳ ሁለተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ሰው የተፈጠረበትን ዓላማ እና ክብሩን ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች እያብራሩ ይመልሳሉ።

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***" እኛ ፍጥረቱ ነንና እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን"*** ኤፌ 2፡10

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘፍ 1፡31፤2፡7-25፤መዝ 8፡4-8፤ኤፌ 2፡10፤1ኛ ቆሮ 16

***መግቢያ"ሰው ምንድን ነው? በራሱ መለኮታዊ ነው ?ወይስ ምድራዊ ፍጡር ?"*** የሚሉ ጥያቄዎች በተደጋጋሚ ይነሣሉ። እነዚህን በትክክል የምንመልሰው ሰው የተፈጠረበትን ምክንያት ማብራራት ስንችል ነው።

እግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነና ይህንን ፍቅሩን ለመግለጥ እንዲሁም በፍቅሩ ሰንሰለት ሊያኖረን ፍጥረታትን መፍጠር ፈለገ።

ከእርሱ የምትገኘውን ሕይወት እና ደስታ ሲሰጠን የክብሩ ተካፋዮችም አደረገን። ዓላማውም ሰው ሕያው እንዲሆንና በደስታ እንዲኖር ነው።ዮሐ.1፡1-4

### የትምህርቱ ይዘት፡-

**ሰው የእግዚአብሔር አምሳል ነው።**

እግዚአብሔር ሌሎች ፍጥረታትን ሲፈጥር እና ሰውን ሲፈጥር የተናገረው የተለያየ ቃል ነው። ለሌሎቹ ‹‹***ይሁን***›› ሲል ለሰው ግን ***‹‹እግዚአብሔር አለ ሰውን በመልካችን እንደምሳሌአችን እንፍጠር››*** ዘፍ 1፡26 ብሎ ነው።

www.zeorthodox.org

***"በመልካችን"*** የሚለው ቃል ነጻ ፈቃድን እና ምክንያታዊነትን ያመለክታሉ። በነጻ ፍቃድ ውስጥ ያለው የሓላፊነት ሹመት ደግሞ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያመለክታል። ስለዚህም እርሱን ለማወቅ እንድንችል እና ከእርሱ ጋር አንድነት እንዲኖረን አድርጎ በመልኩ ፈጥሮናል።

***"እንደ ምሳሌያችን"*** የሚለው ቃልም ሰው በመልካምነት እና በቅድስና የሚደርስበትን ደረጃ

ያመለክታል። እርሱን እግዚአብሔርን በመልካምነት እና ቅድስና መምሰል። ኃጢአት ሰውን የእግዚአብሔርን መልክ እንዲያጣ አያደርገውም /መልክ የተፈጥሮ ነውና።/ በጎነት እና ቅድስና በሰው ነጻ ምርጫ ይያያዛሉ፤ ኃጢአት ስንሠራ ሰው ስንሆን የተሰጠንን የእግዚአብሔር ምሳሌነት ያሳጣናል።

*"ሰውን.......እንፍጠር"* ሲልም ነፍሱን ብቻ ወይም *ሥጋውን* ብቻ አያመለክትም። ሁለቱንም ያስተባበረ አንድ ሰውን *ያመለክታሉ*። ሰው *ሥጋ* ስላለው ከመላእክት አያንስም። እንደውም ሰው የበለጠ ፍጹም ተፈጥሮ ያለው እና ትልቁ አቅም የተሰጠው ትንሽ ዓለም ነው። በእርግጥም ሰው የመንፈሳዊው ዓለም እና የቁሳዊው ተፈጥሮ መገናኛ ነጥብ ነው።እንደዚህ ከሆነም ሰው በተፈጥሮ ሁሉ ላይ የተሾመ ካህን ነው ማለት ነው።አዳም ካህን ነበር ገዢም ነበር።

***"ሰው በእግዚአብሔር መልክ"*** ተፈጥሯልና በልቡ ውስጥ ያለውን እግዚአብሔርን ማየት ይችላል። በእምነት እና በሥጋችን ውስጥ ባለ ነፍስ ዕውቀት ውስጥ ስንሆን ***" የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችን "*** ሉቃ 17፡21 መሆንዋን እንረዳለን።

ቅዱስ እንጦስ *"ራሱን ያወቀ እግዚአብሔርን ያውቃል"* ብሏል። ሶርያዊው ቅዱስ ይስሐቅም ***"ንጹሕ ልብ ካለህ መንግሥተ ሰማያት ካንተ ጋር ናት "*** ይለናል። በቅዱስ ጳኩሚስም ***"የማይታየውን እግዚአብሔርን ከልብ ንጽሕና የተነሣ በግልጥ መስታወት እንዳለ ሆኖ ያዩታል።"*** ተብሎ ነበር። እነዚህ ሁሉ የአባቶች ትምህርቶች***‹‹ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው፤እግዚአብሔርን ያዩታልና ››*** ማቴ.5፡8 የሚለውን የጌታ ትምህርት የያዙ ናቸው።

ሰው በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠረ ከመሆኑ የተነሣ እያንዳንዱ የሰው ዘር ምን ኃጥአተኛ እና የመልካም *ሥራ* ደሀ ቢሆንም በእግዚአብሔር እይታ የተወደደ ነው። የእስክንድርያው ቅዱስ ቀሌምንጦስ ***" ወንድምህን ስታይ የእግዚአብሔርን ሥዕል እያየህ ነው"*** ብሏል። የጌታ ወዳጅ ዮሐንስም ***‹‹እግዚአብሔርን ማንም ከቶ አላየውም፤ እርስ በርሳችን ብንዋደድ እግዚአብሔር በእኛ ይኖራል ፍቅሩም በእኛ ፍጹም ሆኖአል።››*** (1ኛ ዮሐ.4፡12)ይላል።

www.zeorthodox.org

ከዚህም ጋር ሰው በእግዚአብሔር መልክ ስለተፈጠረ ነፍሱ ሕያዊት ናት።***"የሕይወት እስትንፋስ እፍ አለበት"*** (ዘፍ.2፡7) ከሰው ጀርባ ያለው ምስጢራዊው ኃይል ይህ ነው። በሐዲስ ኪዳን እንደምናስታውሰው ክርስቶስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ***"እፍ አለባቸው እና መንፈስ ቅዱስን***

***ተቀበሉ።"*** (ዮሐ 20፡22)

ሕያውነት የነፍስ ነው። ***"አፈርም ወደ ነበረበት ምድር ሳይመለስ ነፍስም ወደሰጠው ወደ እግዚአብሔር ሳይመለስ"*** መክ.12 ፡ 7 ፤ ይህም ሆኖ ከመሬት የተፈጠረው የሰው *ሥጋ* ክፉ አይደለም፤ የዚያ *ሥጋ* ጥንተ ተፈጥሮ ከውድቀቱ በፊት ‹‹***አዳም መልካም ነበረ***›› ተብሎለታልና። እግዚአብሔር ክፉ አልፈጠረም፣ ንጹሕ እና ቅዱስ በሆነው ጥንተ ተፈጥሮ እና ኃጢአት ወደ ዓለም ከገባ በኋላ በመጣው መርገም መሐል ልዩነት አለ።

***ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው።*** የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከቱ፡-ዘፍ 2፡21-25 ማቴ 19፡4-6 ኤፌ 5፡28-32 ቅዱስ ጳውሎስ፤ ከእርሱ አጥንት የተወሰደች አጥንት እና ከእርሱ *ሥጋ* የተወሰደች *ሥጋ* ናት፤ ከሚለው ጋር ተመሳሳይ አገላለጥ በመጠቀም፤ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እና በእኛ መካከል ያለውን መንፈሳዊ ግንኙነት ሲያመለክት፤ ***"የአካሉ ሕዋሳት ስለሆንን "*** ኤፌ 5፡30 ብሏል።

የአዳም እና ሔዋን ተፈጥሮአዊ አንድነት የተጀመረው ከአንድ አካል በመገኘት ነው። የእኛ አንድነት የበለጠ የመጣው የተሰጠንም በጌታችን በኢየሱስ እና ሁለቱን አንድ በሚያደርግ የመንፈስ ቅዱስ ምስጢር ነው፣ ያን ጊዜም ባል እና ሚስት ይባላሉ።

ይህ አዲስ የተዋሐደ አካል የቤተ ክርስቲያን እርሾ ይሆናል። ከክርስቶስ አካል ጋር የሚቀላቀሉ አባላትን የያዘ ነውና። ይህም የሚያመለክተን ጾታዊ ልዩነቶችን መሠረት አድርገው ከመብት እና ሥራ አንፃር የሚነሡ ልዩነቶች እንደሌሉ ነው። እነዚህ ልዩነቶች ማኅበራዊም ሆነ የመንፈሳዊነት ከፍታ እና ዝቅታን አያመለክትም። ቅዱስ ጳውሎስ ይሄንን በአጽንኦት ሲገልጥ፤ ***"ወንድም ወይም ሴት የለም ፤ ሁሉም በክርስቶስ አንድ ናቸው"*** ብሏል።ገላ 3፡28

www.zeorthodox.org

3. **እግዚአብሔር ሕግን ለአዳም ለምን ሰጠው ?** ነፍስ ከእግዚአብሔር የተገኘች ናት። ስለዚህም ጥበብ፣ ነጻነት፣ ፈቃድ አለው (ተሰጥቶታል)። ለዚህም ነው ነፍስ አዋቂ ናት ምንለው። ከዚህም በላይ የምንጠቀመው ችሎታ ከእግዚአብሔር የተሰጠን መሆኑም የተረጋገጠ ነው። በዚህ እይታ መሠረትም እግዚአብሔር ለአዳም ሕግ ሲሰጠው አስፈላጊነቱን ፤ ነፃነቱን ፣ ፍቃዱን እና ጥበቡን ተጠቅሞ ራሱን ለተፈጠረበት ግብ እንዲያደርስ ነበር። ‹‹***መልካምንና ክፉውን የሚያስታውቀውንም ዛፍ አበቀለ።"*** ዘፍ.2፡9

ለአዳም የተሰጠው ሕግ ነጻነቱን የሚያስረግጥ እንጂ ሊደርስበት ከሚገባው መዓርግ የሚያስቀረው አልነበረም። ቢበላ ክፉን ባይበላ መልካሙን የሚያሳውቅ የመታዘዝ ምልክት የበረከት ምንጭ ነበር። ከዚህ በላይም ሕጉ በእግዚአብሔር እና በሰው መካከል የነበረ የፍቅር ማሰሪያ ነው። አዳም የእግዚአብሔርን ቃል እንደ ፍቅር ምልክት አድርጎ ሲታዘዝ እና በእግዚአብሔር ሲያምን የሚበልጠውን ስጦታ በምትኩ ሊቀበል ነበር። ትእዛዚቱ የፈጣሪ እና የፍጡርነት መለያም ነበረች፤ አምላኩን እንዲያስብ የምታደርገውም ናት።

4 **ሰው እንዴት ወደቀ ?** የአዳም ባሕርይ ለክፉ የሚወድቅ አልነበረም። ውድቀቱ ከነጻ ፈቃድ ምርጫው የወጣ ነው፤ የተከለከለውን ሲፈልግ ሁሉን አጣ። ለክፉ በመታዘዝ አዳም ወደቀ፤ ለክፉ የታዘዘም ሆነ። ይህ ከዚህ በፊት የማያውቀው አዲስ ክሥተት ነበር። ምን አወቀ ስንልም የኃጢአት ውጤቱ ሞት እንደሆነ አወቀ።

5 **ሰው ከውድቀት በኋላ** ይወደው የነበረውን እግዚአብሔርን መፍራት ጀመረ። የመርገም እና የቅጣት ድምፅ ከበበው ፣***"ምትን ትሞታለህ"*** ተባለ። የእግዚአብሔር መንፈስ ስለራቀው መልካም የመሥራት ፈቃድ እና ኃይል አጣ። ይልቁንም የመልካም እና ክፉ ዕውቀቶች ተደራርበው በውስጥ ግጭት ተያዘ። ይህም ለሰው የማይቻል፣ሊቋቋመው የማይችል ሆነበት፤ ለዘላለማዊ ሕይወቱ አንድ እርምጃ መራመድ የሚያቅተው ሆነ።ነፍስ አቅምዋን አጥታ ወደ ዕውቀት የሚያደርሳትን ከቁስ በላይ የሆነ ዕውቀት አጥታ ከቁስ በታች ስለሆነች ነው።

**የሰው ልጅ ስብራት :-**

ሀ. **በራሱ ውስጥ፡-** በመንፈሱ እና በአካሉ ከሕሊናው እና ከእራሱ ጋር ሙግት ውስጥ ገብቶ ከራሱ ጋር ተጣላ።

ለ. **ከራሱ ጋር እና ከሌሎች ጋር** :-ተጣላ ጥላቻ እና መቅበዝበዝ ውስጥ ገባ። (ለዚህ የቃየልን ታሪክ በሚገባ ተመልከቱ)

ሐ. **ከተፈጥሮ ጋር፡-** ***‹‹በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው ››*** ዘፍ.1:28 በመባል በተፈጥሮ ላይ የተሾመው ሰው የእግዚአብሔርን መልክ ሲያጣ በተፈጥሮ እና መሬት ላይ የነበረውን ኃይል አጣ ፤ በእርሱ ላይም ተነሡበት።

www.zeorthodox.org

6 **የሰው ድኅነት** የሰው ልጅ ድኅነት በክርስቶስ ሥጋ መልበስ የተሰጠ ነው።(በከበረ ደሙ ፈሳሽነት) በዚህ መንገድ እግዚአብሔር ከሰው ጋር ታረቀ ፈቃዱም ወደ ሰው ሆነ፤ በማስከተልም ስጦታውን መለሰለት። በሌላ አገላለጥ ሰው የእግዚአብሔርን መልክ መልሶ አገኘ። የእግዚአብሔርን

ፍቅር፣ ክብር እና ቅድስና ተሳተፈ። ይህ ማለት ግን ሰው የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ባሕርይ አገኘ ማለት አይደለም። በጸጋ ነው እንጂ! ይህም ቅዱስ ጴጥሮስ እንዳለው *"ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች ።"* 2ኛ ጴጥ 1፡4 እንድንሆን ሰጠን።

እግዚአብሔር ለኛ ያለውን ፍቅር የፍቅሩንም መገለጫ ተማርን ተለማመድንም። የፍቅርን ክብርና መጠን አውቀን ለሌላው ማሳየትን በየደረጃው ማለትም በቤተሰብ፤በቤተ ክርስቲያን፤በሀገር፤ለዓለም በሙሉ እንድንገልጠው አስቻለን ማለት ነው። ክርስቶስ የነገረንም ይኸንኑ ነው። *"እኔ እንደወደድኳችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ"* ዩሐ 15፡12

7 ክርስቲያናዊ ፍቅር የሚከተሉትን ባሕርያት ያካትታል።ራስን በመሠዋት ይመሠረታል። *"እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቶአልና በዚህ ፍቅርን አውቀናል ፤ እኛም ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባናል።"* 1ኛ ዩሐ 3፡16በማካፈል የተጌጠ ነው። *"ወንድመሙን ሲያጣ አይቶ ያልራራለት ማንም ቢሆን የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ እንዴት ይኖራል›› *1ኛ.ዮሐ.3፡17

በፈቃድ እና በተግባር ይቀርባል።‹‹ *ልጆቼ ሆይ በሥራ እና በእውነት እንጂ በቃል እና በአንደበት አንዋደድ››*1ኛ ዮሐ.3፡18

በነጻ ያለ ምክንያት የሆነ ፍቅር ነው።*‹‹ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቶአልና። ስለ ጻድቅ የሚሞት በጭንቅ ይገኛልና ስለቸር ሰው ግን ሊሞት እንኳን የሚደፍር ምናልባት ይገኝ ይሆናል ፤ ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለእኛ ሞቶልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል።››* ሮሜ.5፡6-8

በመከራ ያሉትን፣የተቸገሩትን እና የተገፉትን በቀጥታ መውደድ እና መድረስ። **‹‹ንጹሕ የሆነ ነውርም የሌለበት አምልኮ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ይህ ነው፤ወላጆች የሌላቸውን ልጆች ባልቴቶችንም በመከራቸው መጠየቅ በዓለምም ከሚገኝ እድፍ ሰውነቱን መጠበቅ ነው።››** *ያዕ*.1፡27

8 ሰው *መለኮታዊ ሓላፊነት ተሰጥቶታል።* ይ--ህንን በመፈጸም ወደ ሙሉው ሰብእናው ይደርሳል።

www.zoorthodox.org

*" እኛ ፍጥረቱ ነንና እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን"* ኤፌ 2፡10 ለክርስቲያን በክርስቶስ ያለውን እምነት ከያዘና ካወቀ በኋላ አቅሙን በፍቅር እንዲጠቀም መልካም እንዲሠራ እና የክርስቶስን መንገድ ሊከተል ያስፈልጋል።

**በንግግር፡-** በንግግራችን ልንገልጠው ይገባናል፡፡

**በቃላት፡-** ከልቡ መልካም መዝገብ አውጥቶ በአፉ ይናገራል፡፡

**በሥራ፡-** ያደፈው ባሕርያችንን ካደሰልን በኋላ ሥራ ማኅበራዊ ግዴታ ብቻ መሆኑ ቀርቷል፡፡

**አምልኮት፡-** በውስጣችን እንደመላእክት ሁሌም ማመስገን እና ለእግዚአብሔር ፈቃድ መታዘዝ ይገባል፡፡

በውጪ፡-በቤተ ክርስቲያናችን አገልግሎቶች መሳተፍ፤ ማስቀደስ፣ ኪዳን ማድረስ፣ መቊረብ፣ የተቸገሩትን መርዳት እና መጎብኘት፡፡

## ተግባር

መዝሙራትንና ቅዳሴ አጥኑ፡፡

ፍቅርን ለሌሎች በማካፈል ግለጡ፡፡

**ጥያቄዎች፡-**

1. ‹‹ሰው የእግዚአብሔር አምሳል ነው›› በማለት የቀረበው ሐረግ ምን ማለት ነው? ከጥቅስ ጋር አብራሩ፡፡
2. ሰው ‹‹አታድርግ›› የተባለው ትእዛዝ ጥሶ በማድረጉ ወደቀ፡፡ ከውድቀት በኋላ ምን ተባለ? ምንስ መጣበት?
3. ለሰው ልጅ ድኅነት/መዳን/ የተሰጠው እንዴት ነው? እግዚአብሔር ከሰው ጋር የታረቀው በምንድነው? አብራሩ፡፡
4. ክርስቲያናዊ ፍቅር የሚያካትታቸው/የሚገለጽባቸው/ ባሕርያት ምን ምን ናቸው? አብራሩ፡፡

www.zeorthodox.org

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

# ዋቢ መጻሕፍት

- ሃብተማርያም ወርቅነህ (ሊቀ ሥልጣናት)፣ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ ማተሚያ ቤት፣ 1963 ዓ.ም
- ሃይማኖተ አበው፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1986 ዓ.ም
- አባ መልከ ጼደቅ (ሊቀ ጳጳስ)፣ ትምህርተ ክርስትና፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት፣ 1984 ዓ.ም።
- አባ ጎርጎርዮስ (ሊቀ ጳጳስ)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1974 ዓ.ም።
- ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ሊቃውንት ቤተክርስቲያን (አዘጋጆች)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓት አምልኮና የውጭ ግኝኙነት፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም.
- ሊቃውንት ቤተክርስቲያን (አዘጋጆች)፣ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትናንትና ዛሬ፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1990 ዓ.ም.
- ሉሌ መልአኩ (መምህር)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1997 ዓ.ም።
- መሐሪ ትርፌ (ሊቀ ሊቃውንት)፣ መጽሐፈ ሐዲሳት ሠለስቱ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1989 ዓ.ም።
- መጽሐፈ ስንክሳር፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም
- መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም።
- መጽሐፈ ስንክሳር፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም
www.zeorthodox.org
- መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም
- ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1988 ዓ.ም
- ዳኛቸው ካሳሁን (መልአከ ሰላም)፣ ክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባር፣ አዲስ አበባ፣ ማኅበረ ቅዱሳን፣ 2003 ዓ.ም
- ደረጀ ጅማ (መጋቤ አእላፍ)፣ ምን ያስጨንቃችኋል ክፍል ፪፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 2002 ዓ.ም።

- መጽሐፍ ቅዱስ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980 ዓ.ም
- ሐረገ ወይን ቸርነት፣ ሴትና አህያ፣ አዲስ አበባ፣ 2005 ዓ.ም፡፡
- ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል (ዶ/ር)፣ ጠቅላላ የቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ 2000 ዓ.ም
- ኅሩይ ኤርምያስ (መምህር)፣ መዝገበ ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ 2002 ዓ.ም
- የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ 1996 ዓ.ም፡፡
- ቸርነት አበበ (መምህሩ)፣ የመጽሐፍ ቅድስ ጥናት፣ አዲስ አበባ፣ 2003 ዓ.ም
- H.G. Bishop Moussa@ The Characteristics of Orthodox Teaching@ Bishopric of Youth@ Harmony Press, 2007.
- H.G. Bishop Mouusa, An Introduction to the New Testament, Bishopric of youth, Dar EL Geel Press, 2001.
- H.G. Bishop Raphail, The Meaning of Miracles, Bishopirc of Youth, 2010.
- Sunday School Curriculum, Grade 1 to Grade 12. The Coptic Orthodox Diocese of The Southern USA.
- Sunday School Lessons, Class 1 to Class 10, E.O.T.C Latin America Diocese.

www.zeorthodox.org